# መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት።

# በግእዝና ፡ በአማርኛ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡
ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲፭ኛው ፡ ዘመነ ፡ ፓትርያርክነት ፡ ለመጀመሪያ ፡
ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታተመ።


<u>አሳታሚ</u> ፡– ትንሣኤ ፡ ማሳተሚያ ፡ ድርጅት፡
አ·አ· ፲፱፻፺፮ ፡ ዓ·ም


Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

### ክፍል፡፩።
### አሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፤፲፯፤፰-፲፮።

፰፤ ወመጽአ ፡ አማሌቅ ፡ ይትቃተል ፡ ምስለ ፡ ደቂቀ፡እስራኤል፡በራፌድ።

፱፤ ወይቤሎ፡ሙሴ፡ለኢያሱ፡ኅረይ፡ለከ፡ዕደወ፡ወፃእ፡ወተአኀዝ፡ለአማሌቅ፡ጌሠመ፡ወናሁ፡አነ፡እቀውም፡ዲበ፡ርእሰ፡ወግር፡ወበትር፡ዘእግዚአብሔር፡ውስተ፡እዴየ።

፲፤ ወገብረ፡ኢያሱ፡በከመ፡አዘዞ፡ሙሴ፡ወተራከበሙ፡ለአማሌቅ፡ወሙሴ፡ወአሮን፡ወሖር፡ዐርጉ፡ውስተ፡ርእሰ፡ወግር።

፲፩፤ ወሶበ፡ያነሥእ፡ሙሴ፡እደዊሁ፡ይትዌፀዑ፡እስራኤል፡ወሶበ፡የዐፅብ፡ሙሴ፡ያወርድ፡እደዊሁ፡ይትዌፀኡ፡አማሌቅ፡ወእደዊሁ፡ለሙሴ፡ክቡዳት፡ወአንበሩ፡ሎቱ፡ዕብነ፡ወነበረ፡ላዕሌሁ።

፲፪፤ አሮን፡ወሖር፡ይጸውሩ፡እደወ፡ሙሴ፡አሐዱ፡በለፌ፡ወአሐዱ፡በለፌ፡ወቆማ፡እደዊሁ፡ለሙሴ፡ርቡባቲሆን፡እስከ፡ዕርበተ፡ፀሐይ።

፲፫፤ ወሜጠሙ፡ኢያሱ፡ለአማሌቅ፡ምስለ፡ሕዝቡ፡ወቀተሎሙ፡በኅፂን።

፲፬፤ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ጸሐፍ፡ለዝ፡ለተዝካር፡ወአይድዕ፡ለኢያሱ፡ድምሳሴ፡እደመስሶሙ፡ለአማሌቅ፡እምታሕተ፡ሰማይ።

፲፭፤ ወአሕነጸ፡ሙሴ፡ምሥዋዐ፡ለእግዚአብሔር፡ወሰመዮ፡ስሞ፡መምሕፃን፤ወይቤ፡እስመ፡በእድ፡ኅብእት፡ይጸብዮሙ፡እግዚአብሔር፡ለአማሌቅ፡ለዘመደ፡ዘመድ።

#### ትእዛዝ።

ወእምዝ፡ይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወይበል፡ካህን፡ጸሎተ፡አኰቴት፡ወያዐርግ፡ዕጣነ፡ወይበል፡ጸሎተ፡ዕጣን፡ወይበል፡በእንተ፡ሰላም፡ወበእንተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወበእንተ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወበእንተ፡ማኅበር።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

### ክፍል፡፩።
### ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፤፲፯፤፰-፲፮።

፰፤ አማሌቅም፡ከእስራኤል፡ልጆች፡ጋራ፡በራፌድ፡ይዋጋ፡ዘንድ፡መጣ።

፱፤ ሙሴም፡ኢያሱን፡አርበኞችን፡መርጠህ፡ወጥተህ፡ነገ፡አማሌቅን፡ተዋጋው፤እግዚአብሔር፡ታምራት፡ያደረገባትን፡በትር፡በእጄ፡ይገዥ፡እነሆ፡እኔም፡በኮረብታው፡ራስ፡ላይ፡እቆማለሁ።

፲፤ ኢያሱም፡ሙሴ፡እንዳዘዘው፡አደረገ፤አማሌቅንም፡ተዋጋው፤አሮንና፡ሙሴ፡ሖርም፡ወደ፡ኮረብታው፡ራስ፡ወጡ።

፲፩፤ ሙሴም፡እጆቹን፡በዘረጋ፡ጊዜ፡እስራኤል፡ድል፡ያደርጉ፡ነበር፤አማሌቅንም፡ድል፡ይነሡ፡ነበር፤ሙሴም፡ተጨንቆ፡እጆቹን፡በሰበሰበ፡ጊዜ፡አማሌቅ፡ድል፡ያደርጉ፡ነበር፤የሙሴም፡እጆች፡ያን፡ጊዜ፡ከብደው፡ነበር፤በኮረብታው፡ላይም፡ደንጊያን፡አኖሩለት፤እርሱም፡በደንጊያው፡ላይ፡ተቀመጠ።

፲፪፤ ሖርና፡አሮንም፡አንዱ፡በአንድ፡ወገን፡አንዱ፡በአንዱ፡ወገን፡ሁነው፡የሙሴን፡እጆች፡ይሸከሙ፡ነበር፤የሙሴም፡እጆቹ፡ፀሐይ፡እስኪገባ፡ድረስ፡ተዘርግተው፡ይውሉ፡ነበር።

፲፫፤ ኢያሱም፡ከወገኖቹ፡ጋራ፡ተዋግቶ፡አማሌቅን፡መለሳቸው፤በጦርም፡አጠፋቸው።

፲፬፤ እግዚአብሔር፡ሙሴን፡መታሰቢያ፡ሊሆን፡ይህን፡ነገር፡ጻፈው፤አማሌቅን፡ከሰማይ፡በታች፡ፈጽሜ፡እንዳጠፋቸው፡ለኢያሱ፡ንገረው፡አለው።

፲፭፤ ሙሴም፡ለእግዚአብሔር፡መሥዋዕት፡የሚሠዋበትን፡አሠራ፤እግዚአብሔር፡በማትመረመር፡ሥልጣን፡አማሌቅን፡እስከ፡የልጅ፡ልጅ፡ድረስ፡ያጠፋቸዋልና፡ብሎ፡ስሙን፡መማጠኛ፡አለው።

#### ትእዛዝ።

ከዚህ፡በኋላ፡ካህናት፡በቤተ፡ክርስቲያን፡ይሰብሰቡ፤ካህኑም፡ጸሎተ፡አኰቴት፡ንአኵቶ፡ይበል፤ዕጣን፡ያሳርግ፤ጸሎተ፡ዕጣኑን፡ይድገም፤ስለ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ስለ፡ሰላም፡ስለ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ስለ፡ማኅበሩ፡ይጸልይ።

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

ወእምድኅረዝ ፡ ይበሉ ፡ ሕዝብ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ ይእዜኒ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፤ ወይበሉ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ወይድግሙ ፡ መዝሙረ፡ዳዊት፡ወይዐድ፡ካህን፡ቤተ፡ክር ስቲያን ፡ በማዕጠንት ፡ ወኢይትአምኑ ፡ በእምኃ ፡ ወያንብቡ ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ በንባብ፡ማኅዘኒ።

ግብረ፡ሐዋርያት።

ምዕ፩፡፲፭–፳።

፲፭ ወውእተ፡አሚረ፡ተንሥአ፡ጴጥሮስ፡ወቆመ፡ማእከለ፡አኀዊሁ፡ወይቤሎሙ፡እንዘ፡ሀለዉ፡ሀየ፡ሰብእ፡ወየአክሉ፡ምዕተ፡ወዕሥራ።

፲፮ ስምዑ፡አ፡አኀዊነ፡አማን፡ሀለዎ፡ይብጻሕ፡ቃለ፡መጽሐፍ፡ዘይቤ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በአፈ፡ዳዊት፡በእንተ፡ይሁዳ፡ዘውእቱ፡ኮኖሙ፡መርሐ፡ለእለ፡አኀዝዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ።

፲፯ እንዘ፡ኍሉቍ፡ውእቱ፡ምስሌነ፡ወከፈሎ፡ዘንተ፡መልእክተ።

፲፰ ወእምዝ፡ተሣየጠ፡ዐጸደ፡በዐስበ፡ዐመፃሁ፡ወተነፅነ፡ላዕለ፡ምድር፡በገጹ፡ወተሠጥቀ፡ገቦሁ፡ወተክዕወ፡ኵሉ፡አማዑቲሁ።

፲፱ ወተሰምዐ፡ነገሩ፡በኀበ፡ኵሎሙ፡እለ፡ይነብሩ፡በኢየሩሳሌም፡ወተሰምየ፡ዓጸዱ፡ዘተሣየጠ፡በዐስቡ፡ሰመይዎ፡በነገሮሙ፡ሐቅለ፡ድማህ፡ገራህተ፡ደም፡ብሂል።

፳ በከመ፡ይቤ፡መጽሐፈ፡መዝሙር፡ለትኩን፡ሀገሩ፡በድወ፡ወአልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴታ፡ወሢመቶሂ፡ይንሣእ፡ባዕድ።

ክፍል፡፪።
ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፶፪፡፩፡፲፯፡፳፪።

፩ እመልክተ፡ሲኖዲቆን፡ዘአብ፡ንጹሕ፡አባ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ፡ኀበ፡አቡነ፡ሚናስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእለእስክንድርያ።

ወሶበ፡ፈነወ፡ንጉሠ፡ሮሜ፡ወሞቅሖ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ፡በውነት፡ምስጋና፡ይገባል፡ይበሉ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ይበሉ ፤ የዳዊትንም ፡ መዝሙር፡ይድገሙ፤ካህኑም፡ቤተ፡ክርስቲ ያኑን ፡ እያጠነ ፡ ይዞር ፤ እጅ ፡ አይነሳው ፤ በንባብ ፡ ማኅዘኒ ፡ ማለት ፤ (በውርድ ፡ ንባብ) የሐዋርያትን፡ሥራ፡ያንብቡ።

የሐዋርያት፡ሥራ።

ምዕ፩፡፲፭–፳።

፲፭ ያን፡ጊዜም፡ጴጥሮስ፡ተነሥቶ፡በወንድሞቹ፡መካከል ፡ ቆመ ፤ መቶ ፡ ሃያ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ከዚያ፡ሳሉ፡እንዲህ፡አላቸው።

፲፮ ወንድሞቻችን ፡ ስሙ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዳዊት ፡ አድሮ ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ የተናገረው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ አለው ፤ ይኸውም ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን፡ ለያዙት፡መሪ፡የሆናቸው፡ነው።

፲፯ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ የተቈጠረና ፡ ይኸንንም ፡ አገልግሎት፡ያደለው፡ሲሆን።

፲፰ ከዚህም፡በኋላ፡በዐመፅ፡ዋጋው፡ቦታን፡ገዛ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ፍግም ፡ ብሎ ፡ ወድቆ፡ጐኑ፡ተቀዶ፡የውስጥ፡አንጀቱ፡ሁሉ፡ተዘረገፈ።

፲፱ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩት ፡ ሁሉ ፡ ዜናው ፡ ተሰማ፤በዐመፅ፡ዋጋ፡የገዛውን፡ቦታ፡በቋንቋቸው ፡ ሐቅለ ፡ ድማህ ፡ አሉት ፤ ይኸውም ፡ የደም፡ምድር፡ማለት፡ነው።

፳ የመዝሙር፡መጽሐፍ፡እንደ፡ተናገረ፡አገሩ፡ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሁን ፤ በውስጥዋም ፡ የሚቀመጥ፡አይኑር፤ሹመቱንም፡ሌላ፡ይውሰድበት፡ብሎ።

ክፍል፡፪።
የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፶፪፡፩፡፲፯፡፳፪።

፩ ንጹሕ፡አባት፡የአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ ከላከው፡መልእክት።

የሮሙም፡ንጉሥ፡ልኮ፡የአንጾኪያውን፡ሊቀ፡

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእንጸኪያ፡
ለአቡነ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእንጸኪያ፡
ወወሰዶ፡ቍስጥንጥንያ፡ወአብጽሖ፡ኀቤሁ፡
እንዘ፡ሀሎ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘቍስጥንጥንያ፡
ወካህናት፡ወመላሕቅተ፡ንጉሥ።ወተዋሥኦ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘቍስጥንጥንያ።

፲፯፡ ወይቤ፡ ታጤይቁነኑ፡ እምነገረ፡ ቅዱስ፡ ዘዘከ ቄርሎስ፡ ስምዐ፡ ዝንቱ፡ ተዋሕዶ፡ ዘዘከ
ርከሙ፡ወአስፈውናሁ፡ከመ፡ንሕነ፡ንገብር፡
ዘንተ። (ቊጥር፡እያለፈ፡እያለፈ፡ነው።)

፳፬፡ ወከመ፡ ዝ፡ ውእቱ፡ ርትዐ፡ ስምዓት፡
ዘጸሐፍነ፡ ለሙ፡ በጽርእ፡ እንዘ፡ ናጸድቅ፡
ትምህርታተ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ።

ወቅድመ፡ ዘዘከረ፡ ቄርሎስ፡ እምድርሳነ፡
ቅዱስ፡አትናቴዎስ፡በእንተ፡ሥጋዌሁ፡ለእግ
ዚአብሔር፡ቃል፡ውስተ፡ድርሳኑ፡እንበይነ፡
ድያድርስ፡ወእንበይነ፡ሳምሳጢ።

ወይቤ፡ውእቱሰ፡ክመ፡ውእቱ፡ወልደ፡እግዚ
አብሔር፡በመንፈስ፡ውእቱሰ፡ክመ፡ወልደ፡
ዕጓለ፡እመሕያው፡በሥጋ።

ወኢንቤ፡ ከመ፡ ቦቱ፡ ክልኤቱ፡ ህላዌያት፡
ለዝኩ፡ ወልድ፡ ዋሕድ፡ አሐዱ፡ ዘይሰገድ፡
ወካልኡ፡ዘኢይሰገድ፡አላ፡አሐዱ፡ህላዌ፡ዘእ
ግዚአብሔር፡ ቃል፡ ዘተሠገወ፡ ወሎቱ፡
ንሰግድ፡ምስለ፡ሥጋሁ፡አሐተ፡ስግደተ።

፳፭፡ እምቃለ፡ ቅዱስ፡ ዮልዮስ፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ፡
ዘሮሜ፡ ዘይቤ፡ በድርሳኑ፡ እንዘ፡ ያስተኑ
ፍሮሙ፡ ለዐላውያን፡ በእንተ፡ ተሠግዎቱ፡
ለእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ወዕሪናሁ፡ ምስለ፡
መለኮት፡ወድንግልሰ፡ሶበ፡ወለደቶ፡ለሥጋ፡
ለቃልሂ፡ ወለደቶ፡ ወበእንተ፡ ዝንቱ፡
ወላዲተ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ይእቲ።
ወአይሁድኒ፡ሶበ፡ሰቀልዎ፡ለሥጋ፡ሰቀልዎ፡
ለእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ወአልቦ፡ ፍልጠት፡
ማእከለ፡ቃል፡ወሥጋ፡ለግሙራ።

፳፮፡ ወካዕበ፡ይቤ፡በመልእክቱ፡ኀበ፡ዲዮናስዮስ፡
ኤጲስቆጶስ፡ዘቆጵሮስ፡ያጌብሮሙ፡እንከሰ፡
ለእለ፡ ይትአመኑ፡ በክልኤቱ፡ ህላዌያት፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ጳጳሳት፡አባታችን፡አባ፡ዮሐንስን፡በአጋዘው፡
ጊዜ፡ወደ፡ቍስጥንጥንያ፡ወሰደው፤የቍስጥንጥ
ንያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ካህናቱም፡የንጉሡም፡ሹማ
ምንት፡ ሳሉ፡ ወደ፡ እርሱም፡ አደረሰው፤በአቀ
ረበው፡ጊዜ፡የቍስጥንጥንያው፡ሊቀ፡ጳጳሳትም፡
ተከራከረው።

፲፯፡ የተናገራችሁትን ፡ የዚህን ፡ የተዋሕዶ፡
ምስክር፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡ከተናገረው፡አምጥ
ታችሁ ፡ ታስረዱናላችሁን ፡ አለ፤ አዎን፡
ይህን፡እናመጣለን፡አልነው።

፳፬፡ ቅዱስ፡ቄርሎስ፡ያስተማረውን፡ትምህርት፡
እያስረዳን፡በጽርእ፡ቋንቋ፡የጻፍንላቸው፡የም
ስክሮች፡ዕውነተኛነት፡እንደዚህ፡ነው።

የጻፍነውም፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ሰው፡ስለ፡
መሆኑ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡አትናቴዎስ፡ከተና
ገረው፡ከድርሳኑ፡አምጥቶ፡ስለ፡ድያድርስና፡
ስለ፡ ሳምሳጢ፡ ጳውሎስ፡ በጻፈው፡ ድርሳን፡
አስቀድሞ፡የተናገረውን፡ነው።

በመለኮት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ፤
እርሱ፡ መቼም፡ መች፡ ያው፡ ነው፤በሥጋም፡
ከሰው ፡ የተወለደ ፡ እርሱ ፡ መቼም፡ መች፡
ያው፡ነው።

ተቀዳሚ፡ተከታይ፡ለሌለው፡ለዚህ፡ለወልድ፡
አንዱ፡የሚሰገድለት፡አንዱ፡የማይሰገድለት፡
ሁለት፡ባሕርያት፡እንዳሉት፡አንናገርም፤ሰው፡
የሆነ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡አንድ፡ባሕርይ፡
ነው፡እንጂ፤ሥጋው፡ልዩ፡ነው፡ሳንል፡ለእርሱ፡
አንዲት፡ስግደትን፡እንሰግዳለን፡ብሏል።

፳፭፡ የሮም፡ ኤጲስቆጶስ፡ ቅዱስ፡ ዮልዮስ፡ መናፍ
ቃንን፡ ዘልፎ፡ እግዚአብሔር፡ ቃል፡ ሥጋን፡
የመዋሐዱን፡ሥጋም፡ከመለኮት፡ጋራ፡አንድ፡
የመሆኑን፡ነገር፡በተናገረበት፡ድርሳኑ፡ከተና
ገረው፡ቃል፤ድንግልስ፡ሥጋን፡በወለደችው፡
ጊዜ፤ቃልንም፡ወለደችው፤ስለዚህ፡የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡እናት፡ተባለች።
አይሁድም፡ሥጋን፡በሰቀሉት፡ጊዜ፡እግዚአ
ብሔር፡ቃልን፡ሰቀሉት፤በቃልና፡በሥጋም፡
መካከል፡ፈጽሞ፡ልዩነት፡የለም።

፳፮፡ ዳግመኛ፡ ወደ፡ ቆጵሮስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ወደ፡
ዲዮናስዮስ፡ በላከው፡ መልእክቱ፡ እንዲህ፡
አለ፤ እንኪያስ፡ ሁለት፡ አካል፡ ሁለት፡

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

ለአሐዱ፡ ይሰግዱ፡ ወለካልኡ፡ ኢይሰግዱ፡ ለአምላካዊ፡ ይጠመቁ፡ ወበትስብእታዊ፡ ኢይጠመቁ።

አመሰ፡በሞተ፡ክርስቶስ፡ ንጠመቅ፡ በ፩ዱ፡ ሀላዌ፡ ንትአመን፡ ወኢንከፍሎ፡ ለእግዚአብሔር፡ቃል፡ ኀበ፡ ክልኤቱ፡ ክፍል፡ ወኢ፡ ኀበ፡ክልኤቱ፡ህላዌያት።

ንሕነሰ፡ ነአምን፡ ወንትአመን፡ በአሐዱ፡ ሀላዌ፡ ወበአሐዱ፡ ገጽ፡ ወበአሐዱ፡ አካል፡ ቃል፡ዘተሠገወ፡ወተሰብአ።

ወንሰግድ፡ ሎቱ፡ ምስለ፡ ሥጋሁ፡ አሐተ፡ ስግደተ፡ ወመለኮትሰ፡ ኢሐማሚ፡ ውእቱ፡ ወበሥጋ፡ ባሕቲቱ፡ ሐመ፡ ከመ፡ ትኩን፡ ጥምቀትነ፡ በእግዚአብሔር፡ ወፍጻሜሃኒ፡ በሞተ፡ እግዚአብሔር።

በረከቶሙ፡ ለእሉ፡ መምህራን፡ የሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

በጸሎተ፡ ሐሙስ፡ ነግህ፡ ዘይትነበብ፡ ተግሣጽ፡ ዘዮሐንስ፡ አፈ፡ ወርቅ፡ በረከቱ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዛቲ፡ ይእቲ፡ ዕለት፡ እንተ፡ ንቀርብ፡ ኀበ፡ ዘንቲ፡ማእድ፡ መፍርህ። ንቅረብኬ፡ ኵልነ፡ በንቁሀትነ፡ወናስተዳሉ፡ወኢይኩን፡አሐዱ፡ እምኔነ፡ከመ፡ ይሁዳ፡ ወኢ፡ እኩየ፡ ዘቦቱ፡ ጽልሑት።

ወኢይበል፡ በልሳኑ፡ እኩየ፡ ነገረ፡ ወኢም ንትኒ፡ ወበልቡ፡ ካልአ። እስመ፡ ነዋ፡ ክርስቶስ፡ ሀሎ፡ዝየ፡ዘሜጠ፡ለውእቱ፡ማዕድ፤ ወውእቱ፡ጊዜ፤ነዋ፡ውእቱ፡በዐይኑ፡ይኔጽር፡ ነዋ፡ዝየ።

ወአልቦ፡ውእቱ፡ዘይዌልጦ፡ለቍርባን፡ንቡር፡ ዘይሬስዮ፡ሥጋሁ፡ወደሞ፡ለክርስቶስ።

አላ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ዕንለ፡ እመሕያው፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ባሕርይ፡ብለው፡ለሚያምኑ፡ለአንዱ፡እንዲ ሰግዱ፡ለአንዱ፡እንዳይሰግዱ፡በአምላካዊ፡ ባሕርይ፡ እንዲጠመቁ፡ (እንዲከብሩ)፡ በሰብአዊ፡ባሕርይ፡እንዳይጠመቁ፡(እንዳይ ከብሩ)፡ግድ፡ይሆንባቸዋል።

በክርስቶስ፡ሞት፡የምንጠመቅ፡(የምንከብር)፡ ከሆነ፡አንድ፡ባሕርይ፡ብለን፡እናምናለን፤እግ ዚአብሔር፡ቃልን፡ወደ፡ሁለት፡ወገን፡ወደ፡ ሁለት፡ባሕርያት፡አንከፍለውም፤

እኛስ፡ነፍስን፡ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡የሆነ፡ ቃል፡አንድ፡ባሕርይ፡አንድ፡ገጽ፡አንድ፡ አካል፡እንደሆነ፡እናምናለን፤እንታመናለን፤

ሥጋው፡ልዩ፡ነው፡ሳንል፡ለእርሱ፡አንድ፡ ስግደትን፡እንሰግዳለን፤መለኮትስ፡ሕማም፡ የሌለበት፡ ነው፤ ጥምቀታችን፡ (መክበ ራችን)፡ በእግዚአብሔር፡ ትሆን፡ ዘንድ፡ ፍጻሜዋም፡በእግዚአብሔር፡ሞት፡ትሆን፡ ዘንድ፡ብቻ፡በሥጋ፡ታመመ፡እንጂ።

የእነዚህ፡መምህራን፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

በረከቱ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ለዘላለሙ፡ ትኑርና፡ በጸሎተ፡ሐሙስ፡በነግህ፡የሚነበብ፡የዮሐንስ፡ አፈወርቅ፡ምክር፡ተግሣጽ፡ይህ፡ነው።

፩፤ ወደዚህ፡ወደሚያስፈራው፡ማእድ፡የምንቀርብ ባት፡ቀን፡ይህች፡ናት፤እንግዲህ፡ነቅተን፡ እንቅረብ፤ ራሳችንንም፡ እናዘጋጅ፤ ከእኛ፡ ውስጥ፡አንዱም፡አንዱ፡እንደ፡ይሁዳ፡አይሁን፤ ወይም፡ሽንገላ፡ያለበት፡ክፉ፡አይሁን።

፪፤ በአንደበቱም፡ ምንም፡ ምን፡ ክፉ፡ ነገርን፡ አይናገር፤ በልቡም፡ ሌላ፡ ኀሳብ፡ አያስብ፤ በዚያን፡ጊዜ፡ማእዱን፡የለወጠው፡ክርስቶስ፡ እነሆ፡በዚህ፡አለና፤እነሆ፡ከዚህ፡ሁኖ፡በዐይኑ፡ እነሆ፡በዚህ፡አለ።ወደዚህ፡የሚመለከት፡እነሆ፡በዚህ፡አለ።

፫፤ እርሱ፡የተዘጋጀውን፡ቍርባን፡ለውጦ፡የክር ስቶስ፡ሥጋና፡ደም፡የሚያደርገው፡ነውና።

፬፤ ይህም፡እንደ፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ባሕርይ፡አይደለም፤

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

በግዕዛን ፡ ዳእሙ ፡ ውእቱ ፡ ክር ስቶስ ፡ ዘተሰቅለ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ በአ በእንቲአነ ፡ ወካህን ፡ ይፌጽም ፡ ምሳሊሁ።

፳፮፤ ወንሕነኒ፡ንብል፡በከመ፡ይቤ፡ውእቱ፡ጳጋሰ፡ ወክሂል፡ለእግዚአብሔር፡ውእቱ።

፳፯፤ ይቤ፡ገ፡ውእቱ፡ሥጋየ፡ዛቲ፡ቃል፡ትዌልጥ፡ ቍርባነ፡ዘንቡር።

፳፰፤ ወበከመ ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘይቤ ፡ በውስተ ፡ አሪት ፡ ብዝኀ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልዕዋ ፡ ለምድር፡ይቤ፡ምዕረ፡ወኮነ፡ይገብር፡ውስተ፡ ፍጥረትነ፡ትገዝምዳተ፡ወትውልዳተ።

፳፱፤ ከማሁኬ ፡ ገንቱ ፡ ቃል ፡ ይቤ ፡ ምዕረ ፡ ወውእቱኬ ፡ ቃል ፡ ይፌጽም ፡ ኵሎ ፡ መሥዋዕተ ፡ ዘንቡር ፡ ውስተ ፡ ኵሎን ፡ አብያተ፡ክርስቲያናት፡ዘኵላ፡ምድር።

፴፤ ወበእንተዝ፡ኢ፡መፍትው፡ይቅረብ፡ኅቤሃ፡ ዘቦቱ፡ቂም፡ውስተ፡ልቡ፡ወጽልሑት፡ውስተ፡ ኅሊናሁ፡ወኢ፡ዘውስተ፡ነፍስቱ፡ጕህሉት፡ እምዝ፡ከመ፡ኢይንሣእ፡ለነፍሱ፡ኵነኔ።

፴፩፤ እስመ፡በውእቱ፡ጊዜ፡እምድኅረ፡ነሥአ፡ ይሁዳ፡ቍርባነ፡ቦአ፡ላዕሌሁ፡ሰይጣን።

፴፪፤ አኮ ፡ እንከሰ ፡ ስሑት ፡ ለፍትሐ ፡ እግ ዚአብሔር፡ እግዚእነ ፡ ዳእሙ ፡ ነሳር ፡ ለይ ሁዳ ፡ በእንተ ፡ ጕህሉቱ ፡ ለአጠይቆ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይትሜጠዉ ፡ ቁርባነ ፡ እንዘ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ይሰርር ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ ሰይጣን ፡ ወይበውእ ፡ ወየኀድር ፡ ውስቴቶሙ፡በከመ፡ኮኖ፡ለይሁዳ፡በውእቱ፡ ጊዜ፡እስመ፡ጸጋ፡በከመ፡ትበቍዕ፡ለእለ፡ ይደልዎሙ።

፴፫፤ ወዘሰ ፡ ዘእብል ፡ ዘንተ ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ እክላዕክሙ፡ እምተመጥዎ ፡ ምሥጢሩ ፡ ንጹሕ ። ዳእሙ ፡ ትትዐቀቡ ፡ ወትዕቀቡ ፡ ዘንተ።

፴፬፤ ወኢይኩን፡መኑሂ፡እምኔክሙ፡ከመ፡ይሁዳ፡ ወኢይምጻእ፡ዝየ፡ዘቦቱ፡ቂም፡ውስተ፡ልቡ፡ ወኢ፡ሕምዝ፡ወኢ፡ጕህሉት፡እስመ፡ሲሳይ፡ መንፈሳዊ፡ውእቱ፡ቍርባን።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከሁለት፡ አካል፡አንድ፡አካል፡የሆነ፡ስለ፡እኛ፡በዕንጨት፡ መስቀል፡ላይ፡የተሰቀለ፡ክርስቶስ፡ነው፡እንጂ፡ ካህኑም፡በዚሁ፡አምሳል፡ይፈጽማል።

፳፮፤ እኛም ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ችሎታና፡ ስጦታ፡ለእግዚአብሔር፡ነው፡እንላለን።

፳፯፤ ይህ ፡ ሥጋየ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ይቺ ፡ ቃል ፡ የተዘጋ ጀውን፡ቍርባን፡ትለውጣለች።

፳፰፤ እንደዚህም፡ያ፡ቃል፡በኦሪቱ፡ብዙ፡ተባዙ፡ ምድርን፡ምሉዋት፡ብሎ፡አንድ፡ጊዜ፡የተና ገረው ትውልዶችን ፤ ነገዶችን ፡ በማስገኘት፡ በተፈጥሮአችን፡ባሕርይ፡ሲሠራ፡ይኖራል፡

፳፱፤ እንደዚሁም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ ተናገረ፤ ያ ፡ ቃል ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ በአሉ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚዘጋጀውን፡ መሥዋዕት፡ሁሉ፡ሲፈጽም፡ይኖራል፡

፴፤ ስለዚህ ፡ በልቡ ፡ ቂም ፡ በኅሳቡም ፡ ሽንገላ፡ በሰውነቱ ፡ ተንኮል ፡ ያለበት ፡ እንግዲህ፡ ወደርሷ ፡ ሊቀርብ ፡ አይገባውም ፤ ከሱ፡ የተነሣ፡በነፍሱ፡ላይ፡ፍዳ፡እንዳያመጣ፡

፴፩፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይሁዳ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን፡ ከተቀበለ፡በኋላ፡ሰይጣን፡አድሮበታልና፡

፴፪፤ እንግዲህ፡የበደለ፡የጌታ፡የእግዚአብሔር፡ ፍርድ፡በነፍሱ፡ለመቀበል፡ብቻ፡አይደለም፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሰይጣን ፡ እንዳደረ ፡ ስለክፋቱ፡ ልናው ፡ ሐሣር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሳይገባቸው፡ ሥጋውን፡ደሙን፡በሚቀበሉ፡ላይ፡ሰይጣን፡ መጥቶ ፡ በውስጣቸው ፡ እንዲያድርባቸው፡ እኛን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ፤ በዚያን ፡ ጊዜ፡ በይሁዳ፡እንደ፡ሆነበት፡ለሚገባቸው፡የምት ጠቅም፡ስጦታ፡ናትና።

፴፫፤ ይህንንም ፡ የምለው ፡ ንጹሕ ፡ የሆነው፡ ሥጋውን፡ደሙን፡ከመቀበል፡ልንከለክላችሁ፡ አይደለም፤ነገር፡ግን፡ይህን፡የምንነግራችሁ፡ ልትጠብቁትና፡ልትጠነቀቁበት፡ነው፡እንጂ፡

፴፬፤ ከእናንተ፡ማንም፡ማን፡እንደ፡ይሁዳ፡ሁኖ፡ በልቡ ፡ ቂም ፡ ወይም ፡ መርዝ ፡ የሆነ ፡ ነገር፡ ሽንገላ ፡ ይዞ ፡ ወደዚህ ፡ ማእድ ፡ አይምጣ፡ ሥጋውና፡ደሙ፡መንፈሳዊ፡ምግብ፡ነውና፡

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

…ወበከመ፡ሲሳይ፡ሥጋዊ፡ለእመ፡በልዕዎ፡
…እንዘ፡ሀሎ፡ደዌ፡እኩይ፡ውስተ፡ክርሥ፡
…ይጸንዕ፡ሕማመ፡ዲበ፡ድውይ።

…አኮ፡እምግዕዘ፡ሲሳይ፡አላ፡እምሕማም፡
ዘሀሎ…።

…ወከመ፡ዝ፡ይእቲ፡ምሥጢር፡መንፈሳዊት፡
…ለእመ፡በአት፡ውስተ፡ነፍስ፡ብእሲ፡ወይእቲ፡
…ምልአት፡እምእከይ፡ታማስና፡ወታሀጕላ።

…አኮ፡እምግዕዘ፡ምሥጢራት፡አላ፡
…ሰሙ፡እምሕማመ፡ነፍስ፡እንተ፡
ተመጠወት።

…ናድሪከ፡ነፍሳቲነ፡ወናንጽሕ፡አልባቢነ፡
…ሰብ፡ፈቀድነ፡ለተመጥዎ፡እማእደ፡ሕይወት፡
ወለእመ፡ኮነ፡ዘንትሜጠ፡እማእድ፡ጽሩይ፡
ወንጹሕ።

…ወለእመ፡ትቤ፡እፎ፡ናጸሪ፡ወናነጽሕ፡አነ፡
…አርእየከ፡ለእመ፡ሀሎ፡ውስተ፡ልብከ፡ቂም፡
…ዲበ፡እኁከ፡ኅድጋ፡ለመዐት፡ወግድፋ፡
…ለጽልእ፡እስመ፡አንተ፡ትቀርብ፡ኀበ፡
…መሥዋዕት፡መፍርህት።አክብራ፡እንከ፡
ወፍርሃ፡እስመ፡ክርስቶስ፡ማእከለ፡እደዊከ፡
ተጠብሐ።

…ወዘተጠብሐሰ፡ከመ፡ይግበር፡ሰላመ፡
ማእከለ፡ሰማያውያን፡ወምድራውያን፡
እስመ፡ውእቱ፡ወለጠ፡ነፍሶ፡ህየንተ፡እለ፡
ተሰቅሎ፡ሰብእ።

…ወአንተሰ፡ዘትጸልእ፡ቢጸከ፡ዘዕሩይ፡
በግብርናት፡ወውእቱ፡ኢተከልአ፡እሞት፡
በእንቲአከ፤ወአንተሰ፡ኢኀደገ፡መዐተ፡
ዘማእከሌከ፡ወማእከለ፡እኁከ፤ወበአይ፡
ግብር፡ተሐውር፡አንተ፡ኀበ፡ዝንቱ፡
ምሥጢር፡ግሩም፡ወበአይ፡ኀሩየ፡
ታስተርኢ።

…ወለእመ፡ትቤ፡እስመ፡አነ፡ጽሑቅ፡ይእዜ፡
ወእበጽሕ፡ኀበ፡ትካዝየ፡ትቤ፡ውስተ፡ቅኔ፡
…ንቱ፡ዓለም፡ወውስተ፡ፍቅሩ።

…ወባሕቱ፡ኢሰቀሉከ፡በከመ፡ሰቀሉ፡
አይሁድ፡እግዚአሙ።

…ወአንተሰ፡ኢትትየዋህ፡ለጸላኢከ፡ወኢት
…ትከዝ፡ለነፍስከ።እስመ፡እግዚአብሔር፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፲፬፡ ክፉ፡ደዌ፡በሆድ፡ሳለ፡ሥጋዊ፡ምግብን፡
ቢመገቡት፡በበሽተኛው፡ላይ፡ደዌን፡እንደ
ሚጨምርበት፡እንዲሁ፡ነው።

፲፭፡ ይህም፡ከምግቡ፡ጠባይ፡አይደለም፤
አድሮበት፡ካለው፡ደዌ፡የተነሣ፡ነው፡እንጂ።

፲፮፡ እንደዚሁም፡መንፈሳዊት፡ምሥጢር፡የሆነች፡
ሥጋውና፡ደሙ፡ክፋትን፡ከተመላች፡ከሰው፡
ሰውነት፡ውስጥ፡ብትገባ፡ፈጽማ፡ትጐዳለች።

፲፯፡ ይህም፡ከሥጋው፡ከደሙ፡አይደለም፤በደዌ፡
ኃጢአት፡ሁና፡ከተቀበለች፡ከደዌ፡ነፍስ፡
ነው፡እንጂ።

፲፰፡ ከሕይወት፡ማድ፡ለመቀበል፡በፈለግን፡ጊዜ፡
ሰውነታችንን፡ልቡናችንን፡ፈጽመን፡
እናንጻ፤ከጸሩና፡ከነጻ፡ማእድ፡የምንቀበል፡
ከሆን።

፲፱፡ ሰውነታችንን፡ፈጽመን፡የምናነጻውና፡የምና
ጠራው፡እንዴት፡ነው፡ብትል፡እኔ፡አሳይ
ሃለሁ፤በወንድምህ፡ላይ፡በልብህ፡ቂም፡ቢኖር፡
ቍጣህንና፡ጥላቻህን፡ፈጽመህ፡ተዋት፤አንተ፡
ወደምታስፈራ፡መሥዋዕት፡ትቀርባለህና፤
እንግዲህ፡አክብራት፤ፍራት፤ክርስቶስ፡
በእጆችህ፡መካከል፡ተሠውቷልና።

፳፡ የተሠዋውም፡በምድራውያንና፡በሰማያ
ውያን፡መካከል፡ፍቅር፡አንድነትን፡ያደርግ፡
ዘንድ፡ነው፤እርሱ፡በተከተሉት፡ሰዎች፡
ፈንታ፡ነፍሱን፡ለውጧልና።

፳፩፡ አንተ፡ግን፡በተገዢነት፡የሚተካከልህን፡
ወንድምህን፡የምትጠላ፡እርሱም፡ጌታ፡ስለ፡
አንተ፡ከመሞት፡ያልተከለከለ፡ሲሆን፤
አንተ፡ግን፡በወንድምህና፡በአንተ፡መካከል፡
ያለውን፡ቂም፡በቀል፡ሳትተው፡ወደዚህ፡
ግሩም፡ምሥጢር፡በምን፡ሥራ፡ትቀርባለህ?
በየትስ፡ክርስቲያንነትህን፡ትገልጣለህ?

፳፪፡ እኔ፡ዛሬ፡የተጋሁ፡ሁኛለሁና፡ወደ፡
መተከዝም፡እደርሳለሁ፡ብትል፡ወደ፡ዓለም፡
ተገዥነትና፡በፍቅሩም፡ወደ፡መያዝ፡እደር
ሳለሁ፡አልክ።

፳፫፡ ነገር፡ግን፡አይሁድ፡ጌታቸውን፡እንደ፡
ሰቀሉ፡አልሰቀሉህም።

፳፬፡ አንተ፡ግን፡ለጠላትህ፡ሞኝ፡አትሁን፡ተስፋ፡
ቆርጠህም፡በሰውነትህ፡አትተክዝ፡ልዑል፡

Scanned by CamScanner

ከመ : ነፍስ : ልዑል : ኢይጸልእ : ምንተኒ : ቀናኢ፡ወመስተበቅል።

፳፭፤ ወአጠየቀ : ቃሎ : ወይቤ : ሶበ : ታቀርብ : ቍርባነከ : ቅድመ : ምሥዋዕ : ወተዘከርከ : በሀየ : ከመ : ቦ : እኁከ : ዘተሐየሰከ : ኅድግ : ሀየ፡ ቍርባነከ : ሑር : ወተዓረቅ : ምስለ : እኁከ።

፳፮፤ ወይእዜኒ : አነ : እሬእዮሙ : ለብዙኃን : ይትመጠዉ፡ሥጋሁ፡ለእግዚእነ፡ክርስቶስ።

፳፯፤ እሬ : እንከ : ተበውሖ : ለሐዊር : እንዘ : ይተልዉ : በዝንቱ : ልማድ : ዘአልቦ : ሕግ : ዘይገብሩ : ከመ : ገ : ሶበ : በጽሐ : ጾም : ወፋሲካ ። ወኢ : መፍትው : ይነጽሩ : ጾመ : ወኢ : በዐላተ : ዳእሙ : አንጽሖ : ነፍስ : ወሥጋ።

፳፰፤ ወእምድኅረ : ዝንቱ : ይትመጠዉ : እምሥጢራተ : ቅድሳት : እስመ : ኢኮነ : ርኩሰ : ወኢደነሰ፡ኢ፡በበዐል፡ወኢ፡በጾም።

፳፱፤ ወኢኮነ፡ድልወት፡ይትመጠዉ፡እምሥጋሁ፡ መፍርህ : ለቡ : እንከ : እሬ : ኮኑ : ውስተ : ሥርዐት : ብሉይ : ሶበ : ሐሩ : ውስተ : ምሥዋዕ፡ ኮኑ : ያጸርዩ : ነፍሶሙ : ጥንቁቀ : ጽርየተ : ወያስተናጽሑ : ነፍሰ : ወሥጋ : በኵሉ፡ምግባሮሙ።

፴፤ ወአንተሰ : ትቀርብ : ኀበ : ምሥዋዕ : ዘመላእክት : ይደነግፁ : ወይርዕዱ : እምኔሁ ፤ ወታቀርብ፡በአዕዳው፡ርኩሳት፡ወርሱሐት፡ ወሥጋ : ግሙን : ወትደፍር : ኀበ : ዝንቱ : ማእድ፡ወትትኃበል።

፴፩፤ ወሚመ : ኢሰማዕከኑ : ዘይብል : ቅድሳት : ለቅዱሳን።

ወዘኮነ : ውስተ : ጸጋ : ነሳሒያን : ወለእመ : አልቦ : ይባእ : እምዝንቱ : መካን።

፴፪፤ ወፈቀድኩ : እኑኅ : ነገረ : በእንተ : ዝንቱ : ወባሕቱ : ከልአኒ : ሐዘን : ልብየ : በእንቲ : አክሙ።

፴፫፤ ለብዉ : እንከ : ወእንጽሖ : ልበክሙ : ወሥጋክሙ : ከመ : ትትመጠዉ : በድልወት



እግዚአብሔር : እንደ : ቂመኛና : እንደ : ተበቃይ፡ምንም፡ምን፡አይጠላምና።

፳፭፤ በቃሉም : አስረድቷል ፤ እንዲህ : ሲል : መባህን፡ወደ፡መሠዊያው፡በምታቀርብበት፡ ጊዜ : የተጣላህ : (የተጣላኸው) : ወንድም : እንዳለ : ብታስብ : መባህን : ከዚያ : አኑረህ፡ ሂደህ፡ከወንድምህ፡ጋር፡ታረቅ።

፳፮፤ አሁንም : እኔ : የጌታ : ክርስቶስን : ሥጋ፡ ሲቀበሉ፡ብዙዎችን፡አያቸዋለሁ።

፳፯፤ እንግዲህ፡ሕግ፡በሌለው፡በዚህ፡ልማድ፡እየተ ከተሉ፡ለመሔድ፡እንዴት፡ሠለጡ? ይህንንም፡የሚያደርጉ፡ፋሲካና፡ጾም፡ሲደርስ ነው ፤ ጾምን : ወይም : በዓላትን : መመልከት፡ ብቻ አግባብ : አይደለም ፤ ሥጋንና፡ ነፍስን፡ ሁልጊዜ፡ማንጻት፡ነው፡እንጂ።

፳፰፤ ከዚህ : በኋላ : ከሥጋው : ከደሙ : ይቀበል ፤ ልቡን : ካነጻ : በበዐልም : ቢሆን : በጾምም፡ ቢሆን፡ርኩስ፡አይሆንምና።

፳፱፤ ከሚያስፈራ : ሥጋው : ይቀበሉ : ዘንድ፡ አግባብ : አይደለም ፤ እንግዲህ : በኦሪት፡ ሥርዓት : እንኳን : ወደ : መስዋዕት : በሚሔዱበት : ጊዜ : በሥራቸው : ሁሉ : ተጠንቅቀው፡ ሰውነታቸውን : በውስጥ : በአፍአ፡ እንዴት፡እንደሚያነጹ፡አስተውል።

፴፤ አንተ፡ግን፡መላእክት፡ከእርሱ፡የሚደነግጡ ለትና፡የሚንቀጠቀጡለት፡ሲሆን፡ወደዚህ፡ መሥዋዕት : ትቀርበዋለህ ፤ በረከሰው፡ሰውነ ትህም፡ወደዚህ፡ማእድ፡በድፍረት፡ቀርበህ፡ ደፍረህ፡ትቀበለዋለህ።

፴፩፤ ወይስ : ሥጋው : ደሙ : ለበቁ : (ቅዱሳን)፡ ነው፡ያለውን፡አልሰማህምን?

በንስሐ : ውስጥ : ከአሉት : ወገን : የሆነ፡ ወደዚህ : ቦታ : ይግባ ፤ (ይገባ : ዘንድ)፡ የማይችል፡ቢሆን፡ነው።

፴፪፤ ስለዚህም : ነገር : ማስረዘም : ፈልጌ : ነበር፡ ነገር : ግን : ስለ : እናንተ : የልቤ : ሐዘን፡ ገታኝ።

፴፫፤ እንግዲህ : አስተውሉ ፤የጌታችንንና : የመድኃኒታችን : የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሥጋውንና፡ደሙን፡

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

እምሥጢራተ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
ዘሎቱ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ይእዜኒ ፡
ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በ፪ኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ዘከመ፡አስተርአየቶሙ፡ለአርድእት፡አባ፡
በርሱማ፡በአምሳለ፡ርግብ፡ጸዓዳ።

ወካ፡ሶበ፡አልጸቀ፡ጊዜ፡ጽባሕ፡ቆመ፡ቅዱስ፡
ግሬ ፡ በርሱማ ፡ ወጸለየ ፡ ጸሎተ ፡ ወበከየ፡
ወአንበበ፡እምነ፡መዝሙር፡ዘልማድ፡ወሥሩዕ፡
ከመ፡ይጸሊ፡ኪያሆን፡ጸሎተ፡ነግህ።

ወሶበ ፡ አርመሙ ፡ ነፋሳት ፡ አርመመ ፡
ማዕበለ፡ ባሕር ፡ ወኮኑ ፡ ርእሰ ፡ ሐመር ፡
ወኖትያት ፡ ወጉባኤ ፡ ብዙኅ ፡ ዘሀለዉ ፡
ውስቴታ ፡ ለሐመር፡ ይመስሎሙ ፡ ከመ ፡
ዘኢይሬእዩ ፡ ውእቶሙ ፡ የብሰ ፡ ወኢ
ይበጽሑ፡ኀቤሁ፡ለዓለም፡በእንተ፡ዘቀብጹ፡
ሐይወ።

ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ጸሎቶ ፡ ቅዱስ ፡ ርእዩ ፡
አርድእት ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ጸዐዳ ፡ እንዘ ፡
ትሰርር፡እስከ፡በጽሐት፡ኀቤሆሙ።
ወያደት ፡ ዐውደ ፡ ሐመር ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ፡
ወሰረረት ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ እንተ ፡ መጽአት ፡
እምኔሁ።

ወረሰየት፡ሐመረ፡ትሑር፡ድኅሬሃ፡ይእቲ፡
ያፍ፡ከመ፡ዘእሰርት፡ቦቱ።
ወይቤሉ፡መንፈቆሙ፡ለአርድእት፡ምንትኑ፡
ዝንቱ፡ያፍ፡ትእምርት፡ሠናይ፡ዘፈነዎ፡እግ
ዚአብሔር ፡ ኀቤነ ፡ ዘያበሥረነ ፡ ለወጺእ ፡
እምዝንቱ፡ሐመር፡በዳኅን።
ርእዩኬ፡አ፡ሕዝበ፡ክርስቲያን፡ውሉዳ፡ለእግ
ዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡
አምላክ፡ዘሥዩም፡ውስተ፡አፉክሙ፡ዝክረ፡
ስማ፡ዘከመ፡አድኀነቶሙ፡ለአርድእት፡አባ፡
በርሱማ ፡ ወአስተርአየቶሙ ፡ በአምሳለ ፡
ርግብ፡ጸዓዳ።
እስመ ፡ ረድኤታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። 

በሚገባ ፡ ትቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ልቡናችሁንና ፡
ሰውነታችሁን፡አንጹ።
፴፬፤ ለእርሱ፡ክብር፡ምስጋና፡ዛሬም፡ዘውትርም፡
ለዘላለሙ፡ይሁን፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡
ይኑርና፡ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡
የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመ
ቤታችን ፡ ማርያም ፡ ያረደገችው ፡ ተአምር ፡
ይህ፡ነው።

፩፤ ለአባ ፡ በርሱማ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ በነጭ ፡
ርግብአምሳል፡እንደ፡ተገለጸችላቸው።
፪፤ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ የንጋት ፡ ጊዜ ፡ ሲቃረብ ፡
መምህር ፡ ቅዱስ ፡ በርሱማ ፡ ቁሞ ፡ ጸለየ ፤
አለቀሰም ፤ ለነግህ ፡ ጸሎትም ፡ የተሠሩትንና ፡
የተለመዱትን፡ከዳዊት፡መዝሙር፡አነበበ።
፫፤ ነፋሱ፡ጸጥ፡ባለ፡ጊዜ፡ማዕበሉም፡ጸጥ፡አለ፤
ነገር ፡ ግን ፡ የመርከቡ ፡ ባለሥልጣንና ፡
የመርከቡ፡ሠራተኞች፡በመርከቡም፡ውስጥ፡
ተሰብስበው ፡ የነበሩ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡
የመዳንን ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ቆረጡ ፡ የብስን ፡
የማያዩና፡ወደ፡የብስም፡የማይደርሱ፡ይመስ
ላቸው፡ነበር።
፬፤ ቅዱስ፡በርሱማም፡ጸሎቱን፡በፈጸመ፡ጊዜ፡
ወደ፡እሳቸው፡እስክትደርስ፡በነጭ፡ርግብ፡
አምሳል፡ስትበርር፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡አዩ።
፭፤ እርሷም፡መርከቡን፡ሦስት፡ጊዜ፡ዞራ፡ወደ፡
መጣችበት፡ቦታ፡በረረች።

፮፤ ከመርከቢቱም ፡ እንደ ፡ ታሠረች ፡ መስላ ፡
በኋላዋ፡መርከቢቱን፡እንድትሄድ፡አደረገች።
፯፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እኩሌቶቹ ፡ ከዚህ ፡
መርከብ፡በደኅና፡ለመውጣት፡የሚአበስረን፡
እግዚአብሔር ፡ ወደኛ ፡ የላከው ፡ ይህ ፡ ያፍ ፡
በጎ፡ምልክት፡ምንድነው፡አሉ።
፰፤ አምላክን ፡ የወለደች ፡ የእመቤታችን ፡
የድንግል፡ማርያም፡ልጆቿ፡የሆናችሁ፡የክር
ስቲያን ፡ ወገኖች ፡ በአንደበታችሁ ፡ ስም ፡
አጠራሯ፡የተሾመባችሁ፡የአባ፡በርሱማን፡
ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ በነጭ ፡ ርግብ ፡ አምሳል ፡
ተገልጻ፡እንደ፡አዳነቻቸው፡እዩ።
፱፤ የእመቤታችን፡ማርያም፡ረድኤት፡በሁሉ፡

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

ይትረከብ ፡ በኵሉ ፡ ገጸ ፡ መካን ። ጸሎታ ፡ ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

**ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር ፡ ወመንክር ፡ ዘገብረ ፡ **እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ነገር ፡ በእንተ ፡ ፍሥሐ ፡ ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፩፤ ወጸቢሖ፡ዕለተ፡ፍሥሕ፡ወውእቱ፡ዕለተ፡ ኀሙስ ፡ ዘኮነ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ሖረ ፡ **እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ምስለ፡ዐሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡አርዳኢሁ፡ቢታንያ፡ወቦአ፡ቤተ፡ አልዓዛር፡ዘአንሥአ፡እምውስተ፡መቃብር፡ እምድኅረ፡ረቡዕ፡መዋዕል፡ወነበረ፡ህየ።

፪፤ አሜሃ ፡ ቀርበ ፡ በዓለ ፡ ናእት ፡ ዘይብልዎ ፡ ፋሲካ።

፫፤ ወይቤሎሙ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ** ፡ ለአርዳኢሁ፡እስመ፡ቀርበ፡ፋሲካ፡ወፈተውኩ፡ እግበር ፡ ምስሌክሙ ፡ ፋሲካ ፡ እምቅድመ ፡ ጊዜየ።

፬፤ ወእምዝ፡ጸውዖሙ፡ለጴጥሮስ፡ወለዮሐንስ፡ ፍቁሩ፡ወይቤሎሙ።

፭፤ ሑሩ ፡ ሀገረ ፡ ዘቅድሜክሙ ፡ ወትረክቡ ፡ ውስቴታ፡ብእሴ፡ዘይጸውር፡ጸሕበ፡ማይ፡ ወበልዎ ፡ ለበዓለ ፡ ውእቱ ፡ ቤት ፡ እስመ ፡ መድኅን፡ይፈቅድ፡ይግበር፡ፋሲካ፡ምስለ፡ አርዳኢሁ።

፮፤ ወውእቱ ፡ ያርእየክሙ ፡ ጽርሐ ፡ ዐቢየ ፡ ወንጹሐ፡ወሠናየ፡ወንጹፈ፡ወአስተዳልዉ፡ በህየ፡ኵሎ፡ዘይትፈቀድ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ወይበል ፡ ካህን ፡ ጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ **እግዚእ ብሔር ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።** ወያዕርግ፡ዕጣነ።

**ይ፡ዲ፡**ቅድመ፡ወንጌል።

መገ፤፲፬፡፳፩፤፲፪።

ወጽሕደ፡እምቅብዕ፡ነገሩ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ቦታ ፡ ይገኛልና ። ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

**ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘለ ዓለሙ ፡ ይደርብንና ፡ **ጌታችን ፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ስለ፡ አይሁድ ፡ ፋሲካ ፡ በዓል ፡ ያደረገው ፡ ድንቅ፡ ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ በፋሲካ ፡ በዓል ፡ ይኸውም ፡ ዕለተ ፡ ሐሙስ፡ ነው ፤ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ በዚያን ፡ ወራት ፡ **ጌታ፡ ኢየሱስ፡**ከዐሥራ፡ሁለቱ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ሂዶ ፡ ከዐራት ፡ ቀን፡ በኋላ፡ ከመቃብር ፡ ካስነሣው ፡ ከአልዓዛር፡ ቤት፡ገብቶ፡በዚያ፡ተቀመጠ።

፪፤ ያን፡ጊዜ፡ፋሲካ፡የሚሉት፡የቂጣው፡በዓል፡ ተቃርቦ፡ነበር።

፫፤ **ጌታ፡ኢየሱስም፡**ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ፋሲካ፡ ደርሷልና ፡ ጊዜየ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ፋሲካ ፡ አደርግ ፡ ዘንድ፡ ወደድኩ፡አላቸው።

፬፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚወደውን ፡ ዮሐንስን፡ ጴጥሮስን፡ጠርቶ፡እንዲህ፡አላቸው።

፭፤ ወደፊታችሁ ፡ ወደ ፡ አለች ፡ መንደር ፡ ሂዱ፤ በውስጥዋም ፡ የውኃ ፡ ማድጋ ፡ የተሸከመ፡ ሰው፡ታገኛላችሁ፤ከገባበት፡ቤት፡ደርሳችሁ፡ ለቤቱ፡ባለቤት፡መምህር፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ ጋራ፡ፋሲካ፡ለማድረግ፡ይወዳል፡በሉት።

፮፤ እርሱም፡ንጹሕ፡የሆነ፡የተነጠፈ፡መልካም፡ ታላቅ፡አዳራሽ፡ያሳያችኋል፤በዚያም፡የሚያስፈልገውን፡ሁሉ፡አዘጋጁ፡አላቸው።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ካህኑ ፡ የወንጌል ፡ ጸሎት ፡ የሆነ ፡ **እግዚአ ብሔር፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡**ይበል፡ ዕጣንም፡ያሳርግ።

**ዲያቆን፡**ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መገ፤፲፬፡፳፩፤፲፪።

ነገሩ፡ከቅቤ፡የለዘበ፡ሆነ።

Scanned by CamScanner

...ምንቱ፡ማዕበል፡ያስጥሙ።
...ለነ፡ጸዐለኒ፡እምተዓገሥኩ፤ወሶበሂ፡
...ፉኢ፡አዕበየ፡አፉሁ፡ላዕሌየ፡እምተኀባ
...ሁ።

## ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፪፡፩–፲፬።

...ቀርበ፡በዓለ፡መጸለት፡ዘስሙ፡ፋሲካ።
...የኀሥሡ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወጸሐፍት፡በዘ
...ይቀትልዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወኮኑ፡ይፈር
...ሀዎሙ፡ለሕዝብ።
...ቦአ፡ሰይጣን፡ውስተ፡ልበ፡ይሁዳ፡
...አስቆሮታዊ፡ዘእምዐሠርቱ፡ወክልኤቱ፡
...ኡልቍ።
...ሖረ፡ወተናገሮሙ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ወለጸ
...ሐፍት፡ዘከመ፡ያግብኦ፡ሎሙ።
...ወተፈሥሑ፡ወተሰነዐዉ፡ምስሌሁ፡ወተና
...ገርዎ፡የሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ወአስተኀለቁ፡
...ነገረ።
...የኀሥሥ፡ሳሕተ፡ያግብኦ፡ሎሙ፡እንዘ፡
...አልቦ፡ሰብእ።
...በጽሐት፡ዕለተ፡መጸለት፡አመ፡ይጠብሑ፡
...ፍሥሓ።
...ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለጴጥሮስ፡
...ወለዮሐንስ፡ሑሩ፡ወአስተዳልዉ፡ለነ፡
...ፍሥሓ።
...ወይቤልዎ፡በአይቴ፡ትፈቅድ፡ናስተዳሉ፡
...ለከ፡ፍሥሓ።
...ወይቤሎሙ፡በዊዐክሙ፡ሀገረ፡ትረክቡ፡
...ብእሴ፡ዘይጸውር፡ጸሕበ፡ማይ፡ወትልውዎ፡
...ኪያሁ፡ኀበ፡ቦአ፡ቤተ።
...ወበልዎ፡ለበዐለ፡ውእቱ፡ቤት፡ይቤለከ፡
...ሊቅ፡አይቴኑ፡ቤት፡ኀበ፡እበልዕ፡ፍሥሓ፡
...ምስለ፡አርዳእየ።
...ወውእቱ፡ያርእየክሙ፡ጽርሐ፡ዐቢየ፡
...ምንጹፈ፡ወሥርግወ፡ወበህየ፡አስተዳልዉ፡
...ለነ።
...ወሐዊሮሙ፡ረከቡ፡በከመ፡ይቤሎሙ፡ወአስ
...ተዳለዉ፡ፍሥሓ።
...ወሶበ፡ኮነ፡ጊዜሁ፡ለድራር፡ረፈቀ፡እግዚእ፡



እነሱ፡ማዕበል፡ናቸው፡ያሰጥማሉ። ጠላት፡ ሰድቦኝ፡ቢሆን፡በታገሥሁት፡ነበር። ጠላትም፡በእኔ፡ላይ፡አፉን፡ከፍ፡ቢያደርግ፡ በተሸሸግሁት፡ነበር፡ይበል።

## የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፪፡፩–፲፬።

፩፤ ፋሲካ፡የሚባለው፡የቂጣ፡በዓል፡ቀርቦ፡ነበር።

፪፤ የካህናት፡አለቆችና፡ጸሮችም፡ጌታ፡ኢየሱስን፡ሊገሉት፡ይሹ፡ነበር፤ግን፡ሕዝቡን፡ይፈሩአቸው፡ነበር።

፫፤ ቍጥሩ፡ከዐሥራ፡ሁለቱ፡ወገን፡በነበረው፡በአስቆሮቱ፡ይሁዳ፡ልብ፡ሰይጣን፡ገባ፡(አደረ)።

፬፤ ሂዶም፡የካህናት፡አለቆችንና፡ጸሮችን፡አሳልፎ፡እንዲሰጣቸው፡ተነጋገራቸው።

፭፤ ደስ፡ብሏቸው፡ከእርሱ፡ጋራ፡ተሰማምተው፡ሠላሳ፡ብር፡ሊሰጡ፡ተነጋገሩትና፡ነገር፡ቆረጡ።

፮፤ ሰው፡ሳይኖር፡ለነርሱ፡አሳልፎ፡ሊሰጣቸው፡ምቹ፡ጊዜ፡ይሻ፡ነበር።

፯፤ በጉን፡የሚያርዱባት፡የቂጣ፡በዐል፡ደረሰች።

፰፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ጴጥሮስንና፡ዮሐንስን፡ሂዱና፡የምንበላውን፡የፋሲካውን፡በግ፡አዘጋጁልን፡አላቸው።

፱፤ በጉን፡ወዴት፡ልናዘጋጅልህ፡ትወዳለህ፡አሉት።

፲፤ ወደ፡ሀገር፡በገባችሁ፡ጊዜ፡የውኃ፡ማድጋን፡የተሸከመ፡ሰው፡ታገኛላችሁና፡ወደሚገባበት፡ቤት፡ተከተሉት።

፲፩፤ የዚያን፡ቤት፡ጌታም፡መምህር፡ከደቀ፡መዛሙርቴ፡ጋራ፡በጉን፡የምበላበት፡ቤት፡ወዴት፡ነው፡ብሎሃል፡በሉት።

፲፪፤ እርሱም፡የተነጠፈ፡ያጌጠ፡ታላቅ፡ቤት፡ያሳያችኋል፤ በዚያም፡አዘጋጁልን፡አላቸው።

፲፫፤ ሂደውም፡እንዳላቸው፡አገኙና፡በጉን፡አዘጋጁ።

፲፬፤ የራት፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ/ነግህ።

ኢየሱስ ፡ ወዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሐዋር
ያቲሁ፡ምስሌሁ።

ድኅረ ፡ ወንጌል ፡ በጸሎተ ፡ ሐሙስ ፡ ጽባሕ ፡
እምግብረ፡ሕማማት፡ቅድስት፡ዘይትነበብ።
፩፡ ዕለተ፡ፋሲካ፡ናሁ፡ቀርበ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡
ንግረነ ፡ መካነ ፡ ዘናስተዳልዎ ፡ ለከ ፡ ይቤሉ ፡
አርድእት።
፪፡ ፋሲካ ፡ ስውር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ፈነወ ፡ ክልኤተ ፡ እምአርዳኢሁ ፡ ኬፋሃ ፡ ወዮ
ሐንስሃ።
፫፡ ወይቤሎሙ ፡ ተንሥኡ ፡ ወሑሩ ፡ ኀበ ፡
ሀገር ፡ ወትረክቡ ፡ ብእሴ ፡ ዘይጸውር ፡ ጸሕበ ፡
ማይ።
፬፡ ወሶበ፡ሖረ፡ትልውዎ፡አንትሙኒ፡ኀበ፡ቦአ፡
ወበልዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ውእቱ ፡ ቤት ፡ ይቤለከ ፡
ሊቅ፡አይቴአ፡መካን፡ዘእፌጽም፡ውስቴቱ፡
ፋሲካ።
፭፡ ወውእቱ ፡ ያርእየክሙ ፡ ጽርሐ ፡ ልዕልተ ፡
ወስርጉተ ፡ ወንጽፍተ ፡ ወአስተዳልዉ ፡
ፍሥሐ፡በውእቱ፡መካን።
፮፡ ከመዝ ፡ ገብሩ ፡ በከመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር።
፯፡ ንዑ፡አሕዛብ፡ተፈሥሑ፡ወተኀሠዩ፡እስመ፡
ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ለክሙ ፡ ፋሲካ ፡
ፍሥሐ፡ቀዳሚ፡ከመ፡በግዕ፡አድኃነ፡ሕዝበ፡
እምቅኔ።
፰፡ ወፍሥሕሰ፡ሐዲስ፡ውእቱ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ዘአድኃነ፡ዓለመ፡እምሀጕል፡በምግ
ባራት ፡ ብዙኃት ፡ ወበአምሳላት ፡ ብዙኃት ፡
አስተዳለወ ፡ ባልሐተ ፡ ወመድኃኒተ ፡
ዘለዓለም።
፱፡ ወዝንቱ፡መድኃኒት፡ለኵሉ፡ዓለም፡ውእቱ፡
እምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ሰሐበ ፡ ኵሎ ፡
ኀበ፡ ልዕልና ፡ በብዝኀ ፡ ምሕረቱ ፡ ወጸጋሁ ፡
እንተ ፡ ሰጣ ፡ ውስተ ፡ ኵሎን ፡ መካናት ፡
ዘለዓለም።ነሥአ፡ዘለነ፡ወረሰዮ፡ዘምስሌሁ፡
ወወሰከነ፡ኂሩቶ።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።
ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ለራት ፡ ተቀመጠ ፤ ዐሥራ ፡ ሁለቱም ፡
ሐዋርያት፡ከእርሱ፡ጋር፡ተቀመጡ።

በጸሎተ፡ሐሙስ፡በጥዋት፡በከበረች፡ግብረ፡
ሕማማት፡ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።
፩፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡
እነሆ ፡ የፋሲካ ፡ ቀን ፡ ቀርቧል ፤ የምናዘጋጅ
ልህን፡ቦታውን፡ንገረን፡አሉት።
፪፡ ገና ፡ ያልተገለጸ ፡ ፋሲካ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኬፋንና ፡ ዮሐንስን ፡
ሁለቱን፡ላከ።
፫፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፤ ተነሥታችሁ ፡ ወደ ፡
መንደር ፡ ሂዱ ፤ የውኃ ፡ ማድጋን ፡ የተሸከመ ፡
ሰውንም፡ታገኛላችሁ።
፬፡ በሄደ ፡ ጊዜም ፡ እናንተም ፡ ተከትላችሁ ፡ ወደ
ገባበት ፡ ቤት ፡ ሂዱ ፤ ያ ፡ ቤት ፡ ለጌታ ፡ ይገባል ፤
በውስጡ፡የፋሲካውን፡በዓል፡የምፈጽምበት፡
ቦታ፡ወዴት፡ነው፡ብሎሃል፡መምህር፡በሉት፡
፭፡ እርሱም ፡ ያጌጠችና ፡ የተነጠፈች ፡ ታላቅ ፡
አዳራሽ ፡ ያሳያችኋል ፤ በዚያም ፡ በጉን ፡
አዘጋጁ፡አላቸው።
፮፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ (ትእዛዝ) ፡
እንዲሁ፡አደረጉ።
፯፡ ምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ ኑ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡
ይበላችሁ ፤ የእግዚአብሔር ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡
አስቀድሞ ፡ ለእናንተ ፡ የፋሲካ ፡ በግ ፡ ሁኖ ፡
ተሠውቶ፡ወገኖቹን፡ከግዞት፡አድኗልና።
፰፡ ሐዲሱ ፡ ፋሲካም ፡ በብዙ ፡ ሥራና ፡
በብዙ ፡ ትሩፋት ፡ ዓለምን ፡ ከጥፋት ፡ ያዳነ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ለዘለ
ዓለም ፡ የሚኖር ፡ ፍጹም ፡ ድኅነትን ፡
አዘጋጀ።
፱፡ ይህም፡ለዓለሙ፡ሁሉ፡መድኃኒት፡ነው፡በይ
ቅርታው ፡ ብዛት ፡ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ለዘላለሙ ፡
በአሳደራት ፡ በጸጋው ፡ ከፀሐይ ፡ መግቢያ ፡
እስከ፡ፀሐይ፡መውጫ፡ሁሉን፡ወደ፡ልዕልና፡
ሃይማኖት ፡ ሳበ ፤ የእኛን ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርዩ ፡
አድርጎ፡ቸርነቱን፡አሳደረብን።
መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
መከራ፡ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።
ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትስ፡ከመ፡ቀዳሚ።

Scanned by CamScanner

## ምዕራፍ፡፴፩።

ሠለስቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ፡ዘይትነበብ።

### ክፍል፡፩።

#### ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፴፪፡፴—፴፭።

፴ ወኮነ፡በሳኒታ፡ይቤሎሙ፡ሙሴ፡ለሕዝብ፡
አንትሙ ፡ ጌገይክሙ ፡ ጌጋየ ፡ ዐቢየ ፡
ወይእዜኒ፡አዐርግ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡
አስተሥሪ፡ኃጢአተክሙ።
፴፩ ወገብአ፡ሙሴ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ወይቤ፡
አስአለከ፡እግዚኦ፡ናሁ፡አበሱ፡እሉ፡ሕዝብ፡
አበሳ፡ዐቢየ፡ወገብሩ፡ሎሙ፡አማልክተ፡
ዘወርቅ።
፴፪ ወይእዜኒ ፡ እመ ፡ ተኀድግ ፡ ሎሙ ፡
ዘንተ፡ኃጢአተ፡ኅድግ፡ወእመ፡አኮሰ፡
ደምስስ ፡ ኪያየ ፡ እመጽሐፍከ ፡ ዘጸሐ
ፍከኒ።
፴፫ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ለዘንቱ፡
ሕዝብ፡ዘአበሰ፡በቅድሜየ፡እደመስሶ፡እመ
ጽሐፍየ።
፴፬ ወይእዜኒ ፡ ሑር ፡ ወምርሖሙ ፡ ለሕዝብ ፡
ውስተ፡መካን፡ዘእቤለከ፡ወናሁ፡መልአኪየ፡
የሐውር፡ቅድመ፡ገጽከ፡ወአመ፡ዕለተ፡
እዋገዮሙ ፡ አገብእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡
ኃጢአቶሙ።
፴፭ ወቀተለ፡እግዚአብሔር፡እምሕዝብ፡በእንተ፡
ዘአምለኩ፡ላሕመ፡ዘገብረ፡ሎሙ፡አሮን።

ምዕ፡፴፫፡፩—፫።

፩ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ሑር ፡
ወዕርግ፡እምዝየ፡አንተ፡ወሕዝብከ፡ዘአው
ፃእከ፡እምድረ፡ግብጽ፡ውስተ፡ምድር፡
ዘመሐልኩ፡ለአብርሃም፡ወለይሥሐቅ፡ወለ
ያዕቆብ፡እንዘ፡እብል፡ለዘርዕክሙ፡እሁባ።
፪ ወእፌንዎ፡ለመልአክየ፡ቅድሜከ፡ወያወ
ፅእሙ፡ለከናኔዎን፡ወለአሞሬዎን፡ወለኬ
ጢዎን፡ወለፌርዜዎን፡ወለጌርጌሴዎን፡ወለ
ኤዊዎን፡ወለኢያቡሴዎን።
፫ ወኢያበውአከ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡
ታውሕዝ ፡ ሀሊበ ፡ ወመዐረ ፤ ወኢየዐርግ ፡

## ምዕራፍ፡፴፩።

ሐሙስ፡ከቀኑ፡በሦስት፡ሰዓት፡የሚነበብ።

### ክፍል፡፩።

#### ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፴፪፡፴—፴፭።

፴፤ በማግሥቱ፡እንዲህ፡ሆነ፤ሙሴ፡ሕዝቡን፡
እናንተ፡ጽኑ፡በደል፡በደላችሁ፤ኃጢአታ
ችሁን፡አሥተሰርይላችሁ፡ዘንድ፡አሁንም፡
ወደ፡እግዚአብሔር፡እወጣለሁ፡አላቸው።
፴፩፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሶ ፡
አቤቱ ፡ እለምንሃለሁ ፤ እነዚህ ፡ ወገኖች ፡
እነሆ፡ጽኑዕ፡በደል፡በደሉ፤የወርቅ፡ጣዖታ
ትንም፡ለራሳቸው፡ሠሩ።
፴፪፤ አሁንም ፡ ይህን ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡
ትላቸው፡እንደ፡ሆነ፡ይቅር፡በላቸው፤ይህስ፡
ካልሆነ፡እኔን፡ከጻፍከኝ፡መጽሐፍ፡ከባለሟ
ልነቱ፡ፋቀኝ፡አለ።
፴፫፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በፊቱ ፡ የበደለ ፡
ይህን፡ወገን፡ከመጽሐፍ፡ከባለሟልነቱ፡እፍ
ቀዋለሁ፡አለው።
፴፬፤ አሁንም፡ሂደህ፡ሕዝቡን፡እኔ፡ወዳዘዝኩህ፡
ቦታ፡ምራቸው፤እነሆ፡አገልጋዬ፡በፊትህ፡
ይሄዳል፤በመዐትም፡በጎበኘኋቸው፡ቀን፡የኃ
ጢአታቸውን ፡ ፍዳ ፡ አመጣባቸዋለሁ ፡
አለው።
፴፭፤ አሮን፡የሠራላቸውን፡ላም፡ስለ፡አመለኩ፡
እግዚአብሔር፡ከሕዝቡ፡አጠፋ።

ምዕ፡፴፫፡፩—፫።

፩፤ እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡አንተ፡ከዚህ፡ቦታ፡
ወጥተህ፡ሂድ፤ከግብጽ፡ያወጣሀቸው፡ወገኖ
ችህም፡ወጥተው፡ለልጆቻችሁ፡እሰጣታለሁ፡
ብዬ፡ለአብርሃም፡ለይሥሐቅ፡ለያዕቆብ፡ወደማ
ልኩላቸው፡አገር፡ይሂዱ፡አለው።
፪፤ አገልጋዬን፡(ኢያሱን)፡በፊትህ፡እሰደዋለሁ፤
አሞሬዎንና ፡ ከናኔዎንን ፡ ፌርዜዎንና ፡
ኬጢዎንን፡ኤዊዎንንና፡ጌርጌሴዎንን፡ኢያ
ቡሴዎንንም፡ያስወጣቸዋል።
፫፤ ወተትና፡ማርን፡ወደምታፈሰው፡ምድር፡አላገ
ባህም፤በመንገድ፡እንዳላጠፋቸው፡ወገኖችህ

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ምስሌከ ፡ በእንተ ፡ ሕዝብከ ፡ እለ ፡ ያገዝፉ ፡ ክሣዶሙ፡ከመ፡ኢያኅልቆሙ፡በፍኖት።

ዘሚክያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፪፡፫–፲፫።

፫፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ መከርኩ ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ በዘኢያንሥኡ ፡ እንከ ፡ ክሣዶሙ ፡ ወኢየሐውሩ ፡ እንከ ፡ ርቱዐ ፡ ፍኖተ፡ እስመ ፡ ታዌግበሙ ፡ ዕለት ፡ እኪት።

፬፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይሜስሉ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ምሳሌ ፡ ወታስቆቅዉ ፡ ወትብሉ ፡ ኀሠ
ርነ ፡ ውኀርተምነ፡ ወይሰፍርዋ ፡ በሐብል ፡ ለምድረ ፡ ሕዝብየ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይከልኦ ፡ ወዘያኀድግ ፡ ወይትካፈሉ ፡ ገራውሂሆሙ።

፭፡ በእንተ፡ዝንቱ፡ኢትረክቢ፡ዘያዐውድ፡ለኪ፡ ሐብለ ፡ ዲበ ፡ መክፈልትኪ ፡ እምውስተ ፡ ማኅበር፡እግዚአብሔር።

፮፡ ኢትብክዩ፡ወኢታንብኡ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ እስመ፡ኢይትኀደግ፡ኃሣርክሙ።

፯፡ በእንተ፡ዘአምዕዐ፡ቤተ፡እሥራኤል፡ወቤተ፡ ያዕቆብ፡መንፈሰ፡እግዚአብሔር፡በዝንቱ፡ ጌጋዮሙ፡እንዘ፡ነገሩ፡ሠናይ፡በኀቤሆሙ፡ ወራትዐን ፡ የሐውሩ ፡ ቦቱ ፡ ወይሜልዑ ፡ ቅድመ።

፰፡ ወሕዝብየሰ ፡ ተቃወምዋ ፡ ቅድሜሃ ፡ ለሰላሞሙ፡ወይገፈርዋ፡ወሰለብዎ፡ኩናቶ፡ ወአኀደግዎ ፡ ትውክልቶ ፡ ወይቀጠቅጥዎ ፡ በውስተ፡ቀትል።

፱፡ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ይገድፍዎሙ ፡ ለመ
ላእክተ፡ሕዝብየ፡እምውስተ፡ትርሲተ፡አብ
ያቲሆሙ፡ወይሰድድዎሙ፡እስከ፡እኩይ፡ ምግባሮሙ።

፲፡ ቅረቡ፡አድባር፡ወእለ፡እምፍጥረተ፡ዓለም፡ ተንሥኡ፡ወሑሩ፡እስመ፡ኢኮነት፡እንቲ አክሙ፡ዛቲ፡ዕረፍት።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ክሣደ፡ልቡናቸውን፡ስለአፀኑ፡ከአንተ፡ጋራ፡ አብሬ፡አልወጣም፡አለው።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ሚክያስ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፪፡፫–፲፫።

፫፡ ይህንንም፡ሁሉ፡ስለ፡አደረጉ፡እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡አለ፤ክሣደ፡ልቡናቸውን፡በማያነሡ፡ ገንዘብ፡እነሆ፡እኔ፡በነሀ፡ወገኖች፡ላይ፡ክፉን፡ ምክር፡መከርኩ፤መከራ፡የታዘዘባት፡ቀን፡ታገ
ፈራቸዋለችና፡እንግዲህ፡ወዲህ፡የቀናውን፡ ጎዳና፡አይሄዱም።

፬፡ ያን፡ጊዜ፡እነርሱ፡ተረትን፡ይተርቱባችኋል፤ እናንተም፡ታዝናላችሁ፤በመከራውም፡ተይ
ዛችሁ፡ፈጽመን፡ጐሰቈልን፡ትላላችሁ፤የወገ
ቼንም፡አገር፡በዐይነ፡ገመድ፡ይሰፍሩዋታል፤ ያን፡ጊዜ፡የሚከለክል፡የሚያስተው፡የለም፤እር
ሻቸውንም፡ዕፃ፡በዕፃ፡ብለው፡ይካፈሉታል።

፭፡ ይህን፡ሁሉ፡ስለ፡አደረግሽ፡የተካፈልሽውንም፡ ዕፃ፡ከእግዚአብሔር፡ማኅበር፡ወገን፡(ከነቢያት፡ ከካህናት)፡የሚያካፍልሽ፡አታገኚም።

፮፡ መከራችሁ ፡ አይተውምና ፡ (ኃጢአታችሁ፡ አይሰረይላችሁምና)፡ፈጽመሽ፡አታልቅሽ።

፯፡ ሕጉ ፡ በእነዚያ ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ ቅን ፡ የሆኑ፡ ሰዎችም ፡ በእርሱ ፡ ፀንተው ፡ የሚኖሩ፡ አስቀድሞ፡ወደ፡ሕጉ፡የሚገሠግሡ፡ሲሆን፡ ሁለቱ፡ነገድና፡ዐሥሩ፡ነገድ፡በዚህ፡ኃጢአ
ታቸው፡የእግዚአብሔርን፡ልቡና፡አሳዘኑ።

፰፡ ወገኖቼ፡እስራኤል፡ግን፡ስለምን፡ሕግን፡ ፊት፡ለፊት፡ተቃወሚት? ፊት፡ለፊትም፡ ተጣሏት? ጋሻ፡ጦርንም፡ማርከው፡ይወስዱ
ባታል፤በሰልፍ፡ቀንም፡ያጠፏታል።

፱፡ ሥራቸው፡ክፉ፡ነውና፡ስለዚህ፡በወገኖቼ፡ የተሾሙ ፡ አለቆችን ፡ በሐር ፡ ከተሸለሙ፡ ቤቶቻቸው፡አስወጥተው፡እየወጉ፡ይገሏቸ
ዋልና።

፲፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የነበራችሁ ፡ ተራሮች፡ (ነገሥታት) ፡ ለጥፋት ፡ ቅረቡ ፤ ይህች፡ ዕረፍትም ፡ ለናንተ ፡ አትገባምና ፡ ተነሥ
ታችሁ፡(ተማርካችሁ)፡ሂዱ።

በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወአንተ ፡ ርኵስክሙ ፡ ጠፋእክሙ ፡ ውኀለ
ቅክሙ፡ወገሞየይክሙ፡እንዘ፡አልቦ፡ዘይዴግ
ነክሙ፡ጋኔን፡አቀመ፡ለከ፡ሐሰተ፡ወአው
ጸአከ፡ለተ፡ወይነ፡ወጼተሎ።

ወይከውን፡በነፍኒፎሙ፡ለገዘንቱ፡ሕዝብ፡
ይትጋባእ፡ያዕቆብ፡ምስለ፡ኵሎሙ፡እለ፡
ይጸንሑ፡እምጽንሐሙ፡ለተረፈ፡እስራኤል፡
ወአሐስየ፡ኅቡረ፡ለሚጠቶሙ፡ከመ፡አባግዕ፡
ውስተ፡መጽብብ፡ወከመ፡መርዔት፡ውስተ፡
ምብያቲሁ ፡ ወይትባልሁ ፡ እምሰብእ ፡
እኩያን።

ወበአንተ፡ቅትለቶሙ፡እንዘ፡ይትቃተሉ፡
በቅድመ፡ገጾሙ፡ኅለፉ፡እምአንቀጽ፡
ወወፅኡ፡እንተ፡ውስቴታ፡ወሖረ፡ንጉሦሙ፡
በቅድመ፡ገጾሙ፡ወእግዚአብሔር፡ይመር
ሖሙ።

ጥበበ፡ሲራክ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፳፬፤፩–፲፩።

ጥበብ፡ትዌድስ፡ነፍሳ፡ወትትሜካህ፡
በማእከለ፡አሕዛብ።

ውስተ፡ማኅበረ፡ልዑል፡ትከሥት፡አፉሃ፡
ወትትሜካሕ፡በቅድመ፡ኃይሉ።

አነሰ፡እምአፉሁ፡ለልዑል፡ወፃእኩ፡ወከመ፡
ጊሜ፡ከደንክዋ፡ለምድር።

አነሰ፡ውስተ፡ሰማያት፡ኀደርኩ፡ወመንበ
ርየኒ፡ውስተ፡ዓምደ፡ደመና።

ወዖድኩ፡ባሕቲትየ፡አጽናፈ፡ሰማይ፡ወአንሶ
ሰውኩ፡ውስተ፡ዕመቀ፡ቀላይ።

ወመልዕልተ፡ማዕበለ፡ባሕርኒ፡ወውስተ፡
ኵሉ፡ምድር፡ወኢያጥረይኩ፡በውስተ፡ኵሉ፡
አሕዛብ፤ወውስተ፡ኵሉ፡ሕዝብ።

ወእምድኅረዝ፡ኵሉ፡ዕረፍተ፡ኀሠሥኩ፡
ውስተ፡ርስተ፡መኑ፡እንከ፡አኀድር።



፲፩፤ ጣዖትን ፡ ስለአመለካችሁ ፡ ፈጽማችሁ ፡
ጠፋችሁ ፤ የሚከተላችሁም ፡ ሳይኖር ፡
ሸሻችሁ፤ጋኔን፡(ጠላት)፡አነስተኛ፡ጣዖትን፡
አቆመልህ፤አንተም፡ለጣዖቱ፡የወይን፡ጠጅ፡
ደምንም፡አፈሰስህለት።

፲፪፤ በኒህ ፡ ወገኖች ፡ በልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ዘመን ፡
እንዲህ፡ይሆናል፤የሁለቱን፡ነገድ፡ተስፋ፡ደጅ፡
ከሚጠኑ፡ከዐሥሩ፡ነገድ፡ሁሉ፡ጋራ፡ሁለቱ፡
ነገድ፡ይመለሳሉ፤መንጋ፡በመግቢያው፡ተጨና
ንቆ ፡ እንዲገባ ፤ በጎችም ፡ ወደጉረኖ ፡ ተጨና
ንቀው ፡ እንዲገቡ ፤ መመለሻቸውንም ፡ አንድ
ነት፡አደርጋታለሁ፤ከክፉ፡ሰዎችም፡ይድናሉ።

፲፫፤ ቀድሞ፡ጠላቶቻቸው፡ስለ፡ወጓቸው፡እነሱም፡
በፊታቸው፡እየተዋጉ፡ከበሮቻቸው፡ወጥተው፡
አለፉ ፤ ከውስጥዋም ፡ ወጡ ፤ (ከእርሱም ፡
ወጥተው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዱ) ፡ ንጉሣ
ቸውም ፡ በፊታቸው ፡ እየተዋጋ ፡ ሄደ ፤ ፈጣሪ
ያቸው፡እግዚአብሔርም፡ይመራቸዋል፤(ያዝን
ላቸዋል፤ከባቢሎንም፡መርቶ፡ያወጣቸዋል።)

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑርና ፡
ጥበበኛው፡ሲራክ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፳፬፤፩–፲፩።

፩፤ ጥበብ ፡ ራስዋን ፡ ታመሰግናለች ፤ በአሕዛብ ፡
መካከልም፡ትመካለች።

፪፤ በልዑል ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ ነገሯን ፡ ትገል
ጣለች፤በከሃሊነቱ፡ፊትም፡ትመካለች።

፫፤ እኔ ፡ ከልዑል ፡ አፍ ፡ ወጣሁ ፤ ምድርንም ፡
እንደጉም፡ሸፈንኋት።

፬፤ እኔ፡በሰማያት፡ኖርሁ፤ዙፋኔንም፡በደመና፡
ዐምድ፡ላይ፡ዘረጋሁ።

፭፤ ብቻየን ፡ ዐራቱን ፡ መአዝነ ፡ ዓለም ፡
በሰማይም፡ዳርቻም፡ዞርሁ፤በውቅያኖስም፡
መካከል፡ተመላለስሁ።

፮፤ በባሕርም ፡ ማዕበል ፡ ላይ ፡ በየብስም ፡
መካከል፡ሁሉ፡በሕዝቡ፡በአሕዛቡ፡ሁሉ፡
ጥሪትን፡አላደረግሁም።

፯፤ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ዕረፍትን ፡ ፈለግሁ ፡
እንግዲህ፡በማን፡ርስት፡አድራለሁ?

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፰፡ ወእምዝ ፡ አዘዘኒ ፡ ፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ወአዕረፈ ፡
ሊተ ፡ ፈጣሪ ፡ መንበርየ ፡ ወይቤለኒ ፡ ኀበ ፡
ያዕቆብ ፡ ኅድሪ ወበውስተ ፡ እስራኤል ፡
ተዋረሲ።
፱፡ እምቅድመ፡ይትፈጠር፡ዓለም፡ፈጠረኒ፡ወኢ
ይጠፍእ፡ለዝሉፉ፡ወለዓለመ፡ዓለም።
፲፡ ወተልእኩ ፡ በውስተ ፡ ደብተራሁ ፡ ቅዱስ ፡
በቅድሜሁ፡ወውስተ፡ጽዮን፡አስመኩ።
፲፩፡ ወከማሁ፡ውስተ፡ሀገርኒ፡ቅድስት፡አዕረፍኩ፡
ወበኢየሩሳሌምኒ፡ምኵናንየ፡ኀበ፡አኰነንኒ።

### ክፍል፡፪።

### እምቃለ፡አረጋዊ፡መንፈሳዊ፡ ድርሳን።

ምዕ፡፴፬፡፩–፰።

፩፡ ወጸ.ም ፡ ምስሌሁ ፡ ሶበ ፡ ይጸውም ፡ ወአመ ፡
ይዌልጦ ፡ ለማይ ፡ ወይሬስዮ ፡ ወይነ ፡ ሀሉ ፡
ሶቤሃ፡እንዘ፡ትመልእሙ፡ለመሳብክት፡ማየ፤
ወአመ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ አዘቅት ፡ ምስለ ፡
ሳምራዊት ፡ አጽምዕ ፡ ትምህርተ ፡ ግብር ፡
መንፈሳዊ ፡ ወሰጊደ ፡ ፍጹመ ፡ ዘመንፈስ ፡
ዘኪያሁ፡የኀሥሥ፡አብ።

፪፡ ወአመ ፡ ያነሥእሙ ፡ ለምውታን ፡ አእምር ፡
ከመ፡ለሊሁ፡ውእቱ፡ትንሣኤ፡ሙታን።

፫፡ ወሶበ ፡ ይባርክ ፡ ዲበ ፡ ኅብስት ፡ ጹር ፡ አስፈ
ሬዳተ ፡ በመዛርዲከ ፡ ወሀብ ፡ ለጉቡአን ፤
ወአመ፡የሐውር፡ገዳመ፡ሑር፡ምስሌሁ፡ወአ
ስተፋንዎ ፤ ወአመ ፡ ይነውም ፡ ዲበ ፡ ሐመር ፡
አንቅሆ፡ለሊከ።

፬፡ ወውስተ፡ጉባኤሂ፡ሀሉ፡ምስሌሁ።

ወውስተ፡ፍናዋት፡ሀሉ፡ምስሌሁ።
ወኀበ፡ገዳም፡ሀሉ፡ምስሌሁ።
ወውስተ፡ሐመር፡ሀሉ፡ምስሌሁ።
ኀበ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ሀሉ ፡
ምስሌሁ።
ወውስተ ፡ ምኵራብ ፡ አጽምዕ ፡ ትምህር
ታቲሁ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ አዘዘኝ፤
ፈጣሪም ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ ማደሪያዬን ፡ አዘጋ
ጀልኝ ፤ በያዕቆብ ፡ እደሪ ፤ በእስራኤልም፤
ተወራረሽ፡አለኝ።
፱፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ወለደኝ ፤ ዘወትር ፡ ለዘለዓ
ለምም፡አልለይም።
፲፡ በቅዱስ ፡ ማደሪያው ፡ በፊቱ ፡ አገለገልሁ፤
በጽዮንም፡አደርሁ።
፲፩፡ እንዲሁም ፡ በቅድስት ፡ ከተማ ፡ በአስገዛልኝ፤
በግዛቱ፡በኢየሩሳሌምም፡አረፍኩ።

### ክፍል፡፪።

### ከአረጋዊ፡መንፈሳዊ፡የተገኘ፡ድርሳን፡ ይህ፡ነው።

ምዕ፡፴፬፡፩–፰።

፩፡ ጌታ ፡ በጾመ ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ጹም፤
ውኃውንም ፡ ለውጦ ፡ ወይን ፡ በአደረገው፡
ጊዜ፡ ጋኖቹን ፡ ውኃ ፡ እየመላህ ፡ ያን ፡ ጊዜም፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ኑር ፤ ከሳምራዊት ፡ ሴት ፡ ጋራ፡
በውኃ፡ጉድጓድ፡ዳር፡ሳለ፡ከዚያ፡ሁነህ፡የመ
ንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ ትምህርትን ፡ (ምሥጢር)፡
አድምጥ፤ አብ፡የሚሻውንም፡ረቂቅ፡ፍጹም፡
የባሕርይ፡ስግደትን፡ስገድ።
፪፡ ሙታንንም ፡ በሚያስነሣቸው ፡ ጊዜ፡
የሙታን፡ትንሣኤና፡ሕይወት፡እርሱ፡ራሱ፡
እንደሆነ፡ዕወቅ።
፫፡ በኅብስቱ፡ላይ፡በሚባርክ፡ጊዜ፡በክንዶችህ፡
እንቅቦችን ፡ ተሸክመህ ፡ ለተሰበሰቡት፡
ሰዎች፡ ስጥ ፤ ወደ ፡ በረኻ ፡ በሄደም ፡ ጊዜ፡
ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ሁነህ ፡ ሸኘው ፤ በመርከብ፡
ውስጥ፡በተኛ፡ጊዜ፡አንተ፡ራስህ፡ቀስቅሰህ፡
አንቃው።
፬፡ በተሰበሰበው፡ሕዝብ፡መካከል፡ሲያስተምር፡
ከእርሱ፡ጋራ፡ኑር።
በመንገዶችም፡ሲጓዝ፡አብረህ፡ሂድ።
በበረኻም፡አብረኸው፡ኑር።
በታንኳም፡ሲጓዝ፡አብረህ፡ተጓዝ።
በደብረ ፡ ዘይትም ፡ ሲጸልይ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ፡
ሁን።
በምኵራብም ፡ ሲያስተምር ፡ ትምህርቶቹን፡
አድምጥ።

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወሀሉ፡ውስተ፡መቃብር፡ምስለ፡እልዓዛር፡
ከመ፡ ያንሥእከ ፡ ወትፃእ ፡ ምስሌሁ ፡
እምውሣጤ፡ጽልመት፡ዘእበድ።

ኦርሕስ፡እገሪሁ፡በአናብዒከ፡ከመ፡ማርያም፡
ወመገዝምግዝ ፡ በሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ከመ ፡
ትስማዕ፡እምቃሉ፡ስርየተ፡ኃጢአትከ።

ርፍቅ፡በእንግድዓሁ፡በጊዜ፡ድራር፡ወሶበ፡
ይፈትት፡ኅብስተ፡ተመጠው፡እምእዴሁ።

ወእመ፡የኀፅብ፡እግረ፡አርዳኢሁ፡ቅረብ፡
ኀበ፡ምኅፃብ፡ከመ፡ይኅፅብከ፡እምኃጣ
ውኢከ።

መልእክት፡ሣልሲት፡ኀበ፡አሐዱ፡እኁ፡
ዘከነ፡ያፈቅሮ፤ወእምዝ፡ገነየ፡ለሰይጣን፡
ወአኀዘ፡ይፅርፍ፡ለአረጋዊ፡ላዕሌሁ።

ወይቤ፡አንሰ፡እትፌሣሕ፡ፈድፋደ፡ሶበ፡
ተሐምየኒ፡ወትጼዕለኒ፡እኁልቆ፡አነ፡ከመ፡
ዘበቍዔት፡አላ፡አንተሰ፡ትብለኒ፡ሶበ፡
እጼዕሎ፡ለምንት፡ይትዔገሠኒ።

ስማዕ፡ይእዜ፡ዘእነግረከ፡ይቤ፡እግዚእነ፡
ብየ፡ ጥምቀት ፡ ዘእጠመቅ ፡ ወሀለወኒ ፡
እፈጽማ፡ዘውእቱ፡አንሰ፡ድልው፡ለሞት፡
ወእጸንሕ፡መቃብረ።

ወባሕቱ፡አ፤፡መፍትው፡ለይሁዳ፡ፍቁሩ፡
ከመ፡ያግብእ።

### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፻፫፡፭፤፲–፲፬።

እመልእክተ፡ሲኖዲቆን፡ዘአብ፡ንጹሕ፡አባ፡
ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ፡ኀበ፡አብ፡
ንጹሕ፡አባ፡ሚናስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእስክን
ድርያ፡ወግብጽ፡ወምዕራብ።

ንአምን፡በአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
ሥላሴ፡ዕሩያን፡በህላዌ።

እንዘ፡፩መለኮቱ፡ወአሐቲ፡ኃይል፡ወአሐቲ፡
ሥልጣን ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ሊሉያን ፡
በገጻት፡ዘበአማን።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፩፤ ከድንቁርና ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ አውጥቶ ፡
ከእርሱ፡ጋራ፡ያስነሣህ፡ዘንድ፡ከአልዓዛር፡
ጋር፡በመቃብር፡ውስጥ፡አብረኸው፡ኑር።

፪፤ ከአንደበቱ፡የኃጢአትህን፡ስርየት፡ትሰማ፡
ዘንድ፡እንደ፡ማርያም፡እንተ፡ዕፍረት፡በዕንባ
ዎችህ፡እግሮቹን፡እርስ፤በራስህም፡ጠጕር፡
እሸው፤(ወልውለው።)

፫፤ በራት፡ጊዜም፡በአጠገቡ፡ተቀምጠህ፡እንጀ
ራውን፡ሲቆርስ፡ከእጁ፡ተቀበል።

፬፤ የደቀ፡መዛሙርቱንም፡እግር፡በሚያጥብ፡
ጊዜ ፡ ወደመታጠቢያው፡ ቅረብ ፤ ከኃጢ
አትህ፡ያጥብህ፡ዘንድ።

፭፤ ቀድሞ፡ይወደው፡ለነበረ፡ኋላ፡ለሰይጣን፡
ተገዝቶ፡አረጋዊን፡ይነቅፍ፡ዘንድ፡ለጀመረ፡
ለአንድ ፡ ወንድም ፡ የጻፋት ፡ ሦስተኛው ፡
መልእክት፡ይህች፡ናት።

፮፤ አረጋዊውም፡በምታማኝና፡በምትሰድበኝ፡
ጊዜ፡እጅግ፡ደስ፡ይለኛል፤እንደ፡ጥቅም፡እቆ
ጥረዋለሁ፤አንተ፡ግን፡ስሰድበው፡ለምን፡
ይታገሠኛል፡ትላለህ፡እንጂ።

፯፤ አሁን፡የምነግርህን፡ስማ፡ጌታችን፡የምጠ
መቃት ፡ ጥምቀት ፡ አለችኝ ፤ እፈጽማትም ፡
ዘንድ፡አለኝ፡አለ፤ይህም፡ለሞት፡ዝግጁ፡ነኝ፡
መቃብርንም፡እጠብቃለሁ፡ማለት፡ነው።

፰፤ ነገር፡ግን፡ወዳጁ፡የነበረ፡ይሁዳ፡አሳልፎ፡
ይሰጠው፡ዘንድ፡አግባብ፡አይደለም።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፻፫፡፭፤፲–፲፬።

፩፤ ከአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ንጹሕ፡አባት፡
አባ፡ ዮሐንስ ፡ የእስክንድርያ ፡ የግብጽ ፡
የምዕራብ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወደ፡ሆነው፡ወደ፡
ንጹሕ ፡ አባት ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ የተላከው ፡
ሲኖዶሳዊ፡መልእክት።
በባሕርይ፡አንድ፡በሚሆኑ፡በሦስቱ፡አካላት፡
በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናም
ናለን።
በዕውነት ፡ ሦስቱ ፡ አካላት ፡ በመለኮት ፡
በኃይል፡በሥልጣን፡አንድ፡ሲሆኑ፡በገጻት፡
የተለዩ፡ናቸው።

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፩፡ ዓዲ ፡ ንሕነሰ ፡ ንትአመን ፡ ወንብል ፡ በእንተ ፡ ትሥግተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አሐዱ ፡ ህላዌ፡ ወአሐዱ ፡ አካል ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢ፡ተፈልጦ፡ወኢ፡ሚጠት።

፲፪፡ እስመ ፡ክርስቶስ ፡ ኃይሉ ፡ ውእቱ ፡ለእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወጥበቡ ፡ ዘቦቱ ፡ ኵሉ ፡ መዛግብተ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአእምሮ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፈቀደ ፡ ይእዜ ፡ ይትመሰለነ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም፡ ሕጸጸነ፡ ወያንሥአነ፡እምድቀትነ፡ ዘወደቅነ፡ባቲ፡ወበጸሕነ፡ለሙስና፡ወኃጕል፤ ወኢ፡ንትነሣሥ ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምኅሊና ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፤ ወዳእሙ ፡ ንትአመን ፡ ትሥጉቶ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንበለ ፡ ዕቅፍት ፡ ወኢ፡ተወላውሎ ፤ ወኢ፡ንክሐድ ፡ ከመ፡ውእቱ፡አሐዱ፡ህላዌ፡ወአሐዱ፡አካል፡ ቃል፡ዘተሠገወ፡በእንቲአነ።

፲፫፡ ወዓዲ ፡ ኢ፡ንትቄከፍ ፡ ንባቦ ፡ ለዮልያኖስ ፡ ፈረሳዊ ፡ ዘይቤ ፡ ምትሐት ፡ ውእቱ ፡ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይብል ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኢ፡ፍጡር ፡ ወኢ፡ግቡር ፡ ኢ፡የሐምም ፡ ወኢ፡ይመውት ፤ ወዝንቱ ፡ ንባብ ፡ ይትማሰል ፡ ምስለ ፡ ንባቡ ፡ ለማኒ ፡ ረሲዕ ፡ ዘይቤ ፡ ምትሐት ፡ ውእቱ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፤ ወውእቱሰ ፡ እንዘ፡ያከብር፡ሥጋሁ፡ለእግዚእነ፡ክርስቶስ፡ ያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ዕልወት ፡ ወካሕድ ፡ ሕማማቲሁ፡ ለክርስቶስ ፡ ማህየዊ ፤ ወዓዲ ፡ ይቤ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ዘፍጡር እምእግዚአብሔር፡ እምድር ፡ ወእመሬት ፡ ወደየ ፡ ውስቴቱ፡ ነፍሰ ፡ ነባቢተ ፡ ወለባዊተ ፤ ወለሊሁ፡ በህላዌሁ ፡ ኢ፡የሐምም ፡ ወኢ፡ይመውት።

፲፬፡ ንሕነሰ፡ንብል ፤እግዚአብሔር፡ቃል፡ ሐመ፡ በሥጋሁ፡ ወኢ፡የሐምም ፡በመለኮቱ፤ እፎኑ፡ ይደሉ ፡ ይሕምም ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወይጥዐም፡ሞተ፡ዝኩ፡ዘኢ፡ይቀርቦ፡ምንትኒ፡ እሙስና፡ወሐጕል።

፲፭፡ ወባሕቱ፡ኵሎሙ፡ሐዋርያት፡ወንጌላውያን፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፩፡ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኛስ ፡ እግዚአብሔር፡ቃል፡ ሰው፡ስለመሆኑ፡ያለ፡መለወጥ፡ ያለ፡ መናወጥ፡ ያለ ፡ መለየት፡ አንድ፡ አካል፡ አንድ፡ባሕርይ፡ነው፡ብለን፡እናምናለን።

፲፪፡ ክርስቶስ፡የእግዚአብሔር፡አብ፡ ኃይሉ፡የሃይማኖት፡የዕውቀት፡ሀብት፡ሁሉ፡በእርሱ፡የሚገኝበት ፡ ጥበቡ ፡ እርሱ ፡ የጐደለውን፡ ይመላልን ፡ ዘንድ ፡ ወድቀን ፤ ፈጽመን፡ ለጥፋት ፡ ደርሰን ፡ ከነበርንባት ፡ ያነሣን፡ ዘንድ፡እኛን፡ሊመስለን፡ወደደ፤ከሰው፡ልጅ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ የሚሆነውን ፡ እርሱን ፡ እንመርምር ፤እግዚአብሔር፡ቃል፡ ሰው፡ መሆኑን፡ ያለ ፡ ማወላወል ፡ ያለ ፡ መጠራጠር፡ እንመን፡ እንጂ ፤ ስለእኛ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ አንድ፡ አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡እንደሆነ፡አንካድ።

፲፫፡ ዳግመኛም ፡የክርስቶስ፡ሥጋ፡ ምትሐት፡ነው፡ ያለውን ፡ የፈረሰኛውን ፡ የዮልያኖስን፡ አነጋገር ፡ አንቀበልም ፤ እርሱ ፡ ይህ ፡የክርስቶስ፡ ሥጋ ፡ ፍጡር ፡ አይደለም ፤ አይታመምም ፡ አይሞትምም ፡ ይላልና ፤ ይህ፡ አነጋገር ፡ የጌታችን ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ፡ ምትሀት ፡ ነው ፡ ከሚል ፡ ከከሐዲው ፡ ከማኒ፡ አነጋገር ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ እርሱስ ፡የክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ አከበርኩ ፡ ብሎ ፡ የምታድን፡ የክርስቶስን ፡ ሕማም ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ መካድ፡ ያደርሳል ፤ ዳግመኛ ፡ ሥጋ ፡በእግዚአብሔር፡ ሥልጣን ፡ ከምድር ፡ የተፈጠረ ፡ ነው ፤ ከመሬትም፡ፈጥሮ፡ነባቢት፡ለባዊት፡ነፍስን፡ አሳደረበት ፤ እርሱም ፡ በባሕርዩ ፡ አይታመምም፡አይሞትም፡ብሏልና።

፲፬፡ እኛ ፡ ግን ፡እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሥጋው፡ ታመመ ፤በመለኮቱ ፡ ግን ፡ አይታመምም፡ ሕማም፡ሞት፡የለበትም፡እንላለን፤ከሕማም፡ ከሞት፡ወገን፡ምንም፡ምን፡የሌለበት፡እርሱ፡ በመለኮቱ፡ ባሕርይማ፡እንዴት፡ሊታመም፡ ሞትን፡ሊቀምስ፡ይገባል?

፲፭፡ ነገር፡ግን፡ሐዋርያት፡ሁሉ፡ደጋጎች፡ወንጌላ

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ጌሬን፡ወኵሎሙ፡ማኅበራነ፡ምሥጢራት፡
ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡ሰበኩ፡ገሀደ።

በረከቶሙ ፡ ለእሉ ፡ መምህራን ፡ የሀሉ ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፩ ወከነ፡በአሐቲ፡ዕለት፡እንዘ፡የዐውድ፡ካህን፡
መየዐጥን፡ቤተ፡ክርስቲያን፡በጽሐ፡ኀበ፡
ሥዕለ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ዘምስለ፡ፍቁር፡
ወልዳ።

፪ ወቀጸበ፡መልአከ፡እግዚአብሔር፡ወይቤሎ፡
ዕጥን፡ሥዕለ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ወሀባ፡
ሰላመ፡ወኢትጕጕዕ።

፫ ወገብረ፡ከማሁ፡ወገሠሠ፡ዐምደ፡በእዴሁ፡
እንዘ፡ይኤምኃ፡ለሥዕለ፡እግዝእትነ፡
ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡
ወላዲተ፡አምላክ፡ወአሠረ፡እዴሁ፡ለውእቱ፡
ካህን፡ኮነት፡ቅርጽተ፡ውስተ፡ዓምድ፡
ዘሥዕል፡ወሀለወት፡እስከ፡ዮም።

፬ ወፈጸሞ፡አባ፡ብንያሚ፡ቅዳሴ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡ገብረ፡በዐለ፡ኤጲፋንያ፡ወአንቅዐ፡
ሎሙ፡እግዚአብሔር፡ማየ፡ወሰመይዎ፡
ዮርዳኖስ። ወተጠምቀ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡
ብንያሚ፡ወኵሉ፡ጉባኤ።

፭ ወፈጸሞ፡ኵሎ፡ሥርዐተ፡ተመይጠ፡ኀበ፡
እስክንድርያ።

፮ ወለአከ፡ኀበ፡ንጉሥ፡ወዜነውዎ፡ኵሎ፡ዘኮነ፡
ተፈሥሐ፡ዐቢየ፡ፍሥሐ፡ንጉሥኒ፡ወሰብአ፡
መንግሥቱ፤ ወሰምዐት፡ኢላርያ፡ወለተ፡
ዘይኑን፡ንጉሥ፡ጐየት፡እምአቡሃ፡
ወበጽሐት፡ኀበ፡ደብረ፡አስቄጥስ፡ወመን
ኰሰት፡በህየ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ውያን ፡ እና ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
የምሥራቅ ፡ ማኅበር ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡
ገልጸው፡አስተማሩ።
የእኒህ፡መምህራን፡በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋር፡
ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ በዕውነት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ለዘላለሙ ፡ ይኑርና ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡
በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ አምላክን ፡
የወለደች፡ንጽሕት፡እመቤታችን፡ማርያም፡
ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ በአንዲት፡ቀንም፡እንዲህ፡ሆነ፤ካህኑ፡ቤተ፡
ክርስቲያኒቱን፡እያጠነ፡ሲዞር፡ከተወደደ፡
ልጅዋ፡ጋር፡ከተሣለች፡ወደ፡እመቤታችን፡
ማርያም፡ሥዕል፡አጠገብ፡ደረሰ።

፪፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ጠቀሰው ፤
በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡
አምላክን ፡ የወለደች ፡ የክብርት ፡ እመቤ
ታችን፡ ማርያምን ፡ ሥዕል ፡ ዕጠን ፤ ሰላም
ታንም፡ስጣት፤አትቸኩልም፡አለው።

፫፤ እንዲሁም ፡ አደረገ ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡
በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ አምላክን ፡
የወለደች ፡ የክብርት ፡ እመቤታችን ፡
ማርያምን ፡ ሥዕል ፡ እጅ ፡ ሲነሣ ፡ ሥዕሏ ፡
ያለበትን፡ዐምድ፡በእጁ፡ዳሰሰ፤የጣቶቹም፡
አሻራ፡(ምልክት)፡በሥዕሉ፡ዓምድ፡ላይ፡
ተቀረጸች፤እስከ፡ዛሬም፡ትኖራለች።

፬፤ አባ ፡ ብንያሚም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ቅዳሴውን፡ቀድሶ፡ሲፈጽም፡የኤጲፋንያን፡
በዐል፡አከበረ፤እግዚአብሔርም፡ውኃን፡አፈ
ለቀላቸው፤ስሙንም፡ዮርዳኖስ፡አሉት፤ሊቀ፡
ጳጳሳቱ፡አባ፡ብንያሚም፡ተጠመቀ፤የተሰበሰ
ቡትም፡ሁሉ፡ተጠመቁ።

፭፤ ሥርዐቱንም፡ሁሉ፡ከፈጸመ፡በኋላ፡ወደ፡እስ
ክንድርያ፡ተመለሰ።

፮፤ ወደ ፡ ንጉሥም ፡ መልእክተኞችን ፡ ልኮ ፡
የሆነውን፡ሁሉ፡ነገሩት፤ንጉሡም፡የንጉሥም፡
ቤተሰቦች ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤
የንጉሥ ፡ ዘይኑን ፡ ልጅ ፡ ኢላርያ ፡ ይህንን ፡
በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ከአባቷ ፡ ኰበለላ ፡ ወደ፡
አስቄጥስ፡ገዳም፡ደርሳ፡በዚያ፡መነኰሰች።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፮፤ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ መኳንንተ ፡ ግብጽ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ኵሎ ፡ ጸባሕተ ፡ ለግብረ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ለመፍቅደ ፡ መነኰሳት ፡ ወለአ ብያተ፡መነኰሳት።

፯፤ ወፈጸሙ ፡ ዘንተ ፡ ተገዚካረ ፡ ሠናየ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት፡ በጸሎታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

፰፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ሖሩ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ፡ ወረከብዎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘአመሮሙ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፱፤ ወነገርዎ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ ወውእቱሂ ፡ አርአዮሙ፡ጽርሐ።ወአስተዳለዉ፡ውስቴታ፡ ኵሎ፡ዘይትፈቀድ፡ለበዓል።

፲፤ ወአይሁድሰ ፡ ወሀቡ ፡ ሕልያነ ፡ ለብዙኃን ፡ ሕዝብ ፡ እምሐራ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ለእመ ፡ ርኢክምዎ ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ በበዓል ፡ ንግሩነ፡ዜናሁ።

፲፩፤ እስመ ፡ ካህናት ፡ ወሊቃውንት ፡ ተጋብኡ ፡ ወተማከሩ፡ከመ፡ይቅትልዎ።

ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፺፫፡፳፩።

ወይንዕዋ፡ለነፍስ፡ጻድቅ።
ወይኴንን፡ደመ፡ንጹሐ።
ወኮነኒ፡እግዚአብሔር፡ፀወንየ።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፮፡፲፯-፲፱።

፲፯፤ ወበቀዳሚት ፡ ዕለተ ፡ ፍሥሕ ፡ ቀርቡ ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፮፤ ንጉሡም ፡ የግብጽን ፡ ግብሩን ፡ ሁሉ ፡ መነኮሳቱ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ለገዳሙ ፡ ሥራ ፡ ለመነኮሳቱም፡ቤቶች፡መሥሪያ፡ሊሆን፡ያሉ ጥዋቸው፡ዘንድ፡የግብጽን፡ገዥዎች፡አዘዘ።

፯፤ ይህንንም ፡ በጎ ፡ መታሰቢያ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ በፍቅር ፡ አርፎ ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ በጸናች ፡ አምላክን ፡ በወለደች፡በክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም ጸሎት፡ወደ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ገባ።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል፡

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ለዘላለሙ፡በእኛ፡ላይ፡ ይደርና ፡ ጌታችን ፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒ ታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያደረገው፡ ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፰፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዮሐንስና ፡ ጴጥሮስ ፡ ሄደው፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያመለከታ ቸውን፡ያንን፡ሰው፡አገኙት።

፱፤ ያላቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ነገሩት ፤ እርሱም፡ አዳራሹን፡አሳያቸውና፡ለበዐሉ፡የሚያስፈል ገውን፡ሁሉ፡በውስጥዋ፡አዘጋጁ።

፲፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ ከጭፍሮች ፡ ውስጥ ፡ ለብዙዎች ፡ ወገኖች ፡ ጉቦ ፡ ሰጥተው ፡ የማር ያምን ፡ ልጅ ፡ በበዓሉ ፡ ውስጥ ፡ ያያችሁት፡ እንደሆነ፡አድራሻውን፡ንገሩን፡አሉዋቸው፡

፲፩፤ ካህናቱ፡ታላላቆቹ፡ሁሉ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡ ተማክረዋልና።

ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት፡።

መዝ፡፺፫፡፳፩።

የጻድቁን፡ሰውነት፡ለጥፋት፡ይሿታል፡
ንጹሕ፡ደምንም፡የሚአፈስ።
እግዚአብሔር፡ግን፡አምባ፡መጠጊያ፡ሆነኝ፡ይበሉ፡

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፮፡፲፯-፲፱።

፲፯፤ ከፋሲካው፡በዐል፡በመጀመሪያው፡ቀን፡ደቀ

አርዳኢሁ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤልዎ፡
በአይቴ፡ትፈቅድ፡ናስተዳሉ፡ለከ፡ትብላዕ፡
ፋሥሐ።
፲፰ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ሑሩ፡ውስተ፡
ሀገር፡ኀበ፡ዕገሌ፡ወበልዎ፡ለበዐለ፡ውእቱ፡
ቤት፡ይቤለከ፡ሊቅ፡ጊዜየ፡ቀርበ፡ወበኀቤከ፡
እገብር፡ፋሲካ፡ምስለ፡አርዳእየ።
፲፱ ወገብሩ፡አርዳኢሁ፡በከመ፡አዘዞሙ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወአስተዳለዉ፡ሎቱ፡
ፋሥሐ።

ድኅረ፡ወንጌል።

በሠለስቱ፡ሰዓተ፡መዐልት፡ዘሐሙስ፡
ዘየኀብር፡ምስለ፡ትንቢት።

፴ ወሶበ፡ኮነ፡ጽባሐ፡ይቤሎሙ፡ሙሴ፡
ለሕዝብ፡እስመ፡አንትሙ፡አበስክሙ፡አበሳ፡
ዐቢየ፡ወይእዜኒ፡አነ፡አዐርግ፡ኀበ፡እግዚአ
ብሔር፡ለእመ፡ያስተሰሪ፡ለክሙ፡ኃጢአ
ተክሙ።
፴፩ ወገብአ፡ሙሴ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ወአስተ
ብቍዐ፡ወይቤ፡እግዚእ፡እግዚእየ፡ናሁ፡አበሰ
ዝንቱ፡ሕዝብ፡ኀጢአተ፡ዐቢየ።

፴፪ ወገብሩ፡ሎሙ፡አምላከ፡እምወርቅ፤
ወይእዜኒ፡እስእለከ፡ከመ፡ትስረይ፡ሎሙ፡
ኀጢአቶሙ፤ ወለእመ፡ኢትሰሪ፡ሎሙ፡
ደምስስ፡ስምየ፡እመጽሐፍ፡ዘጸሐፍከኒ።
፴፫ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ቅድሜየ፡
ሎቱ፡እደመስሶ፡እምነ፡መጽሐፍየ።

፴፬ ወይእዜኒ፡ተሠወጥ፡ምስለ፡ዝንቱ፡ሕዝብ፡
ኀበ፡ዘእብለከ፡ናሁ፡መልአኪየ፡የሐውር፡
ቅድሜከ፡ወበዕለተ፡ሐዊጾትየ፡እኤንኖሙ፡
በእንተ፡ኃጢአቶሙ።

፴፭ ወዘበጦሙ፡እግዚአብሔር፡ለሕዝብ፡
በእንተ፡ዘአምለኩ፡ላሕመ፡ዘገብረ፡ሎሙ፡
አሮን።
፩ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ሑር፡
እምዝየ፡አንተ፡ወሕዝብከ፡ዘአውፃእኮ፡



መዛሙርቱ፡ወደ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ቀርበው፡
በግዐ፡ፋሲካን፡ትበላ፡ዘንድ፡በየት፡ልናዘጋ
ጅልህ፡ትወዳለህ፡አሉት።
፲፰ ጌታ፡ኢየሱስም፡ከእገሌ፡ዘንድ፡ወደ፡ከተማ፡
ሂዳችሁ፡ባለቤቱን፡መምህር፡ጊዜዬ፡ደርሷ
ልና፡ከደቀ፡መዛሙርቴ፡ጋር፡ፋሲካን፡ካንተ፡
ዘንድ፡አደርጋለሁ፡ብሎሃል፡በሉት፡አላቸው።
፲፱ ደቀ፡መዛሙርቱም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡እንደ፡
አዘዛቸው፡አድርገው፡በግዐ፡ፋሲካን፡አዘጋ
ጁለት።

ከወንጌል፡በኋላ።

ከትንቢቱ፡ቃል፡ጋር፡የሚስማማ፡ሐሙስ፡
ከቀኑ፡በሦስት፡ሰዓት፡የሚነበብ፡ይህ፡ነው።

፴ ንጋት፡በሆነም፡ጊዜ፡ሕዝቡን፡ሙሴ፡
እንዲህ፡አላቸው፤እናንተ፡ታላቅ፡በደል፡
በደላችሁ፤አሁንም፡ኃጢአታችሁን፡ይቅር፡
ቢላችሁ፡እኔ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡
እወጣለሁ፡አላቸው።
፴፩ ሙሴም፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ተመልሶ፡
እንዲህ፡ብሎ፡ማለደ፤አቤቱ፡ጌታዬ፡እነሆ፡
ይህ፡ወገን፡ታላቅ፡ኀጢአት፡በመስራት፡
በደለ።
፴፪ ጣዖትንም፡ለራሳቸው፡ከወርቅ፡ሠሩ፤
አሁንም፡ኃጢአታቸውን፡ይቅር፡ትላቸው፡
ዘንድ፡እለምንሃለሁ፤ይቅር፡የማትላቸው፡
ከሆነ፡ከጻፍከኝ፡መጽሐፍ፡ፋቀኝ፡አለው።
፴፫ እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡እንዲህ፡አለው፤
እርሱን፡የበደለኝን፡ከመጽሐፌ፡(ከባለሟ
ልነቴ)፡እፍቀዋለሁ።
፴፬ አሁንም፡ከሕዝቡ፡ጋር፡ወዳዘዝኩህ፡ቦታ፡
ተመለስ፤እነሆ፡አገልጋዬ፡(ኢያሱ)፡
በፊትህ፡ይሄዳል፤በመዐትም፡በምጐበ
ኛቸው፡ቀን፡ስለ፡ኃጢአታቸው፡እቀጣቸ
ዋለሁ፡አለው።
፴፭ አሮን፡የሠራላቸውን፡ላም፡ስለ፡አመለኩ፡
እግዚአብሔር፡ከሕዝቡ፡ውስጥ፡ብዙ፡
አጠፋ።
፩ እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡ከግብጽ፡ያወጣ
ሃቸው፡ወገኖችህ፡እና፡አንተ፡ከዚህ፡ለአብ

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እምድረ፡ግብጽ፡ኀበ፡ምድር፡ዘመሐልኩ፡ለአብርሃም፡ወለይሥሐቅ፡ወለያዕቆብ፡ከመ፡አሀባሃ፡ለዘርዖሙ።

፰፤ ወናሁ፡እፌኑ፡መልአኪየ፡ቅድሜከ፡ኀበ፡ምድር፡እንተ፡ታውኅዝ፡ሐሊበ፡ወመዐረ።

፱፤ ርእዩ፡እ፡እኀው፡ኀበ፡ፍቅረ፡ዝንቱ፡ዐቢይ፡ነቢይ፡ወአስተብቍዖቱ፡ኀበ፡**እግዚኡ፡**በእንተ፡መድኃኒተ፡ሕዝቡ።

፲፤ ወኮነ፡አምሳለ፡ዛቲ፡ግብር፡ዘሀለወት፡ትኩን፡እስመ፡**እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ሶበ፡ፈቀደ፡ነጺሐ፡ሕዝቡ፡በደም፡ሐመ፡አፍአ፡ሀገር።

፲፩፤ ወንንጻሕኬ፡ንሕነኒ፡ካዕበ፡ኀቤሁ፡አፍአ፡እምትዕይንት፡ጸዊረነ፡ጽዕለቶ፡እስመ፡አልብነ፡ሀገር፡ዝየ፡ዘትነብር።

፲፪፤ ወባሕቱ፡ንሴፎ፡መንግሥተ፡ዘሀለወት፡ትምጻእ።

፲፫፤ ወላዕለ፡እዴሁ፡ናዕርግ፡ስብሐተ፡መሥዋዕተ፡ኵሎ፡ጊዜ፡ኀበ፡**እግዚአብሔር፡**እንተ፡ይእቲ፡ፍሬ፡ከናፍሪነ፡ዘተአኵት፡ለስሙ።

፲፬፤ ወንስእሎ፡ድኅነ፡እምአበሳቲነ፡ወዳኅፃቲነ፡**ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡**መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዓ፡ዛቲ፡በል።

## ምዕራፍ፡፹፪።

### ክፍል፡፩።

**በስድስቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።**

ዘኤርምያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፯፡፲–፲፭።

፲፤ ወይቢ፡ቁም፡ውስተ፡አናቅጸ፡ቤተ፡**እግዚአብሔር፡**ወአንብብ፡ዘንተ፡ነገረ፡ወበል፡ስምዑ፡**ቃለ፡እግዚአብሔር፡**ኵሉ፡ይሁዳ፡እለ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ርሃም፡ለይሥሐቅ፡ለያዕቆብም፡ለዘራችሁ፡እሰጣታለሁ፡ብዬ፡ወደማልኩላቸው፡አገር፡ሂድ፡አለው።

፰፤ እነሆ፡አገልጋዬን፡ኢያሱን፡ማርና፡ወተትን፡ወደምታፈስ፡ሀገር፡በፊትህ፡እሰዳለሁ፡አለው።

፱፤ ወንድሞች፡ሆይ፡ስለወገኖቹ፡ድኅነት፡**ከጌታው፡**ዘንድ፡ወደ፡አማላጅነቱና፡ወደዚህ፡ወደታላቅ፡ነቢይ፡ፍቅር፡እዩ።

፲፤ ትሆን፡ዘንድ፡ላላት፡ለዚች፡ሥራ፡አምሳል፡ሆነ፤**ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**የሕዝቡን፡በደም፡መንጻት፡በወደደ፡ጊዜ፡በከተማ፡አፍ፡መከራ፡ተቀበለ።

፲፩፤ ዳግመኛ፡እኛም፡ከከተማ፡ውጭ፡ስድቡን፡ተግዳሮቱን፡ተሸክመን፡በእርሱ፡ዘንድ፡እንንጻ፡በዚህ፡ለዘላለሙ፡የምትኖር፡አገር፡የለችንምና።

፲፪፤ ነገር፡ግን፡ትመጣ፡ዘንድ፡ያላትን፡መንግሥት፡ተስፋ፡እናደርጋለን፡እንጂ።

፲፫፤ ሁል፡ጊዜም፡በእጁ፡ላይ፡**ለእግዚአብሔር፡**መሥዋዕትን፡እናቅርብ፤ይህቺውም፡ስሙን፡የምታመሰግን፡የአንደበታችን፡ፍሬ፡ናት።

፲፬፤ ከበደላችንና፡ከኃጢአታችን፡የተነሣ፡ድኅነትን፡እንለምነው፡**መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡**ሰው፡ሁኖ፡መከራ፡ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዓ፡ዛቲ፡በል።

## ምዕራፍ፡፹፪።

### ክፍል፡፩።

**ሐሙስ፡ቀን፡በስድስት፡ሰዓት፡የሚነበብ፡**

የነቢዩ፡ኤርምያስ፡ትንቢት፡የአምላኩ፡በረከት፡ለዘላለሙ፡ከሁላችን፡ጋራ፡ይሁን።

ምዕ፡፯፡፲–፲፭።

፲፤ **በእግዚአብሔር፡**ቤት፡ቁመህ፡ይህንን፡ነገር፡በዚያ፡አንብብላቸው፤**ለእግዚአብሔር፡**ልትሰግዱ፡በበሮቿ፡ወደ፡እርሱ፡የምትገቡ፡

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ተዘውሁ ፡ እንተ ፡ እናቅጽ ፡ ውስቴታ ፡
ትስግዱ፡ለእግዚአብሔር።
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ኃያል፡አምላከ፡
እስራኤል ፡ አርትዑ ፡ ፍናዊክሙ ፡ ወምግባ
ረክሙ፡ወአኃድር፡ኀቤክሙ፡ውስተ፡ዝንቱ፡
ቤት።
ኢትትአመኑ ፡ ርእሰክሙ ፡ በነገረ ፡ ሐሰት ፡
እንዘ፡ትብሉ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ንሕነ።

ለእመ ፡ አርታዕክሙ ፡ ፍናዊክሙ ፡ ርቱዐ ፡
ወምግባሪክሙ፡ወለእመ፡ገቢረ፡ገበርክሙ፡
ፍትሐ፡ማእከለ፡ብእሲ፡ወማእከለ፡ቢጹ።
ወኢተዓገልክሙ፡እቤረ፡ወዕጓለ፡ማውታ፡
ወፈላሴ ፡ ወኢከዐውክሙ ፡ ደመ ፡ ንጹሐ ፡
ውስተ፡ዝንቱ፡ቤት፡ወኢሖርክሙ፡ወኢተለ
ውክሙ፡አማልክተ፡ነኪር፡ለእኪትክሙ።

አነብረክሙ ፡ ውስተ ፡ ብሔርክሙ ፡ እንተ ፡
ወሀብክዎሙ ፡ ለአበዊክሙ ፡ እምዓለም ፡
ወእስከ፡ለዓለም።
ወእመሰ፡ተወከልክሙ፡በነገረ፡ሐሰት፡ዘለ
ምንትሂ፡ኢይበቍዓክሙ።
ወቀተልክሙሂ፡ወሰረቅሙ፡ወዘመውክሙ፡
ወመሐልክሙ ፡ በዓመፃ ፡ ወዐጠንክሙ ፡
ለበዐል፡ወሖርክሙ፡ኀበ፡አማልክተ፡ነኪር፡
ዘኢተአምሩ፡ይረክበክሙ፡እኩይ።

ወመጻእክሙ፡ወቆምክሙ፡ቅድሜየ፡ውስተ፡
ዝ፡ቤት፡ኀበ፡ተሰምየ፡ስምየ፡ውስቴቱ፡
ወትብሉ፡ሥልጣን፡ብነ፡ለገቢረ፡ኵሉ፡
ርኩስ።
ቦኑ፡በዓተ፡ፈያት፡ውእቱ፡ቤትየ፡ኀበ፡
ተሰምየ፡ስምየ፡ውስቴቱ፡ህየ፡ወናሁ፡
አንትሙ፡ርኢክሙ፡በአዕይንቲክሙ፡ወአነ፡
ርኢኩ፡ይቤ፡እግዚአብሔር።
ሖሩ፡ርእዩ፡ውስተ፡ቤትየ፡ዘሴሎ፡ኀበ፡
ኀደረ፡ስምየ፡ህየ፡ቀዲሙ፡ወርእዩ፡ዘገበ
ርክዎ፡ሎቱ፡እምገጸ፡እከየ፡ሕዝብየ፡
እስራኤል።



ሐሙስ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል፡ስሙ፡በል፡አለ።
፫፤ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ ኃያል ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ አለ ፤ ጎዳናችሁን ፡ ሥራችሁን ፡
አቅኑ፤ እናንተ ፡ ባላችሁበት ፡ በዚህ ፡ ቤተ ፡
መቅደስ፡በረድኤት፡አድራለሁ፡አለ።
፬፤ እኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ነን ፡
እያላችሁ፡ በሐሰት ፡ ነገር ፡ ራሳችሁን ፡ አትተ
ማመኑ።
፭፤ የቀና ፡ ጎዳናችሁን ፡ ሥራችሁን ፡ ብታቀኑ ፡
በባልንጀራውና ፡ በባልንጀራው ፡ መካከል ፡
እውነት፡ፍርድ፡ብትፈርዱ።
፮፤ እናት፡አባቱ፡የሞቱበት፡ልጅንና፡ባልቴቲቱን፡
ስደተኛውንም ፡ ባትቃወሙ ፡ በዚህ ፡ ቤተ ፡
መቅደስ፡ንጹሕ፡ደምን፡ባታፈሱ፡መከራ፡ልት
መጣባችሁ፡ለመጥፊያችሁ፡የሚሆን፡የባዕድ፡
አማልክትን፡ሂዳችሁ፡ባታመልኩ።
፯፤ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ለአባቶ
ቻችሁ ፡ በሰጠኋቸው ፡ አገራችሁ ፡ አኖራች
ኋለሁ፡አለ።
፰፤ በሐሰት፡ነገር፡ብትተማመኑ፡ግን፡ለምንም፡
ለምን፡አይጠቅማችሁም።
፱፤ ነፍስ፡ብትገድሉ፡ብትሰርቁም፡ብትሰስኑም፡
በሐሰት ፡ ብትምሉም ፡ ለጣዖት ፡ ብታጥኑ ፡
ወደ፡ ማታውቋቸው ፡ ወደባዕድ ፡ አማልክት ፡
ሂዳችሁ ፡ ብታመልኩ ፡ በዚህ ፡ መከራ ፡ ያገኛ
ችኋል፡አለ።
፲፤ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ በዚህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡
መጥታችሁ ፡ በፊቴ ፡ ብትቆሙ ፡ ኃጢአትን ፡
ሁሉ፡ለመሥራት፡ሥልጣን፡አለን፡ብትሉ።

፲፩፤ በውኑ ፡ ያ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሌባ ፡ ዋሻ ፡
የቀማኛ ፡ ጋሻ ፡ ነውን? ስሜ ፡ በተጠራበት ፡
በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ በዚያ ፡ አለን?እግዚ
አብሔርም ፡ እናንተ ፡ በዓይናችሁ ፡ እነሆ ፡
ወደጣዖት ፡ አያችሁ ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡
በመዐት፡ተመለከትኩ፡አለ።
፲፪፤ ቀድሞ ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይጠራበት ፡ የነበረ ፡
በሴሎ ፡ ወዳለ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሂዳችሁ ፡ እዩ፤
ከወገኖቼ ፡ ከእስራኤል ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ያደረ
ግሁበትንም፡እዩ።

## በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፫፡ ወይእዜኒ፡እስመ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ገበርክሙ፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፡ነበብኩክሙ፡ወኢሰማ ዕክሙኒ፡ጸዋዕኩክሙ፡ወኢያውሥእክሙኒ።

፲፬፡ አነሂ፡ይእዜኒ፡እሬስዮ፡ለዝንቱ፡ቤት፡ኀበ፡ ተሰምየ፡ስምየ፡ውስቴቱ፡ዘቦቱ፡ትትዌከሉ፡ ወለብሔርኒ፡ዘወሀብክዎሙ፡ለአበ ዊክሙ፡በከመ፡ረሰይክዎ፡ለሴሎ።

፲፭፡ ወእገድፈክሙ፡እምቅድመ፡ገጽየ፡ከመ፡ገደ ፍክዎሙ፡ለአኀዊክሙ፡ለኵሉ፡ዘርዐ፡ ኤፍሬም።

ዘሕዝቅኤል፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፡፴፱–፵፬።

፴፱፡ ወአንትሙ፡ቤተ፡እስራኤል፡ከመዝ፡ይቤ፡ **አዶናይ፡እግዚአብሔር፡እግዚእ፡**ኵልክሙ፡ ኅድጉ፡ጌጋየክሙ፡ወእምዝ፡ስምዑኒ፡እንከ፡ ወኢታርኵሱ፡ስምየ፡እንከ፡በመባእክሙ፡ ወበጌጋይክሙ።

፵ እስመ፡በደብረ፡መቅደስየ፡ወደብር፡ነዋኅ፡ ዘእስራኤል፡ይቤ፡**አዶናይ፡እግዚአብሔር፡ እግዚእ፡**በህየ፡ይትቀነዩ፡ሊተ፡ኵሉ፡ ቤተ፡እስራኤል፡ለግሙራ፡ወበህየ፡እትዌከ ፈክሙ፡ወበህየ፡እሔውጽ፡ቀዳማያቲክሙ፡ ወቀዳማያተ፡ዘትፈልጡ፡በኵሉ፡ቅድሳ ቲክሙ።

፵፩፡ በመዐዛ፡ሠናይ፡እትዌከፈክሙ፡አመ፡አውፃ እኩክሙ፡እምአሕዛብ፡ወእትሜጠወክሙ፡ ወእመይጠክሙ፡እምኵሉ፡በሐውርት፡ኀበ፡ ተዘረውክሙ፡በውስቴቶሙ፡ወእትቄደስ፡ ብክሙ፡በቅድመ፡አዕይንቲሆሙ፡ ለአሕዛብ።

፵፪፡ ወተአምሩ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡**እግዚአብሔር፡** አመ፡አባእኩክሙ፡ውስተ፡ምድር፡እንተ፡ አንሣእኩ፡እዴየ፡ከመ፡እሀባ፡ለአበዊክሙ።

፵፫፡ ወትዜከሩ፡በህየ፡ፍናዊክሙ፡ወጌጋየክሙ፡ በዘረኰስክሙ፡ወትመትሩ፡ገጸክሙ፡በኵሉ፡ እከይክሙ።

፵፬፡ ወተአምሩ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡**እግዚአብሔር፡** ሶበ፡ገበርኩ፡ላዕሌክሙ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ከመ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

፲፫፡ ዛሬም፡ይህን፡ሁሉ፡አድርጋችኋልና፡አስተማ ርኋችሁ፤ አልሰማችሁኝም፤ በነቢያት፡ አድሬ፡ ጠሯኋችሁ፤ አልመለሳችሁልኝም፡ አለ፡**እግዚአብሔር**።

፲፬፡ እኔም፡ዛሬ፡ስሜ፡የተጠራበት፡እናንተም፡ የምትታመኑበት፡ይህንን፡ቤተ፡መቅደስ፡ለአ ባቶቻችሁ፡የሰጠኋቸውን፡አገር፡ሴሎምንም፡ እንዳደረግኋት፡አደርገዋለሁ፡ሲል።

፲፭፡ ወንድሞቻችሁን፡የኤፍሬምን፡ወገኖች፡ ሁሉ፡እንዳጠፋኋቸው፡እናንተንም፡አጠፋች ኋለሁ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑ ንና፡ነቢዩ፡ሕዝቅኤል፡የተናገረው፡ይህ፡ነው፡

ምዕ፡፳፡፴፱–፵፬።

፴፱፡ እናንተ፡የእስራኤል፡ወገኖች፡**ፈጣሪ፡ጌታ፡ እግዚአብሔር፡**እንዲህ፡አለ፤ሁላችሁ፡ኃጢ አታችሁን፡ተዉ፤ከዚህ፡በኋላ፡ስሙኝ፡ ስሜንም፡እንግዲህ፡ወዲህ፡በኃጢአታ ችሁና፡በመባአችሁ፡አታርክሱ።

፵፡ **ጌታ፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡**እስራኤል፡ በሚያመሰግኑበት፡ከፍ፡ባለ፡ተራራና፡በመ መስገኛዬ፡በቤተ፡መቅደስ፡የእስራኤል፡ ወገኖች፡ሁሉ፡ፈጽመው፡ይገዙልኛል፡ ብሎአልና፡በዚያ፡በረድኤት፡እቀበላች ኋለሁ፤ያዝመራችሁን፡መጀመሪያ፡በመ አችሁ፡ሁሉ፡የለያችሁት፡መጀመሪያ፡የተቀ ለደውን፡ሁሉ፡በዚያ፡እጐበኛለሁ።

፵፩፡ ከአሕዛብ፡አገር፡በአወጣኋችሁ፡ጊዜ፡በት መዐዛ፡አድርጌ፡እቀበላችኋለሁ፤ከእነሳቸው፡ ዘንድ፡ከተበተናችሁበት፡ከአሕዛብ፡አገር፡ መልሼ፡በረድኤት፡እቀበላችኋለሁ፤በአሕ ዛብም፡ፊት፡በእናንተ፡እመሰገናለሁ።

፵፪፡ ለአባቶቻችሁ፡እሰጥ፡ዘንድ፡እጄን፡ወደነሣ ሁበት፡አገር፡በአገባኋችሁ፡ጊዜ፡እኔ፡**እግዚ አብሔር፡**እንደሆንኩ፡ታውቃላችሁ።

፵፫፡ በዚያም፡የረከሳችሁበት፡በደላችሁና፡ ሥራችሁን፡ታስባላችሁ፤በክፉታችሁም፡ ሁሉ፡ፊታችሁን፡ትነጫላችሁ።

፵፬፡ እንደ፡ክፉ፡ጐዳናችሁ፡ጐስቋላ፡ክፉ፡እንደ ሆነም፡ሥራችሁ፡ስሜ፡እንዳይረከስ፡በናንተ

ኢይርኅቦ ፡ ስምየ ፡ በከመ ፡ ፍኖትክሙ ፡
እኩይ፡ ወበከመ ፡ ምግባሪክሙ ፡ ኅሡር ፡
ወኅሡም፡ይቤ፡አዶናይ፡እግዚአብሔር።

ዘተወክፈ፡ነቢየ፡በል።

ዘሚክያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ተሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፱፤፯–፲፫።

፯ በእንተ፡ዘአምዕዑ፡ቤተ፡እስራኤል፡ወቤተ፡
ያዕቆብ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ በገዘንቱ ፡
ጊጋዮሙ፡እንዘ፡ነገሩ፡ሠናይ፡በኀቤሆሙ፡
ወራትዓን ፡ የሐውሩ ፡ ቦቱ ፡ ወይሜልዑ ፡
ቅድመ።

፰ ወሕዝብየሰ ፡ ተቃወምዋ ፡ ቅድሜሃ ፡
ለሰላምሙ፡ወይፃረርዋ፡ወሰለብዎ፡ኩናቶ፡
ወአኅደግዎ፡ትውክልቶ፡ወይቀጠቅጥዎ፡
በውስተ፡ቀትል።

፱ ወበበይነ፡ዝንቱ፡ይገድፍዎሙ፡ለመላእክተ፡
ሕዝብየ፡ እምውስተ ፡ ትርሲተ ፡ አብያ
ቲሆሙ፡ ወይሰድድዎሙ ፡ እስመ ፡ እኩይ ፡
ምግባሮሙ።

፲ ቅረቡ፡አድባር፡ወእለ፡እምፍጥረተ፡ዓለም፡
ተንሥኡ፡ወሑሩ፡እስመ፡ኢኮነት፡እንቲ
አክሙ፡ዛቲ፡ዕረፍት።

፲፩ በእንተ ፡ ርኵስክሙ ፡ ጠፋእክሙ ፡ ወኀ
ለቅሙ ፡ ወጕየይክሙ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡
ዘይዴግነክሙ ፡ ጋኔን ፡ አቀመ ፡ ለከ ፡
ሐሰተ ፡ ወአውጻሕከ ፡ ሎቱ፡ ወይነ ፡
ወጼተሎ።

፲፪ ወይከውን፡በነፍኒፎሙ፡ለዝንቱ፡ሕዝብ፡
ይትጋብኡ፡ያዕቆብ፡ምስለ፡ኵሎሙ፡እለ፡
ይጸንሑ፡እምጽንሐሙ፡ለተረፈ፡እስራኤል፡
ወኣሬስየ፡ኅቡረ፡ለሚጠቶሙ፡ከመ፡አባግዕ
ውስተ፡መጽብብ፡ወከመ፡መርዔት፡ውስተ፡
ምብያቲሁ ፡ ወይትባልሑ ፡ እምሰብእ ፡
እኩያን፤

፲፫ ወበእንተ፡ቅትለቶሙ፡እንዘ፡ይትቃተሉ፡



ይህን ፡ ሁሉ ፡ ባደረግሁ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ፈጣሪ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደሆንኩ ፡ ታውቃላችሁ፡
አለ።

ነቢዩን፡በነቢይ፡ስም፡የተቀበለ፡የነቢዩን፡
ዋጋ፡ያገኛል፡በል።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡ሚክያስ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፱፤፯–፲፫።

፯፤ ሕጉ ፡ በነዚያ ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ ሲሆን ፡ ቅን ፡
የሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ በእርሱ ፡ ጸንተው ፡
የሚኖሩና፡ አስቀድሞም ፡ ወደ ፡ ሕጉ ፡ የሚገ
ሠግሡ ፡ ሲሆን ፡ ሁለቱ ፡ ነገድና ፡ ዐሥሩ ፡
ነገድ፡ በዚህ ፡ ኃጢአታቸው ፡ የእግዚአብ
ሔርን፡ልቡና፡ስለአሳዘኑ።

፰፤ ወገኖቼ፡እስራኤል፡ግን፡ሰላምን፡(ሕግን፡)ፊት፡
ለፊት፡ተቀዋወሚት፤ተጣሏትም፤ጋሻ፡ጦርንም፡
ማርከው ፡ ይወስዱበታል ፤ ተስፋውንም ፡
አስተዉት፤በሰልፍም፡ቀን፡ያጠፉታል።

፱፤ ሥራቸው ፡ ክፉ ፡ ነውና ፤ ስለዚህ ፡
በወገኖቼ ፡ የተሾሙ ፡ አለቆችን ፡ በሐር ፡
በተሸለሙ ፡ ቤቶቻቸው ፡ እየወጉ ፡ ይጥሏ
ቸዋል።

፲፤ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የነበራችሁ ፡ ተራሮች ፡
(ነገሥታት ፡) ለጥፋት ፡ ቅረቡ ፤ ይህች ፡
ዕረፍትም ፡ ለእናንት ፡ አትገባምና ፡ ተነሥ
ታችሁ፡ተማርካችሁ፡ሂዱ።

፲፩፤ ጣዖትን ፡ ስለአመለካችሁ ፡ ፈጽማችሁ ፡
ጠፋችሁ ፤ የሚከተላችሁም ፡ ሳይኖር ፡
ሸሻችሁ፤ አነስተኛ ፡ ጣዖትን ፡ ጋኔን ፡ ጠላት ፡
አቆመልህ፤አንተም፡ለጣዖቱ፡የወይን፡ጠጅ፡
ደምንም፡አፈሰስህለት።

፲፪፤ በእኒህ፡ወገኖች፡በልጅ፡ልጆቻችሁ፡ዘመን፡
እንዲህ ፡ ይሆናል ፤ የሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ተስፋ ፡
ደጅ ፡ ከሚጠኑ ፡ ከዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ይመለሳሉ ፤ መንጋ ፡ ወደመጣ
ቢያው ፡ ተናንቆ ፡ እንዲገባ ፡ በጎችም ፡
ወደጉረኖ ፡ ተጨናንቀው ፡ እንዲገቡ ፡ መመለ
ሻቸውንም ፡ አንድነት ፡ አደርጋታለሁ ፡
ከክፉዎች፡ሰዎችም፡ይድናሉ።

፲፫፤ ቀድሞ፡ጠላቶቻቸው፡ስለወጓቸው፡እነርሱም፡

በ፯፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

በቅድመ ፡ ገጾሙ ፡ ኀለፉ ፡ እምአንቀጽ ፡ ወወፅኡ፡እንተ፡ውስቴታ፡ወሖረ፡ንጉሦሙ፡ በቅድመ ፡ ገጾሙ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ይመርሐሙ።

ምዕ፡፫፡፩–፰።

፩፡ ወይብል ፡ ስምዑ ፡ ዘንተ ፡ መኳንንተ ፡ ቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ ወተረፈ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ኢኮነ ፡ ለክሙ ፡ አእምሮ ፡ ጥበብ ፡ ወፍትሕ ፡ እለ ፡ ትጸልዑ፡ሠናየ፡ወትገብሩ፡እኩየ።

፪፡ ወትመሥጥዎሙ ፡ አምእስቲሆሙ ፡ እምላዕሌሆሙ፡ወሥጋሆሙኒ፡እምውስተ፡አዕፅምቲሆሙ።

፫፡ ወበከመ ፡ በልዑ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ወአውጽኡ፡አምእስቲሆሙ፡እምላዕለ፡አዕፅምቲሆሙ ፡ ወገመዱ ፡ መሌሊቶሙ ፡ ከመ ፡ ሥጋ ፡ ውስተ ፡ ጽሕርት ፡ ወከመ ፡ አባል ፡ ውስተ፡መቅጹት።

፬፡ ቀዲሙ ፡ ከማሁ ፡ ይጸርሑ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢይሰምዖሙ ፡ ወይመይጥ ፡ ገጾ ፡ እምኔሆሙ፡ይእተ፡አሚረ፡እስመ፡አሕሰሙ፡ገቢረ፡ላዕሌሆሙ።

፭፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ላዕለ፡ነቢያት፡ እለ፡ያስሕትዎሙ፡ለሕዝብየ፡ወእለ፡ይኔዝርዎሙ ፡ በስነኒሆሙ ፡ ወይሰብኩ ፡ ሎሙ ፡ ሰላመ፡ዘአልቦ፡ዘአዘዝክዎሙ፡ወአንሥኡ፡ላዕሌሆሙ፡ቀትለ።

፮፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሌሊተ ፡ ይከውነክሙ ፡ ራእይክሙ ፡ ወጽልመተ ፡ ይከውነክሙ ፡ ሰገልክሙ ፡ ወየዐርብሙ ፡ ፀሐይ ፡ ለነቢያቲክሙ፡ወይጸልሞሙ፡መዐልት።

፯፡ ወይትኀፈሩ፡ሐላምያነ፡ሕልመ፡ሐሰት፡ወይሥሕቅዎሙ፡ለሰብአ፡ሰገል፡ወየሐምይዎሙ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

በፊታቸው፡እየተዋጉ፡ከበሮቻቸው፡ወጥተው፡ አለፉ፤ከእርሱም፡ወጥተው፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ ሄዱ ፤ ንጉሣቸውም ፡ በፊታቸው፡ እየተጓ ሔደ፤ ፈጣሪያቸው ፡ እግዚአብሔርም፡ ያጠፋ ቸዋል፤ከባቢሎንም፡ያወጣቸዋል።

ምዕ፡፫፡፩–፰።

፩፡ የያዕቆብ፡ወገኖች፡ሹማምንት፡ከእስራኤል፡ ወገን ፡ የቀራችሁ ፡ እናንተም ፡ ይህን፡ነገር፡ ስሙ ፤ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ለምትሠሩ፡በጎውን፡ ነገር፡ለምትጠሉ፡ሕጉን፡ማወቅ፡ፍርዱንም፡ መጠንቀቅ፡ለእናንተ፡አልሆነላችሁም፡አለ።

፪፡ ከላያቸው፡ላይ፡ቆዳቸውን፡ትገፍፋላችሁ፡ ሥጋቸውንም ፡ ከአጥንታቸው ፡ ላይ ፡ ትለያላችሁ።

፫፡ የወገኖቼን ፡ ሥጋቸውን ፡ (ከብታቸውን) እንደበሉ፡ቆዳቸውንም፡ከሰውነታቸው፡እንደገፈፉ ፡ የሰውነታቸውንም ፡ ሥጋ ፡ በምንቸት፡ ታላቅ ፡ ታናሽም ፡ በብረት፡ ጋን እንዲቀቀል፡ቆራረጡአቸው።

፬፡ በመከራ ፡ ተይዘው ፡ አስቀድመው፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ጮኹ፤እሱም፡አልሰማቸውም፡ በእነሱ ፡ ዕዳ ፡ የሚሆን ፡ ክፉ ፡ ሥራ፡ሠርተዋልና፡ያን፡ጊዜም፡ፊቱን፡ከእነርሱ፡ይመልሳቸዋል።

፭፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለ፤ ወገኖቼን፡ በሚያስቷቸው፡በሥልጣናቸውም፡በሚያስፈሩአቸው፡እኔ፡ያላዘዝኋቸውን፡ሰላም፡ሰላም፡ እያሉ፡በሚያስተምሯቸው፡በእነርሱ፡ሞትን፡ በሚያስነሡባቸው ፡ በነቢያት ፡ ላይ፡ በመዐት፡አለሁ።

፮፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ አደረጋችሁ ፡ ያያችሁት፡ ራእይ ፡ ሌሊት ፡ ይሆንባችኋል ፤ ጥንቆላ ችሁም፡ ጨለማ ፡ ይሆንባችኋል፤ ለነቢያቶችሁም ፡ ፀሐይ ፡ ይጠልቅባቸዋል ፤ የተናገሩትም፡ትንቢት፡ይቀርባችኋል፤ቀኑ፡ይጨልምባችኋል፡(ዕውቀቱም፡ይሠወርባችኋል)።

፯፡ ሐሰት፡ሕልምንም፡አለምን፡የሚሉ፡ሰዎች፡ በዚያ፡ወራት፡ያፍራሉ፤ጠንቋዮችንም፡ይ

Scanned by CamScanner

ለሰትሎሙ።

፰ ወአልቦ፡ዘያጸምአሙ፡ እንከ፡ ለእመ፡ አነ፡ ኢመላዕኩ፡ኃይለ፡መንፈሰ፡እግዚአብሔር፡ ኃይለ፡ወፍትሐ፡ከመ፡ይንግርዎ፡ለያዕቆብ፡ ኃጢአቶ፡ወለእስራኤልኒ፡ጌጋዮ።

ዘሶፎንያስ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

ምዕ፡፩፡፯–፲፰።

፯ እስመ፡አልጸቀት፡ዕለተ፡እግዚአብሔር፡ እስመ፡ አስተዳለወ፡ እግዚአብሔር፡ መሥዋዕቶ፡ ወቀደሶሙ፡ ለኅሩያኒሁ፡ ፍርሁ፡ እምቅድመ፡ ገጹ፡ ለእግዚአብሔር፡አምላክ።

፰ ወይከውን፡በዕለተ፡መሥዋዕቱ፡ለእግዚአብሔር፡ ወእትቤቀሎሙ፡ ለመላእክት፡ ወለቤተ፡ንጉሥ፡ወለኵሎሙ፡እለ፡ይለብሱ፡ አልባሰ፡ነኪር።

፱ ወእትቤቀሎሙ፡ለኵሎሙ፡ገሀደ፡በውስተ፡ አናቅጽ፡ይእተ፡አሚረ፡እለ፡ይመልዑ፡ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፡ ዐመጻ፡ ወጽልሑተ።

፲ ወይከውን፡ ይእተ፡ ዕለተ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ቃለ፡ አውያት፡ እም አናቅጽ፡ እምእለ፡ ይወግዑ፡ ውውዓ፡ እምውስጥ፡ ወቀትል፡ ዐቢይ፡ በውስተ፡አውግር።

፲፩ ብክዩ፡እለ፡ትነብሩ፡በውስተ፡ቀትል፡እስመ፡ ይመስሉ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛበ፡ ከነዓን፡ ወተሠረዉ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይትዔበዩ፡ በወርቅ።

፲፪ ወይከውን፡ይእተ፡ዕለተ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡





ቁባቸዋል፤ይዝቱባቸዋል፤ሁሉንም፤አንድ፡ አድርገው፡ያሟቸዋል።

፰፡ ዕውቀትን፡ ፍርድን፡ ገልጠው፡ ለያዕቆብ፡ ኃጢአቱን፡ለእሥራኤል፡በደሉን፡ይነግሩት፡ ዘንድ፡የእግዚአብሔርን፡የመንፈስ፡ኃይል፡ካላ ሳደርኩባቸው፡የሚሰማቸው፡የለም፡አለ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ትኑርና፡ ነቢዩ፡ ሶፎንያስ፡ የተናገረው፡ ትንቢት፡ይህ፡ነው፤አሜን።

ምዕ፡፩፡፯–፲፰።

፯፡ የእግዚአብሔር፡ ቀን፡ ደርሳለችና፡ እግዚአብሔርም፡ የሰውን፡ጥፋት፡መሥዋዕት፡አድርጎ፡ አዘጋጅቶታልና፡ለሹመት፡ለምክር፡የተመረ ጡትን፡ሰዎች፡ለይቶአቸዋልና፡ከፊጣሪያችሁ፡ ከእግዚአብሔር፡ገጸ፡መዐት፡የተነሣ፡ፍሩ።

፰፡ የእግዚአብሔርም፡ በመሥዋዕቱ፡ ቀን፡ እንዲህ፡ ይሆናል። አለቆችንም፡የንጉሥንም፡ ወገኖች፡ የባዕድ፡ (የጣዖቱን)፡ ልብስ፡ የሚለብሱ፡ሰዎችንም፡ሁሉ፡እበቀላቸዋለሁ።

፱፡ በፈጣሪያቸው፡ በእግዚአብሔር፡ ማደሪያ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ዐመፅን፡ ተንኰልን፡ የሚመሉ፡ ሰዎችን፡ ሁሉ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ተገልጬ፡በአደባባይ፡እበቀላቸዋለሁ፡አለ።

፲፡ ያን፡ ቀን፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤ እየደነፉ፡ ከሚወጉት፡ሰዎች፡የተነሣ፡የጩኸት፡ቃል፡ በአደባባይ፡ ይሰማል፤ በውስጥ፡ ዕኑ፡ ግርግርታ፡ሰልፍም፡በኮረብታው፡ይደረጋል፡ አለ፡እግዚአብሔር።

፲፩፡ እስራኤል፡ሁሉ፡የከነዓንን፡ሰዎች፡መስለ ዋልና፡በወርቃቸውም፡ብዛት፡የሚታበዩም፡ ሰዎች፡እልም፡ብለው፡ጠፍተዋልና፡ወደ ሰልፉ፡ወጥታችሁ፡የተቀመጣችሁ፡ሰዎች፡ እዘኑ፤አልቅሱ።

፲፪፡ እግዚአብሔር፡ያን፡ቀን፡እንዲህ፡ይሆናል፡

በ፲፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እፈትና ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በማኅቶት ፡
ጥበብ ፡ ወእትቤቀሎሙ ፡ ለእደው ፡
እለ ፡ ያስተሐቅሩ ፡ ሕጎሙ ፡ እንዘ ፡
ይብሉ ፡ ኢያሤኒ ፡ ወኢያኂሥም ፡ እግ
ዚአብሔር።
፲፫፡ ወየኃሥር ፡ ኃይሎሙ ፡ ወይትበረበራ ፡
አብያቲሆሙ ፡ የሐንጹ ፡ አብያተ ፡ ወኢይነብ
ርዎን ፡ ይተክሉ ፡ ወይነ ፡ ወኢይሰትይዎ ፡
ለወይኖሙ።

፲፬፡ እስመ ፡ አልጸቀት ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዐባይ ፡ ቀርበት ፡ ወአልጸቀት ፡ ወአፍጠነት ፡
ጥቀ፡ድምፃ፡ለዕለተ፡እግዚአብሔር፡መራር፡
ወእኪት፡ወጽንዕት።

፲፭፡ ይእቲ ፡ ዕለተ ፡ መንሱት ፡ ዕለተ ፡
ሕማም፡ወምንዳቤ፡ዕለተ፡ምምዓ፡ወሙስና፡
ዕለተ ፡ ጽልመት ፡ ወቆባር ፡ ዕለተ ፡ ደመና ፡
ወጊሜ።
፲፮፡ ዕለተ ፡ ቀርን ፡ ወውውዓ ፡ ላዕለ ፡
አህጉር ፡ ጽኑአት ፡ ወላዕለ ፡ በሐውርት ፡
ልዑላት።
፲፯፡ ወአመነድቦሙ ፡ ለሰብእ ፡ ወየሐውሩ ፡
ከመ ፡ ዕውራን ፡ እስመ ፡ አበሱ ፡ ላዕለ ፡
እግዚአብሔር፡ ወእክዐው ፡ ደሞሙ ፡
ከመ ፡ ማይ ፡ ወሥጋሆሙ ፡ ከመ ፡
ጸፍዕ።
፲፰፡ ወኢያድኅኖሙ ፡ እንከ ፡ ወርቆሙ ፡
ወብሩሮሙ ፡ እምዕለተ ፡ መዐቱ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ወእምእሳተ ፡ ቅንዓቱ ፡
ትጠፍእ ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡ እስመ ፡
ፍጡነ ፡ ያኃልቆሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡
ውስቴታ።

ምዕ፡፪፡፩-፫።

፩፡ ተጋብኡ፡ወተጋነዩ፡ሕዝብ፡አብዳን።

፪፡ ዘእንበለ፡ትኩኑ፡ከመ፡ጽጌ፡ይቡስ፡ዘወድቀ፡
ወዘእንበለ፡ትብጻሕክሙ፡መቅሠፍተ፡እግዚ
አብሔር፡ወዘእንበለ፡ትምጻእክሙ፡ዕለተ፡
መዐቱ፡ለእግዚአብሔር።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

አለ፤ኢየሩሳሌም፡በዕውቀት፡ፋናዬ፡እፈት
ታለሁ፤እበረብራታለሁ፤እግዚአብሔር፡በ
ነገር ፡ አያደርግም ፤ ክፉም ፡ አያደርግም
እያሉ፡ ሕጋቸውን ፡ የሚንቁ ፡ የሚአቃልሉ
ሰዎችንም፡እበቀላቸዋለሁ።
፲፫፤ ኃይላቸው ፡ ይደክማል ፤ ቤቶቻቸውም ፡ ይፈ
በራሉ ፤ እንኖርባቸዋለን ፡ ብለው ፡ ቤቶችን
ይሠራሉ፤ግን፡አይኖሩባቸውም፤እንጠጣለን
ብለው፡ወይን፡ይተክላሉ፤ወይናቸውን፡አይጠ
ጡትም፡አለ።
፲፬፤ የእግዚአብሔር ፡ ታላቂ ፡ ቀን ፡ ደርሳለችና፡
እስራኤል ፡ የሚጠፉባት ፡ ፈጽማ ፡ ቀረበች
ፈጠነችም፤ፈጥናም፡ደረሰች፤የዚያችም፡የእ
ግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ድምጿ ፡ መራራ፡እጅግ፡
የምታሳዝን፡ክፉ፡ናት፤የጸናችም፡ናት።
፲፭፤ ያችም ፡ ቀን ፡ የፈተና ፡ ቀን ፡ ናት ፤ የመከራና፡
የጭንቀት ፡ ቀን ፡ ናት ፤ የሽሽትና ፡ የጥፋትም፡
ቀን ፡ ናት ፤ የጨለማና ፡ የጭጋግ ፡ ቀን፡ናት፤
የደመናና፡የጉም፡ቀን፡ናት።
፲፮፤ በጽኑዕ፡አምባዎች፡በታላላቆችም፡መንደሮች፡
ላይ፡ውጋ፡ውጋ፡የሚል፡ነጋሪት፡የሚሰማባት፡
ግርግርታም፡የሚደረግባት፡ቀን፡ናት።
፲፯፤ ሰዎችንም ፡ አስጨንቃቸዋለሁ ፤ እግዚአብ
ሔርን ፡ በድለዋልና ፡ ዕውር ፡ እየዳሠሠ፡
እንዲሄድ ፡ እየዳሠሡ ፡ ይሄዳሉ ፤ ደማቸ
ውንም፡ እንደ ውኃ ፡ አፈስሰዋለሁ ፤ ሥጋቸ
ውንም፡እንደፈረስ፡እጥለዋለሁ።
፲፰፤ ከእግዚአብሔር፡የቁጣ፡ቀን፡የተነሣ፡እግዚ
አብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ ካመጣት ፡ ፀዋዩ፡
ብራቸውና፡ወርቃቸው፡ከእንግዲህ፡ወዲህ፡
አያድናቸውም፤በዚያ፡የሚኖሩትን፡ፈጥኖ፡
ያጠፋቸዋልና ፤ ከቅናቱም ፡ እሳትነት፡
የተነሣ፡ምድር፡ሁላ፡ትጠፋለች።

ምዕ፤፪፡፩-፫።

፩፤ እናንተ ፡ ሰነፎች ፡ ወገኖች ፡ በንስሐ ፡ ተሰብሰ
ባችሁ፡ተለማመጡ።
፪፤ እንደ ፡ ወደቀ ፤ እንደ ፡ ደረቀ ፡ አበባ ፡ ሳትሆኑ፡
የእግዚአብሔርም ፡ መቅሠፍቱ ፡ ሳትደርስ
እግዚአብሔርም፡የሚቆጣባት፡ቀን፡
ሳትመጣባችሁ።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

...ሣዕ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵል
...ከመ ፡ ትሑታን፡ ምድር ፡ ተገበሩ ፡
...ደኒቶ ፡ ወኅሥዋ ፡ ለርትዕ ፡ ወአው
...ሥኦ፡ከመ፡ትድኅኑ፡እምዕለተ፡መዐቱ፡
ለእግዚአብሔር።

...ተመከፈ፡ነቢዩ፡በል።

...ግበበ፡ሲራክ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፲፪፡፲፫-፲፰።

...መኑ፡ያስተምህሮ፡ለአርዌ፡ምድር፡ወለኵሉ፡
አርዌ፡አኩይ።

...ከማሁ፡ዘየሐውር፡ምስለ፡ብእሲ፡ኃጥእ፡
ወይዴመር፡ምስለ፡ኃጢአቱ።

...ለአንተ፡ምዕር፡ይቀውም፡ምስሌከ፡ወእስከ፡
ትትመየጥ፡ኢትሬእዮ፡እንከ፡ወኢይት
ዓገሥ፡ምስሌከ።

...በከናፍሪሁሰ፡ያስተጥዕም፡ለከ፡ቃሎ፡
ጸላኢከ፡ወበልቡ፡ይመክር፡ውስተ፡ግብ፡
ያውድቀ፡ወዐይናሂ፡ያነብዕ፡ለከ፡ጸላኢከ፡
ወእምከመ፡አስሐተከ፡ኢይጸግብ፡
እምደምከ።

...ወእመኒ፡ተመንደብከ፡ቅድመ፡ኵሉ፡
ትረክቦ፡ቅድመ፡ገጽከ፡ወከመ፡ዘይረድአከ፡
ያቴሕት፡ርእሶ፡ታሕተ፡ሰኰናከ።
...ወይጠፍሕ፡በእደዊሁ፡ወየሐውስ፡
ርእሶ፡ወእምዝ፡ይመይጥ፡ገጾ፡ወይ
ትቃጸበከ።

ምዕ፡፫፡፩።

...ዘገሠሠ፡ፒሳ፡ይትአኀዝ፡ቦቱ፡ወዘተአረኮ፡
ለዕቡይ፡ይከውን፡ከማሁ።

## ክፍል፡፪

...ምድርሳነ፡ስምዖን፡ዓምዳዊ።
...እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሀበኒ፡ከመ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፫፤ በዚህ፡ዓለም፡የተዋረዳችሁ፡ሁሉ፡እግዚአብ
ሔርን፡በሕግ፡በአምልኮት፡ፈልጉት፤
ዕውነት፡ነገርን፡ሥሩ፤የቀናችውንም፡ነገር፡
ፈልጓት፤እግዚአብሔርም፡ቁጣውን፡ከሚያ
ደርግባት፡ቀን፡ትድኑ፡ዘንድ፡ሕጉን፡
ተማሩለት።

የነቢይን፡ዋጋ፡የተቀበለ፡በል።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፡
ጥበበኛው፡ሲራክ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፲፪፡፲፫-፲፰።

፲፫፤ ለምድር፡እባብና ለክፉ፡አውሬስ፡ሁሉ፡
መንከስን፡ማን፡ያስተምረዋል?

፲፬፤ ከኃጢአተኛም፡ሰው፡ጋር፡የሚሄድ፡በኃጢ
አቱም፡የሚተባበር፡እንዲሁ፡ነው።

፲፭፤ ጠላት፡ከአንተ፡ጋር፡አንድ፡ጊዜ፡ይቆማል፤
ነገር፡ግን፡እስከትመለስ፡ድረስ፡አታየውም፤
ካንተም፡ጋር፡መከራህን፡አይታገሥም።

፲፮፤ ጠላትህ፡በከንፈሩ፡ወንድሜ፡ምን፡አገኘህ፡
እያለ፡ነገሩን፡ያጣፍጥልሃል፤በጉድጓድ፡
ይጥልህ፡ዘንድ፡በልቡ፡ይመክራል፤ለእገሌ፡
ጉድጓድ፡ስቆፍርለት፡ውዬ፡መጣሁ፡ይላል፤
ይኸውም፡ጠላትህ፡ወንድሜ፡ምን፡አገኘህ፤
እያለ፡ዐይኑን፡ይጨምቅልሃል፤ካሳተህ፡
በኋላ፡ግን፡ከደምህ፡አይጠግብም።

፲፯፤ የሚረዳህም፡መስሎ፡ራሱን፡ከጫማህ፡
በታች፡ያዋርዳል፤ብትቸገርም፡ከሁሉ፡
አስቀድሞ፡ከፊትህ፡ታገኘዋለህ።

፲፰፤ ራሱንም፡እየነቀነቀ፡ጭኑን፡በእጁ፡ይጸፋል፤
ከዚህም፡በኋላ፡ይህ፡እንጂ፡መከራ፡
የመጣበት፡በኃጢአቱ፡ነው፡እያለ፡ፊቱን፡
መልሶ፡ይጠቃቀስብሃል።

ምዕ፡፫፡፩።

፩፤ አዶሮ፡ማርን፡የያዘ፡ሰው፡በእርሱ፡ይያዛል፤
ትዕቢተኛንም፡ወዳጅ፡ያደረገው፡ሰው፡
እንደርሱ፡ይሆናል።

## ክፍል፡፪

ከዐምዳዊው፡ስምዖን፡ድርሳን፡የተገኘ።

፩፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ንጹሐት፡

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እሕቅፍ፡አእጋሪከ፡ንጹሐተ።
፲፱፡ ወአጼኑ፡እምኔሆን፡መዐዛ፡ሕይወት፡ወአር
ሐሶን፡በአንብዐ፡አዕይንትየ፡ወእመዘምዘን፡
በሥዕርተ፡ርእስየ፡ከመ፡ትበለኒ፡በሰላም፡
ሑር፡ተኀድገ፡ለከ፡ኃጢአትከ፡ወስምከ፡
ይኩን፡ጽሑፈ፡ውስተ፡መጽሐፈ፡ሕይወት፡
ሀበኒ፡ዘንተ፡በከንቱ፡በእንተ፡ስምከ፡ቅዱስ።

፳፡ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘኀፀብከ፡
እግረ፡አርዳኢከ፡ኀፅበኒ፡እምአበሳየ፡ወእምኃ
ጢአትየ።
፳፩፡ ወንዛህ፡ላዕሌየ፡አዛበከ፡ከመ፡እንጻሕ፡
ፈድፋደ፡እምአስሐትያ።

### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፻፩፡፩–፫።

፩፡ እመልእክተ፡ሲኖዲቆን፡ዘአብ፡አባ፡
ፊላታዎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእስክንድርያ፡
ዘፈነዎ፡ኀበ፡አባ፡ዲዮናስዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ዘአንጾኪያ፡ለበውኩ፡ዘጸሐፍከ፡ሊተ፡አ፡
እኁ፡ፍቁር፡ወክቡር፡እግዚአብሔር፡ያኑኅ፡
መዋዕሊከ፡ወያፈድፍድ፡ጸጋከ፡ወያግርር፡
ፀረከ፡ወይዕቀብከ፡በትንብልናሃ፡ለእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡
ወኵሎሙ፡ቅዱሳን።
፪፡ ወናሁ፡አእመርኩ፡ስእለተከ፡ዘሰአልከኒ፡
ዘኀለየ፡ልብከ፡ያቅም፡እግዚአብሔር፡
ወይሕፅኖ፡በሐሜት፡ዘውእቱ፡በእንተ፡ሞተ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወሶበ፡
ተፈልጠት፡ነፍስ፡እምነ፡ሥጋ፡ኢተፈልጠ፡
መለኮት፡እምነ፡ሥጋ፡ወኢ፡እምነ፡ነፍስ፡
ዘተፈልጠት፡እምነ፡ሥጋ፡ወኢቆመ፡
መለኮት፡ዘኀዱር፡በሥጋ፡ህየንተ፡ነፍስ፡
እመሰ፡ኮነ፡ከመዝ፡እምኢጥዕመ፡ሞተ፡
እስመ፡መለኮትሰ፡ዐቢይ፡ወክቡር፡ውእቱ፡
ወኢይክል፡ላዕሌሁ፡ሞት፡ወለሊሁ፡መዋዒ፡
ሞት፡ውእቱ፡ወባሕቱ፡ጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ፡
ዘነሥአ፡እምእግዝእተ፡ኵልነ፡ማርያም፡
ድንግል፡እንዘ፡ይትዋሐድ፡ምስሌሁ፡
መለኮት፡ወኢተፈልጠ፡እምኔሁ፡ለግሙራ።
፫፡ ወይእዜኒ፡ንበል፡እግዚአብሔር፡ቃል፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

የሆኑ፡እግሮችህን፡አቅፋቸው፡ዘንድ፡ስጠኝ፡
፲፱፡ ከእርሳቸውም፡የሕይወት፡መዐዛን፡አሸት፡
ዘንድ፤ከዐይኖቼ፡በሚፈስ፡ዕንባ፡እርሳቸው፡
ዘንድ፤በራሴ፡ጸጉርም፡አሻቸው፡ዘንድ፡
ኃጢአትህ፡ተፍቆልሃል፤በሰላም፡ሂድ፡
ትለኝ፡ዘንድ፤ስምህም፡በሕይወት፡
መጽሐፍ፡ይጻፍ፡ትለኝ፡ዘንድ፡የ፱ን፡ስለ፡
ተቀደሰው፡ስምህ፡ያለዋጋ፡ስጠኝ።
፳፡ የደቀ፡መዛሙርትህን፡እግር፡ያጠብህ፡
ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤ከኃጢ
አቴና፡ከበደሌ፡እጠበኝ።
፳፩፡ በላዬም፡የንስሐ፡ውኃን፡እርጨኝ፤ከበረድ፡
እጅግ፡እነጻ፡ዘንድ።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፻፩፡፩–፫።

፩፡ የእስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ፊላታዎስ፡
ወደ፡አንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወደ፡አባ፡ዲዮ
ናስዮስ፡ከላከው፡ሲኖዶሳዊ፡መልእክት፡
የከበርክ፡የተወደድክ፡ወንድም፡ሆይ፡የጻፍ
ልኝን፡አስተውየዋለሁ፤እግዚአብሔር፡
ዘመንህን፡ያብዛ፤ሹመትህን፡ከፍ፡ያድርግ፤
ጠላትህን፡ያድክም፡በእመቤታችን፡
ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡አማላጅነት፡
በቅዱሳንም፡ሁሉ፡አማላጅነት፡ይጠብቅህ።
፪፡ እነሆ፡የለመንኸኝን፡ልመና፡ዐውቄዋለሁ፡
ልብህ፡ያሰበውን፡እግዚአብሔር፡ይፈጽም፤
በተድላ፡በደስታም፡ያጽናው፤ይኸውም፡ስለ
ጌታችን፡ስለ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሞት፡ነው፡
ነፍስ፡ከሥጋ፡በተለየች፡ጊዜ፡መለኮት፡ከሥጋ፡
አልተለየም፤ከሥጋ፡ከተለየች፡ነፍስም፡አልተ
ለየም፤ከሥጋ፡ጋር፡የተዋሐደ፡መለኮት፡
በነፍስ፡ፈንታ፡ምትክ፡ሆኖ፡አልገባም፤እንዲህ
ቢሆን፡ኖሮ፡ክርስቶስ፡ባልሞተም፡ነበር፡
መለኮት፡ኃያልም፡ክቡርም፡ነውና፤የማይደ
ፈርም፡ነውና፤ሞትም፡ሊሠለጥንበት፡አይች
ልም፤ሞትንም፡ድል፡የሚነሣው፡እሱ፡ነውና፡
መለኮት፡ከእመቤታችን፡ከድንግል፡ማርያም
በነሣው፡ሥጋ፡እርሱን፡ተዋሕዶ፡ሞትን፡
ቀመሰ፡እንጂ፤ከሥጋም፡ፈጽሞ፡አልተለየም።
፫፡ አሁንም፡እግዚአብሔር፡ቃል፡በሥጋው፡

ፈጠረ፡ለኵ፡ሥጋ፡ውስተ፡ከርሠ፡ድንግል፡
ማርያም፡ወነሥአ፡ለኵ፡ሥጋ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡
ነባቢት፡ወለባዊት፡ወእምላክ፡ቃል፡
ተዋሐደ፡ምስሌሁ፡እንበለ፡ተፈልጦ፡
ወኢውላጤ፡ወውእቱ፡አሐዱ፡አካል፡እምሠ
ለስቱ፡አካላት፡እለ፡ፍሉጣት፡በገጻት፡
ወእሙንቱ፡በጽምረተ፡አሐዱ፡መለኮት፡
በከመ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡ዘኑሲስ፡
በውስተ፡ድርሳኑ፡ዘደረሰ፡በእንተ፡
ትስብእቱ፡ለመድኅን፡ቃል፡እስመ፡በጊዜ፡
ዘወረደ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ላዕለ፡ድንግል፡
ኀደረ፡ላዕሌሃ፡ኃይል፡አርያማዊ፡ከመ፡
ያቅም፡እምኔሃ፡ብእሲ፡ሐዲስ፤ዘተሰምየ፡
ብእሴ፡ሐዲሰ፡በተወልዶ፡ልደት፡ነኪር፡
ወአኮ፡በከመ፡ልማደ፡ዕንሶን፡ለአንስት፡ወወ
ሊዶቶን፡እንዘ፡ይትዋሐድ፡ምስለ፡እግዚአ
ብሔር፡በጊዜሁ።

፬ ወንለቡ፡ይእዜ፡ተዋሕዶተ፡እግዚአብሔር፡
ቃል፡ምስለ፡ሥጋሁ፡ዘነሥአ፡ለኵሉ፡ወቦቱ፡
ሐመ፡ወሞተ፡እስመ፡መለኮቱ፡ኢሐማሚ፡
ወኢመዋቲ፡ውእቱ፡ወበጊዜ፡ሕማሙሂ፡
ወሞቱ፡ኢተፈልጠ፡እምኔሁ፡መለኮት፡
ለግሙራ፡እስመ፡ብሂልሰ፡ከመ፡እግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ሐመ፡ወሞተ፡በፈቃዱ፡በእን
ቲአነ፡ቃል፡እሙን፡ወጽድቁ፡ወርቱዕ፡
ውእቱ፡እስመ፡ሕማመሰ፡ወመዊተ፡ረሰየ፡
ለሥጋ፡ባሕቲቱ፡እንዘ፡ኢይትፈለጥ፡
እምኔሁ፡መለኮት።

፭ ወባሕቱ፡እስመ፡ብሂልሰ፡ወንባብ፡ከመ፡
መለኮት፡ሐመ፡ወሞተ፡ንባብ፡ሙሱን፡
ወዕልወት፡ውእቱ፡እስመ፡ህላዌ፡መለኮትሰ፡
ኢይትዌለጥ፡ወኢይቀርቦ፡ሕማም፡ወሞት፡
ለግሙራ፡ወባሕቱ፡ሞተ፡በሥጋሁ፡ወተፈ
ልጠት፡ነፍሱ፡እምሥጋሁ፡ወአኮ፡
እመለኮቱ። ወመለኮቱሰ፡ኢተፈልጠ፡
እምነፍሱ፡ወኢእምሥጋሁ፡ወባሕቱ፡
ይትዋሐድ፡ምስለ፡ክልኤሆሙ፡እሉ፡
እሙንቱ፡ሥጋ፡ወነፍስ።
በረከቶሙ፡ለእሉ፡መምህራን፡የሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እመጽሐፈ፡ስንክሳር።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
አሐዱ፡አምላክ።

 

ማርያም፡ማሕፀን፡ሊዋሐደው፡ሥጋን፡
ፈጠረ፤የምትናገር፡የምታውቅ፡
ነፍስ፡ያለችውን፡ሥጋ፡ነሣ፡እንበል፤
አምላክ፡ቃል፡ያለ፡መለወጥ፡ያለ፡
መለየት፡ሥጋን፡ተዋሐደ፤ይኸውም፡
በገጽ፡ልዩ፡በአንድ፡መለኮት፡አንድ፡
ከሚሆኑ፡ከሦስቱ፡አካላት፡አንዱ፡አካል፡
ነው፤የኑሲስ፡ኤጲስቆጶስ፡ጎርጎርዮስ፡
መድኅን፡ቃል፡ሰው፡የመሆኑን፡ነገር፡
በተናገረበት፡ድርሳኑ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
በድንግል፡ላይ፡በወረደ፡ጊዜ፡ልዩ፡ልደትን፡
በመወለድ፡ሐዲስ፡ሰው፡የተባለ፡አዲስ፡
ሰውነትን፡ከእርሷ፡ይነሣ፡ዘንድ፡አርያማዊ፡
ኃይል፡በእርሷ፡አደሮአልና፡ብሎ፡እንደተ
ናገረ፡ሥጋም፡ከእግዚአብሔር፡በጊዜ፡
ሲዋሐድ፡እንደ፡ሴቶች፡ፅንስና፡መውለድ፡
ልማድ፡አይደለም።

፬ አሁንም፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ሊዋ
ሐደው፡ከፈጠረው፡ሥጋ፡ጋር፡መዋ
ሐዱን፡መለኮትም፡የማይታመም፡የማይ
ሞት፡ነውና፡በሥጋ፡መታመሙን፡መሞ
ቱን፡እንወቅ፤እናስተውል፤በሕማሙም፡
በሞቱም፡ጊዜ፡መለኮት፡ከሥጋው፡ፈጽሞ፡
አልተለየም፤እግዚአብሔር፡ቃል፡በፈቃዱ፡
ስለ፡እኛ፡እንደታመመ፡እንደሞተ፡መና
ገርስ፡የታመነ፡የተረዳ፡የቀና፡ነገር፡ነው፤
መለኮት፡ከሥጋ፡ሳይለይ፡ሕማምን፡ሞትን፡
ለሥጋው፡አድርጓልና።

፭ መለኮት፡ታመመ፡ሞተ፡ብሎ፡መናገር፡
ግን፡የማይገባ፡አነጋገር፡ክሕደትም፡
ነው፡እኮን፡የመለኮት፡ባሕርይ፡አይለ
ወጥምና፤ሕማም፡ሞትም፡ፈጽሞ፡አያ
ገኘውምና፤ነገር፡ግን፡በሥጋው፡
ሞተ፡ነፍሱም፡ከመለኮቱ፡ያይደለ፡
ከሥጋው፡ተለየች፤መለኮት፡ግን፡
ከነፍሱም፡ከሥጋውም፡አልተለየም፤
ከሁለቱም፡ተዋሕዷል፡እንጂ፤እነዚ
ህም፡ነፍስና፡ሥጋ፡ናቸው።
የእነዚህ፡መምህራን፡በረከታቸው፡ከእኛ፡
ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ከስንክሳር፡መጽሐፍ፡የተገኘ።

በአብ፡በወልድ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡እናምናለን።

| በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፩፤ አመ ፡ ፳ወ፮ ፡ ለመጋቢት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኀፀበ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እግረ ፡ አርዳኢሁ።<br>፪፤ ወይቤሎሙ ፡ አንትሙኒ ፡ ከመዝ ፡ ግበሩ ፡ ለቢጽክሙ።<br>ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | ፩፤ መጋቢት፡ሃያ፡ስድስት፡ቀን፡በዚች፡ዕለ… የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ የደቀመዛ… ርቱን፡እግር፡አጠበ።<br>፪፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፤ እናንተም ፡ ለባልንጀ… ቻችሁ፡እንዲሁ፡አድርጉ።<br>ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘለዓ… ይኑር፡አሜን። |
| ምንተኑ፡በል።<br>ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።<br>በዕለተ፡ፍልሰታ፡ለወላዲቱ፡ዘከመ፡ተክህነ፡እግዚእነ፡በኵሉ፡ጉባኤ።<br>፩፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ኮነ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካህነ ፡ ለሥጋ ፡ ወላዲቱ ፡ ቅድስት ፡ ወቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ውእቱ ፡ ዘያነብብ ፡ መጽሐፈ ፡ ወቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ውእቱ፡ዘይቤ፡ቁሙ፡በሠናይ።<br>፪፤ ወኵሎሙ፡ያዱ፡ምሥዋዐ፡ኵሎሙ፡ምስለ፡እግዚእነ፡ወመድኃኒነ፡ከመ፡ዘአሐዱ፡እድ፡በፈትቶ ፡ ኅብስት ፡ ዘውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለኵሎሙ።<br>፫፤ ወአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ እምየማነ ፡ መድኅን ፡ ይፌጽም ፡ ትሩፋተ ፡ ቀኖና ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን። ወዐተበ ፡ እግዚእነ ፡ ለቍርባን ፡ ከመ ፡ ዘይገብሩ፡ ካህናት ፡ ወአቅረቦሙ ፡ ለአርድእት፡ ወለኵሉ ፡ ጉባኤ።<br>፬፤ ወተደመሩ፡መላእክት፡ምስለ፡ሰብእ፡ውስተ፡ዝኩ ፡ መካን ፡ ወእግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ ንጽሕት፡ተቈረበት፡በአዕዳወ፡ወልዳ፡ፍቁር፡ወአምላካ።<br>፭፤ ወእምድኅረ ፡ ተቈረበት ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ድንግል ፡ ተናገራ ፡ እግዚእ ፡ ወመድኅን ፡ ላቲ ፡ ወይናዝዛ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ወይብል ፡ እ ፡ ወላዲትየ ፡ ድንግል ፡ ዝ ፡ ቍርባን ፡ ለዕለተ ፡ ተዝካረ ፡ ፍልሰትኪ ፡ ውስተ፡ሰማይ፡ዮም።<br>፮፤ በሊ፡ለደቂቅኪ፡ሐዋርያት፡ከመ፡ይስብኩ፡ውስተ፡ክበበ፡ዓለም፡ከመ፡ኵሉ፡ዘይገብር፡ | ምንተኑ፡በል።<br>ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘለዓ… በውነት፡ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንግ… ነፍስ፡የጸናች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማር… ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው፡<br>ጌታችን፡በእናቱ፡ፍልሰት፡ቀን፡በጉባኤ… ሁሉ፡መካከል፡ካህን፡ሁኖ፡እንደ፡አገለገ…<br>፩፤ ከዚህም ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱ… ክርስቶስ ፡ በእናቱ ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ ካህን ፡ ሁኖ… አገለገለ፤ቅዱስ፡እስጢፋኖስም፡መጽሐፍ… ያነብብ፡ነበር፤ቅዱስ፡ዮሐንስም፡በሥርዓ… ቁሙ፡የሚል፡ነበር።<br>፪፤ ሁሉም፡በመሠዊያው፡ዙሪያ፡ቁመው፡ሁ… በእጃቸው፡መካከል፡ኅብስቱን፡በመፈተ… ከጌታችን ፡ ከመድኃኒታችን ፡ ጋር ፡ በአ… ድነት፡የሚአገለግሉ፡ሆኑ።<br>፫፤ አባታችን ፡ ጴጥሮስም ፡ በመድኃኒታችን… ቀኝ፡ ተራዳኢ፡ካህን፡በመሆን፡የቍርባን… ሥርዓት፡ ያከናውን ፡ ነበር ። ጌታችን… ካህናት፡እንደሚያደርጉት፡ቍርባኑን፡ባር… ለውጦ፡ለደቀ፡መዛሙርቱና፡ለተሰበሰቡት… ሁሉ፡አቈረባቸው።<br>፬፤ በዚያም፡ቦታ፡መላእክትና፡ሰዎች፡አንድ… ማኅበር፡ሆኑ፤ንጽሕት፡ድንግል፡እመቤ… ችንም፡በተወደደ፡ልጅዋና፡ፈጣሪዋ፡እጅ… ቈረበች።<br>፭፤ የአምላክ፡እናት፡ድንግልም፡ቍርባኑን፡ከ… ቀበለች ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን… እንደዚህ ፡ ያነጋግራትና ያጽናናት ፡ ነበ… እንዲህም፡አለ፤ድንግል፡እናቴ፡ሆይ፡ይ… ቍርባን፡ዛሬ፡ወደ፡ሰማይ፡ያረግሽበት፡የ… ልሰትሽና፡የዕርገትሽ፡መታሰቢያ፡ነው።<br>፮፤ ዛሬ፡ወደ፡ሰማይ፡ያረግሽበትን፡ይኸው… ነሐሴ፡ዐሥራ፡ስድስት፡ቀን፡የዕርገትሽን… |

በ፲፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ሉ፡ተገዘከረ፡በዐለ፡ዕርገትኪ፡ኀበ፡ሰማይ፡
ሙእቱ፡አመ፡ዐሡሩ፡ወስዱሱ፡ለወርኀ፡
አሐሴ፡ወያስተሐምሙ፡በእንተ፡ቍርባን፡
በዕለተ፡ተገዘካርኪ፡ናሁ፡አነ፡አቄርብ፡ነፍሳ
ቲሆሙ፡ሶበ፡ወፅአ፡እምሥጋሆን፡በውስተ፡
ማኅበረ፡በኵር፡ዘውስተ፡መንግሥተ፡ሰማያት።
ወለኵሉ፡ዘይጽሕፍ፡መጽሐፈ፡ግብርኪ፡
ወተአምርኪ፡ቅድስት፡ወዕርገትኪ፡አነ፡
እጽሕፍ፡ስሞ፡ውስተ፡መጽሐፈ፡ሕይወት።
ወዘኒ፡የሐንጽ፡መርጡለኪ፡በስምኪ፡አነ፡
እጼግዎ፡ሎቱኒ፡ውስተ፡መንግሥተ፡
ሰማያት፡ዕሴቶ።
ወለኵሉ፡ዘያለብስ፡ዕሩቀ፡በእንተ፡ስምኪ፡
አነ፡አለብሶ፡እምዐጽፍ፡ብርሃናዊ፡በውስተ፡
ማኅደረ፡ብርሃን።
ወለዘያበውእ፡ቍርባነ፡አው፡ዕጣነ፡
በእንተ፡ስምኪ፡አነ፡እሁቦ፡ኄራተ፡
ገነት።
ስምዑ፡አ፡ፍቁራንየ፡ወፍቁራኒሃ፡ለእግዝ
እትነ፡ማርያም፡ዘከመ፡ተውህበ፡ለክሙ፡
ዐሥራት፡ወኪዳን፡ወረድኤት፡ወኀይል፡፡።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ትእምርተ፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ዘከመ፡አንሥአ፡ምውተ፡ወዘከመ፡ሰብሕዎ፡
እንስሳ፡ግሀሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመዓለም፡አሜን።
ወሶበ፡ዐርገ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
በበዐለ፡መጸለት፡ነጸረ፡ብእሴ፡እንዘ፡
ያስቆቁ፡ወይበኪ፡በእንተ፡እሁኁ፡ዘሞተ፡
በይእቲ፡ዕለት።
ወምስለ፡ብካዩ፡ኮነ፡ያስተበቍዕ፡ኀበ፡እግዚ
አብሔር፡ወይብል፡ፈኑ፡ለነ፡እግዚኦ፡
ዘትፌኑ፡ኀቤነ፡በእንተ፡መድኃኒትነ፡ከመ፡
ኢንሙት፡በኃጣውኢነ።
ወለዝንቱኒ፡እስራኤላዊ፡እኁየ፡
ዘሞተ፡በኃጢአቱ፡ተሣሃሎ፡አ፡አምላክ፡
እስራኤል።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

መታሰቢያ፡የሚያደርገውን፡ሁሉ፤በዚሁ፡
በመታሰቢያሽ፡ቀን፡መሥዋዕት፡በማቅረብ፡
የሚተጋውን፡ሁሉ፤እነሆ፡እኔ፡ከሥጋቸው፡
ነፍሶቻቸው፡በወጡ፡ጊዜ፡በሰማያዊ፡
መንግሥት፡በቅዱሳን፡ሁሉ፡ማኅበር፡
መካከል፡ነፍሶቻቸውን፡አቄርባለሁ።
፯፤ የከበረች፡የዕርገትሽንና፡የተአምርሽን፡
ሥራ፡የሚጽፈውን፡ሁሉ፡እኔ፡በሕይወት፡
መጽሐፍ፡ስሙን፡እጸፋለሁ።
፰፤ በስምሽም፡ቤተክርስቲያንን፡የሚያሠ
ራውን፡እኔ፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡
ዋጋውን፡እሰጠዋለሁ።
፱፤ ስለ፡ስምሽም፡የተራቆተውን፡ያለበሰውን፡
እኔ፡በብርሃን፡ማደሪያ፡ውስጥ፡ብርሃናዊ፡
ልብስ፡አለብሰዋለሁ።
፲፤ ስለ፡ስምሽ፡ሥንዴ፡ዘቢብ፡ወይም፡ዕጣን፡
የሚያቀርበውን፡በገነት፡የሚገኙ፡በጎ፡
በጎዎቹን፡ነገሮች፡ሁሉ፡እኔ፡እሰጠዋለሁ።
፲፩፤ ወዳጆቼና፡የእመቤታችን፡ማርያም፡
ወዳጆቿ፡ዐሥራት፡ቃል፡ኪዳን፡ረድኤት፡
ኃይል፡እንደተሰጣችሁ፡ስሙ።
ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይደርና።ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ምውት፡እንዳ
ነሣና፡እንስሳትም፡እንዳመሰገኑት፡
የሚናገር፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩፤ ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለቂጣው፡
በዓል፡በወጣ፡ገዜ፡በዚያች፡ቀን፡
ስለ፡ወንድሙ፡ሞት፡እየጮኸ፡የሚያለቅስ፡
ሰው፡አየ።
፪፤ ከልቅሶውም፡ጋር፡አቤቱ፡ስለ፡ድኅ
ነታችን፡ወደ፡እኛ፡የምትልከውን፡
ላክልን፡በኃጢአታችን፡እንዳለን፡
እንዳንሞት።
፫፤ የእስራኤል፡ፈጣሪ፡ሆይ፡ይህንንም፡
በኃጢአቱ፡እንዳለ፡የሞተውን፡እስራኤ
ላዊው፡ወንድሜን፡ይቅር፡በለው፡እያለ፡
ወደ፡እግዚአብሐር፡ይማልድ፡ነበር።

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፬፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ተአምንሁ፡በዘይ
መጽእ፡ወይቤሎ፡አይሁዳዊ፡እስመ፡ዘንሴፎ፡
ምጽአቶ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡
እስራኤል ፡ ወመድኅኖሙ ፡ ለእመ ፡ መጽአ ፡
አአምን ፡ ቦቱ ፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
አነ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡ፈራቂሁ፡ለዓለም።
፭፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡
ዘርእየኒ ፡ ዳንኤል ፡ በደመና ፡ ሰማይ ፡ አነ ፡
ወልዱ፡ለብሉየ፡መዋዕል፡ዘአግባእክዋ፡ለኢ
የሩሳሌም ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለናቡከደነጾር ፡
ጸላኢሃ።
፮፡ ወእምዝ፡ይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለውእቱ፡
ብእሲ ፡ እመ ፡ አንሣእክዎ ፡ አነ ፡ ለእጓኩ ፡
ተአምንሁ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡
መድኃኔ፡ዓለም።
፯፡ ወይቤሎ፡ውእቱ፡ብእሲ፡አመንኩ፡እግዚኦ፡
ከመ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈጣሪሁ ፡
ለአዳም፡ወለዘርዑ።
፰፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አ፡ብእሲ፡ነዐ፡
ንሖር፡ቤተከ።
፱፡ ወሶበ፡ሖሩ፡ወበጽሑ፡ቤቶ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡
መፅኡ ፡ እምቤቱ ፡ ብዙኃን ፡ አባግዕ ፡ ከመ ፡
ይትረዐዩ።
፲፡ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እንዘ ፡
ይመጽእ፡ተናገሩ፡በልሳነ፡ዕጓለ፡እመሕያው
፡ ወይቤሉ ፡ ሐዊሳ ፡ ለምጽአትከ ፡ አ ፡ ወልደ ፡
እግዚአብሔር፡ወወልደ፡ዳዊት፡በሥጋ።
፲፩፡ ወዓዲ፡ተቀበሎ፡ላሕም፡ዘይፈቅድ፡እግዚኡ፡
ይጥብሖ።
፲፪፡ ወእመ ፡ ርእዮ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ጸርሐ ፡
ውእቱሂ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ወይቤ ፡ ወልደ ፡
ዳዊት፡ተሣሃለኒ፡አ፡ዘኢይረክቦ፡ልቡና፡ወኢ
ይበጽሖ፡ኅሊና፡ተሠሃለኒ፡ወአድኅነኒ።
፲፫፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ድኅን ፡
ወኩን፡እንስሳ፡ዘኢይጠባሕ፡ለዝሉፉ፡ከመ፡
ትኩነኒ፡ ሰማዕተ ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ትውልድ ፡
እኪት ፡ ወግዝፍት ፡ ወሖረ ፡ ውእቱ ፡ ላሕም ፡
ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወእምአሚሃ ፡ ኢርእዮ ፡
እግዚኡ።
፲፬፡ ወካዕበ፡ይቤሎን፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለእልኩ፡
አባግዕ፡አንትንኒ፡አባግዕ፡በእንተ፡ዘኮንክን፡
ስምዐ ፡ ለስብሐትየ ፡ አግዐዝኩክን ፡ እምተ

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፬፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በሚመጣው ፡ ታ[illegible]
ለህን ፡ አለው ፤ አይሁዳዊውም ፡ [illegible]
ጣቱን ፡ ተስፋ ፡ የምናደርገው ፡ እርሱ[illegible]
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ መዳኛችውም
ነውና ፡ ቢመጣ ፡ አምነበታለሁ
አለ።
፭፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ዓለምን፡የፈጠርኩ፡እኔ፡[illegible]
በሰማይ፡ደመና፡በሰው፡ልጅ፡አምሳል፡ዳኒኤ[illegible]
ያየኝ፡እኔ፡ነኝ፤ኢየሩሳሌምንም፡በጠላቷ፡በ[illegible]
ከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ የሰጠኋት ፡ የብሉ[illegible]
መዋዕል፡የአብ፡ልጅ፡እኔ፡ነኝ፡አለው።
፮፡ ከዚህ፡በኋላ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ያንን፡ሰው፡[illegible]
ድምህን፡እኔ፡ባስነሣው፡የዓለም፡መድኃኒ[illegible]
ክርስቶስ ፡ እኔ ፡ እንደሆንኩ ፡ ታምናለህ[illegible]
አለው።
፯፡ ያም ፡ ሰው ፡ አዳምንና ፡ ዘሮቹንም ፡ የፈጠር[illegible]
አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደሆንክ ፡ አቤቱ
አመንኩ፡አለው።
፰፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ና ፡ ወ[illegible]
ቤትህ፡እንሂድ፡አለው።
፱፡ ወደዚያው ፡ ሰው ፡ ቤትም ፡ በደረ[illegible]
ጊዜ ፡ ሊሠማሩ ፡ ብዙ ፡ በጎች ፡ ከቤ[illegible]
ወጡ።
፲፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ሲመጣ፡በአዩት፡ጊዜ፡በ[illegible]
ዚአብሔር፡የባሕርይ፡ልጅ፡በሥጋ፡የዳዊ[illegible]
ልጅ ፡ የሆንክ ፡ ለመምጣትህ ፡ ፍቅር፡ሰላ[illegible]
ይገባል፡እያሉ፡በሰው፡አንደበት፡ተናገሩ
፲፩፡ ዳግመኛም ፡ ጌታው ፡ ሊያርደው ፡ ያዘጋጀው
በሬ፡ተቀበለው።
፲፪፡ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ
ቃል፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆይ፡ ልቡና ፡ የማይደ[illegible]
ምረው፡ኅሊና፡የማይደርስበት፡ሆይ፡ራራል[illegible]
አዘንልኝ፡ብሎ፡ጮኸ፤አድነኝም፡አለው።
፲፫፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በዚች ፡ በደነደነችና፡ክፉ
በሆነች ፡ ትውልድ ፡ ላይ ምስክር ፡ ትሆነኝ
ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡ ዳን ፤ የማይታረድ
እንስሳም፡ ሁን ፡ አለው ፤ ያም ፡ በሬ ፡ ወደ
በረኻ፡ ሄደ ፤ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ጌታው
አላየውም።
፲፬፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ዳግመኛ፡እነዚያን፡በጎ[illegible]
እናንተ፡በጎች፡ለጌትነቴ፡ምስክሮች፡ስለሆ[illegible]
ችሁኝ ፡ ከመገዛት ፡ ነፃ ፡ አውጥቻችኋለሁ

ዘ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ቀንየ፡እምይእዜሰ፡ኢይክል፡መኑሂ፡ይቅን
ይኑ፡እስከ፡ዳግም፡ምጽአትየ።
፲፫ ኢትንሰ፡ብዝኀ፡ወተባዝኀ፡ወይምላዕ፡
ገጸ፡ዘርዕክን፡ከመ፡ትኩና፡ስምዐ፡ላዕለ፡
ዛቲ፡ትውልድ፡እኪት።
፲፬ ወበአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ቤቶ፡ለውእቱ፡
ብእሲ፡ዘኮነ፡ይበኪ፡በእንተ፡እኁሁ፡ወስሙ፡
በግልስማን።
፲፭ ወሶበ፡ርእየ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለእኁሁ፡
ዘሞተ፡ይቤሎ፡እስራኤል፡ተንሥእ፡
እምትከ።
፲፮ ወተንሥአ፡ሶቤሃ፡ፍጡነ፡ከመ፡ዘይነቅህ፡
ብእሲ፡እምንዋሙ፡ወቆመ፡በእገሪሁ፡
ወሰገደ፡ሎቱ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡
አንተ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ቀዳማዊ፡ወውእቱ፡ተለዎ፡ወኢተ
ፈልጠ፡እምኔሁ።
፲፯ ወነጸሮሙ፡አይሁድ፡ወሳምራውያን፡ኀበ፡
እሉ፡ሠለስቱ፡ተአምራት፡ዘገብሮሙ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡በይእቲ፡ጊዜ፡አብዝኁ፡
አንክሮ።
፳ ወይቤሉ፡በበይናቲሆሙ፡ቦኑ፡ዝንቱ፡
ውእቱ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ዘይ
ሴፈውዎ፡አሕዛብ፡እስመ፡ትእዛዙ፡ለዓለም፡
ይሄሉ፡ወይሰምዕዎ፡አሕዛብ፡በከመ፡
ተነበየ፡ያዕቆብ፡አቡነ፡ወዳንኤል፡ወኢሳ
ይያስ፡ነቢይ፡እንዘ፡ይብሉ፡ከመ፡ለዓለም፡
ይነብር፡መንግሥቱ፡ዘአልቦ፡ማኅለቅት፡
እስመ፡አልቦቱ፡ጥንት፡እምቅድመ፡
አዝማን፡ህልው፡ውእቱ።
፳፩ ወካልአን፡እምአይሁድ፡ይቤሉ፡ገብረ፡
ዘንተ፡በሥራይ፡ወቦ፡እምኔሆሙ፡ዘይቤ፡
እመሰ፡ብእሲ፡መሠርይ፡ውእቱ፡ወገብረ፡
ዘንተ፡በሥራይ፡ሀለዎ፡ይብጥል፡በሥራይ፡
በከመ፡በጠሉ፡በሥራዮሙ፡ኢያኔስ፡ወኢያ
ንበሬስ፡ቅድሜሁ፡ለሙሴ፡ነቢይ፡
ወኢጸንኡ።
፳፪ ወቦ፡እምኔሆሙ፡ዘይትከሐዱ፡በዝንቱ፡
ከመ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ሕያው፡ውእቱ፡
ዘተነበዩ፡ነቢያት፡በእንቲአሁ።
፳፫ ወይቤሉ፡ወሶበ፡ኢኮነ፡ዝንቱ፡ወልደ፡እግዚ

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ከአሁን፡ጀምሮ፡ዳግም፡እስክመጣ፡ድረስ፡
ማንም፡ይገዛችሁ፡ዘንድ፡አይችልም፡አላቸው።
፲፫፤ እናንተስ፡በዚች፡ክፉ፡ትውልድ፡ላይ፡
ምስክሮች፡ትሆኑኝ፡ዘንድ፡ብዙ፡ተባዙ፡
ዘራችሁም፡በረኻውን፡ይምላ፡አላቸው።
፲፬፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ለወንድሙ፡ወደሚያለ
ቅሰው፡ሰው፡ቤት፡ገባ፤የሰውየውም፡ስም፡
በግልስማን፡ነው።
፲፭፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡የሞተው፡ወንድሙን፡
ባየው፡ጊዜ፡እስራኤል፡ሆይ፡ከሞትህ፡ተነሣ፡
አለው።
፲፮፤ ያን፡ጊዜ፡ከእንቅልፉ፡እንደሚነቃ፡ሰው፡
ፈጥኖ፡ተነሥቶ፡በእግሮቹ፡ቆሞ፡ለጌታ፡
ኢየሱስም፡ሰግዶ፡አንተ፡ተቀዳሚ፡
ተከታይ፡የሌለህ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ነህ፡
አለው፤እርሱም፡ተከተለው፡ከእርሱም፡አል
ተለየም።
፲፯፤ ሳምራውያንና፡አይሁድም፡ጌታ፡ኢየ
ሱስ፡ያደረጋቸውን፡እነዚህን፡ሦስቱን፡
ተአምራቶች፡ተመልክተው፡አድናቆትን፡
አበዙ፡
፳፤ በውኑ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡ተስፋ፡የሚያደርጉት፡
የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ክርስቶስ፡ይህ፡
ይሆን? ተባባሉ፤ትእዛዙ፡ለዘላለም፡የፀና፡
ነውና። አሕዛብም፡ይሰሙታልና፡
አባታችን፡ያዕቆብ፡ኢሳይያስና፡ዳንኤል፡
ፍጻሜ፡የሌለው፡መንግሥቱ፡ለዘለዓለም፡
እንደሚኖር፡ጥንትም፡የለውምና፡እሱ፡
ከዘመናት፡አስቀድሞ፡የነበረ፡ነው፡ብለው፡
ትንቢት፡እንደ፡ተናገሩ።
፳፩፤ ሌሎችም፡ከአይሁድ፡ውስጥ፡ይህን፡
የሠራ፡በሥራይ፡በምትሐት፡ነው፡አሉ፤
ከእርሳቸውም፡መሠርይ፡ሰው፡ከሆነ፡
በሥራያቸው፡ኢያኔስና፡ኢያንበሬስ፡
በነቢዩ፡ሙሴ፡ፊት፡እንደ፡ጠፉና፡እን
ዳልፀኑ፡በሥራዩ፡ይጠፋ፡ዘንድ፡አለው፡
ያሉ፡አሉ።
፳፪፤ ከእነርሱም፡ነቢያት፡ትንቢት፡የተናገሩለት፡
የሕያው፡እግዚአብሔር፡አብ፡ልጅ፡እንደ፡
ሆነ፡በዚህ፡ነገር፡የተከራከሩ፡አሉ።
፳፫፤ የእግዚአብሔርም፡ልጅ፡ካልሆነ፡ሙት፡

## በ፯፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እግዚአብሔር፡እምኢክህለ፡ያንሥእ፡ሙታነ፡ወእ
ምኢተአዘዘ፡ለቃሉ፡እንስሳ፡ወእምኢነበቡ፡
በልሳነ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወእምኢያ
ጽምዑ፡ ነገሮ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘተሰምዐ ፡
እምቅድም ፡ እንስሳ ፡ ዘተናገረ ፡ በቃሉ ፡
ለዕጓለ፡ እመሕያው ፡ ዘእንበለ ፡ እድግቱ ፡
ለበለዓም፡ሰበ፡ወዕአ፡ይርግሞሙ፡ለደቂቀ፡
እስራኤል ፡ እስመ ፡ እድግቱ ፡ ተናገረቶ ፡
በዝንቱ፡ነገር፡ወበዘይመስሎ።
፳፬፤ ወተካሐዱ ፡ እሉ ፡ ሰብእ ፡ በእንተ ፡ ክር
ስቶስ።
፳፭፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘዐርገ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ወነገሮሙ፡ለጸሐፍት፡ወለካህናት፡ወለፈሪሳ
ውያን ፡ ተአምራቲሁ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ዘርእዩ፡ውስተ፡ቤተ፡እስረኤላዊ፡ዘአንሥአ፡
እምውታን፡ወእሙንቱሂ፡አንከሩ፡ወባሕቱ፡
ኢአምኑ፡ቦቱ።
፳፮፤ ወአዘዝዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡
እምከመ ፡ ርኢክምዎ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አይድዑነ፡ዜናሁ።
፳፯፤ ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ካህናት ፡ ከመ ፡ ሀሎ ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ምስለ፡አርዳኢሁ፡ውስተ፡
ቤተ፡መቅደስ፡ተጋብኡ፡ኅቡረ፡ወዕሙረ፡
ወመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይቤልዎ ፡ አ ፡ ሊቅነ ፡
ኄር፡እስመ፡ነአምን፡ከመ፡እምኀበ፡እግዚአ
ብሔር፡ ተፈኖከ፡ወኢይክል፡መኑሂ፡ከመ፡
ይግበር፡ዘንተ፡ተአምረ፡ዘአንተ፡ትገብር።
፳፰፤ መኑ ፡ አቡከ ፡ ወመኑ ፡ ይእቲ ፡ እምከ ፡
ወእምአይ፡ነገድ፡አንተ፡እመሰ፡እምነገደ፡
ትንቢት ፡ አንተ ፡ ይደልወከ ፡ ትግበር ፡
ተአምራተ።
፳፱፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እስመ ፡
መንክራተ ፡ ትሬእዩ ፡ ዘእገብር ፡ አነ ፡
በሥልጣኑ፡አቡየ፡ዘበሰማያት።
ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ አይሁድ ፡ ቃሎ ፡ ነሥኡ ፡
አዕባነ፡ከመ፡ይውግርዎ።
፴፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ በአይ ፡
ግብር፡ ወበአይ ፡ መንክር ፡ ትዌግሩኒ ።
ወእምዝ፡ይቤሎሙ፡አ፡ማኅበረ፡አይሁድ፡
አእምሩ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ተስፋሆሙ ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

ማንሣት፡ባልቻለም፡ነበር፤እንስሳትም፡ለቃሉ
ባልታዘዙ፡ነበር፤በሰው፡ልጅ፡አንደበትም፡ባል
ተናገሩ ፡ ነበር ፤ የተናገራቸውንም ፡ ባልሰሙ
ነበር፡አሉ፤ከበለዓም፡አህያ፡በቀር፡በሰው፡ልጅ
አንደበት ፡ የተናገረ ፡ እንስሳ ፡ እንዳለ ፡ ከጥን
ጀምሮ ፡ አልተሰማምና፤ የእስራኤልን፡ ልጆች
ሊረግም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ አህያዋ ፡ በሰው
አንደበት፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ
ለችና።
፳፬፤ እንደዚህም ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በ
ክርስቶስ፡ ተከራከሩ።
፳፭፤ ከእነርሱም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥቶ
ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ከሞት ፡ ባስነሣው ፡ በእስራ
ላዊው ፡ ቤት ፡ ሲደረግ ፡ ያዩትን ፡ ተአምራቱን
ለጸፎችና ፡ ለካህናት ፤ ለፈሪሳውያንም ፡ የነ
ራቸው፡አለ፤እነርሱም፡አደነቁ፤ነገር፡ግን፡አ
መኑበትም።
፳፮፤ ሕዝቡንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያያችሁት
እንደ ፡ ሆነ ፡ ወሬውን ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ አዘ
አቸው።
፳፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ ገባ ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በቤተ ፡ መቅደ
ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ እንዳለ ፡ ካህናት
በሰሙ፡ ጊዜ ፡ ተሰባስበው ፡ በአንድነት ፡ ወ
እርሱ ፡ መጥተው ፡ ቸር ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተልከሀ ፡ እንደ ፡ መጣ
እናምናለን፡ እኮን ፤ አንተ ፡ የምታደርገው
ተአምራት፡ማንም፡ያደርግ፡ዘንድ፡አይችልም
፳፰፤ አባትህ፡ማነው?እናትህስ፡ማን፡ናት?ከየ
ነገድስ፡ነህ?ትንቢት፡ከተነገረላቸው፡ወገ
ከሆንክ ፡ ተአምራት ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ
ይገባሃል፡አሉት።
፳፱፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እኔ ፡ በሰማያዊው ፡ አባቴ
ሥልጣን፡የምሠራቸውን፡ድንቆችን፡ተአም
ቶችን ፡ ታያላችሁ ፡ አይደለምን ፡ አላቸው
አይሁድም፡ቃሉን፡በሰሙ፡ጊዜ፡ይወግሩት
ዘንድ፡ደንጊያዎችን፡አነሡ።
፴፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በምን ፡ ሥራ ፡ በምን
ድንቅ ፡ ሥራ ፡ ትወግሩኛላችሁ ፡ አላቸው
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው፤ የአይሁድ
ማኅበር ፡ ሆይ ፡ የአሕዛብ ፡ ተስፋቸው ፡ እኔ

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

...ለአዛብ።

...ለምይእዜሰ ፡ እሬኑ ፡ ሐዋርያትየ ፡ ኀበ ፡ ...አሕዛብ፡ነኪራን፡ይጸውዕዎሙ፡ውስተ፡ሃይ ...ማኖትየ።

...ለሙንቱ ፡ ይትዌከፍዎ ፡ ለነገርየ ፡ ወይሴ ...ሰፉ፡ምስለ ፡ አቡየ ፡ ወምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ወይከውኑ ፡ ሕዝበ ፡ ...ሃንቲከሙ።

...ዘለአት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሣህሉ ፡ ...ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

እንደ፡ሆንኩ፡ዕወቁ።

፴፩፤ ከእንግዲህስ፡ልዩ፡ወደ፡ሆኑ፡አሕዛብ፡በእኔ፡ ወደ ፡ ማመን ፡ ይጠሩአቸው ፡ ዘንድ ፡ ሐዋርያ ቶቼን፡እልካለሁ።

፴፪፤ እነርሱም ፡ ትምህርቴን ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብለው ፡ ከአባቴና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ያመሰግኑኛል ፤ በእናንተ ፡ ፈንታም ፡ ወገኖች ፡ ይሆናሉ ፤ ለእግዚአ ብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፤ይቅርታው፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር ፡ አሜን።

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፴፡፲፫-፲፬።

እስመ ፡ ሰማዕኩ ፡ ድምፀ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ...ዐቱ ፡ ዐውድየ ። ሶበ ፡ ተጋብኡ ፡ ኅቡረ ፡ ...ላዕሌየ ። ወተማከሩ ፡ ይምሥጥዋ ፡ ለነ ፍስየ።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፴፡፲፫-፲፬።

በዙሪያዩ፡የከበቡኝን፡የብዙዎችን፡ድምጽ፡ ሰምቻለሁና፤በእኔ፡ላይ፡በአንድነት፡በተሰ በሰቡ፡ጊዜ፤ሰውነቴን፡ሊነጥቋት፡ተማከሩ፡ ይበል።

ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፤፲፬፡፲፪-፲፯።

...ወእመ ፡ ቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ በዐለ ፡ መጸለት ፡ ...ፋሲካ፡እመ፡ይጠብሑ ፡ ፍሥሐ ፡ ይቤልዎ ፡ ...አርዳኢሁ፡በአይቴ፡ትፈቅድ፡ናስተዳሉ፡ለከ፡ ትብላዕ፡ፍሥሐ።

...ወፈነወ ፡ ክልኤተ ፡ እምአርዳኢሁ ፡ ...ወይቤሎሙ ፡ ሑሩ ፡ ሀገረ ፡ ዘቅድሜክሙ ፡ ...ወትረክቡ ፡ ብእሴ ፡ ዘይጸውር ፡ ጸሕበ ፡ ማይ ፡ ...ወትልውዎ፡ኀበ፡ቦአ።

...ወበልዎ ፡ ለበዐለ ፡ ቤት ፡ ይቤለከ ፡ ሊቅ ፡ ...አይቴኑ፡ጽርሕ፡ኀበ፡እበልዕ፡ፍሥሐ፡ምስለ፡ ...አርዳኢየ።

...ወውእቱ ፡ ያርእየክሙ ፡ ጽርሐ ፡ ዐቢየ ፡ ...ንጡፈ፡ወርሡየ፡ወበህየ፡አስተዳልዉ፡ለነ።

...ወሖሩ ፡ አርዳኢሁ ፡ ሀገረ ፡ ወረከቡ ፡ በከመ ፡ ...ይቤሎሙ፡ወአስተዳለዉ፡በህየ፡ፍሥሐ።

የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፬፡፲፪-፲፯።

፲፪፤ በጉን ፡ በሚአርዱባት ፡ ፋሲካ ፡ በምትባለው ፡ በቂጣ ፡ በዓል ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ፋሲካን ፡ ትበላ ፡ ዘንድ ፡ በየት ፡ ልናዘጋጅልህ፡ትወዳለህ፡አሉት።

፲፫፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሁለቱን ፡ ላካቸው ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፤ በፊታችሁ ፡ ወዳለችው ፡ መንደር፡ሂዱና፡የውኃ፡ማድጋ፡የተሸከመ፡ሰው፡ ታገኛላችሁ፤ወደገባበትም፡ቤት፡ተከተሉት።

፲፬፤ ባለቤቱን ፡ መምህር ፡ ከደቀመዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ ፋሲካን ፡ የምበላበት ፡ አዳራሽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ ብሎሃል ፡ በሉት።

፲፭፤ እርሱ፡የተነጠፈ፡የተጋረደ፡ታላቅ፡አዳራሽ፡ ያሳያችኋል፤በዚያ፡አዘጋጁልን።

፲፮፤ ደቀ፡መዛሙርቱም፡ወደ፡ከተማ፡ሄደው፡እንደ፡ ነገራቸው፡አገኙና፡በዚያም፡ፋሲካን፡አዘጋጁ።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ድኅረ፡ወንጌል።

በስድስቱ፡ሰዓት፡እምዕለተ፡ኀሙስ፡ዘይትነበብ።

፩፡ በስድስቱ፡ሰዓት፡እምዕለተ፡ኀሙስ፡ዘይትነበብ። እምትንቢት፡ስምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኦ፡ኵሉ፡ቤተ፡እስራኤል።

፪፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ኃያል፡አምላከ፡እስራኤል፡አርትዑ፡ፍናዊክሙ፡ወአሠንዩ፡ወኢትትወከሉ፡በነገረ፡ሐሰት፡እስመ፡ኢይትዌለጥ፡ወኢይ ታቦተ፡እግዚአብሔር፡ሜንኖ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡ታቦተ፡እግዚአብሔር፡አንትሙ።

፫፡ ወለእመ፡አሠመርክምዎ፡በምግባሪክሙ፡ወኮነት፡ፍኖትክሙ፡ሠናይተ፡ወለእመ፡ፈታሕክሙ፡ማዕከለ፡ብእሲ፡ወቢጹ፡ወዕጓለ ማውታ፡ወመዐስብ፡ወለእለ፡የኀድሩ፡ፈላስያን፡ኢዐመፅክምዎሙ፡ወኢሄድክ ምዎሙ፡ወኢከዐውክሙ፡ደመ፡ንጹሐ፡በውስተ፡ዛቲ፡ሀገር፡ተኀድሩ፡ውስተ፡ምድር፡እንተ፡ወሀብኩ፡ለዓለም፡ለአበዊክሙ።

፬፡ ወከመ፡ዝ፡ነበበ፡ቅዱስ፡ጳውሎስ፡ስምዐ፡ዝንቱ፡ትንቢት፡እንዘ፡ይብል፡አንትሙሰ፡ታቦቱ፡ለእግዚአብሔር፡ሕያው፡አንትሙ፡በከመ፡ተብህለ፡አነ፡አኀድር፡ኀቢሆሙ፡ወአንሶሱ፡ማእከሎሙ፡ወእከውኖሙ፡አምላኮሙ፡ወይከውኑኒ፡ሊተ፡ሕዝብየ።

፭፡ ወበእንተ፡ዝ፡ፃኡ፡እማዕከሎሙ፡ወተፈለጡ፡እምኔሆሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ወኢትግሥሡ፡ርኩሶሙ፡ወአነ፡እትዌከፈክሙ፡ወአነ፡እከውነክሙ፡አበ፡ወአንትሙ፡ትከውኑኒ፡ሕዝብየ፡ውሉደ፡ወአዋልደ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ንጉሠ፡ኵሉ።

፮፡ ለንፍርሆ፡ወንግበር፡ትእዛዞ፡ከመ፡ይትወከፈነ፡ኀቤሁ፡ወይሥረይ፡ለነ፡ኃጢአተነ፡ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ፡ፈጽም፡በል።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ኀሙስ፡ከቀኑ፡በስድስት፡ሰዓት።
ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

፩፡ የእስራኤል፡ወገኖች፡ሁሉ፡ሆይ፡ከትንቢ ትንቢት፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስሙ።

፪፡ የእስራኤል፡ፈጣሪ፡ኃያል፡እግዚአብሔር እንዲህ፡አለ፤ጐዳናችሁን፡(ሥራችሁን)፡አቅኑ አሳምሩ፤በሐሰት፡ነገርም፡አትተማመኑ፤እግ ዚአብሔር፡ማደሪያ፡አይለወጥምና፤እግዚአ ሔርም፡ማደሪያውን፡አይንቅምና፤የእግዚአ ብሔር፡ማደሪያም፡እናንተ፡ናችሁና።

፫፡ በሥራችሁም፡ደስ፡ብታሰኙት፡አካሄ ችሁም፡መልካም፡ብትሆን፤በባልንጀራው በሰው፡መካከል፡በድኃ፡አደጉና፡በባልቴቷ መልካም፡ፍርድ፡ብትፈርዱ፤በእናንተ ዘንድ፡የሚኖሩትን፡ስደተኞች፡ፈጽማችሁ ባትቀሙአቸውም፤በዚች፡አገርም፡ንጹሕ ደምን፡ባታፈሱ፤ለአባቶቻችሁ፡ለዘላለም ርስት፡አድርጌ፡በሰጣኋቸው፡በዚች፡ምድር ትኖራላችሁ፡አለ።

፬፡ የዚህ፡ትንቢት፡ምስክር፡የሆነ፡ቅዱስ ጳውሎስም፡እናንተስ፡የሕያው፡እግዚአብሔር ማደሪያው፡ናችሁ፤እኔ፡በእነርሱ፡ዘንድ፡ አድራለሁ፤በመካከላቸውም፡እመላለሳለሁ፤ አምላካቸውም፡እሆናቸዋለሁ፤እነርሱም፡ለእኔ ወገኖቼ፡ይሆኑኛል፡ብሎ፡እንደ፡ተናገረ፤

፭፡ ስለዚህም፡ከመካከላቸው፡ውጡ፤ከእ ርሱም፡ተለዩ፡አለ፡እግዚአብሔር፡ርኩሳ ቸውንም፡አትዳስሱ፤እኔም፡እቀበላችኋለሁ፤ እኔ፡አባት፡እሆናችኋለሁ፤እናንተም፡ ሴቶችና፡ወንዶች፡ልጆች፡በመሆን፡ወገኖ ትሆኑኛላችሁ፡አለ፡በሁሉ፡ነግሦ፡የሚኖር እግዚአብሔር።

፮፡ ወደ፡እርሱ፡ይቀበለን፡ዘንድ፡ኃጢአታ ችንም፡ያስተሠርይልን፡ዘንድ፡እንፍራው ትእዛዙንም፡እንፈጽም።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሆኖ፡መከራ ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
የጸሎቱም፡ፍፃሜ፡እንደፊተኛው፡ነው።

Scanned by CamScanner

## ምዕራፍ፡፳፪።
### ክፍል፡፩።

ዘተነበ፡ሰዓት ፡ መዓልት ፡ ዘኀሙስ ፡ ዘይት
ነበብ።

#### ኦሪት፡ዘልደት።

ምዕ፡፳፪፡፩–፲፱።

ወኮነ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ መዋዕል ፡
አመከሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡
ወይቤሎ ፡ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ ወይቤ ፡
ነየ፡አነ።

ወይቤሎ ፡ ንሥእ ፡ ለወልድከ ፡ ዘታፈቅር ፡
ይሥሐቅሃ ፡ ወሑር ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ላዕላይ ፡
ወአዕርጎ፡ህየ፡ወሡዖ፡ላዕለ፡አሐዱ፡ደብር፡
ዘእቤለከ።

ወተንሥአ ፡ አብርሃም ፡ በጽባሕ ፡ ወረኀነ ፡
አድጎ፡ወነሥአ፡፪ተ፡ደቀ፡ወይሥሐቅሃኒ፡
ወልዶ።

ወሠፀረ ፡ ዕፀወ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ወአ
ጸረ፡ወሖረ፡ወበጽሐ፡ውስተ፡ውእቱ፡መካን፡
ዘነ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሣልስት ፡
ዕለት።

ወይቤሎሙ፡አብርሃም፡ለደቂቁ፡ንበሩ፡ዝየ፡
ምስለ፡አድግ፡አነ፡ወወልድየ፡ንሐውር፡
እስከ፡ደብር፡ወሰጊደነ፡ንገብእ፡ኀቤክሙ፡
ዝየ።

ወነሥአ፡አብርሃም፡ዕፀወ፡ዘመሥዋዕት፡
ወአጸሮ፡ለይሥሐቅ፡ወልዱ፡ወነሥአ፡
እሳተኒ፡ወመጥባሕተኒ፡ውስተ፡እዴሁ፡
ወሖሩ፡፪ሆሙ፡ኅቡረ።

ወይቤሎ፡ይሥሐቅ፡ለአብርሃም፡አቡሁ፡
አባ፡ወይቤሎ፡ምንት፡ውእቱ፡ወልድየ፡
ወይቤሎ፡ናሁ፡ዕፅ፡ወእሳትኒ፡አይቴ፡ሀሎ፡
በግዕ፡ለመሥዋዕት።

ወይቤሎ፡አብርሃም፡እግዚአብሔር፡ይሬኢ፡
ሎቱ፡በግዐ፡ለመሥዋዕት፡ወልድየ።

ወሖሩ፡ኅቡረ፡ወበጽሑ፡ውስተ፡ውእቱ፡
መካን፡ዘይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ወነደቀ





## ምዕራፍ፡፳፪።
### ክፍል፡፩።

ኀሙስ ፡ ከቀኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ የሚ
ነበብ።

#### ኦሪት፡ዘፍጥረት።

ምዕ፡፳፪፡፩–፲፱።

፩፤ ከዚህም፡ወራት፡በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤እግዚአ
ብሔር፡አብርሃምን፡ፈተነው፤አብርሃም፡
አብርሃም፡ብሎ፡ጠራው፤እርሱም፡እነሆኝ፡
አለሁ፡አለ።

፪፤ የምትወደው፡ልጅህ፡ይስሐቅን፡ይዘኸው፡
ወደ፡ላይኛው፡ተራራ፡ሂድ፤ወደዚያም፡
አውጥተህ፡እኔ፡ባዘዝኩህ፡በአንዱ፡ተራራ፡
ላይ፡ሠዋው፡አለው።

፫፤ አብርሃምም፡በጥዋት፡ተነሥቶ፡አህያውን፡
ጫነ፤ልጁን፡ይስሐቅንና፡ሁለቱ፡ብላቴኖ
ችንም፡ወሰደ።

፬፤ ለመሠዊያ፡የሚሆኑ፡እንጨቶችንም፡
አስፈለጠ፤አሸክሞም፡ሄደ፤እግዚአብሔር፡
ወዳዘዘው፡ወደዚያም፡ቦታ፡በሦስተኛው፡
ቀን፡ደረሰ።

፭፤ አብርሃምም፡ብላቴኖቹን፡አህያውን፡
ይዛችሁ፡በዚህ፡ቆዩ፡(ተቀመጡ)፡እኔና፡
ልጄ፡ግን፡እስከ፡ተራራው፡ሂደን፡ሰግደን፡
ወደ፡እናንተ፡እንመለሳለን፡አላቸው።

፮፤ አብርሃምም፡የመሥዋዕቱን፡እንጨቶች፡
አንሥቶ፡ለልጁ፡ለይሥሐቅ፡አሸክሞ፡ወቅለ
ምቱንና፡እሳቱን፡በእጁ፡ይዞ፡ሁለቱ፡በአን
ድነት፡ሄዱ።

፯፤ ይሥሐቅም፡አባቱ፡አብርሃምን፡አባቱ፡
አለው፤እርሱም፡ልጄ፡ምንድነው፡አለው፤
እሳትና፡እንጨት፡እነሆ፡አለ፤መሥዋዕት፡
የሚሆነው፡በግ፡ወዴት፡አለ፡አለው።

፰፤ አብርሃምም፡ልጄ፡መሥዋዕት፡የሚሆነውን፡
በግ፡እግዚአብሔር፡ያውቃል፡አለው።

፱፤ አንድነት፡ሂደው፡እግዚአብሔር፡ወዳዘዘው፡
ቦታ፡ደረሱ፤አብርሃምም፡በዚያ፡መሥዋዕት፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

አብርሃም፡ምሥዋዐ፡በሀየ፡ወወደየ፡ዕፀወ፡
ወአሰሮ፡ወአዕቀፆ፡ለይሥሐቅ፡ወልዱ፡
ወአስከቦ፡በከብዱ፡ላዕለ፡ምሥዋዕ፡
መልዕልተ፡ዕፀው።
፲፡ ወአልዓለ፡እዴሁ፡አብርሃም፡ከመ፡ይንሣእ፡
መጥባሕተ፡ወይሕርዶ፡ለወልዱ።
፲፩፡ ወጸውዖ፡ **እግዚአብሔር** ፡ለአብርሃም፡
ወይቤሎ፡አብርሃም፡አብርሃም፡ወይቤ፡ነየ፡
አነ።
፲፪፡ ወይቤሎ፡ኢትደይ፡እዴከ፡ላዕለ፡ወልድከ፡
ወኢትግበር፡ቦቱ፡ምንተኒ፡ይእዜ፡
አእመርኩ፡ከመ፡አንተ፡ትፈርሆ፡**ለእግዚአ
ብሔር**፡ወኢመሐኮ፡እምኔየ፡ለወልድከ፡
ዘታፈቅር።
፲፫፡ ወሶበ፡ነጸረ፡አብርሃም፡ወርእየ፡ናሁ፡
አሐዱ፡በግዕ፡እኁዝ፡አቅርንቲሁ፡
በዕፀ፡ሳቤቅ። ወሖረ፡አብርሃም፡
ወነሥአ፡ወሦዖ፡ህየንተ፡ይሥሐቅ፡
ወልዱ።
፲፬፡ ወሰመዮ፡አብርሃም፡ለውእቱ፡መካን፡
ይሬኢ፡**እግዚአብሔር**፡እንዘ፡ይብል፡
ዮም፡አስተርእዮ፡አስተርአየኒ፡**እግዚአ
ብሔር**፡በዝ፡ደብር፡ወበእንተዝ፡ይትበሃል፡
እስከ፡ዮም፡ውእቱ፡ደብር፡**እግዚአብሔር**፡
ይሬኢ።
፲፭፡ ወጸውዖ፡**መልአከ፡እግዚአብሔር**፡ለአብ
ርሃም፡ዳግመ፡እምሰማይ።
፲፮፡ ወይቤሎ፡መሐልኩ፡በርእስየ፡ይቤ፡**እግዚአ
ብሔር**፡እስመ፡ገበርከ፡ለዝንቱ፡ነገር፡
ወኢመሐከ፡እምኔየ፡ለወልድከ፡ዘታፈቅር።
፲፯፡ ከመ፡ባርኮ፡እባርከከ፡ወአብዝኆ፡አስተባ
ዝኆከ፡ለዘርዕከ፡ከመ፡ከዋክብተ፡ሰማይ፡
ወከመ፡ኆፃ፡ዘድንጋገ፡ባሕር፡ወይወርሱ፡
ዘርዕከ፡አህጉረ፡ፀር።
፲፰፡ ወይትባረኩ፡በዘርዕከ፡ኵሎሙ፡አሕዛበ፡
ምድር፡እስመ፡ሰማዕከ፡ቃልየ።
፲፱፡ ወገብአ፡አብርሃም፡ኀበ፡ደቁ፡ወተንሥኡ፡
ወሖሩ፡ኀቡረ፡ወበጽሑ፡ኀበ፡አዘቅተ፡
መሐላ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
ምዕ፡፷፩፡፩-፯።
፩፡ መንፈሰ፡እግዚአብሔር፡ዘላዕሌየ፡ዘበእን

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

የሚሠዋበትን፡አዘጋጅቶ፡እንጨ...
ጨመረ፤ ልጁ፡ይሥሐቅንም፡አስሮ፡በ...
ዋበት፡ላይና፡በእንጨቱ፡ላይ፡በልቡ፡...
አስተኛው።
፲፡ አብርሃምም፡ወቅለምቱን፡አንሥቶ፡ልጁን
ያርደው፡ዘንድ፡እጁን፡አነሣ።
፲፩፡ **እግዚአብሔርም**፡አብርሃምን፡አብርሃ...
አብርሃም፡ብሎ፡ጠራው፤እነሆ፡እኔ፡አለሁ...
አለው።
፲፪፡ በልጅህ፡ላይ፡እጅህን፡አታውርድ፤ምን...
ምን፡ አታድርግበት። ለምትወደው፡ልጅ...
ከእኔ፡ አልራራህለትምና፤ አንተ፡**እግዚአ...
ሔርን**፡እንድትፈራው፡አሁን፡አወቅሁ...
አለው።
፲፫፡ አብርሃም፡ቀና፡ብሎ፡ባየ፡ጊዜ፡ቀንዱ...
ቀንዱ፡ሳቤቅ፡በሚባል፡አረግ፡ተይዞ፡አን...
አንድ፡በግ፡አየ፤ አብርሃምም፡ሄዶ...
አመጣው፤ ስለ፡ልጁ፡ስለ፡ይሥሐቅ...
ፈንታም፡ሠዋው።
፲፬፡ አብርሃምም፡አሁን፡በዚህ፡ተራራ፡**እግዚ...
ብሔር**፡መታየትን፡ታየኝ፡ሲል፡የዚያ...
ቦታ፡ ስሙን፡**እግዚአብሔር**፡ያያል፡ብሎ...
ጠራው።
ስለዚህ፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡**የእግዚአብሔር**
ተራራ፡ይባላል።
፲፭፡ **የእግዚአብሔርም፡መልአክ**፡ከሰማይ...
ወርዶ፡አብርሃምን፡ዳግመኛ፡ጠራው።
፲፮፡ ይህንን፡ነገር፡አድርገኸዋልና፡የምትወደው...
ልጅህንም፡ከእኔ፡አልራራኸለትምና፡በራሴ...
ማልኩ፡አለ፡**እግዚአብሔር**።
፲፯፡ መባረክንም፡እባርክህ፡ዘንድ፡ዘርህንም...
እንደ፡ሰማይ፡ኮከብ፡እንደ፡ባሕር፡አሸዋ...
ማብዛትን፡አበዛዋለሁ፤ልጆችህም፡የጠላት...
አገሮችን፡ይወርሳሉ።
፲፰፡ ቃሌን፡ሰምተሃልና፡የምድር፡አሕዛብም...
ሁሉ፡በዘርህ፡ይከብራሉ፡አለው።
፲፱፡ አብርሃምም፡ወደ፡ብላቴኖቹ፡(አሽከሮቹ)...
ተመለሰ፤ ተነሥተውም፡አንድነት፡ሄዱ...
መሐላ፡ወደ፡ተባለውም፡ጉድጓድ፡ደረሱ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለም...
ትኑር፤ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው...
ምዕ፡፷፩፡፩-፯።
፩፡ በእኔ፡ህልውና፡ያለ፡ያዋሐደኝ፡የባሕርይ...

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ሰአ፡ቀብዓኒ፡ አስተፍሥሆሙ ፡ ለነዳያን ፡
ሰበ፡ ወእፈውሶሙ ፡ ለቀኑሳነ ፡ ልብ ፡
ሰብክ ፡ ግዕዛነ ፡ ለፂውዋን ፡ ወይርአዩ ፡
ሙራን።

ሰምዮ ፡ ለዓመተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኅሩየ ፡
ዕለተ ፡ ፍዳ ፡ ኅሪተ ፡ ወአስተፍሥሖሙ ፡
ለሀዋን።

ሁቦሙ ፡ ክብረ ፡ ለእለ ፡ ይላ
ሁዎ ፡ ለጽዮን፡ ወህየንተ ፡ ሐመድ ፡
ፍረተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ለእለ ፡ ይላህዉ ፡
ልብሰ ፡ ክብር ፡ ህየንተ ፡ መንፈስ ፡
ትክዝ ፡ ወይሰመዩ ፡ ትውልደ ፡ ጻድቃን ፡
ተክል ፡ ዘእምኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለስብ
ሐቲሁ።
ወየሐንጹ ፡ መዘብረ ፡ ዘመዝበረ ፡
ዓለም ፡ ወይቀውሙ ፡ ወያነሥኡ ፡
ወይሔድሱ፡አህጉረ፡ዘመዝበረ፡ለትውልደ፡
ትውልድ።
ወእምዝ ፡ ይመጽኡ ፡ ካልአን ፡ አሕዛብ ፡
ወይርዕዩ ፡ አባግዐኪ ፡ ወሕዝብ ፡ ነኪራን ፡
ይከውኑ ፡ ሰሙ ፡ ሐራስያ ፡ ወአቃብያነ ፡
ወይን።
ወይሰመዩ፡ካህናቲሁ፡ለእግዚአብሔር፡ወአ
ግብርተ፡እግዚአብሔር፡ወይበልዑ፡ኃይለ፡
አሕዛብ፡ወይትሬሰዩ፡በብዕሎሙ።
ወይወርሱ ፡ ካልእተ ፡ ምድረ ፡ ወውስተ ፡
ርእሶሙ፡ትፍሥሕት፡ዘለዓለም።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ።

መንፈስ፡እግዚአብሔር፡ዘላዕሌየ፡እስከ፡
ኀበ ፡ ይብል ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘለዓ
ለም።

ይቤ፡መተርጕም፡ወቃሉሰ፡መንፈስ፡እግዚ
አብሔር፡ዘላዕሌየ፡ይትረጎም፡በእንተ፡
ትኬ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንተ ፡ ርእየ ፡
ዮሐንስ፡መጥምቅ፡በኀበ፡ዮርዳኖስ፡በጊዜ፡
ጥምቀት፡አምላክ፡ቃል።
ሰሙ፡ውእቱ፡ይቤ፡አንሰ፡ርኢኩ፡መንፈስ፡



ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሕይወቴ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡
ድኆችን፡ደስ፡አሰኘቸው፡ዘንድ፡ልባቸው፡የቈ
ሰለውን ፡ አድናቸው ፡ ዘንድ ፡ ለተማረኩም፡
ሰዎች ፡ ነፃ ፡ መውጣትን ፡ እሰብክላቸው ፡ (እስተ
ምራቸው፡ዘንድ)፡ዕውሮችም፡ያዩ፡ዘንድ።
፪፤ እግዚአብሔር ፡ የወሰነውን ፡ ዘመን ፡
የተመረጠ፡ነው፡እለው፡ዘንድ፡ፍዳ፡የሚደረ
ግባትን፡ቀን፡ደግ፡እላት፡ዘንድ፡ያዘኑትንም፡
ሰዎች፡ደስ፡አሰኛቸው፡ዘንድ፡ላከኝ።
፫፤ ለጽዮን ፡ (ለኢየሩሴልም) ፡ ለሚያለቅሱላት ፡
ክብርን ፡ እሰጣቸዋለሁ ፤ የሚአለቅሱትም ፡
ትቢያ ፡ ይቀቡ ፡ ስለነበረ ፡ ፈንታ ፡ ሽቱን ፤ ለሚ
ያለቅሱ ፡ ደስታን ፤ ስለ ፡ አዘነ ፡ ሰውነትም ፡
ፈንታ ፡ የሚያከብር ፡ ልብስን ፡ እሰጣቸዋለሁ።
የጻድቃን ፡ ልጆችም ፡ ሊአመሰግኑት ፡ ከእግዚ
አብሔር፡የተገኘ፡ልጅ፡ተብለው፡ይጠራሉ።
፬፤ ፈጽሞ ፡ የፈረሰውን ፡ ፍራሽ ፡ ይሠ
ራሉ ፤ ተነሥተው ፡ ቁመው ፡ የፈረሰው
ንም ፡ አምባ ፡ ያጸናሉ ፤ ለልጅ ፡ ልጅም ፡
ያድሳሉ።
፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ መጥተው ፡
በጎችሽን ፡ (እስራኤልን) ፡ ይጠብቃሉ ፤
ባዕዳን፡ ሕዝቦችም ፡ አራሾችና ፡ ወይን ፡
ጠባቂዎች፡ይሆኑላቸዋል።
፮፤ የእግዚአብሔር፡አገልጋዮች፡የእግዚአብሔር፡
ባሮች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፤ የአሕዛብን ፡
ገንዘብ፡ይበላሉ፤በገንዘባቸውም፡ያጌጣሉ።
፯፤ ለዘለዓለም፡ተድላ፡ደስታ፡አግኝተው፡ከአሕዛብ፡
አገር፡ሌላ፡የሆነች፡አገርን፡ይወርሳሉ።

የነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ትንቢት፡ትርጓሜ።

የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በሕልውናዬ ፡
ነው፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ የዘለዓለም ፡ ደስታ ፡
እስከሚለው፡ድረስ።
፩፤ ተርጓሚው፡እንዲህ፡ይላል፤ የእግዚአብሔር፡
መንፈስ ፡ በህልውናዬ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡
አካላዊ ፡ ቃል ፡ አምላክ ፡ በዮርዳኖስ ፡
በተጠመቀ ፡ ጊዜ ፡ መጥመቁ ፡ ዮሐንስ ፡
ስላየው፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡ይተረጐማል።
፪፤ እርሱ፡ዮሐንስ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡እየሰሙ፡ የአብ፡

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ቅዱስ፡እንዘ፡ይወርድ፡እምሰማይ፡ወነበረ፡
ዲቤሁ፡ምስለ፡ቃለ፡አብ፡እንዘ፡ይሰምዑ፡
ኵሉ፡ሕዝብ፡እንዘ፡ስምዐ፡ይከውን፡በእንተ፡
ልደቱ።

፫፤ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ቀብዓኒ ፡ ወፈ
ነወኒ ፡ ይተረጐም ፡ በእንተ ፡ ቅብዐት ፡
ካዕበ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘወረደ ፡
ላዕለ ፡ ማርያም ፡ ወአንጽሖ ፡ ሥጋ ፡
ዚአሃ ፡ ለተወክፎ ፡ አምላክ ፡ በከመ ፡
ይቤላ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ይመጽእ ፡ ላእሌኪ ፡ ካዕበ ፡
ይቤላ ፡ እስመ ፡ ዘይትወለድ ፡ እምኔኪ ፡
እመንፈስ፡ቅዱስ፡ውእቱ።

፬፤ ይቤ፡እዜንዎሙ፡ለነዳያን፡ፈነወኒ፡እስመ፡
ተርጐመ፡ውእቱ፡በእንተ፡ዝ፡ለምስኪናን፡
እለ፡ነዳያን፡እምሃይማኖት፡አብዐሎሙ፡በሃ
ይማኖት፡ቦቱ።

፭፤ ይቤ ፡ ወእፈውሶሙ ፡ ለቍሱላነ ፡ ልብ ፡
ይተረጐም ፡ በእንተ ፡ ተሐዝቦቶሙ ፡ ከመ ፡
ኢይከውን፡ጸጋ፡ዘእንበለ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡
እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኅሩያን፡በጸጋ።

፮፤ ወበእንተ ፡ ውእቱኬ ፡ ፈወሰ ፡ እግዚእ ፡
ስዕበተ ፡ ወስብረተ ፡ አልባቢሆሙ ፡ ወሰ
ደደ ፡ እምኔሆሙ፡ ኅሊናሆሙ ፡ እኪተ ፡
ወአብርሆ ፡ አልባቢሆሙ ፡ እስከ ፡ አእመሩ ፡
ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘአምነ ፡ በክርስቶስ ፡ ወገብረ ፡
ትእዛዛቲሁ ፡ ኮነ፡ ሎቱ ፡ ፍጽምና ፡ እምአይ ፡
ሕዝብ፡ውእቱ።

፯፤ ወበእንተ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡
ገሊላ፡ዘአሕዛብ፡ሕዝብ፡ዘይነብር፡ውስተ፡
ጽልመት፡ወጽላሎተ፡ሞት፡ርእዩ፡ብርሃነ፡
ዐቢየ፡ይተረጐም፡ሶበ፡አስተርአየ፡ሎሙ፡
ብርሃን፡አማናዊ፡ዝውእቱ፡ክርስቶስ፡ ሰደደ፡
እምኔሆሙ ፡ ጽልመተ ፡ እበድ ፡ ወበርሆ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ።

፰፤ ይቤ ፡ ወእስብክ ፡ ግዕዛነ ፡ ለፂውዋን ፤
ይተረጐም ፡ እለ ፡ ፄወዎሙ ፡ ሰይጣን ፡
ወሞቅሖሙ ፡ ውስተ ፡ መንሠግ ፡ እስመ ፡
ውእቱ፡አግዐዞሙ፡ባሕቲቱ፡ወአዕረጎሙ፡
ገነተ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ቃል ፡ ስለ ፡ ቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፡ ስለ
ሰክር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከሰማይ
ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ፡ ተቀምጦ ፡ እየሰ
ብሏልና።

፫፤ ስለዚህም ፡ ቀብቶ ፡ ላከኝ ፡ የሚለውን
መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ መንፈስ
ቅዱስ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣል ፤ ከአንቺም
የሚወለደው፡በግብረ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ነው
ብሎ ፡ እንደ ፡ ነገራት ፡ አካላዊ፡ ቃል
አምላክን፡ በድንግልና ፡ ለመፅነስ ፡ እን
ትችል፡በድንግል፡ማርያም፡ላይ፡በወረደ
ከሥስቱ፡ ግብራትም ፡ በከለከላት ፡ በመንፈስ
ቅዱስ፡ ስለ፡ሆነው፡ተዋሕዶ፡ይተረጎማል

፬፤ ለድሆች፡የምሥራች፡እነግራቸው፡ዘንድ፡ላከ
ኝ አለ፤ ስለዚህም፡ከሃይማኖት፡ድኆች፡የሆኑት
መጻተኞችን፡የርሱ፡በሆነ፡ሃይማኖት፡ባለጸጎች
አደረጋቸው፡ብሎ፡ተርጉሞታልና።

፭፤ ልቡናቸው ፡ የቆሰሉትን ፡ እፈውሳቸው
ዘንድ፡ አለ ፤ ልጅነት ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች
በቀር ፡ ለሌሎች ፡ እንደማይሆን ፡ ስለማ
ራጠሩ፡እነርሱ፡በጸጋ፡የተመረጡ፡የእግዚአ
ብሔር፡ ወገኖች፡እንደሆኑ።

፮፤ ስለዚህም፡ጌታ፡ ርኵሰትን፡የልቡናቸውም
ስብራት፡እንደ፡አዳነ፡በተስፋ፡ከእርሳቸውም
ክፉ፡ አሳባቸውንም፡እንደ፡አራቀ፡ከየትም
ወገን፡ቢሆን፡በክርስቶስ፡ አምኖ፡ትእዛዙን
የሚፈጽም፡ሁሉ፡ለእርሱ፡ፍጹም፡ልጅነት
እንዲሰጠው ፡ እስከሚአውቁ ፡ ልቡናቸውን
ብሩህ፡እንዳደረገላቸው፡ይተረጐማል።

፯፤ ስለዚህም፡የከበረ፡ወንጌል፡አሕዛብ፡በሚኖ
ሩባት፡ገሊላ፡በጨለማና፡በሞት፡ጥላ፡ውስጥ
የሚኖር፡ሕዝብ፡ታላቅ፡ብርሃን፡አየ፡አማ
ዕውነተኛ፡ብርሃን፡ይኸውም፡ክርስቶስ፡በተ
ለጸላቸው፡ ጊዜ፡ የልቡናቸውን፡ድንቁርና
ከነሱ ፡ አርቆላቸው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ
ብሩሃን፡ሆኑ፡ብሎ፡ይተረጉማል።

፰፤ ለተማረኩት፡ነፃነትን፡እሰብክ፡ዘንድ፡አለ
ይህም፡ሰይጣን፡ማርኮ፡በመቈለፊያ፡ውስጥ
የዘጋቸውን ፡ ይተረጐማል ፤ እርሱ ፡ ነፃ
አውጥቶ፡ብቻውን፡ወደ፡ገነት፡አሳርጓ
ዋልና።

Scanned by CamScanner

፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ደቤ፡ወይርእዩ፡ዕውራን፡ይተረጕም፡ዘንተ፡
ዘንተ ፡ ውእቶሙ ፡ አብዳን ፡ ወኢ ፡
ምእመናን፡ እስመ ፡ ዕውራነ ፡ አልባብ ፡
እሙንቱ፡እምኀጢአ፡ብርሃነ፡ሃይማኖት፡
ወለበሰ፡አምኑ፡ርእዩ፡ጽድቀ፡ምስለ፡
ግንቃቄሃ፡ሰውረኒ፡ወገሃደኒ።

ደቤ ፡ ወእስምዮ ፡ ለዓመተ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ኅሩየ ፡ ይተረጕም ፡ ከመ ፡
ብሊት፡ኅልቀት ፡ ወተሐደሰት ፡ ዓመት ፡
ፍጽምት፡እንተ፡ይእቲ፡ ኅሪት፡በኀበ፡እግ
ዚአብሔር።

፲፬ ደቤ፡ወዕለተ፡ፍዳ፤ይተረጕም፡ከመ፡ውእቱ፡
ፈደዮሙ፡ለመሃይምናን፡ቦቱ፡ህየንተ፡ርስተ፡
ምድር፡ርስተ፡ሰማይ፡ወህየንተ፡እንስሳ፡
መዋቲ፡ሥጋሁ፡ወደሞ፡ለክርስቶስ፡ዘኢይ
መውት።

፲፭ ደቤ ፡ ወአስተፍሥሐሙ ፡ ለልሕዋን ፡
ይተረጕም ፡ በእንተ ፡ ትኩዛን ፡ ለኀበ ፡
ሰብእ ፡ መሃይምናን ፡ በክርስቶስ ፡ እለ ፡
ትኩዛን፡ እምዓለም ፡ ወእሙንቱ ፡ ዕጉ
ሣን ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ፡ እስመ ፡ ይት
ፌሥሑ ፡ ውእቶሙ ፡ ምስሌሁ ፡ በመን
ግሥተ፡ሰማያት፡በከመ፡ይቤ፡ለሊሁ፡ለአር
ዳኢሁ፡እንትሙሰ፡ትቴክዙ፡ወዓለምሰ፡
ይትፌሣሕ ፡ ወባሕቱ ፡ ሀለወክሙ ፡
ትትፌሥሑ።

፲፮ ወካዕበ ፡ መሃይምናን ፡ በክርስቶስ ፡ ወአር
ድእት፡እመ፡መጠወ፡ነፍሶ፡ለሞት፡ለሐዉ፡
ጥቀ፡ወሶበ፡ተንሥአ፡እሙታን፡ወአስተር
አዮሙ ፡ ወአሰሰለ ፡ እምኔሆሙ ፡ ላሐ ፡
ወተፈሥሐ ፡ አልባቢሆሙ ፡ በእንተ ፡
ትንሣኤሁ።

፲፯ ደቤ ፡ ወሀየንተ ፡ ሐመድ ፡ ዕፍረተ ፡ ትፍ
ሥሕት ፡ ይተረጕም ፡ ዝክተ ፡ ሜሮን ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፪፤ ዕውራን ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፤ እምነት ፡ ስለ
ሌላቸው፡አላዋቂዎች፡ሰነፎች፡ይተረጐማል፤
የሃይማኖትን ፡ ብርሃን ፡ ከማጣት ፡ የተነሣ ፡
እነርሱ ፡ ልባቸው ፡ ታውሮአልና ፤ በአመኑ ፡
ጊዜ፡ ግን ፡ ከተሠወረውም ፡ ከተገለጸውም ፡
ትሩፋቷ፡ጋር፡ጠንቅቀው፡ጽድቅን፡አዩ።

፲፫፤ እግዚአብሔር ፡ የወሰነውን ፡ ዘመን ፡
የተመረጠ፡ነው፡ብየ፡እጠራው፡ዘንድ፡አለ፤
ይህም፡ያረጀችው፡እንደ፡አለፈች፡ፍጽምት፡
የሆነችው ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ታደሰች ፡ ይተረ
ጐማል፤ይህችም፡እግዚአብሔር፡የመረጣት፡
የሥጋዌ፡ዘመን፡ናት።

፲፬፤ የፍዳ ፡ ቀን ፡ አለ ፤ ይህንንም ፡ በእርሱ ፡ ያመኑ
በትን፡ስለ፡ምድራዊ፡ርስት፡ፈንታ፡ሰማያዊ፡
ርስትን ፡ በሞት ፡ ስለሚለወጡ ፡ እንስሶች ፡
ፈንታ፡ የማይሞት ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋውንና ፡
ደሙን፡እሱ፡እንደ፡ሰጣቸው፡ይተረጐማል።

፲፭፤ የሚያለቅሱትን፡ደስ፡አሰኛቸው፡ዘንድ፡አለ፤
ይህንንም፡በክርስቶስ፡አምነው፡ስለሚአዝኑና
በሱ፡ላይ፡ታግሠው፡ከዓለም፡የተነሣ፡ስለሚ
ተክዙ፡ሰዎች፡ይተረጐማል።እነርሱም፡በመከ
ራቸው፡ላይ፡ታግሠው፡ኑረው፡በኋላ፡ከእርሱ፡
ጋራ፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ደስ፡ይላቸዋልና፤
ጌታ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡እናንተ፡አሁን፡ታዝና
ላችሁ፤ትተክዛላችሁ፤ዓለሙም፡ደስ፡ይለዋል፤
ነገር፡ግን፡ደስ፡ይላችሁ፡ዘንድ፡አላችሁ፡እንደ፡
አላቸው።

፲፮፤ ሁለተኛም፡በክርስቶስ፡አስቀድመው፡ያመኑ፡
ምእመናንና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ (ሙቶ ፡ ሃያ ፡
ቤተሰቦቹ)፡ሰውነቱን፡ለሞት፡አሳልፎ፡በሰጠ፡
ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ፤ አለቀሱ ፤ ከሙታንም ፡
ተለይቶ ፡ ተነሥቶ ፡ በተገለጸላቸው ፡ ጊዜ ፡
ልቅሶና፡ ሐዘኑን ፡ ከእርሳቸው ፡ አርቆላቸው ፡
ልቡናቸው፡ስለ፡ትንሣኤው፡ደስ፡አላት።

፲፯፤ ስለ ፡ ሚጤሰው ፡ ሥብ ፡ ፈንታ ፡ ደስ ፡ የሚአ
ሰኝ ፡ ሽቱ ፡ አለ ፤ ይህም ፡ ለከበረች ፡

### በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ቅዱስ ፡ ዘረሰዮ ፡ ለጥምቀት ፡ ቅድስት ፡
እንተ ፡ ይእቲ ፡ ታነጽሕ ፡ ኃጣይአ ፡ ኵሎ ።
እስመ ፡ አልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘኮነ ፡ ይነጽሕ ፡
በሕገ ፡ ኦሪትኒ ፡ ዘእንበለ ፡ በደምኒ ፡
ወሐመድኒ።

፲፭፡ ወፈደየነ ፡ **እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ** ፡ ህየንተ ፡ ዝንቱ ፡ ቅብዐ ፡
ሚሮን ፡ ቅዱስ ፡ ዘውእቱ ፡ ቅብዓ ፡
ትፍሥሕት።

፲፮፡ ይቤ ፡ ወልብሰ ፡ ክብር ፡ ህየንተ ፡ መንፈስ ፡
ትኩዝ ፡ ዛቲኒ ፡ ካዕበ ፡ ትትሜሰል ፡ በኀበ ፡
ጥምቀተ፡**ክርስቶስ**፡ቅድስት።

፲፯፡ ይቤ ፡ ወይሰመዩ ፡ ትውልደ ፡ ጻድቃን ፡
ወተክለ፡ ዘእምኀበ ፡ **እግዚአብሔር** ፡
ለስብሐት ፡ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ መሀይምናን ፡
**በክርስቶስ** ፡ እምኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ይሰመዩ ፡
መሲሐውያነ ፡ እስመ ፡ ተከሎሙ ፡ ውእቱ ፡ በሃ
ይማኖት፡ወጥምቀት፡ወሰመዮሙ፡በስሙ።

፲፰፡ ይቤ ፡ ወየሐንጹ ፡ መዝበረ ፡ ለዓለም ።
ይተረጐም ፡ አሕዛበ ፡ እለ ፡ መለኮሙ ፡
ሰይጣን፡ በአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወረሰዮሙ ፡
መዝበረ ፡ በክህደተ ፡ **እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡
ፈጣሪ**።

ወሶበ፡አስተርአየ፡ሎሙ፡ጽድቅ፡በስብከተ፡
ሐዋርያት ፡ ተሐደሱ ፡ ወተሐንጸት ፡ ልቦሙ ፡
**ታቦተ፡እግዚአብሔር**።

፲፱፡ ይቤ፡ወነኪራን፡ይከውኑ፡ሐረሳውያነ፡ወመ
ስተገብራነ፡ምድር፤ይተረጐም፡ለአሕዛብ፡
ነኪራን፡እለ፡አምኑ፡በእደ፡ሐዋርያት፡ረሰዩ፡
እምኔሆሙ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ወኤጲስቆጶሳተ፡
ቀሳውስተ፡ወዲያቆናተ ። ወኮኑ ፡ መምህራነ፡
ወይጸሐይዩ ፡ አሥዋከ ፡ ወይትጌበርዎሙ ፡
ወይዘርዑ ፡ ውስተ ፡ አልባቢሆሙ ፡ ሠናየ ፡
ዘርዐ፡ዘውእቱ፡ትምህርተ፡ነገረ፡ሕይወት።

### ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ጥምቀት ፡ ያደረገው ፡ የከበረ ፡ ይህንን፡
ሚሮንን፡ ይተረጕማል ፤ ይኸውም ፡
ኃጢአቱን፡ ሁሉ ፡ የምታነፃ ፡ ናትና ፡ በኦሪት
ሕግም ፡ ቢሆን ፡ ሥብ ፡ ሳይጤስ ፡ ደም ፡
ሳይፈስ፡ማንም፡የሚነጻ፡የለም፡ነበርና።

፲፭፡ **ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም** ፡ ስለርሱ፡
ፈንታ ፡ ተድላ ፡ ነፍስ ፡ የሚገኝባት ፡ ልጅነት፡
የምታሰጥ ፡ ጥምቀትን ፡ ቅብዐ ፡ ሚሮን፡
ተካልን ፤ ይኸውም ፡ ቅብዐ ፡ ትፍሥሕት፡
**መንፈስ፡ቅዱስን**፡የሚአሳድር፡ነው።

፲፮፡ ስለ ፡ አዘነ ፡ ሰውነት ፡ ፈንታ ፡ የሚአከብር፡
ልብስ፡ (ይለብሳሉ) ፡ አለ ፡ ይቺም ፡ ሁለተኛ፡
በከበረች፡**በክርስቶስ**፡ጥምቀት፡ትመሰላለች።

፲፯፡ የጻድቃን፡ልጆችና፡ሊአመሰግኑት፡**ከእግዚአ
ብሔር** ፡ የተገኙ ፡ ልጅ ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ፡
አለ ፤ ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ **በክርስቶስ** ፡ ያመኑ፡
ምእመናን ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲባሉ ፡ ይተረ
ጕማል ፤ እርሱ ፡ በሃይማኖት ፡ በጥምቀት፡
ተክሎ፡በስሙ፡እንዲጠሩ፡አድርጓቸዋልና፡

፲፰፡ ፈጽሞ ፡ የፈረሰውን ፡ ፍራሽ ፡ ይሠራሉ፡አለ፡
ይኸውም ፡ ሰይጣን ፡ በአምልኮ ፡ ጣዖት፡
ምክንያት ፡ እጅ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ልዑል፡
ባሕርይ ፡ **ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔርን** ፡ በማ
ካድም፡የተበታተኑትን፡አንድ፡ያደረጋቸው፡
አሕዛብን ፡ ይተረጕማል ። በሐዋርያትም፡
ትምህርት፡እውነተኛ፡ሃይማኖት፡በተገለጸ
ላቸው፡ጊዜ፡ልቡናቸው፡ተሐድሶ፡እግዚአ
**የእግዚአብሔር፡ማደሪያ**፡ሁና፡ተሠራች።

፲፱፡ ልዩ ፡ ወገን ፡ የነበሩ ፡ ምድርን ፡ የሚአርሱ፡
ገበሬዎች፡ይሆናሉ፡አለ፤በሐዋርያት፡ትምህርት፡
ላመኑ ፡ ለተለዩ ፡ ለአሕዛብ ፡ ይተረጕማሉ ፡ ከእ
ርሱም፡የጳጳሳት፡አለቆችን፡ኤጲስቆጶሳትን፡ቀሳ
ውስትን፡ዲያቆናትን፡አድርገው፡ሾሙ። መምህ
ራንንም ፡ ሁነው ፡ እሾህን ፡ ይነቅላሉ ፡ ይጠሩጓ
ዋልም ። በትምህርታቸውም ፡ ከሰዎች ፡ ልቡና፡
ድንቁርናን፡ኃጢአትን፡ክህደትን፡አርቀው፡ከል
ቡናቸው፡ውስጥ፡መልካም፡ዘርን፡ዘሩ፤ይኸውም፡
የሕይወት፡ቃል፡የወንጌል፡ትምህርት፡ነው።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ደቤ ፡ ወአንትሙሰ ፡ ትሰመዩ ፡ ካህናተ ፡
እግዚአ ፡ ወላእካነ ፡ ቤተ ፡ **እግዚአብሔር** ፡
ይተረጐም ፡ ለኅበ ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ ይሜህሩ ፡
ሞርጓቶሙ ፡ ወይትጌበሩ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ለተናገሩ ፡ እምተገብሮ ፡ እስመ ፡ ይደልዎሙ ፡
ይሰመዩ ፡ ካህናቲሁ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ ወላዕ
ኪሁ፡ከመ፡ካህናት፡ሰማያውያን።

ደቤ ፡ ወሀየንተ ፡ ኅሰረትክሙ ፡ ወላሐክሙ ፡
ትነሥኡ ፡ ርስተ ፡ በውስተ ፡ ምድሮሙ ፤
ይተረጐም ፡ በእንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሶበ ፡ አምኑ ፡
ነሥኡ ፡ ርስቶሙ ፡ ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምእመናነ ፡
**ክርስቶስ** ፡ እምደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወሰደ
ደዎሙ ፡ እምድሮሙ ፡ ወውእቶሙ ፡ ወዕኡ ፡
እምርስተ ፡ ምድሮሙ ፡ ወእምርስተ ፡
መንግሥተ፡ሰማያት።

ደቤ ፡ ወውስተ ፡ ርእሶሙ ፡ ትፍ
ሥሕት ፡ ዘለዓለም ፡ ይተረጐም ፡ ከመ ፡
ለመሃይምናን ፡ **በክርስቶስ** ፡ ኢየኅልፍ ፡
ርስቶሙ ፡ ወኢ ፡ መንግሥቶሙ ፤
ደቤ ፡ ወይከውኑ ፡ ኅሩያነ ፡ ወፍሡሐነ ፡
**በክርስቶስ** ፤ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወትረ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዘኢዮብ ፡ ጻድቅ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡
ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ምዕ፡፳፯፡፩–፳፪።

ወደገመ፡ዓዲ፡ኢዮብ፡ወይቤ።
ሕያው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ዘኰነነኒ ፡
ከመዝ ፡ ወዘዘሐሎ ፡ ይመልክ ፡ ዘአምረራ ፡
ለነፍስየ።



ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፷፡ እናንተስ፡**በእግዚአብሔር**፡ቤት፡ውስጥ፡የም
ታገለግሉ፡**የጌታ**፡ካህናት፡ትባላላችሁ፡አለ፤
ይህንንም ፡ ምእመናኖቻቸውን ፡ የሚአስተ
ምሩና ፡ ከሥራ ፡ ያስተማሩትንም ፡ ከእር
ሳቸው፡ ጋራ ፡ ለሚሠሩ ፡ ለካህናት ፡ ይተረ
ጕማል ፤ ለእርሳቸው ፡ እንደ ፡ ሰማያውያን ፡
ካህናት፡መባል፡ይገባቸዋልና።

፷፩፤ ስለ ፡ ጕስቍልናችሁና ፡ ስለ ፡ ልቅሶአችሁ ፡
በምድራቸው ፡ ውስጥ ፡ ርስትን ፡ ትወስዳ
ላችሁ ፡ አለ ፤ ይህንንም ፡ ስለ ፡ አሕዛብ ፡ ይተረ
ጕማል ፤ አሕዛብ ፡ በአመኑ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡
ልጆች ፡ **በክርስቶስ** ፡ ያላመኑትን ፡ ርስታ
ቸውን ፡ ወሰደው ፡ ከርስታቸው ፡ አሳደዱ
አቸው ፤ እነዚያም ፡ ከምድራዊው ፡ ርስትና ፡
ከሰማያዊውም፡ርስት፡ወጡ።

፷፪፤ ለራሳቸውም ፡ የዘለዓለም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
አላቸው ፡ አለ ፤ ይህንም ፡ **በክርስቶስ** ፡ ላመኑ ፡
ርስታቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለዘላለም ፡
እንደማታልፍ ፡ ይተረጕማል ፤ የተመረጡና ፡
**በክርስቶስ** ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የሚኖሩ ፡
ይሆናሉ፡ አለ ፤ ዘወትር ፡ ለእርሱ ፡ ክብር ፡
ምስጋና፡የሚገባው፡ለዘላለሙ፡አሜን።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡
ትኑርና ፡ ጻድቁ ፡ ኢዮብ ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡
ነው።

ምዕ፡፳፯፡፩–፳፪።

፩፤ ዳግመኛም፡ኢዮብ፡ተናገረ፤እንዲህም፡አለ።
፪፤ እንዲህም፡አድርጎ፡የፈረደብኝ፡ሰውነቴንም፡
በመከራ ፡ አጽንቶ ፡ የያዛት ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡
እግዚአብሔር፡ሕያው፡ነው።

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፫፡ ሶበሁ፡ሀለወት፡ነፍስየ፡ወዓዲ፡መንፈስ፡እግዚአብሔር፡ዘያስተናግረኒ፡ከመ፡ኢይንብብ፡ አፉየ ፡ ዓመፃ ፡ ወኢትትመሀር ፡ ነፍስየ ፡ ኃጢአተ።

፬፡ እትሔዘብሰ ፡ እምአርአይኩክሙ ፡ ጽድቀ ፡ ዘእንበለ፡እሙት፡እስመ፡ኢየኃድጋ፡ለየወሀትየ፡(ለሕይወትየ።)

፭፡ እንዘሰ ፡ ጽድቀ ፡ እገብር ፡ ኢይትሐጐል ፡ እስመ፡ኢይትዓወቀኒ፡ዘገበርኩ፡እኩይ።

፮፡ ወባሕቱ፡ሶበ፡ኮኑ፡ጸላእትየ፡ከመ፡ድቀተ፡ኃጥአን፡ወእለሂ፡ይትነሥኡ፡ላዕሌየ፡ከመ፡ሞተ፡ዓማፅያን።

፯፡ ወለምንት ፡ ይጸንሕ ፡ ኃጥእ ፡ ከመ ፡ ይሴሮ ፡ ሐይወ ፡ ወዘኢተወከለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይድኅንኑ፡እንጋ።

፰፡ ወይሰምዖኑ ፡ ጸሎቶ ፡ ወእመሂ ፡ መጽአ ፡ ምንዳቤ ፡ ይረክብኑ ፡ እንጋ ፡ ገጸ ፡ በኀቤሁ።

፱፡ ወእመሂ፡ጸውዖ፡ይሠጠዎኑ፡ወያውሥኦኑ።

፲፡ ወባሕቱ ፡ እነግረክሙ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዘውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር፡ወኢይሔሱ፡ዘሀሎ፡በኀበ፡ዘኵሎ፡ይመልክ።

፲፩፡ ተአምሩ፡ኵልክሙ፡ከመ፡እኪት፡ለእኩያን፡ትመጽእሙ።

፲፪፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ መክፈልቱ ፡ ለብእሲ ፡ ኃጥእ ፡ እምኀበ፡እግዚአብሔር፡ወይበጽሖ፡ንዋየ፡ዓበይት፡ኀቤሁ፡እምኀበ፡ዘኵሎ፡ይመልክ።

፲፫፡ ወእመሂ፡በዝኁ፡ደቂቁ፡ይከውኑ፡ለሙስና፡ ወእመሂ ፡ ጸንዑ ፡ ያስተፍእሙ ፡ ወእለ ፡ በዓውዱ፡ሞተ፡ይመውቱ።

፲፬፡ ወአልቦ፡ዘይምሕሮን፡ለዕቤራቲሆን።

፲፭፡ ወእመሂ ፡ አስተጋብአ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፫፡ ነፍሴ፡ገና፡በእኔ፡ውስጥ፡ሳለች፡እንደ... ሐሰትን ፡ እንዳይናገር ፡ ሰውነቴም... ኃጢአትን፡እንዳትማር፡የሚያናግረኝ፡የእ... ዚአብሔር፡መንፈስ፡ነው።

፬፡ እኔስ፡ሳልሞት፡ደግነቴን፡(ሰውነቴን)፡ከ... ተማመናትምና ፡ እውነት ፡ ነገርን ፡ በነ... ኋችሁ፡ነበር፡ብዬ፡አስባለሁ።

፭፡ ያደረግሁት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አይታወቀኝም... ዕውነት፡ነገርን፡እየሠራሁ፡አልጐዳም፡

፮፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጠላቶቼ ፡ እንደ ፡ ኃጢአተኞች... (እንደ ፡ ጠፉ) ፡ ቢጠፉ ፡ በጠላትነት ፡ የሚ... ሡብኝ፡ሰዎችም፡እንደ፡በደለኞች፡(ሰዎች... እንደ፡ሞቱ)፡ቢሞቱ፡(የተገባ፡ነበር)፡

፯፡ ድኅነትን፡ተስፋ፡ያደርግ፡ዘንድ፡ኃጢአተኛ... ሰው፡ለምን፡ደጅ፡ይጠናል፡በእግዚአብሔር... ያላመነ፡ሰው፡ይድናልን?እንጃ።

፰፡ ልመናውንስ ፡ ይሰማዋልን ? መከራ... ቢመጣበት ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በእርሱ... ዘንድ፡ ገጸ ፡ ረድኤትን ፡ (ባለሟልነትን)... ያገኛልን?እንጃ።

፱፡ ቢጠራውስ፡እግዚአብሔር፡ይቀበለዋልን... ይመልስለታልን?እንጃ።

፲፡ ነገር፡ግን፡በእግዚአብሔር፡እጅ፡ያለውን... ምን፡እንደ፡ሆነ፡እነግራችኋለሁ፡ሁሉን... በሚገዛ፡በእግዚአብሔር፡ዘንድም፡ያለውን... ሥራ፡ሐሰት፡አላደርግም።

፲፩፡ ክፉ፡ነገር፡በክፉዎች፡እንድትመጣባቸው... ሁላችሁም፡ታውቃላችሁ።

፲፪፡ ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የሚገኘው፡የኃጢ... አተኛ፡ሰው፡ዕድል፡ፈንታው፡ይህ፡ነው፡የ... ፈኞችንም፡ሀብት፡ሁሉ፡ከሚገዛ፡ከእግዚአ... ብሔር፡ዘንድ፡ወደ፡እርሱ፡ይደርሳል።

፲፫፡ ልጆቹም ፡ ቢበዙ ፡ ለጥፋት ፡ ይሆናሉ ፡ ቢያድጉም ፡ ለማኞች ፡ ይሆናሉ ፡ በአርሱ... ባይም፡የሞት፡ሞትን፡ይሞታሉ።

፲፬፡ ለባልቴቶቻቸውም፡የሚያዝንላቸው፡ሰው... የለም።

፲፭፡ ብሩን ፡ እንደ ፡ አፈር ፡ ቢሰበስበው ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ለዘፋር፡ወከመ፡ዕቡር፡ዘገበ፡ወርቀ።
ዘትሎ፡ጸድቃን፡ይነሥእዎ፡ወይረክብዎ፡
ለንዋዩ፡ራትዓን።

ወይከውን፡ቤቱ፡ከመ፡ሣሬት፡ወከመ፡
ብልዐ፡ቍንቍኔ።
ፃመ፡ባዕል፡ወአልቦ፡ዘያነቅሖ፡ወይከሥት፡
አዕይንቲሁ፡ወያነክር።

ወይጠብቆ፡ሕማም፡ከመ፡ማይ፡ወይነሥኦ፡
በውሎ።

ወይመስጦ፡ሐሩር፡ወየኀልፍ፡ወይልሕሶ፡
እምነ፡መንበሩ።

ወይመጽእ፡ላዕሌሁ፡ዘኢየአምሮ፡ወኢይ
ምሕኮ፡ወኢያመሥጥ፡እምእዴሁ፡
ወየኃልፍ።

ወይጠፍሕ፡እዴሁ፡በላዕሌሁ፡ወይስሕቦ፡
እምነ፡ቤቱ።

ምዕ፡፳፰፡፩–፲፫።

ቦ፡ብሔር፡እምኀበ፡ይወፅእ፡ብሩር፡
ለወርቅኒ፡ቦ፡ብሔር፡እምኀበ፡የአርርዎ።

ሐፂንሂ፡እምውስተ፡ምድር፡ይትገበር፡
ለብርትኒ፡ከመ፡እብን፡ይፈጽሕዎ።

ለጽልመትኒ፡አዘዘ፡ዕድሜሁ፡ወለኵሉ፡
ውእቱ፡የሐትቶ፡እብነ፡ጽልመት፡
ወጽላሎተ፡ሞት።

ከመ፡ስጥቀተ፡ፈለግ፡ውስተ፡መሬት፡እለ፡
ይረሥዕዋ፡ለፍኖተ፡ጽድቅ፡ደክሙ፡በኃጢ
አቶሙ።

ለምድርኒ፡ይወፅእ፡እምኔሃ፡እክል፡በመትሕ
ቲሃኒ፡ጠብለላ፡በእሳት።

ቦ፡ብሔር፡ዘእብነ፡ሰንፔር፡ወወርቃኒ፡ከመ፡
መሬት።

ፍኖት፡ዘኢርእያ፡ዖፍ፡ወዘኢነጸራ፡ዐይነ፡
ንስር።

ወኢኬድዋ፡ደቂቀ፡ዝኁራን፡በእግር፡
ወኢኀለፈ፡አንበሳ፡በውስቴታ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ወርቁንም፡እንደ፡ጭቃ፡አብዝቶ፡ቢያከማች።

፲፯፤ ይኸንን፡ሁሉ፡ደጋግ፡ሰዎች፡ይወስዱታል፤
ቅን፡ልቡና፡ያላቸውም፡ሰዎች፡ገንዘቡን፡
ያገኙታል።

፲፰፤ ቤቱም፡እንደ፡ሸረሪት፡ድር፡ነቀዝም፡እንደ
ሚበላው፡ነው።

፲፱፤ ባለጸጋም፡የጤና፡እንቅልፍን፡ይተኛል፤ከእ
ንቅልፉም፡የሚቀሰቅሰው፡የለም፤ዓይኖቹን፡
ይከፍታል፡እርሱም፡ያደንቃል።

፳፤ መከራም፡እንደ፡ጐርፍ፡ታገኘዋለች፤በዝቶ፡
በሌሊትም፡አውሎ፡ነፋስ፡ትነጥቀዋለች።

፳፩፤ ጽኑ፡መቅሠፍት፡ነጥቆ፡ይወስደዋል፤
ይሞታልም፤ከመከራውም፡ከአልጋውም፡
(ሞት)፡ያላቅቀዋል።

፳፪፤ የማያውቀውም፡መከራ፡ይመጣበታል፤
መጥቶም፡አይራራለትም፤ከእጁም፡ፈጥኖ፡
አያመልጥም፤ያልፋል፡እንጂ።

፳፫፤ በሱም፡እጁን፡ያጨበጭብበታል፤ከቤቱም፡
ጎትቶ፡ያወጣዋል።

ምዕ፡፳፰፡፩–፲፫።

፩፤ ብር፡የሚወጣበት፡አገር፡አለ፤ወርቅንም፡
የሚለቅሙበት፡አገር፡አለ።

፪፤ ብረቱም፡ከመሬት፡ይሠራል፤ነሐሱንም፡
(መዳብንም)፡እንደ፡ድንጋይ፡ከመሬት፡ይፈ
ነቅሉታል።

፫፤ ለጨለማ፡ወሰንን፡ያደርጋል፤ሁሉንም፡ይመ
ረምረዋል፤የሞት፡ጥላን፡ድንጋይንም፡ይመ
ረምራል።

፬፤ በአፈር፡ምክንያት፡እንደሚከፈል፡ወንዝ፡
የጽድቅን፡መንገድ፡የረሱ፡በኃጢአታቸው፡
ይደክማሉ።

፭፤ እህል፡(እንጀራ)፡ከምድር፡ውስጥ፡ይወጣል፤
በእሳትም፡እንደሚሆን፡ታችኛው፡ይገለ
በጣል።

፮፤ ሰንፔር፡የሚባል፡ዕንቍም፡የሚገኝበት፡
አገር፡አለች፤ወርቋም፡እንደ፡አፈር፡ነው።

፯፤ ወፍ፡ያላየት፡የአሞራም፡ዐይን፡ያልተመለ
ከታት።

፰፤ ትዕቢተኞች፡ልጆች፡በእግር፡ያልተረገጧት፡
አንበሳም፡በስዋ፡ያላለፈባት፡ጐዳና፡አለች።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፱፡ ወአንሥአ ፡ እዴሁ ፡ በእዝኀ ፡ ወአጥፍአሙ ፡ ለአድባር፡እመሠረቶሙ፡ወእምሥርዎሙ።

፲፡ ወሰጠቀ፡አንቅዕተ፡አፍላግ፡ወርእየት፡ኵሎ፡ ክቡራተ።

፲፩፡ ወሰጠቀ ፡ ቀላያተ ፡ ዘአፍላግ ፡ ወአርአየ ፡ ኃይሎ፡በውስተ፡ብርሃን።

፲፪፡ ወእምአይቴ ፡ ተረክበት ፡ ጥበብ ፡ ወአይቴ ፡ ብሔራ፡ለጥበብ።

፲፫፡ ወኢየአምራ፡መዋቲ፡ለፍኖታ፡ወኢሀለወት፡ ኀበ፡ዕጓለ፡እመሕያው።

ትርጓሜ፡ኢዮብ፡(ምሥጢራዊ፡ትርጓሜ)።

ሕያው፡እግዚአብሔር፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ ኀበ፡ዕጓለ፡እመሕያው።

፩፡ ይቤ፡መተርጕም፡ወቃሉሰ፡ለእግዚአብሔር፡ ሕያው፡ዘኰነነኒ፡ከመዝ፤ይተረጐም፡እስመ፡ ጻድቅ ፡ ዘመሐለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘአመ ንደቦ፡በመናስው።

፪፡ ይቤ ፡ ወዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ ዘአምረራ ፡ ለነፍስየ፤ይተረጐም፡ዘንተኒ፡ካዕበ፡ዘረከቦ፡ እምሰያጥንት፡መቃርንተ፡ዚአሁ፡ወዘኮኑ፡ ያከብዱ፡ቦቱ፡እምኀሊና፡እንተ፡ታመርራ፡ ለነፍስ።

፫፡ ይቤ ፡ ሶበሁ ፡ ሀለወት ፡ ነፍስየ ፡ ዓዲ ፡ ውስቴትየ፤ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ ጻድቅ ፡ ኮነ ፡ ያነክር፡እምሕይወቱ፡እንዘ፡ውእቱ፡ውስተ፡ ዝንቱ፡ምንዳቤ፡ዐቢይ።

፬፡ ዘሰምዐ ፡ ዘከማሁ ፡ ወበዘሕቅ ፡ እምዘረከቦ ፡ ለጻድቅ ፡ ሶበ ፡ ረከቦ ፡ ለብእሲ ፡ እምኮነ ፡ የኀድግ፡ሕይወቶ።

፭፡ ወለእመሰ፡ኢኮነት፡ነፍሱ፡ለሰብእ፡ዘይእቲ፡ ሕይወቱ ፡ ሕጽርተ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ልዑል፡በውስቴቱ፡እምኮነት፡ትትፈለጠ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፱፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቡላድ ፡ ድንጋይ ፡ እጁን፡ ይዘረጋል፤ አንሥቶ ፡ ተራሮችን ፡ ከሥር፡ከ ሠረታቸው፡ያጠፋቸዋል።

፲፡ የፈሳሾችንም፡ምንጮች፡ከፈለ፤ ዐይኑም፡የ በሩትን፡ድንቅ፡ነገሮች፡ሁሉ፡አየች።

፲፩፡ በወንዞቹ ፡ ላይ ፡ የሚሄዱ ፡ ምንጮችንም፡ ከፈላቸው፤ በብርሃንም፡ውስጥ፡ከሃሊነቱ፡ ገለጠ።

፲፪፡ ጥበብ፡ከወዴት፡ተገኘች? የጥበብስ፡አገሯ፡ ወዴት፡ነው?

፲፫፡ ሟችም ፡ ሰው ፡ ጐዳናዋን ፡ አያውቃትም፡ በሰውም፡ዘንድ፡የለችም።

የኢዮብ፡ትርጓሜ፡(ምሥጢራዊ፡ትርጓሜ

ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ፡ ኀበ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እስከ ፡ ሚለው፡ ድረስ።

፩፡ ተርጓሚው ፡ የፈረደብኝ ፡ የሕያው ፡ እግዚ ብሔር ፡ ቃሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ አለ፤ በፈተ ናዎች፡ በፈተነው ፡ በእግዚአብሔር፡የማለ ኢዮብ ፡ እውነተኛ ፡ ነውና ፡ እንዲህ፡ይተ ጕማል።

፪፡ ሰውነቴን፡ያስጨነቃት፡ሁሉን፡የሚገዛ፡እግ ዚአብሔር ፡ ነው ፡ አለ፤ ሰውነትን ፡ ከምታ ጨንቅ፡ሐሳብ፡የተነሣ፡ከራሱ፡ጠላቶች፡ሰ ጣናትና፡መከራ፡ከሚያጸኑበት፡የተገኘውን፡ ይህን፡ዳግመኛ፡ይተረጕማል።

፫፡ ነፍሴ ፡ ገና ፡ በውስጤ ፡ ሳለች ፡ አለ ፡ ጻድቅ ኢዮብ፤ በዚህ፡በታላቅ፡መከራ፡ውስጥ፡ሆ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ በመለየቷ ፡ የሚያደንቅ እንደ፡ሆነ፡ይተረጕማል።

፬፡ እንደዚሁም፡የሰማውም፡ጻድቅ፡ኢዮብን፡ከ ኘው፡መከራ፡ጥቂቱ፡ሌላውን፡ሰው፡ቢያገኘው ሕይወቱን፡የሚያሳልፍ፡በሆነ፡ነበር።

፭፡ የሰው፡ነፍስ፡ይቺውም፡ሕይወቱ፡በልዑል እግዚአብሔር ፡ የተጠበቀች ፡ ባትሆን ከውስጡ፡የምትለየው፡በሆነች፡ነበር።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፪ ወይቤ፡መንፈሰ፡እግዚአብሔር፡ዘያስተናግረኒ፤
ይተረጐም፡በእንተ፡ዝንቱ፡ይባቤያተ፡ወስባ
ሔያተ፡ወትንቢታተ፡እለ፡ከና፡ይወፅአ፡እም
እስትንፋሱ፡ቅድስት።

፫ ወይቤ፡እስመ፡ከናፍርየ፡ኢነበባ፡ዐመፃ፡
ወነፍስየ፡ኢተምህረት፡ኃጢአተ፤
ይተረጐም፡በእንተዝ፡ከመ፡ጻድቅ፡
ቀዳሚሁ፡መሐለ፡ዘንተ፡መሐላ፡ዐቢየ፡ከመ፡
ከናፍሪሁ፡ኢነበበ፡ኃጢአተ፡ወኢ፡ነፍሱ፡
ኢተለወት፡ዓመፃ።

፬ ኢይቤ፡ጻድቅ፡ዘንተ፡ተመኪሖ፡አላ፡
ትምህርት፡ለዘውእቱ፡እምድኅሬሁ፡እስመ፡
ዘይሰምዕ፡ምንዳቤሁ፡ይትሔዘብ፡ከመ፡እግ
ዚአብሔር፡አመከሮ።

፭ እመሰኬ፡አሐተ፡ኃጢአተ፡ገብረ፡ፈደየ፡
ሎቱ፡ዕዳ፡በእንተ፡ኃጢአቱ፡በከመ፡ገብረ፡
ላዕለ፡ዳዊት፡ነቢይ፡ከመ፡ሶበ፡ኀጥአ፡
አግብአ፡ውስተ፡እደ፡አቤሴሎም፡ፍዳ፡
ኀጢአቱ።

፮ ወነገረ፡ዝንቱ፡ጻድቅ፡ከመ፡ከናፍሪሁ፡
ኢነበባ፡ጌጋየ፡ወኢነፍሱ፡ኢተምህረት፡
ዐመፃ፤ይተረጐም፡በእንተ፡ውእቱ፡ከመ፡
ኢገብረ፡ውእቱኒ፡ምንተ፡እምግብራተ፡
ኃጢአት፤እስመ፡ይቤ፡ለሊሁ፡ኢነበባ፡
ከናፍርየ፡ጌጋየ።

፯ ዝ፡ውእቱ፡ኢወፅአ፡እምአፉሁ፡ነገረ፡
ፅርፈት፡ወኢ፡ሐሰት፤ወኢክሕዶ፡ለእግዚአ
ብሔር፡ልዑል፡ኢ፡በገቢረ፡ሕይወት፡ወኢ፡
በገቢረ፡ምንዳቤ።

፰ ይቤ፡ወነፍስየ፡ኢተምህረት፡ዐመፃ፤
ዘውእቱ፡ነፍሱ፡ዘበእንተ፡ንጽሒታ፡
ኢኀለየት፡ኀሊና፡እኪተ፡ለሊሃ።

፱ ወኢክህለት፡ትምይንተ፡ሰይጣን፡ከመ፡
ትቅረብ፡ኀቤሃ፡ከመ፡ትርምያ፡ውስተ፡
ኃጢአት።
እስመ፡ዐመፃ፡ኃጢአት፡ይእቲ።

፲ ወካዕበ፡ነበበት፡ትንቢተ፡አፉሁ፡ለጻድቅ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፪፤ የሚያናግረኝ፡የእግዚአብሔር፡መንፈስ፡
ነው፡ አለ፤ስለዚህም፡ከከበረች፡አንደበቱ፡
የሚወጡ፡ምስጋናዎችንና፡ዕልልታዎችን፡
ትንቢቶችን፡ይተረጒማል።

፫፤ ከንፈሮቼ፡ሐሰትን፡አልተናገሩም፤
ሰውነቴም፡ኃጢአትን፡አልተማረችምና፡
አለ፤ስለዚህም፡ጻድቅ፡ኢዮብ፡በአንደበቱ፡
ሐሰት፡እንዳልተናገረና፡ሰውነቱም፡ግፍን፤
ኃጢአትን፡እንዳልሠራች፡አስቀድሞ፡
በዚህ፡በጽኑ፡መሐላ፡እንደ፡ማለ፡ይተረ
ጒማል።

፬፤ ጻድቁ፡ኢዮብ፡በመመካት፡ይህን፡አላለም፤
ከእርሱ፡በኋላ፡ለሚነሱ፡ትምህርት፡ሊሆን፡
ነው፡እንጂ፤መከራውን፡የሰማ፡ሁሉ፡እግዚ
አብሔር፡እንደ፡ፈተነው፡ያስባልና፤
(ይረዳልና)።

፭፤ አንዲት፡ኃጢአት፡ሠርቶስ፡ቢሆን፡ስለ፡
ኃጢአቱ፡ዕዳ፡ሆኖበት፡ፍዳውን፡ለእርሱ፡
በከፈለው፡ነበር፤በነቢዩ፡ዳዊት፡ላይ፡እንዳ
ደረገ፤ዳዊት፡ኃጢአት፡በሠራ፡ጊዜ፡ስለ፡
ኃጢአቱ፡ፍዳ፡በአቤሴሎም፡እጅ፡አሳልፎ፡
ሰጥቶት፡ነበርና።

፮፤ ይህ፡ጻድቅ፡አንደበቱ፡በደልን፡እንዳልተ
ናገረ፡ሐሰት፡በመናገር፡እንዳልበደለ፡
ሰውነቱም፡ዐመፅን፡እንዳልተማረች፡(እንዳ
ላወቀች)፡ተናገረ፤ስለዚህ፡ከኃጢአት፡ሥራ፡
እርሱ፡ምንም፡ምን፡እንዳልሠራ፡ይተረ
ጒማል፤እርሱ፡ራሱ፡ቅሉ፡አንደበቴ፡
በደልን፡አልተናገረም፡ብሏልና።

፯፤ ይህም፡ይህ፡ነው፤ከአንደበቱ፡የስድብ፡ነገር፡
ወይም፡ሐሰት፡አልወጣም፤በጤንነቱም፡
ሆነ፡በመከራው፡ልዑለ፡ባሕርይ፡እግዚአብ
ሔርን፡አልካደውም።

፰፤ ሰውነቴ፡ዐመፅን፡አልተማረችም፡አለ፤
ይህም፡ሰውነቱ፡ስለ፡ንጽሂ፡ክፉ፡አሳብን፡
አላሰበችም።

፱፤ የሰይጣንም፡ተንኰል፡ወደርሷ፡ቀርባ፡
በኃጢአት፡ጦር፡ትወጋት፡ዘንድ፡አልቻ
ለችም፡አለ።
ዐመፅ፡ኀጢአት፡ናትና።

፲፤ ሁለተኛም፡የጻድቁ፡አንደበት፡ስለ፡አካላዊ፡

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|

በእንተ ፡ ትሥግተ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ወቃኒብሮ፡ ውስተ ፡ ዘዘከረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ፡ እስመ ፡ ኢገብረ ፡ ኀጢአተ ፡ ወኢተ ረክበ፡ሐሰት፡ውስተ፡አፉሁ።

፲፭፡ ይቤ፡ወኢይከውኑኒ፡ሊተ፡ከመ፡እበል፡ከመ፡ ጻድቃን፡አንትሙ፡ ይተረጐም፡ከመ፡እለ፡ ኮኑ፡ይገብሩ፡ሠናየ፡ለኀሚሠ፡ስብሐተ፡ ብጡል፡ ወኮኑ፡ ይፈቅዱ፡ ይወድስዎሙ፡ ጻድቃን።

፲፮፡ ለጻድቅሰ፡በእንተ፡ውእቱ፡ኮነት፡ኃይል፡ እንተ፡ሀለወት፡ውስቴቱ፡ትኤምሮ፡ከመ፡ እሙንቱ፡ኢኮኑ፡ጻድቃን።

፲፯፡ ይቤ፡እስመ፡ኢየኃድጋ፡ለእበድየ፡እንዘ፡ ጽድቀ፡እኔጽር፡ኢይትኃጐል፡ይተረጐም፡ ዘንተኒ፡ከመ፡ውእቱ፡ኮነ፡ይዘልፎሙ፡ ለእኩያን፡ወኢይትዌከፉ፡እምኔሁ፡ወይሰ ምዩዎ፡እብደ።

፲፰፡ ወበእንተ፡ውእቱ፡ይቤ፡ሰሎሞን፡ጠቢብ፡ ኢትዝልፎ፡ለአብድ፡ከመ፡ኢይጽላእከ፡ ወዝልፎ፡ለጠቢብ፡ወያፈቅረከ።

፲፱፡ ወኮነ ፡ ጻድቅ ፡ ይብሎሙ ፡ አንትሙሰ ፡ ትብሉኒ፡ አብደ ፡ በእንተ ፡ ተዛልፎትየ ፡ ለከሙ፡ ወአንሰ፡ኢየኃድግ፡ዘንተ፡እበደ፡ ወኢያረምም፡በእንተ፡ጽድቅ።

፳፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ኢይትዐወቀኒ ፡ ዘገበርኩ ፡ እኩይ፡ ይተረጐም ፡ ዘውእቱ ፡ አንሰ ፡ ኢያመርኩ ፡ አድልዎ ፡ ወኢየኃፍር ፡ ከመ ፡ እዝልፎሙ ፡ ለእለ ፡ እሙንቱ ፡ የሐውሩ ፡ ውስተ፡ዘኢኮነ፡ፍኖተ፡እግዚአብሔር።

፳፩፡ ጸላእትየ ፡ ኮኑ ፡ ከመ ፡ ድቀተ ፡ ኃጥአን ፡ ይተረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ጸላእቱ፡ሰይጣናት፡ ሶበ ፡ ሰአልዎ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያብሐሙ፡ላዕለ፡ሥጋሁ፡በትሕዝብት፡ዘእም ኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ይክሐዶ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡በምንዳቤሁ።

፳፪፡ ወሶበ፡ርእዩ፡እሙንቱ፡ዘላዕሌሁ፡እምትዕ ግሥተ ፡ አዳም ፡ ወገድለ ፡ ሥን ፡

ቃል ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ኃጢአት ፡ አልሠራምና ፡ በአንደበቱም ሐሰት፡ አልተገኘምና ፡ ብሎ ፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ ፡ ከጠቀሰው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርጋ ቃስተባብረዋለች።

፲፭፡ እናንተ ፡ ጻድቃን ፡ እንደሆናችሁ ፡ እናገ ዘንድ ፡ ለእኔ ፡ አይሆንልኝም ፡ አለ ፡ ውዳሴ ከንቱ ፡ በመሻት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ስለሆኑ፡ ይተረጐማል ። ጻድቃን ፡ (ደጋጎች) ብለው፡ያመሰግኑአቸው፡ዘንድ፡ይወዳሉና፡

፲፮፡ ለጻድቅ ፡ ለኢዮብ ፡ ግን ፡ በእርሱ ፡ ያደረ ኃይል ፡ ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ጻድቃን ፡ (ደጋጎች) እንዳልሆኑ፡ቃመለክተዋለች።

፲፯፡ እውነትን ፡ ተመልክቼ ፡ እየሠራሁ ፡ ሳለ እናንተ ፡ ስንፍና ፡ የምትሉትን ፡ ተግሣጼን ፡ አ ተውምና ፡ አልጎዳም ፡ አለ ። ይህንንም ፡ እርሱ ክፉዎችን ፡ የሚዘልፋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ እነርሱም ፡ ከርሱ ፡ እንደማይቀበሉት ይልቁንም፡ሰነፍ፡እንደሚሉት፡ይተረጐማል።

፲፰፡ ስለዚህም ፡ ብልሑ ፡ ሰሎሞን ፡ እንዳይጠላህ ሰነፍን ፡ አትዝለፈው ፤ ብልህን ፡ ግን ዝለፈው፡እርሱም፡ይወድሃል፡አለ።

፲፱፡ ጻድቅ ፡ ኢዮብም ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ዘለ ፋችሁ፡ ሰነፍ ፡ ትሉኛላችሁ ፤ እኔም ፡ ይህን ፡ አ ተውም ፤ ስለ ፡ ዕውነት ፡ ዝም ፡ አልልም ፡ (ከመ ገርም፡አንደበቴ፡አልገታም)፡ይላቸው፡ነበር

፳፡ የሠራሁት ፡ ክፋት ፡ አልታወቀኝምና ፡ አለ ይኸውም ፡ እኔ ፡ ማድላት ፡ (ዐድልዎ) ፡ አለመ ቅምና ፤ በእግዚአብሔር ፡ ጐዳና ፡ ባልሆነ የሚሄዱትን ፡ (በሕግ ፡ ጸንተው ፡ የማይኖ ሩትን)፡ እገሥጻቸው ፡ ዘንድ ፡ አላፍርም ማለቴ፡እንደ፡ሆነ፡ይተረጐማል።

፳፩፡ ጠላቶቼ ፡ ኃጢአተኞች ፡ እንደሚጠፉ ፡ ሆኑ አለ ፤ ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ እርሱ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ ይክደው ፡ ዘንድ ፡ ሰይጣናት በሥጋው ፡ ላይ ፡ ያሠለጥናቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚ አብሔርን ፡ በለመኑት ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቹ ፡ እንደ ሆኑ፡ይህን፡ይተረጐማል።

፳፪፡ እነሱም ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ ያለሆነ ትዕግሥቱን ፡ ገድሉንና ፡ ጽድቁን ፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

መጽርዕ፡ተኃፍሩ፡ወኮኑ፡ከመ፡ኃጥአን።

፳፫ አስመ፡ዳዊት፡ነቢይ፡አስተማሰለ፡ኃጥአነ፡
ከመ፡ቆባር፡ዘይግሕሮ፡ነፋስ፡እምገጸ፡
ምድር፡በእንተዝ፡ተመስዉ፡ሰያጥንት፡ከመ፡
ቆባር፡እምቅድመ፡ገጸ፡ጻድቅ።

፳፬ ይቤ፡ምንት፡ውእቱ፡ተስፋ፡ኃጥአን፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ሶበ፡ሞተ፡ኃጥእ፡
ዘበኃጢአቱ፡አልቦቱ፡ተስፋ፡በቅድመ፡እግ
ዚአብሔር፡ወኢምሕረት፡እስመ፡ኢገብረ፡
ውእቱ፡በዘቦቱ፡ተአዘዘ።

፳፭ ይቤ፡አው፡ይሰምዖኑ፡እግዚአብሔር፡ጸሎቶ፡
እምከመ፡ወረደት፡ላዕሌሁ፡በቀል፡
ይተረጐም፡ከመ፡እግዚአብሔር፡ልዑል፡
ኢይሰምዖሙ፡ጸሎቶሙ፡ለኃጥአን፡እለ፡
ያዘልፉ፡ውስተ፡ኃጢአት፡ወያጠብዑ፡
ለገቢሮታ፡አላ፡ይፌኑ፡ላዕሌሆሙ፡በቀለ፡
ወኢይሰምዕ፡ጸሎቶሙ።

፳፮ በከመ፡ይቤ፡በነቢይ፡በእንተ፡እግዚአ
ብሔር፡ልዑል፡እስመ፡ኃጢአትክሙ፡ተንጠ
ልዐት፡ማእከሌየ፡ወማእከለ፡ጸሎታቲክሙ።

፳፯ ይቤ፡ወባሕቱ፡እነግረክሙ፡ምንት፡ውእቱ፡
ዘውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር፡ወኢይሔሱ፡
ዘሀሎ፡ኀበ፡ዘኮሎ፡ይመልክ፡ይተረጐም፡
ከመ፡ውእቱ፡ያእትቶሙ፡ለገባርያነ፡እከይ፡
ወይትከልኡ፡ወይቤሎሙ፡አጤይቀክሙ፡
እንከ፡ዘይከውን፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡
ፍዳ፡ዚአክሙ።

፳፰ ይቤ፡ተአምሩ ኵልክሙ፡ከመ፡እኪት፡
ለእኩያን፡ትመጽእሙ፡ይተረጐም፡ከመ፡
ውእቱ፡ኢይብል፡ለብእሲ፡ሥሙር፡ዳእሙ፡
ለኵሎሙ፡እለ፡ይሰምዑ፡ቃላቲሁ፡ለእግዚአ
ብሔር፡በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡ቅዱስ፡
ዘአብሎ፡ለከሙ፡ለኵልክሙ፡እብሎ።

፳፱ ይቤ፡እስመ፡እኪት፡ለእኩያን፡ትመጽእሙ፡
ይተረጐም፡በከመ፡ይትሄየይ፡ትእዛዛተ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

በአዩ፡ጊዜ፡አፈሩ፤እንደ፡ኃጢአተኞችም፡
ጠፉ።

፳፫፤ ነቢይ፡ዳዊት፡ኃጢአትን፡ከምድር፡ገጽ፡
ነፋስ፡ጠርጎ፡እንዲወስደው፡ጭጋግ፡
አስመስሎ፡ተናግሮአልና፡ስለዚህም፡
ከጻድቁ፡ኢዮብ፡ፊት፡ሰይጣናት፡እንደ፡
ጭጋግ፡በነው፡ጠፉ።

፳፬፤ የኃጥአን፡ተስፋ፡ምንድነው፡አለ፤
ኃጢአተኛ፡በኃጢአቱ፡ሳለ፡የሞተ፡እንደ፡
ሆነ፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡ተስፋ፡
(ምሕረት)፡እንደ፡ሌለው፡ይህን፡ይተረ
ጉማል፤እርሱ፡በሕግ፡የታዘዘውን፡አልሠ
ራምና።

፳፭፤ ስለ፡ኃጢአቱ፡በቀል፡መከራ፡ከወረደበት፡
እግዚአብሔር፡ልመናውን፡ይሰማዋልን ?
አለ፤ይህን፡እንዲህ፡ይተረጉማል፤
ኃጢአትን፡የሚያዘወትሩ፡እርስዋንም፡
ለመሥራት፡የሚበረቱትን፡የበቀል፡ፍርድ፡
ይልክባቸዋል፡እንጂ፤እግዚአብሔር፡ልመና
ቸውን፡እንደማይሰማቸው፡ይህን፡ይተረ
ጉማል።

፳፮፤ ስለ፡ልዑል፡እግዚአብሔር፡በእኔና፡በጸሎ
ታችሁ፡መካከል፡ኃጢአታችሁ፡ተጋር
ዳለች፡ብሎ፡በነቢዩ፡አድሮ፡እንደ፡ተናገረ።

፳፯፤ ነገር፡ግን፡በእግዚአብሔር፡እጅ፡ያለውን፡
ምን፡እንደ፡ሆነ፡እነግራችኋለሁ፤ሁሉን፡
በሚገዛው፡ዘንድ፡ያለውን፡አልዋሽም፡አለ፤
ክፉ፡የሚሠሩትን፡እንደሚአስወግዳቸውና፡
ከእርሱ፡እንደሚርቁ፡ይተረጉማል፤
እንግዲህ፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡የምትቀ
በሉት፡የእናንተ፡ፋዳ፡ይህ፡እንደ፡ሆነ፡አስረ
ዳችኋለሁ፡ይላቸዋል።

፳፰፤ ክፉ፡ነገር፡በክፋዎች፡እንድትመጣባቸው፡
ሁላችሁ፡ታውቃላችሁ፡አለ፤የእግዚአብ
ሔርን፡ነገሮች፡ለሚሰሙ፡ሁሉ፡ነው፡
እንጂ፤በአገልግሎቱ፡ደስ፡ለሚአሰኘው፡
ሰው፡እሱ፡እንደማይናገር፡ይተረጉማል፤
በቅዱስ፡ወንጌል፡ለእናንተ፡የምለውን፡
ለሁላችሁ፡እለዋለሁ፡እንዳለ።

፳፱፤ ክፉ፡ነገር፡በክፋዎች፡ትመጣባቸዋለችና፡
አለ፤ይኸንንም የእግዚአብሔርን፡ትዕዛዞች፡

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እግዚአብሔር ፡ ወይትሉ ፡ ከንቶ ፡ ከማሁኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ይትኄየዮ ፡ ሎቱ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡ ወይሜጥዎ ፡ ለእኩይ ፡ ኵነኔ።

፴፤ ናሁኬ ፡ መጽአ ፡ ሎቱ ፡ እምእከይ ፡ ዘነበረ ፡ መስተሐውዝ ፡ ሎቱ ፡ ወፈጋዒ ፡ ቦቱ ፡ ቀብጸ ፡ ለጽድቅ ፡ ዛ ፡ ይእቲ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወቀሪብ ፡ እምእግዚእ ፡ ክቡር ፡ ስሙ ፤ ወኮነ ፡ ቅብ ላዕለ ፡ እከይ ፡ ዘበአማን ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ጸተ ፡ ብርሃን ፡ ወርኂቅ ፡ እም ፡ እግዚ አብሔር ፡ ወነቢር ፡ ውስተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘለ ዓለም።

፴፩፤ ይቤ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ መክፈልቱ ፡ ለብእሲ ፡ ኃጥእ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይተረጐም ፡ በአማንኬ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ በአምጣነ ፡ ዘአዝለፈ ፡ ላዕለ ፡ ግብሩ ፡ እኩይ ፡ ይከውን ፡ ርኁቀ ፡ እም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይከውን ፡ መክፈልቱ ፡ ምስለ ፡ እኩያን።

፴፪፤ ይቤ ፡ ዝልፈቶሙ ፡ ለኀያላን ፡ ይመጽእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እምኀበ ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ ይተረጐም ፡ በእንተ ፡ ኀያላን ፡ ኀበ ፡ ነገሥት ፡ ከሓድያን ፤ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፌኑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ዘይፀንዕ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወይጊ ውዎሙ።

፴፫፤ ይቤ ፡ ወእመሂ ፡ በዝኁ ፡ ደቂቁ ፡ ለመጥባሕት ፡ ይከውኑ ፡ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ ይቀሥፎሙ ፡ ለደቂቆሙ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወይዘልፎሙ ፡ ቦቱ ፡ ልበሙ።

፴፬፤ ይቤ ፡ ወዘረከቡኒ ፡ ይመውቱ ፡ በሞት ፡ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፌኑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ሞተ ፡ ድንቀተ ፡ ለውሉዶሙ ፡ ወይደመስስ ፡ እንስሳሆሙኒ ፡ ዓዲ ፡ በብድብድ።

፴፭፤ ይቤ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይምሕሮን ፡ ለዕቤራቲሆን ፡ መኑሂ ፡ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያአኪ ፡ አልባቢሆሙ ፡ ለሰብእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ኀቤሆሙ ፡ መዐተ ፡ እግዚአ ብሔር።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ቸል ፡ ብሎ ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የሚከተለውን፡ እንዲሁ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ልዑል ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ቸል ፡ እንደሚለውና ፡ ለጽኑ፡ ሥቃይም፡እንደሚሰጠው፡ይተረጐማል።

፴፤ እነሆ ፡ በመቀማጠልና ፡ በመዝናናት፡ በመደሰት ፡ የነበሩትን ፡ የከፋ ፡ ብድራት፡ መጣለት ፤ ጽድቅን ፡ ከማግኘት ፡ ተስፋ፡ ቆረጠ ፤ ይችም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት፡ናት፤ ስሙ ፡ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ ከሆነ ፡ ከጌታ፡ መቅረብም ፡ ተስፋ ፡ ቆረጠ ፤ በዕውነትም፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሆነ ፤ ይኸውም ፡ ብርሃን፡ ማጣት ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ መራቅ፡ በዘላለም ፡ ሥቃይ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ ነው።

፴፩፤ የኃጥእ ፡ ሰው ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ፊት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ክፉ ፡ ሥራ፡ አዘውትሮ ፡ በመሥራቱ ፡ መጠን ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ የራቀ ፡ እንደሚሆን ፡ ዕድል፡ ፈንታውም ፡ ከክፉዎች ፡ ጋራ ፡ እንደሚሆን፡ ይተረጐማል።

፴፪፤ የኀያላን ፡ ዘለፋቸው ፡ ሁሉን ፡ ከሚገዛ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይመጣባቸዋል ፡ አለ ፤ በከሓ ድያን ፡ ነገሥታት ፡ ዘንድ ፡ ኃያላን ፡ ስለሆኑ፡ ይተረጐማል ፤ ከእነርሱ ፡ የሚጸና ፡ በእነርሱ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይልካል ፤ ይማርኳቸ ዋልም ፡ አለ።

፴፫፤ ልጆቹም ፡ ቢበዙ ፡ ለሾተል ፡ ይሆናሉ ፡ አለ፤ ልጆቻቸውን ፡ ከፊታቸው ፡ እንደሚቀሥፋ ቸውና ፡ በዚህም ፡ ልቡናቸው ፡ በሱ ፡ እንደሚዘ ልፋቸው ፡ ይተረጐማል።

፴፬፤ በክፉታቸው ፡ ሁነው ፡ የተገናኙኝ ፡ በሞት፡ ይጠፋሉ ፡ አለ ፤ እግዚአብሔር ፡ በእነርሱ፡ ላይ ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ እንደሚልክባቸው፡ ልጆቻቸውንና ፡ እንስሶቻቸውንም ፡ ደግሞ፡ በቸነፈር ፡ እንደሚአጠፋ ፡ ይተረጐማል።

፴፭፤ መበለቶቻቸውንም ፡ ማንም ፡ ማን ፡ የሚራራ ላቸው ፡ የለም ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ፡ ወደ ፡ እርሳቸው ፡ ደርሶ ፡ እስኪያጠፋቸው፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእርሳቸው ፡ ላይ፡ የሰዎችን ፡ ልብ ፡ እንደሚያስጨክን ፡ ይተረ ጐማል።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ይቤ፡ወንዋዩ፡ዘኵሉ፡ጻድቃን፡ይነሥእዎ፡
ይተረጕም፡ከመ፡እግዚአብሔር፡የሐይድ፡
ንዋዮሙ፡እምኔሆሙ፡ወይሁቦ፡ለዘያፈቅር።
ወከማሁ፡አዘዘ፡እግዚአብሔር፡ለደቂቀ፡
እስራኤል፡ከመ፡ይንሥኡ፡ንዋየ፡ግብጻ
ውያን፡ጊዜ፡ወአቶሙ፡እምግብጽ።

ይቤ፡ኖመ፡ባዕል፡ወኢይነቅህ፡ወይከሥት፡
አዕይንቲሁ፡ ይተረጕም ፡ ዘንተ ፡ ሞቶ ፡
ለብእሲ፡ዘበኃጢአት፡እስመ፡ኢይሬኢ፡
ውእቱ፡መለኮቶ፡ለእግዚአብሔር።
ይቤ፡ወይጠብቆ፡ሕማሙ፡ከመ፡ማይ፡
ይተረጕም፡ከመ፡ውእቱ፡እምድኅረ፡ሞቱ፡
ይትመነደብ፡በኀሊናሁ፡ወይኔስሕ፡በእንተ፡
ዘተዐወረ፡በአዝማነ፡ንስሓሁ፡ወኢይረክብ፡
ኑዛዜ፡ዳእሙ፡ይከውን፡ስጡመ፡ውስተ፡
ሕማማት፡ወገዐርት፡ከመ፡ዘስጡም፡ውስተ፡
ልኰታተ፡ማያት።
ይቤ፡ወይነሥኦ፡ዐውሎ፡በሌሊት፡
ወይመሥጦ፡ ሐሩር ፡ ወኢይምህኮ ፡
ይተረጕም፡ሌሊተ፡ለኀበ፡ጽልመተ፡
ገሃነም፡ወዐውሎ፡ለኀበ፡ጽልመተ፡አልባ
ቢሆሙ፡ለኃጥአን፡ወሐሩረኒ፡ለኀበ፡ኵነኔ፡
ሲኦል።

ወኢይምህኮ፡ይተረጕም፡ከመ፡አልቦ፡
ዘይምህኮ፡ለኃጥእ፡እምድኅረ፡ሞቱ።

ይቤ፡ቦ፡ብሔር፡እምኀበ፡ይወፅእ፡ብሩር፡
ወለወርቅኒ፡ቦ፡ብሔር፡እምኀበ፡የአርይዎ፡
ወለሐፂንኒ፡ወለብርትኒ፡ካዕበ፡አመረ፡
ጻድቅ።
ዘንተ፡ኀበ፡ዘይትኄየል፡ወያስተጋብእ፡
ዘዘኢአሁ፡ ንዋያተ ፡ ወመዛግብታተ ፡
ወይዘግብ፡ወኢየሐውር፡በፈሪሃ፡እግዚአ
ብሔር፡ዳእሙ፡ይዘግባ፡ወይትዌከል፡ላዕሌሃ፡
ኣላ፡ይከውን፡እንከ፡ላቲ፡ከመ፡መምለክያነ፡
ጣዖታት፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘያፈቅር፡ብሩረ፡ይከውን፡ሎቱ፡መምለኬ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፴፮፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቡን ፡ ደጋጎች ፡ ይወስ
ዱታል፡አለ፤እግዚአብሔርም፡ገንዘባቸውን፡
ከእነርሱ፡ወስዶ፡ለወደደው፡እንደሚሰጥ፡
ይተረጐማል ፤ እንደዚሁም ፡ ከግብጽ ፡
በሚወጡ፡ጊዜ፡የግብጻውያንን፡ገንዘብ፡እን
ዲወስዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆች፡እንደ፡አዘዘ።
፴፯፤ ባለጸጋ ፡ ተኛ ፤ የሚያነቃውም ፡ የለም ፤
ዐይኑንም፡ይገልጣል፡አለ፤ይህም፡በኃጢአት፡
ውስጥ፡ሳለ፡የሞተ፡ሰው፡የእግዚአብሔርን፡
ጌትነቱን፡እንደማያይ፡ይተረጐማል።
፴፰፤ መከራው ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ በዝቶ ፡ ያስጨን
ቀዋል፡ አለ፤ከሞተ፡በኋላ፡በአሳቡ፡እንደሚ
ጨነቅ፡ንስሓ፡በመግቢያው፡ወራት፡ቸል፡
በማለቱ፡እንደሚጸጸት፡የሚጽናናበትም፡እን
ደማያገኝ፡ይተረጐማል፤በመከራና፡በልቅሶ፡
ውስጥ፡ተውጦ፡በውኃዎች፡ጥልቅ፡አዘዋሪ፡
ውስጥ፡እንደ፡ሰጠመ፡ይሆናል፡እንጂ።
፴፱፤ መከራም፡በሌሊት፡ይይዘዋል፤(ይዞ፡ረቂቅ፡
መቅሠፍት፡ያጠፋዋል)፡ሐሩርም፡በቀን፡
ያቃጥለዋል፤አይራራለትምም፡አለ፤ሌሊት፡
ያለውን፡ወደ፡ገሃነም፡ጨለማ፡ዐውሎ፡
ያለውንም ፡ ወደ ፡ ኃጥአን ፡ የልቡና ፡
ድንቁርና፡ ሐሩርንም፡ወደ፡ሲኦል፡ስቃይ፡
ይተረጐማል።
፵፤ አይራራለትምም፡አለ፤ኃጢአተኛ፡ከሞተ፡
በኋላ፡የሚራራለት፡እንደ፡ሌለ፡ይተረ
ጐማል።
፵፩፤ ብር፡የሚወጣበት፡አገር፡አለ፤ወርቅንም፡
የሚለቅሙበት፡አገር፡አለ፡ብሎ፡ተናገረ፤
የሚያወ
ብረቱንም፡መዳቡንም፡ናሐሱንም፡የሚያወ
ጡበት፡አለ፡ብሎ፡ጻድቅ፡አመለከተ።
፵፪፤ ይህንንም ፡ በሚበረታታ ፡ ገንዘብ ፡ ዕቃዎ
ችንና፡ ገንዘቦችን፡በየራሱ፡ሰብስቦ፡የሚያ
ከማች፡በአምልኮተ፡እግዚአብሔር፡ጸንቶ፡
የማይኖር፡ነገር፡ግን፡ገንዘብን፡አከማችቶ፡
በገንዘቡ ፡ የሚታመንባት ፡ እርሱም ፡
እንግዲህ ፡ ጣዖታትን ፡ እንደሚያመልክ ፡
ሆነለት፡እንጂ፤እግዚአብሔርን፡በመፍራት፡
ጸንቶ፡አይኖርም፤እግዚአብሔር፡ገንዘብን፡
የሚወድ፡አምላኪው፡ይሆናል፡ብሎአልና።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፵፫፡ ይቤ ፡ ለጽልመትኒ ፡ አዘዘ ፡ ዕድሜሁ ፡ ይተረጎም፡ውእቱኬ፡በከመ፡ነገረነ፡ዘገብረ፡ ዘንተ ፡ ናሁ ፡ ረሰዮ ፡ መክፈልቶ ፡ ውስተ ፡ ገሃነም።

፵፬፡ ይቤ ፡ እለ ፡ ይረሥዕዋ ፡ ለፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ይተረጎም ፡ ከመ ፡ ደከሙ ፡ በኃጢአቶሙ ፡ እለ፡ ይውዕኡ ፡ እምሕገ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ወሥርዐቱ፡ይወድቁ፡ውእቶሙ፡እምብዝኀ፡ ኃጢአቶሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ተለዉ ፡ ግብረ፡ እንስሳ ፡ በምግባራቲሆሙ ፡ ወአድከሙ፡ልቡናቲሆሙ።

፵፭፡ ይቤ፡ወለምድርኒ፡ይውዕእ፡እምኔሃ፡ኅብስት፤ አመረ ፡ ካዕበ ፡ በእንተ ፡ ምድር ፡ ለኅበ ፡ **መለኮት**፡ወኅብስተኒ፡ለኅበ፡ይባቤያት፡ወስ ባሔያት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ ወኅብስተ ፡ መላእክቲሁ ፡ በልዑ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው።

፵፮፡ ይቤ ፡ ወመትሕቴሃኒ ፡ ጠብለላ ፡ በእሳት ፡ ይተረጎም ፡ ዘንተኒ ፡ መንሡገ ፡ መካነ ፡ ሆነኒያት፡ለኃጥአን።

፵፯፡ ይቤ፡ውብሔረ፡እበኒሁ፡ሰንፔር፡ወምድሩ፡ ወርቅ፡ዝንቱሰ፡ይትሜሰል፡በእንተ፡ክብራ ቲሆሙ፡ለነገሥት፡በከመ፡ነገረ፡ዮሐንስ፡ ወንጌላዊ፡በውስተ፡ራእዩ፡በእንተ፡ኢየሩ ሳሌም፡ሰማያዊት፡ወዘባቲ፡እምአዕናቊ፡ ወባዕድኒ።

፵፰፡ ይቤ ፡ ፍኖት ፡ ዘኢያእመራ ፡ ዖፍ ፡ ወኢ ነጸራ ፡ ዐይነ ፡ ንስር ፤ ይተረጎም ፡ ዝክተኒ ፡ ሰብእ ፡ እኩያን ፡ በላዕተ ፡ ሥጋ ፡ ሰብእ ፡ እስመ ፡ እሙንቱሰ ፡ እለ ፡ ኢድ ልዋን ፡ ከመ ፡ ይብጽሑ ፡ ኀቤሃ ፡ ወኢይሬእ ይዋኒ።

፵፱፡ ወከማሁ፡ይቤ፡ዓዲ፡ከመ፡ውእቱ፡ዘኢርእየ፡ ዐይን ፡ ወኢሰምዐ ፡ እዝን ፡ ወልበ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው፡ዘኢኀለየ፡ዘአስተዳለወ፡**እግዚአ ብሔር**፡ለእለ፡ያፈቅርዎ።

፶፡ ይቤ፡ወኢኬድዋ፡ደቂቀ፡ዝኑራን፡በከመ፡ ዘከርነ፡ከመ፡ኢያድምዕዋ፡ዘእንበለ፡እለ፡ ድልዋን፡ላቲ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፵፫፡ የጨለማውንም ፡ ጊዜ ፡ ወሰነ ፡ አለ ፡ ያ ንንም ፡ እንደ ፡ ነገረን ፡ እነሆ ፡ ዕድሉ ፈንታውን፡በገሃነም፡ውስጥ፡እንዳደረገ፡የሚ ረጉማል።

፵፬፡ ዕውነተኛይቱን ፡ መንገድ ፡ (ሕግ) ፡ የሚሰ ሰዎች ፡ በኃጢአታቸው ፡ ደከሙ ፡ (ተጉዳ) አለ፤**ከእግዚአብሔር**፡ሕግና፡ሥርዓት፡የወጡ አብዝተው ፡ ከሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ የተነሣ በመከራ ፡ እንደሚወድቁ ፡ ይተረጉማል እነርሱ፡የእንስሳትን፡ሥራ፡በመሥራት፡ልቦና ቸውን፡ምውት፡አድርገዋልና።

፵፭፡ እንጀራ፡ከእርሷ፡የሚገኝባት፡ምድር፡አለች አለ፤ይህንንም፡ስለ፡ምድር፡ወደ፡**መለኮት** ሰጥቶ፡ኅብስት፡ያለውን፡ለእርሱ፡ወደሚገቡ ዕልልታዎችና ፡ ምስጋናዎች ፡ ሁለተኛ አመለከተ፤ የመላእክትን ፡ እንጀራ ፡ ሰዎች ተመገቡ፡ብሎ፡ነቢይ፡ዳዊት፡እንደ፡ተናገረ

፵፮፡ ከበታቿም ፡ በእሳት ፡ ጠቀለላት ፡ አለ ለኃጥአን ፡ የሚሆን ፡ ይህን ፡ የስቃይ የቅጣት፡ቦታ፡ቁልፍ፡ይተረጉማል።

፵፯፡ የድንጋዩም፡ሀገር፡ዕንቊ፡ምድሩም፡ወርቅ ነው፡አለ፤ይኸ፡ከዕንቊና፡ከሌላም፡ከከበሩ ድንጋዮች ፡ ያጌጠች ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ፡ ወንጌላዊው ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ተናገረ ፡ በነገሥታቱ ፡ ሀብትና ፡ ክብር ይመሰላል።

፵፰፡ ወፍ ፡ ያላወቃት ፡ የአሞራ ፡ ዐይን ፡ ያላየት ጐዳና ፡ ናት ፡ አለ፤ይኸም ፡ ክፉዎች ፡ የሆኑ የሰውን ፡ ሥጋ ፡ የሚበሉ ፡ (ሐሜተኞች) ሰዎችን፡ይተረጉማል፤እነርሱ፡ወደ፡እርሷ ሊደርሱ ፡ የማይገባቸው ፡ ናቸውና ፡ ሊያዩ ዋትም፡አይችሉምና።

፵፱፡ እንዲሁም፡ዳግመኛ፡እርሱ፡ዐይን፡ያላየው፡ጆሮ፡ያልሰማው፡የሰው፡ልብ፡ያላሰበው፡**እግ ዚአብሔር** ፡ ለወዳጆቹ ፡ ያዘጋጀው ፡ እንደ ሆነ፡ተናገረ።

፶፡ ለእርሷ፡የተገቡ፡ከሆኑት፡በቀር፡እንደማያ ኙዋት፡አስቀድመን፡እንደ፡ወሰነው፡ትዕቢ ተኞች፡ልጆች፡አይረግጧትም፡አለ።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፶፩ ይቤ ፡ ወኢኀለፈ ፡ ውስቴታ ፡ አንበሳ ፡ ይተረጎም ፡ ከመ ፡ ኢይክል ፡ መኑሂ ፡ እምነ ሥተ ፡ ምድር ፡ ይትመጠዋ ፡ በኀይለ ፡ ሰራዊቱ፡ አው ፡ በውሂበ ፡ ንዋዩ ፡ ዳእሙ ፡ በበረ፡ትእዛዛቲሁ፡**ለእግዚአብሔር**፡ወበሃይማኖት፡ቦቱ።

፶፪ ይቤ ፡ ወአንሥአ ፡ እደዊሁ ፡ በርእሰ ፡ ማእዘንት ፡ ይተረጎም ፡ ዘንተ ፡ ስቅለቶ ፡ **ለእግዚእ** ፡ ወሰፍሐተ ፡ እደዊሁ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል።

፶፫ ይቤ ፡ እምርእሰ ፡ ማእዘንት ፡ ይተረጎም ፡ ዘከተረ ፡ በእንተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጽዮን ፡ እንተ፡ ሰፍሐ ፡ እደዊሁ ፡ **እግዚእ** ፡ በውስቴቶን ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ ዘውእቱ ፡ እብን ፡ ኅሩይ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ አንሰ ፡ እነብር ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ፡ እብነ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ፡ማእዘንት ፡ ኅሪት ፡ ወዘአምነ ፡ ባቲ ፡ ኢይትኃፈር።

፶፬ ይቤ ፡ ወይገፈትዖሙ ፡ ለአድባር ፡ እምሥርዖሙ፡ይተረጎም፡ዘንተ፡ለኀበ፡ነገሥት፡ወመቢባን፡እለ፡ኢኮኑ፡ምእመናነ ። እስመ፡ሰበ ፡ ርእዩ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ተሰብረት ፡ ኃይለ ፡ ሰይጣን ፡ እንተ ፡ ውስቴቶሙ፡ወተአዘዙ፡ለኀበ፡ሃይማኖት፡**ዘለክርስቶስ**።

፶፭ ይቤ ፡ ወሠጠጠ ፡ አንቅዕተ ፡ አፍላግ ፡ ይተረጎም ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ትምህርተ፡ርኩስ፡ዘኮነ፡እምኀበ፡ሰይጣን፡ዘሰፈነ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው፡እስመ፡**እግዚአብሔር**፡ሠጠጣ።

፶፮ ይቤ ፡ ወአርአየ ፡ ኃይሎ ፡ በውስተ ፡ ብርሃን ፡ ይተረጎም ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ አርአየ፡ለመሀይምናን ፡ ዘኮነ ፡ ቦቱ ፡ ክቡተ ፡ እምኔሆሙ ፡ እምአእምሮታት ፡ መንፈሳውያት፡በሀብተ፡**መንፈስ፡ቅዱስ**፡ዘሀሎ።

፶፯ ይቤ፡እምአይቴ፡ተረክበት፡ጥበብ፡ወአይቴ፡ብሔራ ፡ ለጥበብ ፡ ወኢየአምራ ፡ መዋቲ ፡ ፍኖታ ፡ ወኢሀለወት ፡ ዝየ ፡ ኀበ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፶፩፤ በውስጧም፡አንበሳ፡አላለፈም፡አለ፤ይኸም፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ማንም ፡ ማን ፡ በሠራዊቱ፡ ኃይል ፡ ገንዘብን ፡ በመስጠት ፡ ሊይዛት፡እንደማይችል፡ይተረጉማል፤ነገር፡ ግን ፡ **የእግዚአብሔርን** ፡ ትእዛዞች ፡ በመሥራትና፡እርሱን፡በማመን፡ነው፡እንጂ።

፶፪፤ በማእዘን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቹን ፡ አነሣ ፡ አለ፤ ይህንም ፡ **የጌታን** ፡ ስቅለቱንና ፡ እጆቹን ፡ በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ መዘርጋቱን ፡ ይተረጉማል።

፶፫፤ ከማእዘን ፡ ራስ ፡ አለ፤ይኸንንም፡**ጌታ**፡በውስጣቸው፡በዕፀ፡መስቀል፡ላይ፡እጆቹን፡የዘረጋባቸው፡ስለ፡ኢየሩሳሌምና፡ስለ፡ጽዮን፡ይተረጉማል ፤ ይኸውም ፡ የተመረጠ ፡ ድንጋይ ፡ ነው፤ ሐዋርያው፡ከማእዘን፡ራስ፡ላይ፡የተመረጠች፡የከበረች፡ድንጋይን፡አኖራለሁ፤ያመነባትም፡ለዘላለሙ፡አያፍርም፡እንዳለ፡(ይህ፡**ጌታ፡ክርስቶስ**፡ነው)።

፶፬፤ ተራሮችን ፡ ከሥራቸው ፡ እገለብጣቸዋለሁ ፡ አለ፤ይኸንንም፡ወደ፡ነገሥታትና፡ምዕመናን፡ወደ፡ ሆኑ ፡ ብልሃተኞች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይተረጉማል፤ አስደናቂዎች፡ተአምራቶችን፡በአዩ፡ ጊዜ ፡ በእነርሱ ፡ አድራ ፡ የነበረች ፡ የሰይጣን ፡ ኃይል ፡ ጠፍታላቸው ፡ **በክርስቶስ** ፡ ለሆነች ፡ ሃይማኖት፡ታዛገሮችና፡ተቀባዮች፡ሁነዋልና።

፶፭፤ የፈሳሾችን፡ምንጮች፡ሠነጠቀ፡አለ፤እርሱ፡በሰው፡ልጆች፡ላይ፡ተስፋፍቶ፡ያለ፡የረከሰ፡ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ትምህርትን ፡ **እግዚአብሔር**፡አጥፍቶታልና፤ ስለሱ ፡ ይህን ፡ ይተረጉማል።

፶፮፤ በብርሃን ፡ ውስጥ ፡ ኃይሉን ፡ አሳየ ፡ አለ፤ ይህን ፡ ከእነርሱ ፡ ተሠውሮ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የነበረ ፡ **በመንፈስ፡ቅዱስ**፡ሰጭነት፡ከሚገኝ፡መንፈሳዊ፡ (ረቂቅ) ፡ ዕውቀት ፡ ብዙ ፡ ሥውር ፡ ለሆነባቸው ፡ ለምዕመናን፡ይህንን፡እንደ፡ገለጸ፡ይተረጉማል።

፶፯፤ ጥበብ ፡ ከወዴት ፡ ተገኘች ? የጥበብ ፡ አገርዋስ፡ ወዴት ፡ ነው ? ሟች ፡ ጐዳናዋን ፡ አያውቃትም ፤ በሰውም ፡ ዘንድ ፡ የለችም ፡ አለ።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ይትረጎም፡ዘንተኒ፡እለ፡ኢኮኑ፡ምእመናን፡ እስመ ፡ ኢየአምሩ ፡ እሙንቱ ፡ ፍኖተ ፡ መድኃኒት፡ወኢየሐውሩ፡ኀበ፡ፍኖት፡እንተ፡ ታበጽሖሙ ፡ ኀበ ፡ መለኮት ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ ዘተወልዱ፡እምብርሃን።

፶፰፤ ወንሕነኒ ፡ ንስአሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ያብርህ ፡ ልቡናቲነ ፡ ከመ ፡ ንሑር ፡ በፍኖቱ ፡ ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወትረ ፡ እስከ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዘሚልክያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡ ትኩን፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ምዕ፡፩፡፱–፲፬።

፱፤ ወይእዜኒ ፡ ተጋነዩ ፡ ለገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ። ወሰአልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ፡ በእዴክሙ ፡ ተገብረ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ወትሬእዩ ፡ ለእመ ፡ አደሉ ፡ ለገጽክሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ።

፲፤ እስመ፡በእንቲአክሙ፡ተዐፅወ፡ኆኅት፡ወኢታንድዱ፡ መሥዋዕትየ ፡ በከንቱ ፡ ወኢይፈቅድ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ፡ ወኢይትሜጠ ፡ ለክሙ ፡ መሥዋዕተ፡እምእዴክሙ።

፲፩፤ እስመ ፡ እምሥራቀ ፡ ፀሐይ ፡ እስከ ፡ ዐረብ ፡ ይሴባሕ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ ወእምኵሉ ፡ በሐውርት፡ያመጽኡ፡ዕጣነ፡ለስምየ፡ቅዱስ፡ ወመሥዋዕተ፡ንጹሐ፡እስመ፡ዐቢይ፡ስምየ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ።

፲፪፤ አንትሙሰ፡ታረኵስዎ፡ለመሥዋዕተ፡እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ትብሉ ፡ ማእደ ፡ እግዚአብሔር፡ነውር፡ወእክሉሂ፡ዘውስቴቱ፡ምኑን፡ ውእቱ።

፲፫፤ ወትብሉ ፡ ዝንቱኒ ፡ እምእኩይ ፡ ሕማም ፡ ውእቱ ፡ ወነፋሕክምዎ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ እስመ ፡ ታበውዑ ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ይህንንም ፡ እንዲህ ፡ ይተረጉማል ፤ አማኞች ፡ ያልሆኑ ፡ እነርሱ ፡ የድኅነትን ፡ መንገድ ፡ አያ ውቁምና ፤ ወደ ፡ ጌታ ፡ የምታደርሳቸውንም ፡ ጎዳና ፡ አይሄዱባትምና ፤ ከብርሃን ፡ የተወለዱ ፡ አይደሉምና።

፶፰፤ እኛም፡ልቡናችንን፡ብሩህ፡አድርጎልን፡በሕጉ፡ ጸንተን፡እንኖር፡ዘንድ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን ፡እንለምነው ፤ ለእርሱም፡እስከ፡ዘላለም፡ ዘወትር፡ምስጋና፡ይገባዋል፡አሜን።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ለዘላለሙ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ሚልክያስ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፩፡፱–፲፬።

፱፤ አሁንም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ እጅ ፡ (በእናንተ ፡ ቃል) ፡ ተደርጓልና ፤ ዛሬም ፡ የፈጠረያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገጸ ፡ ረድኤቱን ፡ ለማግኘት ፡ እየተለማመጣችሁ ፡ እግዚአብሔርን ለምኑት ፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊታችሁ ፡ አደላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታያላችሁ፡አለ።

፲፤ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ የሰማይ ፡ ደጅ ፡ ተዘግቷልና፡መሥዋዕቴን፡በከንቱ፡አታንድዱት፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሥዋዕቱንም ፡ ከእጃችሁ ፡ ወድጄ ፡ አልቀበለውም ፡ አለ።

፲፩፤ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መግቢያ፡ድረስ፡በአሕዛብ፡ዘንድ፡ስሜ፡ይመሰገናልና ፤ በአህዛብ ፡ ዘንድም ፡ ስሜ ፡ ገናና ፡ ነውና፡ከሀገሩ፡ሁሉ፡ለከበረ፡ስሜ፡ዕጣንን፡ ያመጣሉ ፤ ንጹሕ፡መስዋዕትንም፡ያቀርባሉ፡ ይላል፡ሁሉን፡የሚገዛ፡እግዚአብሔር።

፲፪፤ እናንተስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ የተነቀፈ ፡ ነው ፤ በውስጡም ፡ የተሠራው ፡ እኽሉ፡የተናቀ፡ነው፡ብላችኋልና፡የእግዚአብሔርን፡መሥዋዕት፡አረከሳችሁት።

፲፫፤ ይኸውም፡ከክፉ፡መከራ፡(ከድርቅ)፡የተገኘ፡ ነው፡ ትላላችሁ ፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እፍ ፡ አልሁት ፡ አለ ፤ (ረድኤት ፡

...ርብከሙ ፡ ሐንካሰ ፡ ወድውየ ፡ ውስተ ፡
...ምዋዕየ ፡ ወእመሂ ፡ አምጻእክሙ ፡
...ምዋዕተ ፡ ኢይትሜጠዎ ፡ እምእ
...ዴክሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡
...ይመልክ።

...ርጉመ ፡ ለይኩን ፡ ኵሉ ፡ ዘቦ ፡ ውስተ ፡
...መራዕይሁ ፡ ተባዕት ፡ ዘቦ ፡ ብፅዓት ፡ ወእንዘ ፡
...ይትከሃሎ ፡ ዘይሠውዕ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
...ዘቦ ፡ ነውር ፡ እስመ ፡ ዐቢይ ፡ ንጉሥ ፡ አነ ፡
...ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡
...ወይሰማዕ ፡ ስምየ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡
...አሕዛብ።

ምዕ፡፪፡፩–፱።

...ወይእዜኒ፡ዛቲ፡ትእዛዝ፡ለክሙ፡ለካህናት።

...ለእመ ፡ ኢሰማዕክሙ ፡ ወኢቦአ ፡ ውስተ ፡
...ልብክሙ ፡ ከመ ፡ ተሀቡ ፡ አኰቴተ ፡ ለስምየ ፡
...ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡
...ወእፌኑ ፡ ላዕሌክሙ ፡ መርገመ ፡ ወእረግማ ፡
...ለበረከትክሙ ፡ ወእመይጣ ፡ ወኢትሄሉ ፡
...እንከ፡ ውስቴትክሙ ፡ እስመ ፡ ኢተኀልይዋ ፡
...በልብክሙ።

...ናሁ ፡ አነ ፡ እመይጥ ፡ ዘባነክሙ ፡ ወእዘሩ ፡
...ኀፍረተ ፡ ውስተ ፡ ገጽክሙ ፡ ወአኀሥር ፡
...ወእሥዕር ፡ በዐላቲክሙ ፡ ወእነሥእክሙ ፡
...ኅቡረ።

...ወተአምሩ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ፈነውኩ ፡ ለክሙ ፡
...ዛንተ ፡ ትእዛዘ ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ ሥርዐትየ ፡ ኀበ ፡
...ሌዋውያን ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡
...ይመልክ።

...ዘተወክፈ፡ነቢየ፡በል።

## ክፍል፡፪።
## ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፹፰፡፰–፲።

...ይቤ፡ዝንቱ፡ቅዱስ፡አባ፡ያዕቆብ፡ዘሥሩግ፡
...በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ድርሳኑ ፡ ዘዘከርነ ፡

 

ነሣሁት)፡የቀማችሁትን፡በሽተኛውንና፡አን
ካሳውን ፡ ወደ ፡ መሠዊያዬ ፡ ታገባላችሁና ፡
ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ያለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ብታመጡ ፡ ወድጄ ፡
ከእጃችሁ፡አልቀበለውም፡አለ።

፲፬፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ገናና ፡
ንጉሥ ፡ ነኝ፤ ስሜም ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ፡
ይሰማል ፡ ብኋልና ፤ ከመንጋው ፡ ጠቦት ፡
ያለውና ፡ ስእለትም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ደኅና ፡ መሥዋዕት ፡ መሠዋት ፡
ሲቻለው ፡ ነውር ፡ ያለውን ፡ የሚሠዋ ፡ ሰው ፡
ርጉም፡ይሁን፡አለ።

ምዕ፡፪፡፩–፱።

፩፤ አሁንም፡ይህች፡ትእዛዝ፡ለናንተ፡ለካህናት፡ናት።

፪፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለስሜ ፡
ምስጋና፡ታቀርቡ፡ዘንድ፡የነገርኋችሁን፡ካልሰ
ማችሁኝ፡ነገሬንም፡ወደ፡ልቡናችሁ፡ካልገባ፡
መርገምን ፡ በናንተ ፡ አመጣለሁ ፤ በረከታች
ሁንም ፡ አጠፋታለሁ ፤ ከእናንተም ፡ እመልሳ
ታለሁ፤ይህችን፡በልቡናችሁ፡አታስቧትምና፡
እንግዲህ፡ወዲህ፡በእናንተ፡ዘንድ፡አትኖርም።

፫፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ ጀርባችሁን ፡ እመልሳለሁ ፤ ፊታች
ሁንም ፡ አሳፍረዋለሁ ፤ በዐሎቻችሁንም ፡
ፈጽሜ፡ አጠፋችዋለሁ ፤ ሁላችሁንም ፡
አንድነት፡እወስዳችኋለሁ፤(አስማርካችኋለሁ)።

፬፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥርዓቴ ፡
በሌዋውያን ፡ ጸንቶ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡
ትእዛዝ ፡ ያመጣሁባችሁ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንኩ ፡
ታውቃላችሁ፡አለ።
በነቢይ፡ስም፡በል

## ክፍል፡፪።
## የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፹፰፡፰–፲።

፰፤ በተናገርነው ፡ በዚህ ፡ ድርሳኑ ፡ የሥሩግ ፡ ኤጲ.
ስቆጶስ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

በመንክር ፡ ትሕትና ፡ ወረደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ቃል ፡ እንከሩ ፡ ሐራ ፡ ልዑላን ፡
እለ ፡ ኢያስተርእዩ ፡ ርዕዱ ፡ ላዕካኒሁ ፡
መላእክት ፡ በመካኑ ፡ ልዑል ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡
እንዘ ፡ ይትለአክ ፡ ለአርድእት ፡ ደንገፁ ፡
ብርሃናት ፡ እመ ፡ ነጸሩ ፡ ትሕትናሁ ፡ ለእሳት ፡
ግሩም ፡ ከመ ፡ ያርትዕ ፡ አዕጋረ ፡ አሕዛብ ፡
በፍቅረ፡ትሕትና።
፪፡ አንከሩ ፡ ጥቀ ፡ ወተደሙ ፡ አግብርተ ፡
አቡሁ ፡ እምነ ፡ ወልድ ፡ ዘወረደ ፡ ይኩን ፡
ገብረ ፡ ወበመለኮቱስ ፡ እንበለ ፡ ሕማም ፡
እንከሩ ፡ ሐራ ፡ እምነ፡ መክፈ ፡ ለንጽ ፡
ዘቅኑት ፡ በሐቌሁ ፡ ዘሀሎ ፡ ስሙ ፡ እም
ቅድመ ፡ ፀሐይ ፡ ወእምቅድመ ፡ ወርኅ ፡ ኮነ ፡
ገብረ።

፫፡ ሱራፌል ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ሕያው ፡ ወኢይሬእዩ ፡ መካኖ ፡
ወእግዚአ ፡ ሱራፌል ፡ ቅኑት ፡ ሐቌሁ ፡
በመክፈ ፡ ለንጽ ፡ በድራር ፡ እሳት ፡ ዘኢይት
ረአይ፡በፍርሀት፡ከመ፡ኢያውዒ፡ወውእቱ፡
ኀበ ፡ አርድእት ፡ ከዊኖ ፡ ላእከ ፡ ከመ ፡
ያመክሮሙ ፡ ሦጠ ፡ ማየ ፡ በንብቲራ ፡ ዘበት
ሕትና፡ወፀውዖ፡ለጴጥሮስ፡ሊቀ፡አርድእት፡
ይኅፅብ፡እገሪሁ።

ምዕ፡፻፰፡፩፡፮–፱።

፬፡ ዓዲ ፡ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአባ ፡
ፊላታዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡
ዘፈነዎ፡ኀበ፡አባ፡አትናቴዎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ዘአንጾኪያ፡አውሥአተ፡መልእክቱ፡ኀቤሁ።
ነአምን፡በአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
ሥላሴ፡ዕሩያን፡በመለኮት፡ወአሐቲ፡ህላዌ፡
ወአሐቲ፡ መንግሥት፡ ወአሐቲ ፡ ሥምረት ፡
ወአሐዱ፡ፈቃድ።
፭፡ ወዓዲ፡ንትአመን፡በወልደ፡እግዚአብሔር፡
ዋሕድ ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡
ኵሉ ፡ መዋዕል ፡ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡
አምላክ ፡ ጽድቅ ፡ ዘእምአምላክ ፡ ጽድቅ ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

አለ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሚያስደንቅ፡
ትሕትና ፡ ወረደ ፤ ሰው ፡ ሆነ ፤ የማይታዩ፡
ረቂቃን ፡ መላእክት ፡ አደነቁ ፤ በልዑል፡
ዙፋኑ፡ ሳለ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሲያገለግል፡
ባዩት ፡ ጊዜ ፡ አገልጋዮች ፡ መላእክት ፡ ደነገጡ፤
ትሕትና ፡ ባለው ፡ ፍቅር ፡ የአሕዛብን ፡ እግረ፡
ልቡና ፡ ያቀና ፡ ዘንድ ፡ የግሩም ፡ እሳት ፡ ትሕት
ናውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃናት ፡ ደነገጡ።
፪፡ አገልጋይ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም፡
ከመጣ ፡ ከወልድ ፡ የተነሣ ፡ የአባቱ ፡ አገል
ጋዮች ፡ መላእክት ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፤
በመለኮቱ፡ ግን ፡ መከራ ፡ (ማገልገል) ፡
የለበትም ፤ በወገቡም ፡ ከታጠቀው ፡ የተነሣ፡
(ማድረቂያ ፡ ፎጣ) ፡ አይተው ፡ መላእክት፡
አደነቁ ፤ ስሙ ፡ ከፀሐይና ፡ ከጨረቃ ፡ በፊት፡
የነበረ፡እርሱ፡አገልጋይ፡ሆነ።
፫፡ ሕያው ፡ ጌታን ፡ ሱራፌል ፡ ያመሰግኑታል፤
ቦታውንም ፡ ግን ፡ አያውቁም ፤ የሱራፌል፡
ጌታ ፡ እርሱ ፡ በራት ፡ ጊዜ ፡ ወገቡን ፡ ዘርፍ፡
ያለው ፡ ዝናር ፡ ታጠቀ ፤ እንዳያቃጥል፡
በመፍራት ፡ የማይታይ ፡ እሳት ፡ ነው ፤ እሱም፡
ለሐዋርያት ፡ አገልጋይ ፡ ሁኖ ፡ ይመክራቸው፡
(አብነት) ፡ ይሆናቸው ፡ ዘንድ ፡ የትሕትና፡
ሥራን ፡ የሚሠራበትን ፡ ውኃ ፡ በኮስኩስት፡
ቀዳ ፤ የደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አለቃ ፡ ጴጥሮ
ስንም፡ጠርቶ፡እግርህን፡ልጠብህ፡አለው።

ምዕ፡፻፰፡፩፡፮–፱።

፬፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡
ፊላታዎስ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡
ወደ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስ ፡ በላከው ፡ ሲኖዶሳዊ፡
የመልእክት ፡ መልስ ፡ በመለኮት ፡ የሚተ
ካከሉ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ መንግሥት፡
አንድ ፡ አሳብ ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ በሆኑ ፡ በሦስቱ፡
አካላት ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ፡
እናምናለን። (ቁጥሩአያለፈነው።)
፭፡ ዳግመኛም ፡ ከዘመን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ፡
ከአብ፡ በተወለደ ፡ ከብርሃን ፡ በተገኘ ፡ ብርሃን፡
ከባሕርይ ፡ አምላክ ፡ በተገኘ ፡ የባሕርይ ፡
አምላክ ፡ የአብ ፡ የአካሉ ፡ የመልኩ ፡
መታወቂያ ፡ በሚሆን ፡ ተቀዳሚ ፡

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ዘአ፦መለከሁ፡ወእካሉ፡ለአብ።
ወዘ፡ፈቀደ ፡ ይምሀር ፡ ፍጥረቶ ፡ ወያድ
ኅኖሙ፡እምነ፡መርገም፡ዘኀደረ፡ላዕሌሆሙ፡
ዘእንተ፡ዕልወተ፡አቡሆሙ፡አዳም።
እኖነ ፡ ሰማያተ ፡ ወወረደ ፡ እንዘ ፡ ኢየ
ዉቅ ፡ እመንበረ ፡ መለኮቱ ፡ ወኀ
ደረ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ድንግል ፡
ማርያም፡

ወተሰብአ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእምኔሃ ፡
ወእምዘርዑ፡አባላ፡ለንጽሕት፡ወድንግልት።

ወረሰዮ ፡ ለሥጋ ፡ ይትዋሐድ ፡ ምስሌሁ ፡
በአሐዱ ፡ አካል ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡
ወለባዊት፡በከመ፡ይቤ፡ክቡር፡አትናቴዎስ፡
ሐዋርያዊ፤
ወለዝንቱሰ፡ሥጋ፡አምላክ፡ቃል፡ቦቱ፡ነፍስ፡
ነባቢት፡ወለባዊት፤
ወተፀገሠ ፡ ለተፀንሶ ፡ ተስዐቱ ፡ አውራኀ ፤
ወወፅአ፡እምኔሃ፡ብእሲ፡ፍጹም፡ዘበአማን፡
አሐዱ፡አካል፡ወአሐዱ፡ገጽ።
በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወኢይት
ሐተት፡ኮነ፡ዝንቱ፡ልደት።
ወኢይክል ፡ ልቡና ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡
የአምር ፡ ልደቶ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ፡
ወባሕቱ ፡ አእምሮሰ ፡ ንኅድግ ፡ ሎቱ ፡
ለባሕቲቱ ። ወጠበወ ፡ ሀሊበ ፡ ወልህቀ ፡
በበሕቅ፡ከመ፡ሕፃናት፡ወተመሰለነ፡በኵሉ፡
ግብር፡ዘእንበለ፡ኃጢአት፡ባሕቲታ ። ወእም
ድኅረ፡ትስብእቱ ፡ ህልው ፡ ውእቱ ፡ በተዋ
ሕዶተ፡አሐዱ፡ህላዌ፡ወኢወሰከ፡በኍልቈ፡
ሥላሴ፡ምንተኒ፡ፍድፋዴ፡ወተውሳከ።
ወውእቱ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ዕሩይ ፡
ምስለ፡አብ፡በመለኮቱ፡ወይትዔረየነ፡ለነ፡
በትስብእቱ ፡ ውእቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ወውእቱ ፡
ምድራዊ።
ያስተርኢ፡ወኢያስተርኢ።
ይትገሠሥ፡ወኢይትገሠሥ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ተከታይ፡በሌለው፡በእግዚአሔር፡ልጅ፡እናምናለን፤
ፍጥረቶቹን፡ይቅር፡ብሎ፡በአባታቸው፡በአዳም፡
ትእዛዝ፡ማፍረስ፡ምክንያት፡ከተፈረደባቸው፡ፍዳ፡
መርገም፡ሊያድናቸው፡በወደደ፡ጊዜ፤
ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡
ከልዑል ፡ ዙፋኑ ፡ ሳይለይ ፡ ወርዶ ፡
በድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕፀን ፡
አደረ፤

በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከእርሷ ፡
ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ከፍጹም ፡ አካልዋ ፡
ነፍስን፡ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡ሆነ።

፯፤ ሥጋንም ፡ የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡
ያለችው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ በመሆን፡ ከእርሱ ፡
ጋር፡ እንዲዋሐድ ፡ አደረገው ፡ የከበረ ፡
ሐዋርያዊ ፡ አትናቴዎስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤
አምላክ ፡ ቃል ፡ ለተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡
የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ አለችው ፤
ተፀንሶ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከአምስት ፡ ቀን ፡ ቈዩ ፤
በዕውነት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ፡ ገጽ ፡
በመሆን፡ፍጹም፡ሰው፡ሆኖ፡ከእሷ፡ተወለደ።

፰፤ ይህ ፡ ልደት ፡ በማይመረመር ፡ በማይነገር ፡
ድንቅ፡ በሚሆን ፡ ምሥጢር ፡ ተደረገ ፤ የሰው ፡
ልቡና ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልደቱን ፡
ሊያውቅ ፡ አይችልም ፤ ዕውቀትን ፡ ስለ ፡ እሱ ፡
ብቻ፡እንተው፡እንጂ፤እንደ፡ሕፃናት፡ወተት፡
ጠብቶ ፡ በየጥቂቱ ፡ አደገ ፤ ከኀጢአት ፡ ብቻ ፡
በቀር ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ፤ ሰው ፡
ከሆነም፡በኋላ፡አንድ፡አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡
ሆኖ ፡ በተዋሐደው ፡ ተዋሕዶ ፡ ጸንቶ ፡ ኖረ ፤
በሦስት ፡ አካላት ፡ የአካል ፡ አራተኛ ፡
የባሕርይ፡ሁለተኛ፡አልጨመረም።

፱፤ በእውነት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የሆነ ፡ እሱ ፡
ነው ፤ በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤
ሰው ፡ በመሆኑም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤
እርሱ፡ሰማያዊ፡ነው፡ምድራዊም፡ነው።
ይታያል፤አይታይምም፤
ይዳሠሣል፡አይዳሠሥምም።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ቅሩብ፡ውእቱ፡ወውእቱ፡ርሑቅ።
ይትረከብ፡ወኢይትረከብ።

የሐምም፡ወኢየሐምም።
ወባሕቱ፡ሐመ፡በሥጋ፡ወኢሐማሚ፡ውእቱ፡
በህላዌ ፡ መለኮቱ ። በረከቶሙ ፡ ለእሉ ፡
መምህራን፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ተግሣጽ፡ዘአቡነ፡ቅዱስ፡ወብፁዕ፡ዮሐንስ፡
አፈ ፡ ወርቅ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ እሬኢ ፡ የም ፡ ብዙኃን ፡ እመሀይምናን ፡
ያፈጥኑ፡ይንሥኡ፡እምሥጢር፡መፍርሀት፡
ወመደንግፅት።

፪፡ አነ፡እሜህረክሙ፡በቃልየ፡ከመ፡ይኩን፡
ለክሙ፡ረባሐ፡እምክልኤቱ፡ገጽ።

፫፡ ሑሩ ፡ በፍርሀት ፡ ወበረዓድ ፡ ወበድንጋጼ ፡
ከመ፡ ትርከቡ ፡ ሠናየ ፡ በሱታፌ ፡ ዝንቱ ፡
ምሥጢር፡ቅዱስ፡ወንጹሕ።

፬፡ አ ፡ ፍቁራንየ ፡ እግዚእ ፡ ገብአ ፡ ኀበ ፡
አይሁድ ፡ እምኀበ ፡ ይሁዳ ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡
ሶበ ፡ ሰማዕከ ፡ ከመ ፡ ገብአ ፡ እግዚእ ፡
ወመጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ለሞት፡ ኢታሕሥም ፡
ገጸከ ። አ ፡ ፍቁር ፡ አላ ፡ አሕሥምኒ ፡
ወብኪ ፡ ብዙኀ ፡ ጥቀ ። አኮ ፡ ላዕለ ፡ ዘገብአ ፡
አላ ፡ ላዕለ ፡ ዘአግብአ ፡ እንበይነ፡ ይሁዳ ፡
እስመ ፡ ዘገብአሰ ፡ ነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ፡
ዘበሰማያት።

፭፡ ውእቱኬ ፡ ንጉሥ ፡ ዘበአማን ፡ ዘኢየኃልቅ ፡
መንግሥቱ፡ወንጉሥ፡ውእቱ፡ላዕለ፡ኵሉ።

፮፡ ወዘአግብአሰ ፡ ወረደ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቀ ፡
ሲኦል።ውእቱ፡እስከ፡ዮም፡ውስተ፡ገሃነም፡
ጽኑሕ፡ሎቱ፡ዘይበዝኅ፡ኩነኔ።

፯፡ ጕጕኡ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወብክዩ ፡ ብዙኀ ፡
እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐዘነ ፡ በእንቲአሁ ።
እስመ ፡ ናሁ ፡ መሐረነ ፡ ይደልወነ ፡ ንሕነኒ ፡
ከመ፡ንሕዝን፡በእንቲአሁ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እርሱ፡ቅርብ፡ነው፤ሩቅም፡ነው።
ይገኛል ፡ አይገኝም ፤ ይመረመራል ፤ አይመረ
መርም።
ይታመማል፤አይታመምም።

በሥጋ ፡ ታመመ ፡ እንጂ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ
መታመም ፡ የለበትም ፤ የእነዚህም ፡
መምህራን ፡ በረከታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑርና፡
ንጹህ፡ክቡር፡የተመሰገነ፡የቅዱስ፡ዮሐንስ፡
አፈ፡ወርቅ፡ተግሣፅ፡ምክር፡ይህ፡ነው።

፩፡ ከምዕመናን ፡ ወገን ፡ ብዙዎቹ ፡ ከምታስፈራ፡
ከምታስደነግጥ፡ከከበረች፡ምሥጢር፡ከሥጋው፡
ከደሙ፡ይቀበሉ፡ዘንድ፡ሲፋጠኑ፡ዛሬ፡አያለሁ።

፪፡ ከሁለት ፡ ወገን ፡ ረብሕ ፡ ጥቅም ፡ ለእናንተ፡
ይሆን፡ዘንድ፡እኔ፡በቃሌ፡አስተምራችኋለሁ።

፫፡ ንጹሕ፡ክቡር፡ከሆነ፡ከሥጋው፡ከደሙ፡በመቀበ
ላችሁ፡መልካም፡ነገር፡ታገኙ፡ዘንድ፡በመፍራት
በመንቀጥቀጥ፡በመደንገፅም፡ሁናችሁ፡ሂዱ።

፬፡ ወዳጆቼ፡ሆይ፡በይሁዳ፡በኩል፡ጌታ፡ተላልፎ
ለአይሁድ፡ተሰጠ፤ነገር፡ግን፡ጌታ፡በአይሁድ፡
እጅ ፡ ነፍሱን ፡ ለሞት ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በሰማህ፡
ጊዜ፡ፊትህን፡አትቋጥር፤አታክፋ፡እንጅ፡ግን፡
ወዳጅ፡ሆይ፡እጅግ፡እዘን፤በብዙም፡አልቅስ፡
እንጂ ፤ ተላልፎ ፡ በተሰጠው ፡ አይደለም፡
አሳልፎ፡ስለ፡ሰጠው፡ስለ፡ይሁዳ፡ነው፡እንጂ፡
ተላልፎ ፡ የተሰጠውስ ፡ በሰማያት ፡ በአባቱ፡
ቀኝ፡(ዕሪና)፡ተቀምጧልና።

፭፡ እርሱማ ፡ መንግሥቱ ፡ የማያልፍ ፡ የባሕርይ፡
ንጉሥ፡በሁሉም፡ላይ፡ነግሦ፡የሚኖር፡ነው።

፮፡ አሳልፎ፡የሰጠው፡ግን፡ወደ፡ሲኦል፡አዘቅት፡
ወረደ፤እስከ፡ዛሬም፡በገሃነም፡ውስጥ፡ብዙ፡
የሆነ፡ሥቃይ፡ተጠብቆለት፡ይኖራል።

፯፡ ስለዚህ ፡ ቾኹሉ ፤ ብዙም ፡ አልቅሱ ፤ ስለ፡
እርሱ፡ ጌታ ፡ አዝኖአልና ፤ እነሆ ፡ አስተምሮ
ናልና ፡ እኛም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ እናዝን ፡ ዘንድ፡
ይገባናል።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

...ኡ፡ ባዕለ ፡ ዘሐመ ፡ አላ ፡ ለዘገብረ ፡
...ኡየ፡ እስመ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይብክዩ ፡
...ሁ ፡ በዙሉ ፡ መካን ፡ እስመ ፡ ዘይ
...ር ፡ ዐመፃ ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡
ዘሐመ፡እኩይ።

...ንተ፡ ሐማማቲሁ ፡ **ለክርስቶስ** ፡ ንበውእ ፡
...ት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወእመሰ ፡
...ብረ፡እኩየ፡በጌጋዩ፡ገብአ፡ለሊሁ፡ውስተ፡
...ሃነም፡ወዙነኔ።እስመ፡ይቤ፡ብፁዓን፡ነዳያን፡
...ለ፡ይሰደዱ፡በእንተ፡ጽድቅ፡እስመ፡ሎሙ፡
ይእቲ፡መንግሥተ፡ሰማያት።

ወአመሰ፡ዘገብረ፡እኩየ፡እስመ፡ሎቱ፡ኵነኔ፡
ወገዐር።

ወዝንቱ፡ተግሣጽ፡ዘአቡነ፡አባ፡ዮሐንስ፡
አፈ፡ወርቅ፡ዘተናገረ፡ምስሌነ፡ዘንተ፡
ተግሣጸ፡በእንተ፡መድኃኒተ፡ነፍስነ።
**ወስብሐት፡ለሥሉስ፡ቅዱስ፡አብ፡ወወልድ፡**
**ወመንፈስ፡ቅዱስ፡** ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡
ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

**ተአምሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡**
**ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡**
አምላክ ፡ ዘከመ ፡ አስተርአየቶ ፡ ለአባ ፡
ሰረባሞን ፡ ሰማዕት ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዘ ፡
ሀሎ ፡ ንዑስ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይጠመቅ ፡
ዓዲ ፡ መርሐቶ ፡ ኀበ ፡ ጥምቀተ ፡ ክር
ስትና ፡ ወአሚነ ፡ **ወልዳ ፡ ክርስቶስ ፤**
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሃሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ኮነ፡እምዘመዱ፡ለእስጢ
ፋኖስ፡እምነገደ፡ሌዊ፡እምኢየሩሳሌም።
ወኮነ፡ስመ፡አቡሁ፡አብርሃም፡ወልደ፡ሌዊ፡
ወልደ፡ዮሴፍ፡እኁሁ፡ለስምዖን፡እኁሃ፡
ለእሙ፡እስጢፋኖስ።
ወበጊዜ፡ልደቱ፡ሰመይዎ፡በስመ፡አቡሁ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፰፤ መከራ ፡ ለተቀበለው ፡ አይደለም ፤ ክፉ ፡ ለሠራው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ሊያዝ ኑለት ፡ ይገባልና ፤ ዓመፅ ፡ ተንኰል ፡ የሚያ ደርግ፡ነው፡እንጅ፡ክፉ፤መከራ፡የሚቀበል፡ ክፉ፡አይባልማና።

፳፱፤ **በክርስቶስ** ፡ መከራ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንገባለን ፤ ክፉ ፡ የሠራ ፡ ቢኖር ፡ በበደሉ ፡ ወደ ፡ ገሃነምና ፡ ወደ ፡ ሥቃይ ፡ ገባ ፤ ስለ ፡ ዕውነት ፡ የሚሰደዱ ፡ ድኆች ፡ የተመ ሰገኑ፡ናቸው፡ብሏልና፤መንግሥተ፡ሰማያት፡ የእርሳቸው፡ናትና።

፴፤ ክፉ ፡ የሠራ ፡ ቢኖር ፡ ሥቃይና ፡ ጨኸት ፡ ለእርሱ፡ይገባዋልና።

፴፩፤ ይህ ፡ ምክርና ፡ እዝናት ፡ ስለ ፡ ነፍሳችን ፡ ድኅነት ፡ አባታችን ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ የተናገረው ፡ ነው ፤ **ልዩ ፡ ሦስት ፡ ለሆኑ ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ክብር** ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፤ ዛሬም ፡ ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ በእውነት ፡ ይደርብንና ፡ **በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡** ታናሽ፡ክርስ ቲያን ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ሰማዕት ፡ ለሆነው፡ለአባ፡ሰረባሞን፡እንደ፡ተገለጸለችለት፡ **ልጅዋ፡** ዳግመኛም፡ወደ፡ክርስትና፡ጥምቀትና፡ **ክርስቶስን** ፡ ወደ ፡ ማመን ፡ እንደ ፡ መራችው ፡ የሚናገር፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ ይህም፡ቅዱስ፡ከኢየሩሳሌም፡ከሌዊ፡ነገድ፡ ከእስጢፋኖስ፡ወገን፡ነው።

፪፤ የአባቱም፡ስም፡የእስጢፋኖስ፡የእናቱ፡ወንድም፡ ስምዖን፡የስምዖን፡ወንድም፡የዮሴፍ፡ልጅ፡ሌዊ፡ የሌዊ፡ልጅ፡አባቱ፡አብርሃም፡ይባል፡ነበር።

፫፤ በተወለደም፡ጊዜ፡በአባቱ፡ስም፡ጠሩት።

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። ... ክር

፱፡ ወሶበ፡ሞተ፡አቡሁ፡ፈተወ፡ከመ፡ይኩን፡ክር
ስቲያናዊ።
፲፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ወአዘዞ፡ከመ፡ይሑር፡ኀበ፡ኤጲስ
ቆጶስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወሖረ ፡ ኀቤሁ ።
ወከሠተ፡ሎቱ፡ምሥጢረ፡ትስብእቱ፡ለክር
ስቶስ፡አምላክ።
፲፩፡ ወባሕቱ ፡ ኢተጋበለ ፡ ከመ ፡ ያጥምቆ ፡
ጥምቀተ፡ ክርስትና ፡ በሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
በእንተ፡ፍርሀቶሙ፡ለአይሁድ፡አዝማዲሁ።
፲፪፡ ወኮነ፡ኤጲስ፡ቆጶስ፡ይኄሊ፡ምንተ፡ይግበር፡
በእንቲአሁ።
፲፫፡ ወአስተርአየት፡ሎቱ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡
ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡
አምላክ፡ቃል፡ወአዘዘቶ፡ከመ፡ይሑር፡ሀገረ፡
እስክንድርያ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ቴዎናስ ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት።
፲፬፡ ርእዩ፡ሕዝበ፡ክርስቲያን፡ምእመናን፡ዘከመ፡
አስተርአዮቶ፡ለአባ፡ሰረባሞን፡እንዘ፡ሀሎ፡
ንዑሰ፡ክርስቲያን፤
ነገረ ፡ ኂሩታሰ ፡ ኢይትፌጸም ፡ በብዝኀ ፡
አዝማን።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
፲፭፡ ወእምዝ ፡ በድራረ ፡ ዕለተ ፡ ፋሲካ ፡ ቦአ ፡
እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡
አርዳኢሁ ፡ ውስተ ፡ እንታክቲ ፡ ጽርሕ ፡
ጽርሐ፡ኒቆዲሞስ፡ይእቲ።
፲፮፡ ወተጋብኡ ፡ ዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አር
ዳኢሁ ፡ ወነበሩ ፡ ዐውዶ ፡ ወአቅረቡ ፡
ማእደ ፡ ወዲቤሁ ፡ ኅብስተ ፡ ናእት ፡
ወበግዐ፡ጥቡስ፡ወዓሣ፡ዘተቀልወ።ወነበሩ፡
ምስሌሁ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፱፡ አባቱም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሆን፡
ዘንድ፡ወደደ።
፲፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ተገለጸ፡
ወደ፡ኤጲስቆጶሱ፡ወደ፡አባ፡ዮሐንስ፡ይሔድ፡
ዘንድ ፡ አዘዘው ፤ ወደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስም፡ሔደ፡
እርሱም ፡ የፈጣሪ ፡ ክርስቶስ ፡ የሥጋዌውን፡
ምሥጢር፡ገልጾ፡አስተማረው፡
፲፩፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዘመዶቹ ፡ አይሁድን ፡ በመ
ፍራት፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሀገር ፡ የክርስትና፡
ጥምቀትን፡ያጠምቀው፡ዘንድ፡አልደፈረም፡
፲፪፡ ኤጲስቆጶሱም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ምን ፡ እን
ሚሠራ፡ያስብ፡ነበር፤
፲፫፡ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡
አካላዊ ፡ ቃል ፡ የሆነ ፡ አምላክን ፡ የወለደች፡
ክብርት፡እመቤታችን፡ተገልጻ፡ወደ፡እስክን
ድርያ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ወደ ፡ አባ፡
ቴዎናስ፡ይሔድ፡ዘንድ፡አዘዘችው።
፲፬፡ የክርስቲያን፡ወገን፡ምእመናን፡ታናሽ፡ክርስ
ቲያን፡ሆኖ፡ሳለ፡ለአባ፡ሰረባሞን፡እንደ፡ተገ
ለጸችለት፡እዩ።
ነገር፡ግን፡የቸርነቷ፡ነገር፡በብዙ፡ዘመናት፡
ተነግሮ፡አይፈጸምም።
ልመናዋና፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፤አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል፡

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡በእኛ፡ላይ፡ለዘላለሙ፡
ይደርብንና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።
፲፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በፋሲካው ፡ ዋዜማ ፡ ዕለት፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከደቀ፡
መዛሙርቱ፡ጋር፡የኒቆዲሞስ፡አዳራሽ፡ወደ፡
ሆነችው፡ወደዚያች፡አዳራሽ፡ለራት፡ገባ፡
፲፮፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ተሰብ
ስበው ፡ በዙሪያው ፡ ተቀመጡ ፤ ማእድም፡
አቀረቡ ፤ በማእዱም ፡ ላይ ፡ ያልቦካ ፡ ቂጣ፡
የተጠበሰ ፡ በግና ፡ የተቆላ ፡ ዓሣ ፡ ነበረ፡
በማእዱም፡አብረው፡ከርሱ፡ጋር፡ተቀመጡ፡

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፫ ወሖረ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ ዘንተ ፡ ገብረ ፡ ዘአክበርዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ፡ ጽርሕ ፡ ቀንአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዐቢየ ፡ ቅንአተ።

፬ ወሖረ ፡ ፍጡነ ፡ ኀበ ፡ አይሁድ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ምንተ ፡ ትሁቡኒ ፡ ለእመ ፡ አግባእክዎ፡ ለክሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ መስሐቲ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት።

፭ ወይቤልዎ ፡ ንሁበከ ፡ ሠላሳ ፡ ብሩረ ። ወተሰነዉ ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ የሀብዎ ፡ ዘንተ ፡ ወውእቱኒ ፡ ያግብእ ፡ ሎሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፮ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ምሴተ ፡ ነሥአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ ፡ መክፈ ፡ ለንጽ ፡ ወቀነተ ፡ ቦቱ፡ሐቌሁ፡ወወደየ፡ማየ፡ውስተ፡ንብቲራ፡ ወነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ ወአኀዘ ፡ ይኅፅብ ፡ እገረ፡ አርዳኢሁ ፡ ወይመዝምዝ ፡ በለንጽ ፡ ዘቀነተ።

፯ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ይመጥዎ ፡ ሎቱ ፡ እገሪሁ ፡ ወይቤሎ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ይትለአክ ፡ ለገብሩ።

፰ ወአውሥአ ፡ እግዚእነ ፡ ወይቤሎ ፡ አማን ፡ እብለከ ፡ አ ፡ ስምዖን ፡ ለእመ ፡ ኢኀደገኒ ፡ እኅፅብ ፡ እገሪከ ፡ አልብከ ፡ ክፍል ፡ ምስሌየ ፡ በመንግሥትየ።

፱ ወይቤሎ ፡ ስምዖን ፡ እግዚእየ ፡ እመሰ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ግብሩ ፡ አኮ ፡ እገርየ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘተኀፅበኒ ፡ ዓዲ ፡ እደውየኒ ፡ ወርእስየኒ ፡ ወመጠዎ ፡ ሎቱ ፡ እስከ ፡ ኀፀበ ፡ ኵሎ ፡ ወምሕረቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ይዲ፡ ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፳፱፡፩።

እግዚአብሔር ፡ ይሬእየኒ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየኃ

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፫፤ የአስቆሮቱ ፡ ሰው ፡ ይሁዳም ፡ በቢታኒ ፡ አዳራሽ፡ ውስጥ ፡ ለጌታችን ፡ የተደረገውን ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ ቅናትን ፡ ቀና።

፬፤ ወደ ፡ አይሁድም ፡ ፈጥኖ ፡ ሂዶ ፡ (ሎቱ ፡ ስብሐት፡) ያን ፡ መስሐቲ ፡ ኢየሱስን ፡ ለእናንተ፡ አሳልፌ ፡ብሰጣችሁ ፡ ምን ፡ ትሰጡ ኛላችሁ፡አላቸው።

፭፤ እነርሱም ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ እንሰጥሃለን ፡ አሉት፤ እርሱም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ለእነርሱ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጣቸው ፡ እነሱም ፡ ይህን ፡ ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ሊሰጡት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር፡ተስማሙ።

፮፤ ምሽትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ሽርጥ፡(ግልድም)፡ወስዶ፡በወገቡ፡ ታጠቀ ፤ ውኃም ፡ በኵስኵስት ፡ ጨመረ ፤ በመቀመጫ ፡ ላይም ፡ ተቀምጦ ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እግር ፡ ማጠብ ፡ ጀመረ፤ በታጠቀውም፡ፎጣ፡ማድረቂያ፡ሽርጥ፡(ግልድም)፡ ይወለውል፡ነበር።

፯፤ እግሩንም ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ደረሰ፤እርሱም፡ጌታዬ፡ሆይ፡ጌታ፡ ባርያውን ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡ አለው።

፰፤ ጌታችንም፡ ስምዖን፡ሆይ፡እግርህን፡አጥብህ፡ ዘንድ ፡ ካልተውከኝ ፡ በመንግሥቴ ፡ ውስጥ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደሌለህ ፡ በውእነት፡እነግርሃለሁ፡ብሎ፡መለሰለት።

፱፤ ስምዖንም፡ጌታዬ፡ሆይ፡ነገሩ፡እንዲህ፡ከሆነ፡ የምታጥበኝ ፡ እግሮቼን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ደግሞ ፡ እጆቼንም ፡ ራሴንም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አለው ። እስካጠበውም ፡ ድረስ ፡ እግሩን ፡ ሰጠው ። ይቅርታው ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፡፳፱፡፩።

እግዚአብሔር፡ ይጠብቀኛል፡የሚያሳጣኝም፡

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ጥእኒ ። ውስተ ፡ ብሔር ፡ ሥዑር ፡
ህየ ፡ ያኀድረኒ፡ ውኀበ ፡ ማየ ፡ ዕረፍት ፡
ሐፀነኒ።

### ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፪፡፯-፲፫።

፯፤ ወበጽሐት፡ዕለተ፡መጸለት፡አመ፡ይጠብሑ፡
ፍሥሓ።
፰፤ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ለጴጥሮስ ፡
ወለዮሐንስ ፡ ሑሩ ፡ ወአስተዳልዉ ፡ ለነ ፡
ፍሥሓ፡ዘንበልዕ።
፱፤ ወይቤልዎ ፡ በአይቴ ፡ ትፈቅድ ፡ ናስተዳሉ ፡
ለከ፡ፍሥሓ።
፲፤ ወይቤሎሙ ፡ በዊአክሙ ፡ ሀገረ ፡ ትረክቡ ፡
ብእሴ፡ዘይጸውር፡ጸሕበ፡ማይ፡ወትልውዎ፡
ኪያሁ፡ኀበ፡ቦአ፡ቤት።
፲፩፤ ወበልዎ ፡ ለበዐለ ፡ ውእቱ ፡ ቤት ፡ ይቤለከ ፡
ሊቅ፡ አይቴኑ ፡ ቤት ፡ ኀበ ፡ እበልዕ ፡ ፍሥሓ ፡
ምስለ፡አርዳእየ።
፲፪፤ ወውእቱ ፡ ያርእየክሙ ፡ ጽርሐ ፡ ዐቢየ ፡ ወን
ጹፈ፡ወሥርግወ፡ወበህየ፡አስተዳልዉ፡ለነ።
፲፫፤ ወሐዊሮሙ፡ረከቡ፡በከመ፡ይቤሎሙ፡ወአስ
ተዳለዉ፡ፍሥሓ።

### ድኅረ፡ወንጌል።

በተሰዐቱ ፡ ሰዓት ፡ እምዕለተ ፡ ኀሙስ ፡ዘይት
ነበብ፡ዘየኀብር፡ምስለ፡ትንቢት።

፩፤ ወተለዓለ፡አብርሃም፡ወዐብየ፡በቅድመ፡ እግ
ዚአብሔር፡ፈድፋደ፡እምኵሉ፡ዘመደ፡ዕጓለ፡
እመሕያው፡ወረከበ፡ሞገሰ።
፪፤ ወአስተርአዮ፡ሎቱ፡ወተናገሮ፡እንዘ፡ይብል፡
አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ ዘእነ ፡ አፈቅሮ ፡
አጽምዕ፡ ኀበ ፡ ቃላትየ ፡ ወግበር ፡ ፈቃድየ ፡
ንሥእ ፡ ለወልድከ ፡ ይሥሐቅ ፡ ፍቁር ፡
ወአዕርጎ፡ ሊተ ፡ ቍርባነ ፡ በውስተ ፡ አሐዱ ፡
እምአድባራት።
፫፤ ወተንሥአ፡አብርሃም፡በከመ፡ ቃለ፡እግዚአ
ብሔር ፡ወነሥአ ፡ ለወልዱ ፡ ፍቁር ፡ ወለክ
ልኤቱ ፡ ደቂቁ ፡ እምአግብርቲሁ ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ነገር ፡ የለም ፤ በለመለመ ፡ መስክ ፡ በዚያ፡
ያኖረኛል ፤ ዕረፍት ፡ በአለበት ፡ ውኃም፡
አሳደገኝ፡ይበል።

### የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፪፡፯-፲፫።

፯፤ በጉን ፡ የሚያርዱባት ፡ የቂጣ ፡ በዐል፡
ደረሰች።
፰፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን፡
ሒዱና ፡ የምንበላው ፡ በጉን ፡ አዘጋጁልን፡
አላቸው።
፱፤ በጉን ፡ ወዴት ፡ ልናዘጋጅልህ ፡ ትወዳለህ፡
አሉት።
፲፤ ወደ፡ሀገር፡በገባችሁ፡ጊዜ፡የውኃ፡ማድጋ፡
የተሸከመ ፡ ሰው ፡ ታገኛላችሁና ፡ ወደ፡
ሚገባበት፡ቤት፡ተከተሉት።
፲፩፤ የዚያን ፡ ቤት ፡ ጌታም ፡ መምህር ፡ ከደቀ፡
መዛሙርቴ ጋራ ፡ በጉን ፡ የምበላበት ፡ ቤት፡
ወዴት፡ነው፡ብሎሃል፡በሉት።
፲፪፤ እርሱም፡የተነጠፈ፡ያጌጠ፡ታላቅ፡ቤት፡ያሳ
ያችኋል፤በዚያ፡አዘጋጁልን፡አላቸው።
፲፫፤ ሄደውም ፡ እንዳላቸው ፡ አገኙና ፡ በጉን፡
አዘጋጁ።

### ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

ኀሙስ ፡ ከቀኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ከትንቢቱ፡
ጋር፡የሚስማማ፡ይህ፡ነው።

፩፤ ከሰው ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር፡ፊት፡
አብርሃም ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ባለሟልነ
ትንም፡አገኘ።
፪፤ ጌታም ፡ ለእርሱ ፡ ተገለጸለት ፤ እንዲህ፡
ብሎም፡ ተናገረው ፤ አብርሃም ፡ አብርሃም፡
ሆይ ፡ እኔ ፡ የምሻውን ፡ ወደምነግርህ ፡ ነገር፡
አድምጥ ፤ ተወዳጅ ፡ ልጅህ ፡ ይሥሐቅን፡
ወስደህ ፡ ከተራራዎች ፡ በአንዱ ፡ ላይ፡
መሥዋዕት፡አድርገህ፡አሳርግልኝ፡አለው።
፫፤ አብርሃምም፡ የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ሰምቶ፡
እንደ ፡ አዘዘው ፡ ተወዳጅ ፡ ልጁን ፡ ከአገል
ጋዮቹ ፡ ሁለቱን ፡ አገልጋዮች ፡ ይዞ ፡

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወሖረ፡አድኅነ፡ወሐረ።
ወዘ፡ርእየ፡እምርኁቅ፡ኀበ፡ደብር፡
ገብርሆሙ፡ለአግብርቲሁ፡ወለአድግ፡
ምስሌሆሙ።

፭ ወይቤሎሙ፡አነ፡ወወልድየ፡ነሐውር፡ከመ፡
ናዕርግ፡መሥዋዕተ፡ወንገብእ።

፮ ወአጸሮ፡ዕፀ፡ለወልዱ፡ወመጥባሕት፡
ወነሥአ፡ውስተ፡እዴ፡አብርሃም፡ወዐርጉ፡
ክልኤሆሙ፡ላዕለ፡ደብር፡ቅዱስ፡መካን፡
ዘአመሮ፡እግዚ፡ኵሉ።

፯ ይቤሎ፡ይሥሐቅ፡ለአብርሃም፡አቡሁ፡
እ፡አባ፡ናሁ፡ዕፅ፤አይቴ፡በግዑ፡ይቤ፡
አብርሃም፡እ፡ወልድየ፡እግዚአብሔር፡
ይሬኢ፡በግዖ፡ለጥብሐት፡ውኩፈ፡
ዘያሠምሮ።

፰ ወአስተጋብአ፡አእባነ፡ወነደቀ፡ምሥዋዐ፡
ወአዕረገ፡ወአንደደ፡እሳተ። ወበጊዜሃ፡
አሰረ፡እደ፡ወልዱ፡ወአዕረጎ፡መልዕልተ፡
ዕፅ።

፱ ወይቤሎ፡ይሥሐቅ፡እ፡አባ፡ናሁ፡
ቍርባንከ፡ውኩፍ፡ዘትገብር፡ፍጡነ፡
ግበር።

፲ ወአንሥአ፡እዴሁ፡አብርሃም፡ወነሥአ፡
መጥባሕተ፡ከመ፡ይፈጽም፡ግብሮ። ወናሁ፡
ቃል፡ኮነ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር።

፲፩ ወአንጸረ፡ኀበ፡አብርሃም፡ወይቤሎ፡አኅዝ፡
እዴከ፡ወኢትግበር፡ቦቱ፡እኩየ።

፲፪ ናሁ፡አእመርኩ፡አፍቅሮተከ፡ሊተ፡
በዚኒ፡ይበዝኅ፡ይሥሐቅ፡በዲበ፡
ምድር፡ወበከመ፡ኢመሀኮ፡ለበኵርከ፡
እነ፡እባርከ፡ሎቱ፡ወለዘርዑ፡ኅቡረ፡
ወይከውን፡ከመ፡ከዋክብት፡ወከመ፡ኆፃ፡
ባሕር።

፲፫ ወተመይጠ፡አብርሃም፡ወርእየ፡ኀበ፡በግዕ፡
እሱር፡አቅርንቲሁ፡በዕፀ፡ሳቤቅ፡ወፈትሖ፡
ለይሥሐቅ፡እማእሰር፡ወጠብሖ፡ለበግዕ፡
ህየንቴሁ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። 

አህያውን፡ጭኖ፡ሒደ።

፬፣ ከሩቅ፡ሳለ፡ወደ፡ተራራ፡በተመለከተ፡ጊዜ፡
አገልጋዮቹን፡ከዚያ፡ተዋቸው፤አህያውንም፡
ከእነሱ፡ጋራ፡ትቶ።

፭፣ እኔና፡ልጄ፡መሥዋዕት፡እናሳርግ፡ዘንድ፡ወደ፡
ተራራው፡ሔደን፡እንመለሳለን፡አላቸው።

፮፣ ዕንጨቱንም፡ለልጁ፡አሸከመ፤ሾተልና፡
እሳትም፡በአብርሃም፡እጅ፡ነበር፤ሁለቱም፡
የሁሉ፡ፈጣሪ፡ወደ፡አመለከተው፡ክቡር፡
ቦታ፡ወዳለው፡ተራራ፡ወጡ።

፯፣ ይሥሐቅም፡አባቱ፡አብርሃምን፡አባት፡ሆይ፡
ዕንጨት፡እነሆ፡አለ፤በጉ፡ወዴት፡አለ፡
አለው፤አብርሃምም፡ልጄ፡ሆይ፡ደስ፡የሚያሰ
ኘውንና፡የሚቀበለውን፡የመሥዋዕት፡በግ፡
እግዚአብሔር፡ያያል፡(ያውቃል፡)አለው።

፰፣ ደንጊያዎችንም፡ሰብስቦ፡መሠዊያ፡ሠራ፤
እንጨቱን፡አዘጋጅቶ፡እሳቱን፡አነደደ፤
ወዲያውኑ፡የልጁን፡እጁን፡አስሮ፡በመሠ
ዊያው፡ላይ፡ካለው፡እንጨት፡ላይ፡አወጣው።

፱፣ ይሥሐቅም፡አባት፡ሆይ፡እነሆ፡መሥዋዕትህ፡
የተወደደ፡እግዚአብሔር፡የሚቀበለው፡ነው፤
የምትሠራውን፡ፈጥነህ፡ሥራ፡አለው።

፲፣ አብርሃምም፡ሥራውን፡ይፈጽም፡ዘንድ፡
እጁን፡ዘርግቶ፡ሾተሉን፡ወሰደ፤(አነሣ)፡
እነሆ፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ቃል፡መጣ።

፲፩፣ ወደ፡አብርሃምም፡አመልክቶ፡እጅህን፡ግታ፡
ክፉንም፡አታድርግበት።

፲፪፣ እነሆ፡እኔን፡መውደድህን፡አወቅኹ፤
ይሥሐቅም፡በምድር፡ላይ፡መብዛትን፡
ይበዛል፤ለበኵር፡ልጅህም፡እንዳልራራህ፡
እኔም፡እርሱንና፡ዘሩን፡በአንድነት፡እባርክ
ዋለሁ፤እንደ፡ሰማይ፡ከዋክብትና፡እንደ፡
ባሕር፡አሸዋም፡ይሆናል፡አለው።

፲፫፣ አብርሃምም፡መለስ፡ብሎ፡ቀንዶቹ፡በነጭ፡
አረግ፡ወደ፡ታሰረው፡በግ፡ተመለከተ፤ይሥ
ሐቅንም፡ከማሰሪያው፡ፈትቶ፡በእርሱ፡
ፈንታ፡በጉን፡አረደው።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወእግዚአብሔር፡ ባረከ፡ለአብርሃም፡እስመ፡ረከበ፡ዘያፈቅሮ።
፲፬፡ ወገብአ፡አረጋዊ፡ወነሥአሙ፡ለደቂቁ፡ወለይሥሐቅ፡ወልዱ።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡ መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኀነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፲፰።

### ትእዛዝ።

ወእምድኅሬሁ፡ሥርዐተ፡ኀፅበተ፡እግር፤ ወያንብር፡ዲያቆን፡ክልኤተ፡ንብቲራተ፡ወይደይ፡ማየ፡ውስቴቶን፡ወይምልዖን፡አሐዱ፡ለኀፅበተ፡እግር፡ወአሐዱ፡ለኀፅበተ፡እድ፡ወይበል፡ካህን፡ጸሎተ፡አኰቴት፡እስከ፡ተፍጻሜቱ፡ወያዕርግ፡ዕጣነ፡ወይበል፡ጸሎተ፡ዕጣን፤ በእንተ፡ሰላም፡ወበእንተ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወበእንተ፡ማኅበር።

ወይበሉ፡ሕዝብ፡ስብሐት፡ለአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ወይበሉ፡አቡነ፡ዘበሰማያት፡ወመዝሙረ፡ዘኀምሳ።

ክፍል፡፩።
አሪት፡ዘልደት።

ምዕ፤፲፰፤፩–፳፫።

፩፡ ወአስተርአዮ፡እግዚአብሔር፡ ለአብርሃም፡በኀበ፡ዕፀ፡መምሬ፡እንዘ፡ይነብር፡ኀበ፡ኆኅተ፡ሐይመት፡ቀትረ።
፪፡ ወሶበ፡አልዓለ፡አዕይንቲሁ፡ወነጸረ፡ወናሁ፡ሠለስቱ፡ዕደው፡ይቀውሙ፡መልዕልቴሁ፡ወርእየ፡ወሮጸ፡ለተቀብሎቶሙ፡እምኆኅተ፡ሐይመት፡ወሰገደ፡ውስተ፡ምድር።
፫፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ እመሰ፡ረከብኩ፡ሞገሰ፡በቅድመ፡አዕይንቲከ፡ኢትትዓደዎ፡ለገብርከ።
፬፡ ናምጽእ፡ለክሙ፡ማየ፡ወንኅፅብ፡እገሪክሙ፡ወታጽልሉ፡ታሕተ፡ዕፅ።
፭፡ ወናምጽእ፡ኅብስተ፡ወትብልዑ፡ወእምዝ፡ተሐውሩ፡ኀበ፡ኀለይክሙ፡እምከመ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እግዚአብሔርም፡ አብርሃምን፡ ባረከው፡ የሚወደው፡ሁኖ፡አግኝቶታልና።
፲፬፡ አረጋዊ፡አብርሃምም፡ልጁንና፡አሽከሮችን፡ ይዞ፡ተመለሰ።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ ሰው፡ሁኖ፡መከራ፡ ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፲፰።

### ትእዛዝ።

ከዚህ፡በኋላ፡የእግር፡እጥበት፡ሥርዓት፡ነው፤ ዲያቆን፡ሁለት፡ኵስኵስቶች፡ያቅርብ፤በውስ ጣቸውም፡ውኃ፡ይምላባቸው፤ አንዱ፡ ለእግር፡ አንዱ፡ ለእጅ፡ መታጠቢያ፡ እንዲሆን፤ ካህኑም፡ እስከ፡ መጨረሻው፡ ጸሎተ፡አኰቴት፡ይበል፤ጸሎተ፡ዕጣኑንም፡ ደግሞ፡ዕጣኑን፡ያሳርግ፤ስለ፡ሰላም፡ስለ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ስለ፡ማኅበር፡ይጸልይ።

ሕዝቡም፡ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ ምስጋና፡ ይሁን፤ ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘላለሙ፡አሜን፤ይበሉ።

አቡነ፡ዘበሰማያትም፡ይበሉ፤ኀምሳኛውንም፡ የዳዊትን፡መዝሙር፡ይበሉ።

ክፍል፡፩።
ኦሪት፡ዘፍጥረት።

ምዕ፤፲፰፤፩–፳፫።

፩፡ በቀትር፡ጊዜ፡በድንኳን፡ደጃፍ፡በመምሬ፡ ዛፍ፡ሥር፡ተቀምጦ፡ሳለ፡እግዚአብሔር፡ለአ ብርሃም፡ተገለጸለት።
፪፡ ዓይኑን፡አቅንቶ፡በአየ፡ጊዜ፡እነሆ፡ሦስት፡ ሰዎች፡ በፊቱ፡ ቆመው፡ አየ፤ አይቶም፡ ከድኳኑ፡በር፡እነርሱን፡ሊቀበላቸው፡ሮጠ፡ በምድርም፡ላይ፡ሰገደ።
፫፡ አቤቱ፡ በፊትህስ፡ባለሟልነትን፡አግኝቼ፡ እንደ፡ሆነ፡ባሪያህን፡አትለፈው።
፬፡ ውኃ፡አምጥተን፡እግራችሁን፡እንጠብቃችሁ፡ ከጥላው፡ዕረፉ።
፭፡ እንጀራን፡እናምጣላችሁና፡ብሉ፤በኋላ፡ወደ፡ ያችሁ፡ዘንድ፡ካረፋችሁም፡በኋላ፡ወደ፡

፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ግሙ፡ሁመ ፡ ኀበ ፡ ገብርክሙ ፡ ወይቤልዎ ፡
ግበር፡ከማሁ፡በከመ፡ትቤ።
ወርጸ ፡ አብርሃም ፡ ኀበ ፡ ሣራ ፡ ብእሲቱ ፡
ውስተ፡ ሐይመታ ፡ ወይቤላ ፡ አፍጥኒ ፡
ወአብሕኢ ፡ ሠለስተ ፡ መሥፈርተ ፡ ስንዳሴ ፡
ወግበሪ፡ዳፍንተ።
ወርጸ፡አብርሃም፡ኀበ፡አልሕምት፡ወነሥአ፡
አልደ፡ላሕመ ፡ ንዑሰ ፡ ወሠናየ ፡ ወወሀቦ ፡
ለቍልዔሁ፡ወአፍጠነ፡ገቢሮቶ።

ወአምጽአ፡ዕቋነ፡ሐሊበ፡ወመዐረ፡ወውእተ
ላሕመ፡ዘገብረ፡ወአቅረበ፡ሎሙ፡ወበልዑ፤
ወውእቱሰ ፡ ይቀውም ፡ ኀበ ፡ ዕፀ ፡ ወይሜ
ጥዎሙ።
ወይቤልዎ፡አይቴ፡ሣራ፡ብእሲትከ፡ወይቤሎ፡
ነያ፡ውስተ፡ሐይመት።

ወይቤሎ ፡ ሶበ ፡ ገባእኩ ፡ እመጽእ ፡ ኀቤከ ፡
ዓመ፡ ከመ ፡ ዮም ፡ ትረክብ ፡ ሣራ ፡ ወልደ ፤
ወሰምዐት ፡ ሣራ ፡ እንዘ ፡ ትቀውም ፡ ኀበ ፡
ኆኅት፡እንዘ፡ሀለወት፡ድኅሬሁ።
ወአብርሃምሰ፡ወሣራ፡ልሕቁ፡ጥቀ፡ወኀለፈ፡
መዋዕሊሆሙ ፡ ወኀደጋ ፡ ለሣራ ፡ ትክቶ ፡
አንስት።
ወሠሐቀት ፡ ሣራ ፡ በባሕቲታ ፡ እስመ ፡ ትቤ ፡
በልባ ፡ ዓዲየኑ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ እግዚእየኒ ፡
ልሕቀ።
ወይቤሎ፡**እግዚአብሔር፡** ለአብርሃም ፡ ምንት፡
አሥሐቃ ፡ ለሣራ ፡ በባሕቲታ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡
ዓዲየኑ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ወእግዚእየኒ ፡ ልሕቀ ፡
ወአማንኑ፡እወልድ፡ወናሁ፡ረሣእኩ፡አንሰ።
ቦኑ ፡ ነገር ፡ ዘይሰአኖ ፡ **ለእግዚአብሔር ፡**
በዝንቱ፡ጊዜ፡አመ፡ከመ፡ዮም፡ሶበ፡ገባእኩ፡
ኀቤከ፡ትረክብ፡ሣራ፡ወልደ።
ወክሕደት፡እንዘ፡ትብል፡ኢሠሐቁ፡እስመ፡
ፈርሀት፡ወይቤላ፡አላ፡ሠሐቂ።
ወተንሥኡ ፡ ፪ቱ ፡ ዕደው ፡ እምህየ ፡
ወተመይጡ ፡ ወሐሩ ፡ መንገለ ፡ ሰዶም ፡
ወጎሞራ፡ወሖረ፡አብርሃም፡ምስሌሆሙ፡ያስ
ተፋንዎሙ፡ወተመይጠ፡አብርሃም፡ወቆመ፡
ቅድመ፡**እግዚአብሔር።**

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ችሁት፡ትሄዳላችሁ፡አለ፤እነሱም፡እንዳልክ፡
እንዲሁ፡አድርግ፡አሉት።
፮፡ አብርሃምም ፡ በድንኳኗ ፡ ወዳለች ፡ ወደ ፡
ሚስቱ ፡ ወደ ፡ ሣራ ፡ ሮጠ፤ፈጥነሽም ፡ ሦስት ፡
መስፈሪያ ፡ (ቁና) ፡ ሥንዴ ፡ አቡክተሽ ፡ ዳቦ ፡
ጋግሪ ፡ አላት።
፯፤ አብርሃምም ፡ ወደ ፡ ላሞቹ ፡ ሮጦ ፡ ያማረ ፡
ትንሽ፡ አንድ ፡ ወይፈንም ፡ አምጥቶ ፡ ለብላ
ቴናው ፡ ሰጠው ፤ ብላቴናውም ፡ ፈጥኖ ፡
አረደው።
፰፤ ማር፤እርጎና፡ወተት፤ያን፡ያረደውን፡ሥጋ፡
አምጥቶ ፡ አቀረበላቸው ፤ እነርሱም ፡ በሉ ፤
እርሱም ፡ በዛፍ ፡ ሥር ፡ ቁሞ ፡ ያሳልፍላቸው ፡
ነበር።
፱፤ እርሱም ፡ ሚስትህ ፡ ሣራ ፡ ወዴት ፡ ናት ፡
አለው፤ እነሆ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ አለች ፡
አለው።
፲፤ እንደ ፡ ዛሬው ፡ የዛሬ ፡ ዓመት ፡ ወዳንተ ፡
ተመልሼ፡በመጣሁ፡ጊዜ፡ሣራ፡ወንድ፡ልጅ፡
ታገኛለች፡አለው፤ሣራም፡በኋላው፡በደጃፍ፡
ቁማ፡ሳለች፡ሰማች።
፲፩፤ አብርሃምና፡ሣራ፡ግን፡ፈጽመው፡አርጅተው፡
ነበር፤ዘመናቸውም፡አልፎ፡ነበርና፤ሣራንም፡
የሴቶች፡ግዳጅ፡ትቷት፡ነበር።
፲፪፤ በልቧ፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡ገና፡ቆንጆ፡ነኝን?
ጌታዬም ፡ አብርሃም ፡ አርጅቷል ፡ ብላለችና ፡
ሣራ፡ብቻዋን፡ሣቀች።
፲፫፤ **እግዚአብሔርም፡** አብርሃምን፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡
ገና ፡ ቆንጆ ፡ ነኝን ? ጌታዬ ፡ አርጅቷል ፤ እነሆ፡
እኔም፡ አርጅቼአለሁ፤ በውነት፡ ልጅን፡ እወልዳ
ለሁን?ስትል፡ሣራን፡ምን፡አሣቃት፡አለው።
፲፬፤ በውኑ ፡ **ለእግዚአብሔር ፡** የሚሳነው ፡ ነገር ፡
አለን?እንደ፡ዛሬ፡የዛሬ፡ዓመት፡ወደ፡አንተ፡
በተመለስኩ፡ጊዜ፡ሣራ፡ልጅን፡ታገኛለች።
፲፭፤ ሣራም ፡ ፈርታለችና ፡ አልሣቅሁም ፡ ብላ ፡
ካደች፤ስቀሻል፡እንጂ፡አላት።
፲፮፤ ሁለቱ፡ሰዎች፡ከዚያ፡ተነሡ፤ተመልሰውም፡
ወደ ፡ ገሞራና ፡ ወደ ፡ ሰዶም ፡ ሄዱ ፤ አብር
ሃምም፡ ይሸኛቸው ፡ ዘንድ ፡ ከነሳቸው ፡ ጋራ ፡
ሄደ፤አብርሃምም፡ተመልሶ፡**በእግዚአብሔር፡**
ፊት፡ቆመ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፯፡ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ ኢየኀብእ፡እምቍ
ልዔየ፡አብርሃም፡ዘእገብር፡አነ።
፲፰፡ እስመ፡ሕዝበ፡ዐቢየ፡ወብዙኀ፡ይከውን፡
አብርሃም፡ወይትባረኩ፡ቦቱ፡ኵሎሙ፡
አሕዛበ፡ምድር።
፲፱፡ እስመ፡አአምር፡ከመ፡ሀለዎ፡ለአብርሃም፡
የአዝዞሙ፡ለደቂቁ፡ወለቤቱ፡ወያዕቅቦሙ፡
ፍናዊሁ፡ለእግዚአብሔር፡ከመ፡ይግበሩ፡
ምጽዋተ፡ወፍትሐ፡ከመ፡ይግበር፡ሎሙ፡እግ
ዚአብሔር፡ኵሎ፡ዘይቤሎ፡ለአብርሃም።

፳፡ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለአብርሃም፡
ጽራሐሙ፡ለሰዶም፡ወለገሞራ፡በጽሐ፡
ኀቤየ፡ወኃጢአቶሙኒ፡በዝኀት፡ጥቀ።
፳፩፡ እወርድ፡እንከሰ፡ወእርአይ፡ለእመ፡በከመ፡
ጽራሐሙ፡እንተ፡ትመጽእ፡ኀቤየ፡
ይፌጽምዋ፡ወእመ፡አኮሰ፡አአምር።

፳፪፡ ወሶበ፡ተመይጡ፡እምህየ፡እልክቱ፡ዕደው፡
መጽኡ፡ውስተ፡ሰዶም፡ወአብርሃምሰ፡ሀሎ፡
ዓዲ፡ይቀውም፡ቅድመ፡እግዚአብሔር።
፳፫፡ ወቀርበ፡አብርሃም፡ወይቤ፡ኢታማስን፡
እግዚእ፡ጻድቃነ፡ምስለ፡ኃጥአን፡
ወኢይኩን፡ጻድቅ፡ከመ፡ኃጥእ።

ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፬፡፳፱–፴፩፡፲፭፡፲፱።

፳፱፡ ወአመ፡ኀለፉ፡እስራኤል፡ማዕዶተ፡ባሕረ፡
ኤርትራ፡ወኬዱ፡እገሪሆሙ፡ባሕረ።

፴፡ ወጸላእቶሙሰ፡ተሰጥሙ፡ውስተ፡ቀላይ፤
ወተሠግሩ፡እገሪሆሙ፡ወዐመፃሆሙኒ፡ቦአ፡
ውስተ፡ማይ።
፴፩፡ ወእስራኤልሰ፡ወኵሉ፡ቤተ፡ያዕቆብ፡ድኅኑ፡
እሙስና።

ምዕ፡፲፭፡፩።
፩፡ ወይቤሉ፡ዘ፡ቡራኬ፡ንሴብሖ፡ለእግዚአ
ብሔር፡ስቡሐ፡ዘተሰብሐ።

እመጽሐፈ፡ኢያሱ።

ምዕ፡፫፡፲፫፡፲፯።
፲፫፡ ወይእተ፡አሚረ፡ኢያሱ፡ወሕዝብ፡ዐደዉ፡
ዮርዳኖስ፡ወኬዱ፡እገሪሆሙ፡እብነ፡ዘውስተ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፯፡ እግዚአብሔርም፡እኔ፡የምሠራውን፡ከመሰ
ከአብርሃም፡ምንም፡አልሠውርም፡አለ።
፲፰፡ አብርሃም፡የገነነ፡ወገንና፡እጅግም፡የበ
ይሆናልና፤የዚህ፡ዓለም፡አሕዛብም፡ሁሉ
በእርሱ፡ይከብራሉ።
፲፱፡ እግዚአብሔር፡ለአብርሃም፡የነገረውን፡
ሁሉ፡ያደርግላቸው፡ዘንድ፡ምጽዋትን፡እን
መጸውተ፡ፍርድንም፡እንዲያደርጉ፡የእግዚአ
ብሔርንም፡ሕጉን፡አምልኮቱን፡ጠብቁ፡
ብሎ፡ልጆቹን፡ቤተ፡ሰቦቹን፡ያዛቸው፡ዘንድ
እንዳለው፡አውቃለሁና።
፳፡ እግዚአብሔርም፡አብርሃምን፡የገሞራ፡
የሶዶም፡ጩኸታቸው፡ወደ፡እኔ፡ደረሰ፡ኃጢ
አታቸውም፡እጅግ፡በዛች።
፳፩፡ ወደ፡እኔ፡እንደምትመጣ፡ጩኸታቸው፡
ኃጢአታቸውን፡ይጨርሷት፡እንደ፡ሆነ፡እ
ግዲህስ፡እወርዳለሁ፤ አያለሁ፤ እንዲህ፡
ካልሆነ፡አውቃለሁ፡አለው።
፳፪፡ እነዚያ፡ሰዎች፡ከዚያ፡እንደ፡ተመለሱ፡ወደ
ሰዶም፡መጡ፤አብርሃም፡ግን፡ገና፡በእግዚአ
ብሔር፡ፊት፡ቆሞ፡ነበር።
፳፫፡ አብርሃምም፡አቤቱ፡ጻድቃንን፡ከኃጢአ
ተኞች፡ጋር፡አታጥፋ፤ጻድቁም፡እንደ
ኃጥኡ፡አይሁን፡አለ።

ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፬፡፳፱–፴፩፡፲፭፡፲፱።
፳፱፡ እስራኤልም፡ወደ፡ኤርትራ፡ባሕር፡ማዶ
በአለፉ፡ጊዜ፡እግሮቻቸው፡ባሕሩን፡
ረግጠው፡ወጡ።
፴፡ ጠላቶቻቸው፡ግን፡በጥልቁ፡ውስጥ፡ሰጠሙ፡
እግሮቻቸውም፡ተጠመዱ፤ከነዐመፃቸውም
ወደ፡ውኃ፡ውስጥ፡ሰጠሙ።
፴፩፡ የያዕቆብ፡ዘሮች፡እስራኤል፡ሁሉ፡ግን
ከስጥመት፡ጥፋት፡ዳኑ።

ምዕ፡፲፭፡፩።
፩፡ ይኸንንም፡ምስጋና፡እንዲህ፡ብለው፡
አመሰገኑ፤ምስጉን፡ሁኖ፡የተገኘ፡እግዚአብ
ሔርን፡እናመሰግነዋለን።

ከኢያሱ፡መጽሐፍ።

ምዕ፡፫፡፲፫፡፲፯።
፲፫፡ በዚያን፡ጊዜ፡ኢያሱና፡ሕዝቡ፡ዮርዳኖስን፡
ተሻገሩ፤እግሮቻቸው፡በውኃ፡ውስጥ፡ያለ

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።  |
|---|---|
| ግሁ፡ወጸንዐ፡እደዊሆሙ፡ወሞኡ፡ፀሮሙ። | ደንጊያ፡ተረግጠው፡ተሻገሩ፤እጆቻቸውም፡(ሥልጣናቸው)፡በርትተው፡ጠላቶቻቸውን፡ድል፡አደረጉ። |
| ሲሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡ ትኩን፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። | ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘለዓለሙ፡ ትኑር፡አሜን። |
| ምዕ፤፴፤፲፱–፳፩። | ምዕ፤፴፤፲፱–፳፩። |
| ሰአተ፡አሚረ፡ያበርህ፡**እግዚአብሔር**፡በዲበ፡ ምድር፤በምክረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ይዕቀ ብዎሙ፡ወያክብርዎሙ፡ለእለ፡ተርፉ፡እምእ ስራኤል። | ፲፱፤ ከእስራኤል ፡ ከሞት ፡ የተረፉትን ፡ ይጠብቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ያከብሩአቸውም ፡ ዘንድ ፡ የዚያን፡ጊዜ፡**እግዚአብሔር**፡በኢየሩሳሌም፡ በጌትነቱ ፡ ምክር ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡ ያበራል። |
| ወእለሂ፡ተርፉ፡እምጽዮን፡ወተረፈ፡ኢየሩ ሳሌም፡ቅዱሳነ ፡ ይሰመዩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተጽሕፉ፡ወየሐይዉ፡በኢየሩሳሌም። | ፳፤ በኢየሩሳሌምና ፡ በጽዮን ፡ የሚኖሩት ፡ ክቡራን ፡ ይባላሉ ፤ ሁሉም ፡ የተቈጠሩ ፡ ናቸው፤በኢየሩሳሌም፡ይኖራሉ። |
| እስመ ፡ የኀፅቦሙ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ርስሐቶሙ፡ለደቂቀ፡ጽዮን፡ወለአዋልዲሃ። | ፳፩፤ የጽዮንን ፡ ወንዶች ፡ ልጆቿንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቿን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ከኃጢአታቸው ፡ አጥቦ፡ያነጻቸዋልና። |
| ምዕ፤፶፭፤፩–፲፪። | ምዕ፤፶፭፤፩–፲፪። |
| ወይቤ፡ኵሎሙ፡እለ፡ጸምኡ፡ይሑሩ፡ኀበ፡ ማይ፡ወእለሂ፡አልቦሙ፡ወርቅ፡ይሑሩ፡ ወይሣየጡ፡ሎሙ፡ወይስተዩ፡ዘእንበለ፡ ወርቅ፡ወይነ፡ወሐሊበ። | ፩፤ የተጠሙ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ወደ፡ውኃ፡ይሂዱ፤ ገንዘብም፡የሌላቸው፡ሰዎች፡ሂደው፡ዋጋ፡ ሳይሰጡ፡ያለ፡ገንዘብ፡ወይንና፡ወተትን፡ ይጠጡ፡አለ። |
| ለምንት ፡ ትሠይጡ ፡ በወርቅ ፡ ኢይከውነ ከሙ ፡ ለጽጋብ ፡ ፃማክሙ ፡ ስምዑኒ ፡ ወትበልዑ፡በረከተ፡ወትትፌሣሕ፡በበረከት፡ ነፍስክሙ፡ወትልዉ፡ፍኖትየ፡ወስምዑኒ፡ ወተሐዩ፡ነፍስክሙ፡በበረከት። | ፪፤ ውኃን ፡ በብር ፡ ለምን ፡ ትሸጣላችሁ ? ገንዘባችሁ ፡ ለጥጋብ ፡ አይሆናችሁምን ? ቃሌን ፡ ስሙኝ ፤ ድልቡን ፡ ትበላላችሁ ፤ ሰውነታችሁም፡በበረከት፡ደስ፡ትሰኛለች፤ጐዳናዬን፡ ተከተሉ ፤ ቃሌንም ፡ ስሙ ፤ ሰውነታችሁ ፡ በደስታ፡ትኖራለች። |
| ወአሠርዕ፡ለቤተ፡ዳዊት፡ሥርዐተ፡ጽድቅ፡ ዘለዓለም፡እስመ፡ናሁ፡ምእመነ፡ረሰይክዎ፡ ወስምዐ፡ለአሕዛብ፤መስፍነ፡ወመኰንነ፡ ለአሕዛብ። | ፫፤ እነሆ፡ለዳዊት፡ወገን፡ለዘለዓለም፡ጸንቶ፡የሚኖር፡የእውነትን፡ሥርዓት፡እሠራለታለሁ፤የታመነ፡የአሕዛብ፡መምህር፡አድርጌዋለሁና፡ለአሕዛብም፡ፍጹም፡ገገር፡አድርጌዋለሁ። |
| ወሕዝብ፡እለ፡ኢየአምሩከ፡ይጼውዑከ፡ ወሕዝብ፡እለ፡ኢይሌብዉከ፡ይትመኀፀኑ፡ ገቤከ፡በእንተ፡**እግዚአብሔር፡አምላክከ**፡ ቅዱስ፡እስራኤል፡እስመ፡ውእቱ፡አክበረከ። | ፭፤ የማያውቁህ፡ወገኖች፡ይለምኑሃል፤ይጠሩሃል፤ እርሱ፡አክብሮሃልና፤እስራኤልን፡የሚያጸና፡ **ፈጣሪህ፡እግዚአብሔር**፡በአንተ፡ላይ፡በረድኤት፡ስለ፡አደረ፡ልብ፡የማያደርጉህ፡ወገኖችም፡ በአንተ፡ይማፀናሉ፤(ልብ፡ያደርጉሃል)። |
| ኅሥሥዎ፡**ለእግዚአብሔር**፡እምከመ፡ረከብ ክምዎ፡ጸውዕዎ፡እምከመ፡ቀረበክሙ፡ | ፮፤ **እግዚአብሔርን**፡በአምልኮት፡ፈልጉት፤በአገኛችሁትም፡ጊዜ፡አድነን፡ብላችሁ፡ጥሩት፤ |

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ኀቤሁ ፡ ይኅድግ ፡ ኃጥእ ፡ ፍኖቶ ፡ ወብእሲ ፡
ዐማፂ፡ምክሮ።

፯፤ ወይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ወይማኅሎ፡ እንከ ፡ እስመ ፡ ብዙኀ ፡ የኀድግ ፡
ለክሙ፡ኃጢአተክሙ።

፰፤ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ምክርየ ፡ ከመ ፡ ምክርክሙ ፡
ወኢኮነት፡ፍኖትየ፡ከመ፡ፍኖትክሙ ፡ ይቤ ፡
እግዚአብሔር።

፱፤ በከመ ፡ ይርኅቅ ፡ ሰማይ ፡ እምድር ፡ ከማሁ ፡
ይርኅቅ፡ፍኖትየ፡እምፍኖትክሙ፡ወኀሊናየ፡
እምኀሊናክሙ።

፲፤ ከመ ፡ ሶበ ፡ ይወርድ ፡ እምሰማይ ፡ ዝናም ፡
ዐቢይ ፡ ወበረድ ፡ ወኢየኀድግ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡
ያረውያ ፡ ለምድር ፡ ወያበቊል ፡ ወያሠምር ፡
ወይሁብ፡ዘርዐ፡ለዘራዒ፡ወእክለ፡ለሲሳይ።

፲፩፤ ከማሁ፡ውእቱ፡ቃልየ፡ዘይወፅእ፡እምአፉየ፡
ወኢይትመየጥ ፡ እስከ ፡ እገብር ፡ ኵሎ ፡
ዘፈቀድኩ፡ወእሜርኅ፡ፍኖትየ፡ወትእዛዝየ።

፲፪፤ እስመ ፡ በፍሥሐ ፡ ትወፅኡ ፡ ወበሐሤት ፡
ትትነሥኡ፡ያንፈርዕፁ፡አድባር፡ወአውግር፡
ወይጸንሑክሙ ፡ በኀሤት ፡ ወይጠፍሑ ፡
እደዊሆሙ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ፡ በአዕፁ ፡
ቂሆሙ።

፲፫፤ ወይሴብሑ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በትእ
ምርት፡ዘለዓለም፡ዘኢየኀልቅ፡ስብሐቲሁ።

ዘሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፴፮፡፳፭–፳፱።

፳፭፤ ወእነዝኀክሙ ፡ በማይ ፡ ንጹሕ ፡ ወትነጽሑ ፡
እምኵሉ ፡ ርኵስክሙ ፡ ወእነጽሐክሙ ፡
እምኵሉ፡ጣዖትክሙ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

(ለምኑት) ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ ከቀረባችሁ፡
በኋላ፡ ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ኃጢአቱን ፡ በደለኛም፡
ሰው፡ምክሩን፡ይተው።

፯፤ በአምልኮት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመለስ፤
ከዚያም፡በኋላ፡ይቅር፡ይለዋል፤ብዙ፡ኃጢአ
ታችሁን፡ያስተሰርይላችኋልና።

፰፤ እግዚአብሔር ፡ ምክሬ ፡ እንደ ፡ ምክራችሁ፡
አይደለም ፤ መንገዴም ፡ (ሥራየም ፡) እንደ፡
ሥራችሁ፡አይደለችምና፡ይላል።

፱፤ ሰማይ ፡ ከምድር ፡ እንዲርቅ ፡ እንደዚሁ፡
መንገድ ፡ (ሥራዬ) ፡ ከሥራችሁ ፡ አሳቤም፡
ከአሳባችሁ፡ይርቃል።

፲፤ ብዙ ፡ ዝናም ፡ ከሰማይ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ በረዶም
በዘነመ ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ እስኪያረካት ፡ ድረስ፡
መዝነምን ፡ እንዳይተው ፡ ተክሉን ፡ እንዲያ
በቅል፡ መከሩንም ፡ የበጀ ፡ እንዲያደርግ ፡ ለሚ
ዘራ፡ሰው፡ዘርን፤ለምግብ፡እህልን፡እንዲሰጥ።

፲፩፤ ከአንደበቴ፡የሚወጣ፡ቃሌም፡እንዲሁ፡ነው፤
የወደድሁትን ፡ እስካደርግ ፡ ድረስ ፡ አይመ
ለስም ፤ መንገዴንና ፡ (ሥራዬንና) ፡ ትእዛ
ዜንም፡አቀናለሁ፤አከናውናለሁ።

፲፪፤ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ተነሥታችሁ ፡ ትወጣ
ችሁና ፤ ኮረብቶችና ፡ ተራሮች ፡ ደስ ፡
ይላቸዋል፤ (ዐበይት ፡ ነቢያት) (ደቂቀ ፡
ነቢያት) ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይጠብቋችኋል፤
የገዳም ፡ ዛፎች ፡ ሁሉ ፡ በቅርንጫፎቻቸው ፡
ያጨበጭባሉ።

፲፫፤ ጌትነቱ፡ለዘለዓለም፡የማይፈጸም የእግዚአብ
ሔርን፡ስም፡በምልክት፡ያመሰግናሉ።

ነቢዩ ፡ ሕዝቅኤል ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡
የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለም ፡
ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፴፮፡፳፭–፳፱።

፳፭፤ በንጹሕ ፡ ውኃ ፡ እረጫችኋለሁ ፤ ከኃጢአታ
ችሁም ፡ ሁሉ ፡ ትነጻላችሁ ፤ ከጣዖታችሁም፡
ሁሉ፡አነጻችኋለሁ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፳፮ ወእሁበክሙ፡ ልበ፡ ሐዲሰ፡ ወመንፈሰ፡
ሐዲሰ፡እወዲ፡ ላዕሌክሙ፡ ወአወፅእ፡ ልበ፡
እብን፡እምሥጋክሙ፡ ወእሁበክሙ፡ ልበ፡
ዘሥጋ።
፳፯ ወእወዲ፡ መንፈስየ፡ ላዕሌክሙ፡ ወእሬስ
የክሙ፡ ከመ፡ ትሑሩ፡ በሥርዓትየ፡
ወትዕቀቡ፡ኵነኔየ፡ወትግበርዎ፡
፳፰ ወትነብሩ፡ ውስተ፡ ምድር፡ እንተ፡ ወሀብ
ክዎሙ፡ለአበዊክሙ፡ወትከውኑኒ፡ሕዝብየ፡
ወአነሂ፡እከውነክሙ፡አምላክክሙ።
፳፱ ወአድኀነክሙ፡እምኵሉ፡ርኵስክሙ፡ወጌጋ
ይክሙ።

ምዕ፡፵፯፡፩-፱።

፩ ወአውፅአኒ፡ ኆኅተ፡ አንቀጽ፡ ሰሜናዊ፡
ወአየደኒ፡ፍኖተ፡አፍአ፡ኀበ፡አንቀጽ፡ጸናፌ፡
ዘይኔጽር፡ጽባሐ፡ ወናሁ፡ ማያት፡ ይውኅዙ፡
እመትከፍት፡ዘየማን።

፪ ወሶበ፡ወፅአ፡ ዝኩ፡ ብእሲ፡ ጽባሐ፡ ወመሥ
ፈርት፡ ውስተ፡ እዴሁ፤ ወሰፈረ፡ ዐሠርተ፡
ምዕተ፡ በእመት፡ ወአዕደወኒ፡ በማያት፡
ወማያት፡እስከ፡ሜኤፌሳይም፡(ሰኰና)።

፫ ወሰፈረ፡ ዐሠርተ፡ ምዕተ፡ ወአዕደወኒ፡
በማያት፡ወማያት፡እስከ፡አብራክ። ወሰፈረ፡
ዐሠርተ፡ ምዕተ፡ ወአዕደወኒ፡ በማያት፡
ወማያት፡እስከ፡ሐቌ።

፬ ወሰፈረ፡ ዐሠርተ፡ ምዕተ፡ ወናሁ፡
ፈለግ፡ዘኢይክል፡ዐዲዎቶ፡እስመ፡ዐርጉ፡
ማያት፡ማያተ፡ ኖትያ፡ ፈለግ፡ ዘኢየዐድ
ውዎሙ።

፭ ወይቤለኒ፡ርኢከኑ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
ወወሰደኒ፡ወሜጠኒ፡ኀበ፡ድንጋገ፡ፈለግ።

፮ ወሶበ፡ሜጠኒ፡በድንጋገ፡ፈለግ፡ዕፅ፡ብዙኅ፡
ፈድፋደ፡እምለፌሂ፡ወእምለፌሂ።
፯ ወይቤለኒ፡እሉ፡ማያት፡ይወፅኡ፡ኀበ፡ገሊላ፡
ጽባሐዊ፡ ወይወርዱ፡ ላዕለ፡ ዓረብ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፮፤ አዲስ፡ልብን፡እሰጣችኋለሁ፤አዲስ፡ዕውቀ
ትንም፡ አሳድርባችኋለሁ፤ ድንቁርና፡
ያለበት፡ ልብንም፡ ከሰውነታችሁ፡ አርቄ፡
ዕውቀት፡ያለውን፡ልብ፡እሰጣችኋለሁ።
፳፯፤ መንፈስ፡ረድኤቴን፡(ልጅነትን)፡አሳድርባ
ችኋለሁ፤ በሥርዓቴ፡ ጸንታችሁ፡ እንድ
ትኖሩ፡ሕጌንም፡ጠብቃችሁ፡እንድትሠሩት፡
አደርጋችኋለሁ።
፳፰፤ ለአባቶቻችሁ፡በሰጠኋቸው፡አገር፡ትኖራ
ላችሁ፤ ወገኖቼም፡ ትሆኑኛላችሁ፤እኔም፡
አምላካችሁ፡እሆናችኋለሁ።
፳፱፤ ከበደላችሁና፡ከኃጢአታችሁ፡ሁሉ፡አነጻች
ኋለሁ።

ምዕ፡፵፯፡፩-፱።

፩፤ በሰሜኑም፡ በር፡ በኩል፡ አወጣኝ፤
በስተውጭ፡በአለው፡መንገድ፡ምሥራቅን፡
ወደሚመለከተው፡በስተውጭ፡ወደ፡አለው፡
በር፡አዞረኝ፤እነሆም፡ውኆች፡በቀኝ፡በኩል፡
ይፈስሱ፡ነበር።
፪፤ ያም፡ሰው፡ወደ፡ምሥራቅ፡ይዞኝ፡በወጣ፡
ጊዜ፡ በእጁ፡ መሥፈሪያ፡ ይዞ፡ ነበር፤ ሺህ፡
ክንድ፡ ሰፍሮ፡ በውኆቹ፡ ላይ፡ አሻገረኝ፤
ውኆቹም፡እስከ፡ቍርጭምጭምት፡ደረሱ፤
(ጥቂት፡ውኆች)።
፫፤ ሁለተኛ፡ሺህ፡ክንድ፡ሰፍሮ፡በውኆቹ፡ላይ፡
አሻገረኝ፤ውኆቹም፡ከባት፡አልፈው፡እስከ፡
ጉልበት፡ይደርሳሉ፤ሦስተኛም፡ሺህ፡ክንድ፡
ሰፍሮ፡ አሻገረኝ፡ ውኆቹም፡ ከጭን፡
አልፈው፡እስከ፡ወገብ፡ደረሱ።
፬፤ ዐራተኛ፡ሺህ፡ክንድ፡በሰፈረ፡ጊዜ፡እነሆ፡
ልሻገረው፡ የማልችለው፡ ጥልቅ፡ ወንዝ፡
ነው፤ውኆች፡እስከ፡ቃሊማቸው፡ወጥተው፡
ሰዎች፡ዋኝተው፡ሊሻገሩአቸው፡የማይችሉ፡
ጥልቅ፡ወንዝ፡ሆኖአልና።
፭፤ ጠርቶ፡እንዲህ፡አለኝ፤የሰው፡ልጅ፡ሆይ፡
አየህን፡(አስተዋልህን)፡ይህንም፡ተናግሮ፡
ወደ፡ወንዙ፡ዳር፡መለሰኝ።
፮፤ በመለሰኝም፡ ጊዜ፡ እነሆ፡ በወንዙ፡ ዳር፡
በወዲያና፡በወዲህ፡እጅግ፡ብዙ፡ዛፍ፡ነበር።
፯፤ ከዚህ፡በኋላ፡እንዲህ፡አለኝ፤እሊህ፡ውኃዎች፡
ወደ፡ምሥራቅ፡ገሊላ፡(ምድር)፡ይፈስሳሉ፤ወደ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እለ፡ወፅኡ፡ወይ
ወይበውኡ፡ውስተ፡ባሕር፡
ትፌወሱ፡ማያት።

፶፱፡ ወይከውን ፡ ኵሉ ፡ ዘነፍስ ፡ ሕያው ፡ ወይት
ፌወስ፡ኀበ፡ኵሉ፡ዘይበውእ፡ህየ፡ፈለግ፡
የሐዩ።

ክፍል፡፪።

ተማኅጽ ፡ ዘአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡
በረከቱ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፩፡ ንኅፈር ፡ ይእዜኒ ፡ አ ፡ አኀውየ ፡ በእንተ ፡
ዘሐመ፡ በእንቲአነ ፡ ወንፍራህ ፡ በእንተ ፡
ዘቀነተ ፡ ለንጸ ፡ ወወደየ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡
ምኅፃብ፡ ወሐፀበ ፡ እግረ ፡ አርዳኢሁ ፡
በእደዊሁ፡ንጹሐት።

፪፡ ወንግበር ፡ ፍሬ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዕበየ ፡ ዝንቱ ፡
ትሕትና ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሁ ፡ ለነ ፤ ወንነስሕ ፡
ፍጡነ፡እምኃጢአትነ፡ዘነሐውር፡ባቲ።

፫፡ ወሶበ ፡ ኢነሳሕነ ፡ ይብሉ ፡ በእንቲአነ ፡
በውስተ፡ሰማያት፡መፍቀርያነ፡ኃጢአት።

፬፡ ምንትኬ ፡ ንሕነ ፡ እንከ ፡ ዘንሬሮ ፡ ሶበ ፡
ይወስዱነ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወይወድዩነ ፡
ውስተ ፡ ኵነኔ ፡ ወይገድፉነ ፡ በእንተ ፡
ኃጣውኢነ ፡ ወይፌትሑ ፡ ላዕሌነ ፡ ፍትሐ ፡
ኵነኔ፡ምክዕቢተ።

፭፡ ወአልቦ ፡ ዘገበርነ ፡ ዘእንበለ ፡ አእምሮ ፡ አላ ፡
ገበርነ ፡ በአእምሮ ፡ እኩይ ፡ ዘይበዝኅ ፡
ምክዕቢተ ፡ እምዘገበርነ ፡ እንበለ ፡ አእምሮ ፡
ወአኮ ፡ ዘገበርነ ፡ ንሕነ ፡ ኃጢአተ ፡ ባሕቲቶ ፡
አላ፡በእንተ፡ዘኢነሳሕነ።

፮፡ ለምንት ፡ አባግዕ ፡ ዘኢትሰምዑ ፡ ቃለ ፡ ኖላዊ ፡
ዘበአማን ፡ ማሕየዊ ፡ ለኵሉ ፡ ዓለም ። ወዘይ
ጼወኑ ፡ ኪያሁ ፡ ዘተሣየጠሙ ፡ በደሙ ፡
ወሐፀኖሙ።

፯፡ ወአስተጋብአ ፡ ኪያነ ፡ ወበእንቲአነ ፡ ወሀበ ፡
ሥጋሁ ፡ መብልዐ ፡ ንብላዕ ፡ ወደሞ ፡ ንስተይ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡
ወመድኃኒነ ፡ ቃለ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡
ዘየኀድር፡ውስተ፡አርያም፡ዘለዓለም፡ ወለእግ
ዚእነ፡ሎቱ፡ስብሐት፡እስከ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ምዕራብም ፡ (በረኀም) ፡ ይወርዳሉ ፤ ወደ፡
ባሕሩም ፡ ይገባሉ ፤ ወደ ፡ ወጡበት ፡ ባሕርም፡
(ጼው)፡ይገባሉ ፤ ውኆችም፡ይፈወሳሉ።

፶፱፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ፍጥረት፡
ሁሉ ፡ በሚገባበት ፡ ባሕር ፡ የሚኖር ፡ ሕያው፡
ሆኖ፡ይኖራል።

ክፍል፡፪።

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለም ፡ ትኑር፤
ቅዱስ ፡ አባታችን ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ የተናገረው፡
ምክር፡እዝናት፡ይህ፡ነው።

፩፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ መከራ ፡ ስለተ
ቀበለ ፡ አሁን ፡ እንዘን ፤ ሽርጥ ፡ (ዝናር) ፡ ታጥቆ፡
በኵስኵስት ፡ ውኃ ፡ ጨምሮ ፡ የደቀ ፡ መዛሙ
ርቱን ፡ እግር ፡ ንጹሐን ፡ በሆኑ ፡ እጆቹ ፡ ስለ፡
አጠበ፡እንፍራ።

፪፡ ከእርሱ ፡ ለተደረገልን ፡ ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ከፍ፡
ለሚለው ፡ ትሕትና ፡ ታላቅነት ፡ የሚገባ ፡ ፍሬ፡
ክብር ፡ እናቅርብ ፤ በእርስዋ ፡ጸንተን ፡ ካለንባት፡
ኃጢአታችንም፡ፈጥነን፡ንስሐ፡እንግባ።

፫፡ ንስሐ ፡ ካልገባን ፡ በሰማያት ፡ እኛን፡
የኃጢአት፡ወዳጆች፡ይሉናል።

፬፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በሚወስዱን ፡ ስለ ፡ ኃጢአ
ታችን፡ ወደ ፡ ሥቃይ ፡ ውስጥ ፡ በሚጥሉን፡
በእኛ ፡ ላይም ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ የሆነ ፡ ቅጣት፡
በሚፈርዱብንም ፡ ጊዜ ፡ እንግዲህ ፡ እኛ፡
ተስፋ፡የምናደርገው፡ምንድነው?

፭፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ የሠራነው ፡ የለም ፤ ሳናውቅ፡
ከሠራነው ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ የሚበዛ ፡ ክፉ፡
በሆነ፡ እውቀት ፡ ሠራን ፡ እንጂ ፤ እኛ ፡ የሚፈረ
ድብን ፡ በሠራነው ፡ ኃጢአት ፡ ብቻ ፡ አይደለም፡
ንስሐ፡ባለመግባታችን፡ነው፡እንጂ።

፮፡ የዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ መድኃኒት ፡ የሚሆን፡
ዕውነተኛ ፡ ጠባቂ ፡ ክርስቶስን ፡ አባግዕ ፡ የተባ
ላችሁ ፡ ምእመናን ፡ ቃሉን ፡ ለምን፡
አትሰሙም ፤ እርሱን ፡ የሚታመኑት ፡ በደሙ፡
የዋጃቸውና፡ያሳደጋቸው፡ናቸው።

፯፡ ለዘላለሙ ፡ በአርያም ፡ የሚኖር ፡ የአብ፡
አካላዊ፡ ቃል ፡ የአምላክ ፡ ልጅ ፡ ጌታችን ፡ፈጣ
ሪያችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡
አንድነት ፡ እኛን ፡ ሰብስቦ ፡ ስለእኛ ፡ ሥጋውን፡
መብል ፡ ደሙን ፡ መጠጥ ፡ አድርጎ ፡ እንበላ፡
እንጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ለሰጠን ፤ ለጌታችንም፡
ለዘላለሙ፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ትእዛዝ፡ወትብል፡መዝሙረ፡ዳዊት፤(፻)፡
ምዕት፡ምሕረተ፡ወፍትሐ፡እሐሊ፡ለከ። ፻
ወ፲፡(ዘምዕት፡ወዐሥርቱ።) እገኒ፡ለከ፡
እግዚእ፡በኵሉ፡ልብየ። ፻፲ወ፫፡እመ፡
ይወፅኡ። ዘ፰ወ፰፡አድኅነኒ፡እግዚኦ፡እስመ፡
በጽሐኒ፡ማይ፡እስከ፡ነፍስየ።

ወይበል ቀሲስ፡አው፡ዲያቆን፡ስእለታተ፡
ሆሳዕናት፡በእንተ፡ቅድሳት፡ከመዝ።

ወያወሥኡ፡ሕዝብ፡ወይበሉ፡እግዚኦ፡
ተሣሃለነ።

፩ እ፡ዘቀነትከ፡ለንጹ፡ከመ፡ገብር፡ወከደንከ፡
ዕርቃኖ፡ለአዳም፡ወአሠነይከ፡ላዕሌነ፡
በልብሰ፡ልደት፡እምላካዊት፤ ንስእለከ፡
እግዚኦ፡መሐረነ፡ወተሣሃለነ፡ወስምዐነ።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ፤ለለምዕራፉ።

፪ ይ፡ካ፡በእንተ፡ፍቅሩ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡
ዘኮንከ፡ሰብአ፡ወበዕበየ፡ፍቅርከ፡ለነ፡
ቀነትከ፡ለንጹ፡ወኀፀብከ፡እግረ፡አርዳኢከ፡
ወደምሰስከ፡ርስሐተ፡ኃጣውኢነ።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ።

፫ ይ፡ካ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡እ፡ክርስቶስ፡
እምላክነ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ።

፬ ይ፡ካ፡እ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ዘሖርከ፡ዲበ፡
ማይ፡በአፍቅሮትከ፡ሰብአ፡ኀፀብከ፡እግረ፡
አርዳኢከ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡ስምዐነ፡
ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ።

፭ ይ፡ካ፡መሐረነ፡ለኵልነ፡እ፡አምላክነ፡
በከመ፡ዕበየ፡ምሕረትከ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡
እ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ስምዐነ፡ወመ
ሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ።

፮ ይ፡ካ፡ናስተበቍዕ፡አፍቅሮተከ፡ሰብአ፡እ፡
እግዚኦ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ፡ናስተበቍዕ፡
ኀቤከ፡እ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ስምዐነ፡
ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ትእዛዝ፤መቶኛ፡የዳዊት፡መዝሙር፤ምሕረተ፡
ወፍትሐ። መቶ፡ዐሥረኛ፡እገኒ፡ለከ፡እግዚእ፡
በኵሉ፡ልብየ። መቶ፡ዐሥራ፡ሦስተኛ፡እመ፡
ይወፅኡ፡እስራኤል፡እምግብጽ። ስልሳ፡
ስምንተኛ፡አድኅነኒ፡እግዚኦ፡እስመ፡በጽሐኒ፡
ማይ፡እስከ፡ነፍስየ።እነዚህን፡በል።

ቄስ፡ወይም፡ዲያቆን፡ይህን፡የልመና፡ቃል፡
ስለ፡በእንተ፡ቅድሳት፡ፈንታ፡ይበል።

ሕዝቡም፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡እያሉ፡በየም
ዕራፉ፡ይመልሱ።

፩፤ እንደ፡አገልጋይ፡ሽርጥ፡የታጠቅህና፡
የአዳምን፡ዕርቃን፡የሸፈንህ፡ሆይ፡እኛንም፡
አምላካዊ፡በሆነች፡በልጅነት፡ልብስ፡ያገኖና
ጸፍህ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፤ራራልን፡ስማንም።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፤ይበሉ፡በየም
ዕራፉ።

፪፤ ካህኑ፡ስለ፡ሰው፡ፍቅር፡ሰው፡የሆንህ፡ስለ፡
ፍቅርም፡ከፍተኛነት፡ሽርጥ፡(ዝናር)፡ታጥቀህ፡
የደቀ፡መዛሙርትህን፡እግር፡ያጠብህ፡የኃጢአ
ታችንንም፡እድፍ፡አጥፋ፤(እንጻን)፡ይበል።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፫፤ ካህኑ፡ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ወዳንተ፡
እንማልዳለንና፡ስማን፡ይቅር፡በለን፤ይበል።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፬፤ ካህኑ፡በውኃ፡ላይ፡የሄድህ፡ፈጣሪያችን፡
ክርስቶስ፡ሆይ፡ሰውን፡በመውደድህ፡የደቀ፡
መዛሙርትን፡እግር፡ያጠብህ፡ወዳንተ፡እንማ
ልዳለንና፡ስማን፤ይቅርም፡በለን፡ይበል።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፭፤ ካህኑ፡አምላካችን፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡
ገናናነት፡መጠን፡ሁላችንንም፡ማረን፤ፈጣሪ
ያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ወዳንተ፡እንማልዳ
ለንና፡ስማን፡ይቅርም፡በለን፡ይበል።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፮፤ ካህኑ፡አቤቱ፡ሰው፡ወዳጅነትህን፡እንማል
ዳለን፤አቤቱ፡ስማን፤ማረን፤ወዳንተ፡እንማ
ልዳለንና፡አምላካችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡
ስማን፤ይቅር፡በለን፡ይበል።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፯፡ ይ፡ካ፡ አ፡እግዚአ፡አምላክነ፡ እኅዜ፡ ኵሉ፡ ወሀቤ፡ጸጋ፡አምላካዊት፡ ለእለ፡ይትለአኩ፡ ለስምከ ፡ ቅዱስ ፡ ዘያበቍል ፡ ወያበዝኅ ፡ ወየሐፅን ፡ ወይሴስዮ ፡ ለነ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ እንዘ፡ኢይደልወነ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡ አ፡ አምላክነ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚአ፡ተሣሃለነ።

፰፡ ይ፡ካ፡አ፡ዘተሐውር፡ላዕለ፡ደመናት፡ወታስ ተጋብእሙ ፡ ለማያት ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ምጉባእ፡ወረሰይከ፡ሎሙ፡ወሰነ፡ሥሙረ፡ በላዕለ ፡ ማያት ፡ ናስተበቍዕ ፡ ኀቤከ ፡ አ ፡ አምላክነ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚአ፡ተሣሃለነ።

፱፡ ይ ፡ ካ ፡ አ ፡ ዘሐፈንከ ፡ ማያተ ፡ በሕፍንከ ፡ ወሰማያተ ፡ በስዝርከ ፡ ወኵሎ ፡ ፍጥረት ፡ ውስተ ፡ እራኀከ ፡ ናስተበቍዕ ፡ ኀቤከ ፡ አ ፡ አምላክነ፡መሐረነ፡ወስምዐነ።

ይ፡ሕ፡እግዚአ፡ተሣሃለነ።

፲፡ ይ ፡ ካ ፡ አ ፡ ዘረሰይከ ፡ አንቅዕተ ፡ አፍላግ ፡ ይሑሩ፡ በከመ ፡ ሥምረትከ ፡ ቅዱስ ፡ አ ፡ መፍቀሬ፡ሰብእ፡ዘኢይትረከብ፡አስተዳሎከ፡ ለነ፡ኵሎ፡ለቅኔ፡ወፈጠርከ፡ኵሎ፡እምኀበ፡ ኢሀሎ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡ አ፡ ክርስቶስ፡ አምላክነ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚአ፡ተሣሃለነ።

፲፩፡ ይ፡ካ፡ አ፡ ወሀቤ፡ጸጋ፡ዘበአማን፡ወዐቢይ፡ መፍቀሬ፡ሰብእ፡አምላክ፡ምሕረት፡ሐውጽ፡ ምድረ፡ኢትዮጵያ፡በረድኤትከ፡ወአርውያ፡ በርደተ፡ዝናም፡ሠናይ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡ አ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚአ፡ተሣሃለነ።

፲፪፡ ይ ፡ ካ ፡ አ ፡ እግዚአ ፡ አስተፍሥሕ ፡ ገጸ ፡ ለምድር፡በርደተ፡ዝናም፡ሠናይ፡በበ፡መጠኑ፤ ወአርዊ፡ትለሚሃ፤ወአብዝኅ፡እክለ፡ምድረ፡ ኢትዮጵያ፡በርደተ፡ዝናማት፡በከመ፡ሕጉ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፯፡ ካህኑ ፤ የሚያበቅል ፡ የሚያበዛ ፡ የሚያሳድግ፡ ሳይገባን ፡ እኛን ፡ አገልጋዮቹን ፡ የሚመግብ፡ የከበረ ፡ ስምህን ፡ ለሚያመሰግኑ ፡ አምላካዊት፡ ሀብትን ፡ የምትሰጥ ፡ ሁሉን ፡ የፈጠርከ ፡ አቤቱ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንማልዳለን፤ አቤቱ፡ አምላካችን፡ ስማን፤ማረን፡ይበል።

ሕዝቡ፡ አቤቱ፡ ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፰፡ ካህኑ ፤ በደመናት ፡ ላይ ፡ የምትሄድ ፡ ውኃዎ ችንም፡ በአንዲት ፡ መሰብሰቢያ ፡ ውስጥ ፡ የም ትሰበስባቸው ፤ ለውኃዎቹም ፡ ያማረ ፡ የሠመረ፡ ወሰን ፡ የምታደርግላቸው ፡ ፈጣሪ ያችን ፡ ሆይ ፡ ወዳንተ ፡ እንማልዳለን፤አቤቱ፡ አምላካችን፡ ስማን፤ይቅር፡በለን፡ይበል።

ሕዝቡ፡ አቤቱ፡ ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፱፡ ካህኑ ፤ ውኃዎችን ፡ በዕፍኝህ ፡ የዘገንህ ፡ ሰማ ችንም ፡ በስንዝርህ ፡ የለካህ ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ፡ በመሐል ፡ እጅህ ፡ የያዝህ አቤቱ፡ ፈጣሪያችን፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንማልዳለን፤ አምላካችን፡ ይቅር፡በለን፤ስማን።

ሕዝቡ፡ አቤቱ፡ ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፲፡ ካህኑ ፤ ክቡር ፡ በሆነ ፡ ፈቃድህ ፡ የወንዞችን፡ ምንጮች ፡ እንዲሄዱ ፡ የምታደርግ ፡ ሰው ወዳድ ፡ ሆይ ፡ የማይገኘውን ፡ ለሰው ፡ ተግባር፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አዘጋጅተህ ፡ ካለመኖር፡ ወደ ፡ መኖር ፡ አምጥተህ ፡ ፈጠርኸ፤ አቤቱ፡ ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ ስማን፤ትምረን፡ ዘንድ፡ወደ፡አንተ፡እንማልዳለን፡ይበል።

ሕዝቡ፡ አቤቱ፡ ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፲፩፡ ካህኑ፤ የምሕረት ፡ ባለቤት ፡ ሰውን ፡ የምትወድ፡ በዕውነት ፡ ታላቁን ፡ ስጦታ ፡ ልጅነትን ፡ የሰጠህ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምድር ፡ በረድኤትህ ፡ ጎብኝ፡ የምሕረት ፡ ዝናምንም ፡ በማውረድ ፡ የረካች፡ አድርጋት፤ አቤቱ፡ አምላካችን፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፡ ስማን፤ይቅር፡በለን፤ወደ፡አንተ፡እንማልዳለን፡

ሕዝቡ፡ አቤቱ፡ ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

፲፪፡ ካህኑ፤ አቤቱ፡ የምሕረትን፡ዝናም፡በየመጠኑ በማውረድ ፡ የምድርን ፡ ገጽ ፡ ደስ ፡ አሰኝ፡ ትልሟንም፡ አርካ፤ ዝናሙንም ፡ እንደ ፡ ሕጉ፡ በማውረድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምድር ፡ እህል፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወረስዮ ፡ ቡሩክ ፡ ናስተበቍዕ ፡ ኀቤከ ፡
እ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ መሐረነ ፡ ወስ
ምዐነ።

ይ፡ሕ፡እግዚእ፡ተሣሃለነ።
፲፫ ይ፡ካ፡ ባርክ ፡ አክሊለ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረትከ ፡
በኂሩትከ ፡ ወበምሕረትከ ፤ ወምልዖሙ ፡
ቅብዐ፡ ለአሕቃለ ፡ ሣዕረ ፡ ኢትዮጵያ ፤
ወይብዝኁ፡ገራውሂሃ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡
እ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ስምዐነ ፡ ወመ
ሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚእ፡ተሣሃለነ።
፲፬ ይ፡ካ፡ለይትፈሥሓ፡አሕቃላተ፡አድያማተ፡
ኢትዮጵያ ፡ ወይትሐሠያ ፡ አውግር ፡ በበረ
ከትከ፡ወእምነ፡ኂሩትከ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡
እ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ስምዐነ ፡ ወመ
ሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚእ፡ተሣሃለነ።
፲፭ ይ፡ካ፡ አድኅን ፡ እግዚእ ፡ ሕዝበከ ፡ ወባርክ ፡
ርስተከ፤ሐውጽ፡ኵሎ፡በሣህልከ፡ወበምሕ
ረትከ፡ወአልዕል፡ቀርነ፡ክርስቲያን፡በኃይለ፡
መስቀልከ፡ማሕየዊ፡ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡
እ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ስምዐነ ፡ ወመ
ሐረነ።

ይ፡ሕ፡እግዚእ፡ተሣሃለነ።
፲፮ ይ፡ካ፡ጸጕ፡ጥዒና፡ለሕዝብከ፡ወለሀገሪትነ፡
ኢትዮጵያ ፡ በኂሩትከ ፡ ዕቀባ ፡ በኵሎን ፡
አዝማን፤ወፈኑ፡ዝናመ፡ውስተ፡ፍና፡ኀበ፡
ዘይትፈቀድ፡መካን፡እምኀበ፡ኂሩትከ፤ጸጕ፡
ዕረፍተ፡ለነዳያን፡ሕዝብከ።
፲፯ ወምላዕ ፡ ውስተ ፡ አልባቢነ ፡ ፍሥሓ ፡
ወሐሤተ ፡ በአስተብቍዖታ ፡ ለእምከ ፡
ድንግል ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ወቅዱስ ፡
ዮሐንስ፡ መጥምቅ ፡ ወአበዊነ ፡ ሐዋርያት ፤
ንስእለከ፡እግዚእ፡ስምዐነ፡ወመሐረነ፡ወተሣ
ሃለነ፡ሕዝበከ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

መልእክተ፡ጳውሎስ፡ቀዳማዊ፡ኀበ፡
ጢሞቴዎስ።

ምዕ፤፩፡፱–፲፮።

፩ እሙን ፡ ነገሩ ፡ ወርቱዕ ፡ ይትወከፍዎ ፡
በኵሉ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

አብዛ፤ለበረከትም፡አድርገው፤አቤቱ፡ፈጣሪ
ያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ወደ፡አንተ፡እንማልዳ
ለንና፡ስማን፤ይቅር፡በለን፡ይበሉ።
ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።
፲፫ ካህኑ ፡ በቸርነትህ ፡ ዘመን ፡ የተገኘውን ፡
እህሉን፡በፍጹም፡ቸርነትህ፡ባርክ፤የኢትዮጵ
ያንም፡በረኻዎች፡ማሩን፡ቅቤውን፡የቅባት፡
እህሎች ፡ የሚገኝበትን ፡ ሣሩን ፡ ምላባቸው ፤
እርሻዎቿም ፡ ይብዙ ፡ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡
ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንማልዳለን ፤
ስማን፤ይቅርም፡በለን፤ይበል።
ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።
፲፬ ካህኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ የሚገ
ኙትን፡በረኻዎች፡በልምላሜና፡በጠል፡ደስ፡
አሰኝ፤ኮረብታዎችም፡ከቸርነትህ፡በሚገኝ፡
በረከትህ፡ደስ፡ይሰኙ፤አቤቱ፡ፈጣሪያችን፡
ክርስቶስ፡ሆይ፡ ስማን ፤ ይቅር ፡ በለን ፤ ወደ ፡
አንተ፡እንማልዳለን፤ይበል።
ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።
፲፭ ካህኑ፡አቤቱ፡ሕዝብህን፡አድን፤ርስትህንም፡
ባርክ ፤ (ካህናቱን ፡ አክብር) ፤ በይቅርታህና ፡
በቸርነትህ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ በረድኤት ፡
ጎብኝ፤አዳኝ፡በሆነ፡በመስቀልህም፡የክርስቲ
ያንን፡ሥልጣን፡ከፍ፡ከፍ፡አድርግ፤አቤቱ፡
አምላካችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ስማን፤ይቅርም፡
በለን፤ወደ፡አንተ፡እንማልዳለን፡ይበል።
ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበሉ።
፲፮ ካህኑ፡ለወገኖችህ፡ጤንነትን፡ስጥ፤ሀገራችን፡
ኢትዮጵያንም፡በዘመናቱ፡ሁሉ፡በቸርነትህ፡
ጠብቃት፤በሚፈለግበትም፡ቦታ፡ከቸርነትህ፡
የተገኘውን ፡ ዝናም ፡ ላክ ፤ ለድሆች ፡ ወገኖ
ችህም፡እረፍትን፡ስጥ።
፲፯ በእናትህ፡በቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡እማ
ላጅነት ፤ በመጥምቁ ፡ ዮሐንስና ፡ በአባቶ
ቻችን፡ በሐዋርያት ፡ አማላጅነት ፡ ተድላና ፡
ደስታን፡በልቡናችን፡ሙላል አቤቱ፡እንለ
ምንሃለንና፡እኛን፡ወገኖችህን፡ስማን፤ማረን፤
ራራልን፤ለዘላለሙ፡አሜን።

ክፍል፡፫።

መጀመሪያ፡የጳውሎስ፡መልእክት፡
ወደ፡ጢሞቴዎስ።

ምዕ፤፩፡፱–፲፮።

፱ ነገሩ፡ዕውነት፡ነው፤በሁሉም፡ሊቀበሉት፡
ይገባል።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፤ እስመ ፡ በእንተዝ ፡ ንሥርሕ ፡ ወንጼእል ፡
እስመ፡ ተወከልነ፡ በእግዚአብሔር፡ ሕያው፡
ወማሕየዊ፡ለኵሉ፡ሰብእ፡ወፈድፋደሰ፡ለመ
ሀይምናን።
፲፩፤ ከመዝ፡መሀር፡ወገሥጽ።
፲፪፤ ወአልቦ ፡ ዘያስተአብዳ ፡ ለውርዙትከ ፤
ወኩኖሙ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለመሃይ
ምናን፡በቃልከ፡ወበምግባሪከ፡በፍቅር፡ወበሃ
ይማኖት፡ወበንጽሕ።
፲፫፤ ወተዐቀብ ፡ እስከ ፡ እመጽእ ፡ በአንብቦ ፡
ወበምሂር፡ወበገሥፆ፡ወበጸልዮ።
፲፬፤ ወኢታስትት፡ጸጋሁ፡ዘላዕሌከ፡ዘተውህበከ፡
ምስለ፡ተነብዮ፡ወምስለ፡ሢመተ፡እዴሆሙ፡
ለጳጳሳት።
፲፭፤ ዘንተ ፡ አንብብ ፡ ወበዝ ፡ ሀሉ ፡ ከመ ፡
ይትዐወቅ፡ሥላጤከ፡በኵለሄ።
፲፮፤ ዑቅ ፡ እንከ ፡ ርእሰከ ፡ በእንተ ፡ አንብቦ ፡
ወዘልፈ፡ሀሉ፡ባቲ፡ወእመሰ፡ዘንተ፡ገበርከ፡
ርእሰከሂ፡ታድኅን፡ወዘሂ፡ይሰምዐከ።

፩ኛ፡ጢሞ፡ምዕ፤፭፤፩-፲።

፩፤ ሊቃናተ ፡ ኢታመጕጽ ፡ ተአዘዝ ፡ ከመ ፡
ዘለአቡከ፡ወለንዑሳን፡ከመ፡ዘለአኀዊከ።
፪፤ ወለልሒቃትኒ ፡ ከመ ፡ ዘለእምከ ፡ ወለንዑ
ሳትኒ፡ከመ፡ዘለአኀቲከ፡በኵሉ፡ንጽሕ።
፫፤ ወአክብር፡ዕቤራተ፡በጽድቅ።
፬፤ ወእመቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዕቤር ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡
ውሉድ ፡ አው ፡ ደቂቀ ፡ ውሉድ ፡ ይትመሀሩ ፡
ቅድመ፡አሠንዮ፡ለቤቶሙ፡ወይዕስዩ፡አዝማ
ዲሆሙ ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ሠናይ ፡ ወሥሙር ፡
በቅድመ፡እግዚአብሔር።
፭፤ ወእንተሰ፡ዕቤር፡በአማን፡ንጽሕት፡እንተ፡
ባሕቲታ፡ትነብር፡እስመ፡ትውክልታ፡እግዚ
አብሔር ፡ ባሕቲቱ ፡ ትፀመድ ፡ ጸሎተ ፡
ወትስእል፡መዐልተ፡ወሌሊተ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፤ ስለዚህ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ ለምእ
መናን ፡ አዳኝና ፡ ሕያው ፡ በሆነው ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ስም ፡ ስለአመን ፡ እንደክማለን ፤ እንገ
ደባለንም።
፲፩፤ እንዲህ፡ምከር፤አስተምር።
፲፪፤ ወጣትነትህን ፡ የሚንቃት ፡ አይኑር፤በፍቅር፤
በሃይማኖት ፡ በንጽሕና ፡ ፀንተህ ፡ በቃልህም፤
በሥራህም፡ለምእመናን፡ምሳሌ፡ሁናቸው።
፲፫፤ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ በማንበብ ፡ በማስተማር፤
በመምከር፡በመጸለይ፡ጸንተህ፡ኑር።
፲፬፤ ትንቢት ፡ ከመናገርና ፡ በጳጳሳት ፡ እጅ፡ከተሾ
ከው ፡ ሹመት ፡ ጋር ፡ የተሰጠህን፡ባንተ፡ላይ፡ያደ
ረገውን፡የእግዚአብሔርን፡ጸጋ፡አታቃልል።
፲፭፤ ፍጹምነትህ፡በሁሉ፡ይታወቅ፡ዘንድ፡ይህን፡
አንብብ፤በዚህም፡ጸንተህ፡ኑር።
፲፮፤ እንግዲህ ፡ መጽሐፍን ፡ ስለ ፡ ማንበብ ፡ ራስህን፡
ዕወቅ፤ዘወትር፡በዚያው፡ጸንተህ፡ኑር፤ይህንንብታ
ደርግ፡ራስህንም፡የሚሰማህንም፡ታድናለህ።

፩ኛ፡ጢሞ፡ምዕ፤፭፤፩-፲።

፩፤ ሽማግሌዎችን ፡ አታዋርድ ፤ ለአባትህ፡እንደ
ምትታዘዝ ፡ ለታናናሾችም ፡ ለወንድሞችህ፡
እንደምትታዘዝ፡ታዘዝ።
፪፤ ለባልቴቶችም ፡ ለእናትህ ፡ እንደምትታዘዝ፡
ታዘዝ፤ለታናናሾችም፡ለእኅቶችህ፡እንደምት
ታዘዝ፤በፍጹም፡ንጽሕና፡ሁነህ፡ታዘዝ።
፫፤ ባልቴቶችን፡በዕውነት፡አክብር፤ዕርዳ።
፬፤ ከእነርሱ፡ወገን፡ልጅ፡ወይም፡የልጅ፡ልጅ፡
ያላት ፡ ባልቴት ፡ ብትኖር ፡ አስቀድሞ፡
ለቤታቸው፡በጎ፡ማድረግን፡ይማሩ፤ዘመዶ
ቸውንም፡ይርዱ፤እንዲህ፡ያለው፡በእግዚአ
ብሔር፡ፊት፡ያማረ፡የተወደደ፡ነውና።
፭፤ ብቻዋን ፡ የምትኖር ፡ በዕውነት ፡ ንጽሕት፡
የሆነች ፡ ባልቴት ፡ ግን ፡ ተስፋዋ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ብቻ፡ነውና፡ለጸሎት፡ጽሙድ፡ሆና፡
(ጸንታ) ፡ ትኖራለች ፤ በቀንም ፡ በሌሊትም፡
ትለምናለች።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወእንተሰ ፡ ትፌግዕ ፡ ምስለ ፡ ተውኔት ፡
ምውት፡ይእቲ፡እንዘ፡ሕያዋ።
ወከመዝ፡ገሥጽ፡ከመ፡ኢያድልዉ፡ወኢያ
መክንዩ።
ወዘሰ ፡ ኢይኄሊ ፡ ለቤቱ ፡ ወይገድፍ ፡
አዝማዲሁ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡
እምሰብእ ፡ ሃይማኖት ፡ ውእቱ ፡ ክሕደ ፡
ሃይማኖቶ፡ወየአኪ፡እምዘኢየአምን።
ወለእመ፡ኀረይከ፡ዕቤረ፡ኅረይ፡እንተ፡ስሳ፡
ክረምታ፡እንተ፡አሐደ፡ብእሴ፡አውሰበት።

ብእሲት፡እንተ፡ይንዕድዋ፡በኵሉ፡ምግባረ፡
ሠናይ፡ለእመ፡አልሐቀት፡ውሉዳ፡ወለእመ፡
ነግደ፡ተወክፈት፡ወለእመ፡እግረ፡ጻድቃን፡
ሐፀበት፡ወለእመ፡ርኁበ፡አጽገበት፡ወኵሎ፡
ምግባረ፡ሠናይ፡ለእመ፡ተለወት።
ወይበሉ፡ሕዝብ፡ቅዱስ፡ሐዋርያ፡ጳውሎስ።

ወይበል ፡ ካህን ፡ ጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ **እግዚአ
ብሔር፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።**

**ይ፡ዲ፡**ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፶፡፯፤፲።
ትነዝኀኒ፡በአዛብ፡ወእነጽሕ።

ተኀፅበኒ፡እምበረድ፡ወእጻዐዱ።

ልበ፡ንጹሐ፡ፍጥር፡ሊተ፡**እግዚእ።**

ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፤፲፫፡፩–፲፱።
ወእምቅድመ፡በዐለ፡ፋሲካ፡ሶበ፡ኮነ፡የአምር፡
**እግዚእ፡ኢየሱስ፡**ከመ፡በጽሐ፡ጊዜሁ፡ከመ፡
ይፍልስ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡ወየኀውር፡ኀበ፡
አብ፡ዘፈነዎ፡አፍቀሮሙ፡ለእሊአሁ፡እለ፡
ውስተ፡ዓለም፡ወለዝሉፉ፡አፍቀሮሙ።
ወእንዘ፡ይዴረሩ፡ቦአ፡ሰይጣን፡ውስተ፡
ልበ፡ይሁዳ፡ስምዖን፡አስቆሮታዊ፡ከመ፡
ያግብኦ።
ወሶበ፡ኮነ፡የአምር፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡**ከመ፡
አወፈዮ፡**አብ፡**ኵሎ፡ውስተ፡እዴሁ፡ወከመ፡
እምኀበ፡**እግዚአብሔር፡**ወፅአ፡ወኀበ፡**እግዚ
አብሔር፡**የሐውር።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፮፤ ከዘፈን፡ከጨዋታ፡ጋር፡ተድላ፡ደስታ፡የምታ
ደርግ፡ግን፡በሕይወት፡ሳለች፡የሞተች፡ናት።
፯፤ እያመካኙ ፡ እንዳያደሉ ፡ እንዲህ ፡ ምከር ፤
አስተምር።
፰፤ ለቤቱ ፡ የማያስብ ፡ ዘመዶቹን ፡ የሚጥል ፡
ይልቁንም ፡ ከሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡
ሲሆን፡እርሱ፡ሃይማኖቱን፡ክዶአል፤ከማያ
ምነውም፡ይከፋል።
፱፤ ባልቴትን ፤ ብትመርጥ ፡ ዕድሜዋ ፡ ስልሳ ፡
ዘመን ፡ የሆናትን ፡ አንድ ፡ ባል ፡ ያገባች ፡
ባልቴትን፡ምረጥ።
፲፤ በፍጹም፡በጎ፡ምግባር፡የሚያመሰግኑዋት፡ሴት፡
ልጆቿን፡በሥርዓት፡ካሳደገች፡እንግዳን፡ከተቀ
በለች ፡ የድኆችን ፡ እግር ፡ ካጠበች ፡ የተራበ
ውንም፡ ካጠገበች ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ ከተከ
ተለች፡እርሷን፡ምረጥ።
ሕዝቡ ፡ በዜማ ፡ የተመሰገነ ፡ ሐዋርያ ፡
ጳውሎስ፡ይበሉ።
ካህኑም ፡ ጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ **እግዚአብሔር ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ይበል።

**ዲያቆኑ፡**ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፤፶፡፯፤፲።
በአውባን ፡ ቅጠል ፡ ትረጨኛለህ ፤ እኔም ፡
ንጹሕ፡እሆናለሁ።
ታጥበኛለህ፤እኔም፡ከበረዶ፡ይልቅ፡ንጹሕ፡
እሆናለሁ።
**አቤቱ፡**ንጹሕ፡ልብን፡ፍጠርልኝ፡ይበል።

የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፫፡፩–፲፱።
፩፤ ከፋሲካ፡በዐል፡አስቀድሞ፡**ጌታ፡ኢየሱስ፡**
ከዚህ፡ዓለም፡በሞት፡ተለይቶ፡ወደ፡አብ፡
የሚሄድበት ፡ ቀን ፡ ጊዜው ፡ እንደደረሰ ፡
ያውቅ፡ ነበረና፡በዓለም፡ያሉት፡ወገኖቹን፡
ወደዳቸው፤ለዘላለምም፡ወደዳቸው።
፪፤ እራትም፡ሲበሉ፡እንዲያስይዘው፡ስምዖን፡
በሚባለው፡በአስቆሮቱ፡ሰው፡በይሁዳ፡ልብ፡
ሰይጣን፡አደረ።
፫፤ **ጌታ፡ኢየሱስም፡አብ፡**ሁሉን፡በእጁ፡እንደሰ
ጠውና፡**ከእግዚአብሔር፡**እንደወጣ፡ወደ፡
**እግዚአብሔርም፡**እንዲሄድ፡ባወቀ፡ጊዜ፤
(የሚያውቅ፡ስለሆነ)።

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፬፡ ተንሥአ ፡ እምኀበ ፡ ይዴረሩ ፡ ወአንበረ ፡ አልባሲሁ ፡ ወነሥአ ፡ መክፈ ፡ ዘለንጽ ፡ ወቀነተ፡ሐቌሁ። | ፬፡ እራት ፡ ከሚበሉበት ፡ ተነሥቶ ፡ ልብሱን፡ አኖረና፡ሽርጥ፡(ዝናር)፡ወስዶ፡ታጠቀ። |
| ፭፡ ወወደየ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡ ንብቲራ ፡ ወአኀዘ ፡ ይኀፅብ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ወመዝመዘ፡በውእቱ፡መክፈ፡ዘቀነተ። | ፭፡ በኰስኰስቱም፡ውኃ፡ጨምሮ፡የደቀ፡መዛሙ ርቱን ፡ እግር ፡ ያጥብ ፡ ጀመር ፤ በዚያ ፡ በታጠ ቀበት፡ሽርጥም፡(ግልድም)፡ወለወለ። |
| ፮፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤሎ ፡ አንተኑ፡**እግዚኦ**፡ዘተኀፅበኒ፡እገርየ። | ፮፡ ወደ፡ስምዖን፡ጴጥሮስም፡በደረሰ፡ጊዜ፡**አቤቱ**፡ እግሬን፡የምታጥበኝ፡አንተ፡ነህን?አለው። |
| ፯፡ ወአውሥአ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ** ፡ ወይቤሎ ፡ ዘእገብር ፡ አነ ፡ አንተ ፡ ኢተአምር ፡ ይእዜ ፡ ወባሕቱ፡ድኅረሰ፡ተአምሮ። | ፯፡ **ጌታ ፡ ኢየሱስም** ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ አንተ፡ ዛሬ ፡ አታውቅም ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ታውቀዋለህ፡ ብሎ፡መለሰለት። |
| ፰፡ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢትኀፅበኒ ፡ እገርየ ፡ ለዓለም፡ ወአውሥአ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ** ፡ ወይቤሎ ፡ አማን ፡ አማን ፡ እብለከ ፡ እመ ፡ አነ ፡ ኢኀፀብኩከ፡እገሪከ፡አልብከ፡ክፍል፡ምስሌየ። | ፰፡ ጴጥሮስም፡ለዘላለሙ፡አንተ፡እግሬን፡አታጠ ኝም ፡ አለው ፤ **ጌታ ፡ ኢየሱስም** ፡ እውነት፡እው ነት፡እልሃለሁ፤እኔ፡እግርህን፡ካላጠብኩህ፡ከእኔ፡ ጋራ፡ዕድል፡ፈንታ፡የለህም፡ብሎ፡መለሰለት። |

ዘከመ ኀፀበ እግዚእነ እግረ አርዳኢሁ።



ጌታችን የደቀ መዛሙር ቱን እግር እንደ አጠበ

| | |
|---|---|
| ፱፡ ወይቤሎ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ **እግዚኦ** ፡ አኮ ፡ እገርየ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘተኀፅበኒ ፡ ወዓዲ ፡ እደውየኒ፡ወርእስየኒ። | ፱፡ ስምዖን፡ጴጥሮስም፡**አቤቱ**፡እንኪያስ፡የምታ ጥበኝ፡እግሬን፡ብቻ፡አይደለም፤እጆቼንም፡ ራሴንም፡እንጂ፡አለው። |
| ፲፡ ወይቤሎ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ** ፡ ዘሰ ፡ ወድአ ፡ ተኀፅበ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ይትኀፀብ ፡ ዘእንበለ ፡ እገሪሁ፡ዳእሙ፡እስመ፡ንጹሕ፡ኵለንታሁ፡ ወአንትሙሰ፡ንጹሓን፡አንትሙ፡ወባሕቱ፡ አኮ፡ኵልክሙ፡ንጹሓን። | ፲፡ **ጌታ ፡ ኢየሱስም** ፡ መላ ፡ አካሉን ፡ ፈጽሞ፡ የታጠበ፡ከእግሩ፡ብቻ፡በቀር፡ሌላ፡አካሉን፡ ሊታጠብ ፡ አይሻም ፤ ሁለንተናው ፡ ንጹሕ፡ ነውና ፤ እናንተም ፡ ንጹሓን ፡ ናችሁ ፤ ነገር፡ ግን፡ሁላችሁ፡ንጹሓን፡አይደላችሁም። |
| ፲፩፡ እስመ፡የአምር፡**እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ዘያገብኦ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤ ፡ አኮ ፡ ኵልክሙ ፡ ንጹሓን። | ፲፩፡ **ጌታ ፡ ኢየሱስ** ፡ የሚያሲይዘውን ፡ የውቅ ነበረና፡ ስለዚህ ፡ ሁላችሁ ፡ ንጹሓን ፡ አይደላ ችሁም፡አለ። |
| ፲፪፡ ወሶበ፡ኀፀቦሙ፡እገሪሆሙ፡ነሥአ፡አልባሲሁ፡ ወረፈቀ፡ካዕበ፡ምስሌሆሙ፡ወይቤሎሙ፡አእ መርክሙኑ፡ዘገበርኩ፡ለክሙ። | ፲፪፡ እግራቸውን፡ካጠባቸው፡በኋላ፡ልብሱን፡ለብሶ፡ ተቀመጠ፡እን ዳግመኛ፡አብሮአቸው፡በማእድ፡ተቀመጠ፡ያደ ረግሁላችሁን፡አወቃችሁን?አላቸው። |

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፫ አንትሙሰ ፡ ትብሉኒ ፡ ሊቅነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ወሠናየ፡ትብሉ፡እስመ፡ከማሁ፡አነ።

፲፬ ወሶበ፡አነ፡እንከ፡እንዘ፡ሊቅክሙ፡ ወእግዚእክሙ፡ኀፀብኩክሙ፡እገሪክሙ፡ ከማሁኬ፡ አንትሙኒ ፡ ይደልወክሙ ፡ ትኅፅቡ ፡ እግረ ፡ ቢጽክሙ።

፲፭ እስመ፡አርአያየ፡ወሀብኩክሙ፡ከመ፡ትግበሩ፡ አንትሙኒ፡በከመ፡ገበርኩ፡ለክሙ፡አነ።

፲፮ አማን ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ አልቦ ፡ ገብር ፡ ዘየዐቢ ፡ እምእግዚኡ ፡ ወአልቦ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘየዐቢ፡እምዘፈነዎ።

፲፯ ወእመሰ፡ዘንተ፡ተአምሩ፡ብፁዓን፡አንትሙ፡ እመ፡ገበርክምዎ።

፲፰ ወአኮ፡በእንተ፡ኵልክሙ፡ዘእብል፡ዘንተ፡ እስመ፡አነ፡አአምር፡መኑ፡እሙንቱ፡እለ፡ ኀረይኩ፡ወባሕቱ፡ከመ፡ይብጻሕ፡ቃለ፡ መጽሐፍ ፡ ዘይቤ ፡ ዘይሴሰይ ፡ እክልየ ፡ አንሥአ፡ሰኰናሁ፡ላዕሌየ።

፲፱ ወይእዜሰ ፡ እነግረክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ አመ ፡ ኮነ ፡ ትእመኑ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ውእቱ።

### ትእዛዝ።

ይ፡ካ፡እግዚእ፡መሐረነ፡ክርስቶስ፡ሠለስተ፡ ጊዜ፡በዐቢይ፡ዜማ።
ይ፡ሕ፡ከማሁ፤
ይ፡ካ፡ኪርያላይሶን፡አርብዓ፡ወአሐደ፡ጊዜ፡ በንኡስ፡ዜማ።
ይ፡ሕ፡ከማሁ።
ይ፡ካ፡ጸሎት፡በእንተ፡ሰላም፡ወበእንተ፡ ርእሰ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ወበእንተ፡ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ጳጳሳት፡ወኤጲስ፡ቆጶሳት፡ ወበእንተ፡ማኅበር።
ይ፡ሕ፡ጸሎተ፡ሃይማኖት፤እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ ሐመ።
ይ፡ዲ፡ቁሙ፡ወአጽምዑ፤ውስተ፡ጽባሕ፡ ነጽሩ፤ይ፡ሕ፡ምሕረት፡ወሰላም፡ወቡሩክ፡ ኀፀበት፤ይ፡ካ፡ሰላም፡ለኵልክሙ፤ይ፡ሕ፡ ምስለ፡መንፈስከ፤ይ፡ካ፡አልዕሉ፡አልባ ቢክሙ፤ይ፡ሕ፡ብነ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ አምላክነ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፫፡ እናንተ ፡ ጌታችን ፡ መምህራችን ፡ ትሉኛ ላችሁ ፤ መልካም ፡ ትላላችሁ ፤ እንዲሁ ፡ ነኝና።

፲፬፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ጌታችሁ ፡ መምህራችሁ ፡ ስሆን፡እግራችሁን፡ካጠብኋችሁ፡እናንተም፡ እንዲሁ ፡ የወንድሞቻችሁን ፡ እግር ፡ ልታጥቡ፡ይገባችኋል።

፲፭፡ እኔ፡እንዳረግሁላችሁ፡እናንተም፡ታደርጉ፡ ዘንድ፡ምሳሌነቴን፡ሰጥቻችኋለሁና።

፲፮፡ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ ከጌታው ፡ የሚበልጥ ፡ ባርያ ፡ ከላኪውም ፡ የሚበልጥ ፡ መልእክተኛ፡የለም።

፲፯፡ ይህን፡አውቃችሁ፡ከሠራችሁ፡ግን፡ብፁዓን፡ ናችሁ።

፲፰፡ ግን ፡ ይህን ፡ የምናገር ፡ ስለ ፡ ሁላችሁ ፡ አይደለም ፤ የመረጥኋቸው ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ፡እኔ፡አውቃለሁና፤ነገር፡ግን፡እንጀ ራዬን፡የሚመገብ፡ተረከዙን፡በእኔ፡ላይ፡ አነሣ፡ብሎ፡መጽሐፍ፡የተናገረው፡ይደርስ፡ ይፈጸም፡ዘንድ፡ነው።

፲፱፡ አሁን፡ግን፡ሳይደረግ፡አስቀድሞ፡እነግራች ኋለሁ ፤ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እንደሆንኩ ፡ ታምኑ፡ዘንድ።

### ትእዛዝ።

ካህኑ፡በታላቅ፡ዜማ፡ሦስት፡ጊዜ፡እግዚእ፡ መሐረነ፡ክርስቶስ፡ይበል።
ሕዝቡም፡እንደ፡እሱ፡ይበሉ።
ካህኑ፡በንኡስ፡ዜማ፡አርባ፡አንድ፡ጊዜ፡ኪር ያላይሶን፡ይበል።
ሕዝቡም፡እንደ፡እሱ፡ይበሉ።
ስለ፡ሰላም፡ስለ፡ርእሰ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ስለ፡ ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ስለ፡ጳጳሳት፡ስለ፡ኤጲስ፡ ቆጶሳትና፡ስለ፡ማኅበር፡የሚጸለየውን፡ ጸሎት፡ካህኑ፡ይጸልይ።
ሕዝቡ፡የሃይማኖት፡ጸሎት፡ሐመ፡እስኪል፡ ድረስ፡ይበሉ።
ዲያቆኑ፡ ቁሙ፡አድምጡ፡ወደ፡ ምሥራቅም፡ተመልከቱ፡ይበል፤ሕዝቡ፡ቸር ነት፡ፍቅር፡አንድነት፡የተባረከ፡ኀፀበት፡ይበሉ፤ ካህኑ፡ለሁላችሁም፡ፍቅር፡አንድነት፡ይሁን፡ ይበል። ሕዝቡ፡ እንደ፡ ቃልህ፡ ይደረግ ልን፡ይሁንልን፡ይበሉ፡አቡነ፡ዘበሰማያት፡ካህኑ፡ ልቡናችሁን፡ከፍ፡ከፍ፡አድርጉ፡ይበል። ሕዝቡ፡

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ይ፡ካ፡እእኰትዎ፡ለአምላክነ።

ይ፡ሕ፡ርቱዕ፡ይደሉ።
ይ፡ካ፡ዘንተ፡ቡራኬ።
፩፤ እግዚኦ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ወመ
ድኃኒነ፡ ንስእለከ፡ወናዐቢ፡ስመከ፡ፈድፋደ፡
ወዕበየ፡ግህልከ፡ዘኢይትነገር፡ኢታግብአነ፡
ኀበ፡ጌጋይነ፡ዘበከይሲ፡ዘአልቦቱ፡ፍኖተ፡
ሕይወት።

፪፤ ወአዕርገነ፡ዳግመ፡በትሕትናከ፡ኀበ፡ቀዳሚ፡
ክብር።ወጸጎከነ፡ወወሀብከነ፡ምሥጢረ፡በት
ስብእትከ።

፫፤ ቀነትከ ፡ ለንጸ ፡ ወሶጥከ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡
ምኅፃብ፡ወኀፀብከ፡እግረ፡አርዳኢከ፡እንዘ፡
ትብል ፡ አነ ፡ ሊቅክሙ ፡ ወእግዚእክሙ ፡
ኀፀብኩ፡እገሪክሙ።

፬፤ አንትሙኒ፡ርቱዕ፡ይደልወክሙ፡ትኅፅቡ፡
እግረ፡ቢጽክሙ።እስመ፡አርአያየ፡ወሀብ
ኩክሙ፡በከመ፡ገበርኩ፡ለክሙ፡አነ፡ከማሁ፡
አንትሙኒ፡ግበሩ፡ለቢጽክሙ።
ይ፡ዲ፡ጸልዩ።

ይ፡ካ፡ዳግመ፡ዘንተ።
፩፤ ናሁ፡ንስእለከ፡ወናስተበቍዐከ፡በኂሩትከ፡
ሀበነ፡ንፈጽም፡ገቢረ፡ትእዛዝከ፡በዘይደሉ።

፪፤ እስመ፡አንተ፡ነቅዐ፡ምሕረት፡ወፍኖተ፡
ሕይወት፤አንጽሕ፡ነፍሳቲነ፡ወሥጋነ፡
እምኵሉ፡ኃጢአት፤ወአርትዕ፡እገሪነ፡
በዝንቱ፡ምሥጢር።
፫፤ ወምርሐነ፡ኀበ፡ፈቃድከ፡ኄር፡ከመ፡ንርከብ፡
መክፈልተ፡ወርስተ፡ምስለ፡ቅዱሳኒከ፡
በብርሃን፡ወበረከት።

፬፤ ወንሰብሕከ፡በኵሉ፡ጊዜ፡እስመ፡ስምከ፡
ምሉዐ፡በረከት፡ወወልድከ፡ኄር፡ዋሕድ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ማሕየዊ፡ዘዕሩይ፡ምስሌከ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

በፈጣሪያችን፡እግዚአብሔር፡ዘንድ፡ባለሟ
ልነት፡አለን፡ይበሉ፤ካህኑ፡ፈጣሪያችንን፡
አመስግኑ፡ይበል።
ሕዝቡ፡ዕውነት፡ነው፡ይገባል፡ይበሉ።
ካህኑ፡ይህን፡ምስጋና፡ይበል።

፩፤ አቤቱ፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ
ክርስቶስ፡እንለምንሃለን፤ስምህንም፡እጅግ፡
ከፍ፡ከፍ፡እናደርጋለን፤የማይመረመር፡የቸር
ነታህ፡ገናናነትንም፤የሕይወት፡መንገድ፡
ወደሌለው፡በከይሲ፡ምክንያት፡ወደመጣው፡
በደላችን፡አትመልሰን።

፪፤ በመዋረድህ (መከራ፡በመቀበልህ)፡ወደ፡
ቀድሞው፡የክብር፡ቦታ፡አሳርገን፤ሰው፡በመ
ሆንህም፡ልጅነት፡የሚገኝበትን፡ምሥጢር፡
ፈጽመህ፡ሰጠኸን።

፫፤ ሸርጥ፡(ግልድም)፡ታጥቀህ፡ውኃውን፡በሰፍ
ኮስት፡ጨምረህ፡እኔ፡ጌታችሁ፡መምህ
ራችሁ፡ስሆን፡እግራችሁን፡አጠብኩ፡ብለህ፡
የደቀ፡መዛሙርትህን፡እግር፡አጠብክ።

፬፤ እኔ፡ምሳሌነቴን፡ሰጥቻችኋለሁና፤እናንተም፡
የወንድሞቻችሁን፡እግር፡ታጥቡ፡ዘንድ፡አ
ነት፡ነው፡ይገባችኋል፤እኔ፡እንዳደረግሁላችሁ
እንዲሁ፡እናንተም፡ለወንድሞቻችሁ፡አድርጉ
ዲያቆን፡ጸልዩ፡አቡነ፡ዘበሰማያት፡ድገሙ፡
ይበል።
ካህኑ፡ዳግመኛ፡ይኸንን፡ይበል።
፩፤ በሚገባ፡የትእዛዝህን፡ሥራ፡እንፈጽም፡
ዘንድ፡በቸርነትህ፡መፈጸሙን፡እንድትሰጠን፡
እነሆ፡እንለምንሃለን፤እንማልድሃለን።
፪፤ አንተ፡የምሕረት፡መገኛ፡የሕይወትም፡
መንገድ፡ነህና፤ነፍሳችንና፡ሥጋችንን፡
ከኃጢአት፡ሁሉ፡አንጻ፤በዚህም፡ምሥጢር፡
እግረ፡ልቡናችንን፡አቅና።
፫፤ ከቅዱሳኖችህም፡ጋር፡በብርሃን፡በሰን፡
በጣዕም፡በመዐዛ፡የተዘጋጀ፡ርስተ፡
መንግሥተ፡ሰማያት፡እናገኝ፡ዘንድ፡ወደ፡
በጎ፡ፈቃድህ፡ምራን።
፬፤ በጊዜው፡ሁሉ፡እናመሰግንህ፡ዘንድ፡ስምህ፡
በረከትን፡ምስጋናን፡የተመላ፡ነውና፤ቸር፡
የሚሆን፡አንድ፡ልጅህም፡አዳኝ፡የሚሆን፡

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | መንፈስ፡ቅዱስም፡ከአንተ፡ጋራ፡ትክክል፡የሆነ፡ለዘላለሙ፡አሜን። |
| ይ፡ዲ፡አልዕሉ፡አልባቢክሙ፡ኀበ፡እግዚአብሔር። | ዲያቆን፡ልቡናችሁን፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ከፍ፡ከፍ፡አድርጉ፡ይበል። |
| ፳፮ ይ፡ካ፡እወ፡እግዚአ፡አንተ፡ውእቱ፡ዘወሀብከነ፡ሥልጣነ፡ከመ፡ንኪድ፡ከይሴ፡ወዐቃርብተ፡ወአፍዖተ፡ወዲበ፡ኵሉ፡ኃይለ፡ጸላኢ። | ፳፮ ካህኑ፡አዎን፡አቤቱ፡እባቡን፡ጊንጡን፡ኩርፋፍያውን፡ከእግራችን፡በታች፡እንረግጥ፡ዘንድ፡በጠላት፡ኃይል፡ላይ፡ሁሉ፡ሥልጣንን፡የሰጠኸን፡አንተ፡ነህ፡ይበል። |
| ፳፯ ወቀጥቅጥ፡አርእስቲሆሙ፡ለከይሲ፡ፍጡነ፡ታሕተ፡እገሪነ፤ወብትከ፡እምኔነ፡እከየ፡መማግሪሁ፡ዘይትቃረነ፡ምስሌነ፡እስመ፡አንተ፡ንጉሥነ። | ፳፯ የከይሲውንም፡ራሶች፡ፈጥነህ፡ከእግሮቻችን፡በታች፡ቀጥቅጥ፤ከእኛ፡ጋራ፡የሚጣላውንም፡የክፋት፡ወጥመዱን፡ከእኛ፡ቁረጥ፤አንተ፡ንጉሣችን፡ነህና። |
| ፳፰ ወለከ፡ንፌኑ፡ስብሐተ፡ወአኰቴተ፡ወክብረ፡ወሰጊደ፡ምስለ፡አቡከ፡ኄር፡መሐሪ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ማሕየዊ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | ፳፰ ለአንተም፡ቸር፡መሐሪ፡ከሆነ፡አባትህ፡ጋር፡አዳኝ፡ከሆነ፡መንፈስ፡ቅዱስም፡ጋር፡ፍጹም፡ምስጋናን፡ክብርን፡ስግደትን፡እናቀርባለን፤ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን። |
| ፳፱ ይ፡ዲ፡አትሕቱ፡ርእሰክሙ፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡በፍርሀት፤ይ፡ሕ፡ቅድሜከ፡እግዚኦ፡ንሰግድ፡ወንሴብሐከ፤ይ፡ካ፡አንተ፡ውእቱ፡ዘአጽንንከ፡ሰማያተ፡ወወረድከ፡ወተሰባእከ፡በእንተ፡ውሉደ፡ሰብእ። | ፳፱ ዲያቆኑ፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡በፍርሀት፡ራሳችሁን፡ዝቅ፡ዝቅ፡አድርጉ፡ይበል፤ሕዝቡ፡አቤቱ፡በፊትህ፡እንሰግዳለን፤እናመሰግንሃለን፡ይበሉ፤ካህኑ፡ስለ፡ሰው፡ልጆች፡ልዑል፡ባሕርይህን፡ዝቅ፡አድርገህ፡ሰው፡የሆንክ፡አንተ፡ነህ፡ይበል። |
| ፴ አንተ፡ውእቱ፡ዘትነብር፡ዲበ፡ኪሩቤል፡ወሱራፌል፡ወትሬኢ፡ትሑታነ። | ፴ በሱራፌልና፡በኪሩቤል፡ላይ፡አድረህ፡ትሁታኑን፡የምትጠብቅ፡አንተ፡ነህ። |
| ፴፩ ወይእዜኒ፡ናሌዕል፡እግዚኦ፡አዕይንተ፡አልባቢነ፡ኀቤከ።ሰረይ፡ለነ፡ኃጣውኢነ፡ወአድኅን፡ነፍሳቲነ፡እሙስና። | ፴፩ አቤቱ፡አሁንም፡ወደ፡አንተ፡ዐይነ፡ልቡናችንን፡ቀና፡እናደርጋለን፤ኃጢአታችንን፡ይቅር፡በለህ፡ነፍሳችንንም፡ከጥፋት፡አድን። |
| ፴፪ ንሰግድ፡ለኂሩትከ፡ማሕየዊት፤ናስተበቍዕ፡ኀቤከ፡ከመ፡ተሀበነ፡ሰላመ፤እስመ፡ኵሎ፡ወሀብከነ፤ወኢነአምር፡ባዕደ፡አምላከ፡ዘእንበለ፡ስምከ፡ቅዱስ። | ፴፪ አዳኝ፡ለሆነች፡ቸርነትህ፡እንሰግዳለን፤ፍቅር፡አንድነትን፡ትሰጠን፡ዘንድ፡ወዳንተ፡እንማልዳለን፤ሁሉን፡ሰጥተኸናልና፤ከቅዱስ፡ስምህም፡በቀር፡ሌላ፡አምላክ፡አናውቅም። |
| ፴፫ ሚጠነ፡እግዚኦ፡ውስተ፡ፍቅርከ፡ቅዱስ፡ወአእምሮ፡ዚአከ።ርድአነ፡ንትከደን፡በጸጋሎት፡ክነፊከ፡ምስለ፡ኵሎሙ፡ቅዱሳኒከ፡እለ፡ተወከሉ፡ብከ። | ፴፫ አቤቱ፡ልዩ፡ወደ፡ሆነው፡ፍቅርህና፡አንተን፡ወደማወቅ፡መልሰን፤ባንተ፡ከሚታመኑ፡ቅዱሳንህ፡ሁሉ፡ጋራ፡በክንፈ፡ረድኤትህ፡እንሰወር፡ዘንድ፡ርዳን። |
| ፴፬ ወእለ፡አትሐቱ፡እንከ፡አርእስቲሆሙ፡ቅድሜከ፡አልዕሎሙ፡በምሕረትከ፡ወእሰርግዎሙ፡በሠናያቲከ፡ይረሱ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡በሥምረተ፡አብ፡ዘሎቱ፡ይደሉ፡ | ፴፬ እንግዲህ፡ራሳቸውን፡በፊትህ፡ዝቅ፡ዝቅ፡ያደረጉትንም፡በቸርነትህ፡ከፍ፡ከፍ፡አድርጋቸው፤ምስጋና፡በሚገባው፡በአብ፡ፈቃድ፡ከአንተ፡ጋር፡ትክክል፡በሆነ፡ማሕየዊ፡በመንፈስ፡ቅዱስም፡መንግሥተ፡በሚሆን፡ |

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ስብሐት ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ ፡ ዘዕሩይ፡ምስሌከ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ይ፡ዲ፡ ስግዱ፡ለእግዚአብሔር፡ በፍርሀት፤

ይ ፡ ሕ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡ ወንሴብሐከ።

ይ፡ካ፡ጸሎተ፡ንስሓ፤ፍትሐት፡ዘወልድ።

፩፤ እግዚኦ፡እግዚኦ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወልድ፡ዋሕድ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አብ፡ዘበተከ፡እምኔነ ፡ ኵሎ ፡ ማእሰረ ፡ ኃጣውኢነ ፡ በሕማምከ፡ማሕየዊት።ዘነፋሕከ፡ላዕለ፡ገጸ፡አርዳኢከ፡ቅዱሳን፡እንዘ፡ትብል ፡ ንሥኡ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡ ለእለ፡ኀደግሙ፡ኃጢአት፡ይትኀደግ ፡ ሎሙ ፡ ወለእለ ፡ ኢኀደግሙ ፡ ኢይትኀደግ ፡ ሎሙ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ውእቱ፡በእንተ፡አርዳኢከ፡ቅዱሳን፡ገበርከ፡ካህናተ፡ይእስሩ፡ወይፍትሑ፡ኵሎ፡ማእሰረ፡በመገ።

፪፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ናንቀዕዱ ፡ ኀቤከ ፡ ወናስተበቍዐከ፡አ፡መሐሪ፡ወመፍቀሬ፡ሰብእ፡በእንተ፡እሉ፡አግብርቲከ፡አበውየ፡ወአኀውየ፡እለ፡አትሐቱ፡አርእስቲሆሙ፡ቅድሜከ።

፫፤ ወሊተኒ ፡ ተሣሀለኒ ፡ እግዚኦ ፡ ዘትሰሪ ፡ ኃጢአተ፡ኵሉ፡ዓለም።

፬፤ ተወከፍ፡ንስሐሆሙ፡ለአግብርቲከ፡ወለአእማቲከ፡ወስረይ፡ዘአበሱ፡ለከ፡በአእምሮ፡ወእመሂ፡ዘእንበለ፡አእምሮ፡አው፡በቃል፡አው፡በምግባር፡አናሕሲ፡ሎሙ፡አ፡መሐሪ፡ወመስተሣህል፡ተወከፍ፡ስዕለተነ።

፭፤ ወሥረይ፡ኃጢአተነ፡አንጽሐነ፡ወባልሐነ፡እምኵሉ ፡ አበሳ ፡ ወመርገም ፡ ወመሐላ ፡ በሐሰት።

፮፤ ወምላእ ፡ ላዕሌነ ፡ ፈሪሆተከ ፡ ወአሠኒ ፡ ፍኖተነ፡ በሥምረትከ ፡ ማሕየዊት ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ።

፯፤ እስመ፡ለከ፡ይደሉ፡ስብሐት፡ወኃይል፡ምስለ፡አቡከ፡መሐሪ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ማሕየዊ፡እምይእዜ፡ወእስከ፡ለዓለም፡አሜን።

ይ፡ሕ፡እግዚኦ፡ ተሣሀለነ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ሰማያትን፡ይወርሱ፡ዘንድ፡በበጎ፡ሥራ፡አስጊጣቸው፤ለዘላለሙ፡አሜን።

ዲያቆኑ ፡ በፍርሀት ፡ ሁናችሁ ፡ ለእግዚአብሔር፡ስገዱ፡ይበል።

ሕዝቡ፡ አቤቱ፡በፊትህ፡እንሰግዳለን፤እናመሰግንሃለንም፡ይበሉ።

ካህኑ ፡ የንስሓ ፡ ጸሎት ፡ ይበል ፤ ወልድ፡የሚሰጠው፡ሥርየት።

፩፤ አቤቱ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወልድ፡ዋህድ፡የእግዚአብሔር፡አብ፡አካላዊ፡ቃል፡መድኃኒት፡በሆነች፡መከራ፡(ሕማምህ)፡የኃጢአታችንን ፡ ማሠሪያ ፡ (በኃጢአታችን፡ምክንያት፡ የመጣውን ፡ ፍዳ) ፡ ያጠፋህ፡በንጹሐን፡ደቀ፡መዛሙርትህ፡ላይ፡መንፈስ፡ቅዱስን፡ ተቀበሉ፡ብለህ፡በንፍሐት፡ልጅነትን፡ያሳደርክባቸው፡ ይቅር ፡ ላላችኋቸው፡ኃጢአታቸው፡ይቀርላቸዋል፤ይቅርም፡ያላላችኋቸው፡አይቀርላቸውም፡ያልካቸው፤የዐመፅን፡ማሰሪያ፡ሁሉ፡ያስሩ፡ይፈቱ፡ዘንድ፡ስለ፡ንጹሐን፡ደቀ፡መዛሙርትህ፡አንተ፡ካህናትን፡ሹመሃልና።

፪፤ ስለዚህም ፡ ወዳንተ ፡ ቀና ፡ ብለን፡በፊትህ፡ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ስለአደረጉ፡ስለነዚህ፡ባሮችህ፡አባቶቼና፡ወንድሞቼ፡ሰውን፡የምትወድ፡መሐሪ፡ሆይ፡እንማልድሃለን።

፫፤ አቤቱ ፡ የዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት፡የምታርቅ፡እኔንም፡ይቅር፡በለኝ።

፬፤ የወንዶችና፡የሴቶች፡ባሮችህን፡ንስሓቸውን፡ተቀበል፤በማወቅ፡ወይም፡ያለማወቅ፡ቢሆን፡በመናገር ፡ ወይም ፡ በመሥራት፡የበደሉህን፡ይቅር ፡ በላቸው ፤ መሐሪ ፡ ይቅር፡ባይ፡ሆይ፡ልመናችንን፡ተቀበል።

፭፤ ኃጢአታችንንም ፡ አስተሥርይ ፤ ከበደልና፡ከርግማን፡በሐሰትም፡ከመማል፡ፈጽመህ፡አድነን።

፮፤ አንተን ፡ መፍራትንም ፡ በላያችን፡አሳድር፡መድኃኒት፡በሆነች፡ፈቃድህ፡ሁልጊዜ፡አካሄዳችንን፡አሳምርልን።

፯፤ ከይቅር፡ባይ፡አባትህና፡ማሕየዊ፡ከሚሆን፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ ጋራ፡ዛሬም፡ለዘላለሙ፡ክብር፡ምስጋና፡ኃይል፡ለአንተ፡ይገባል፡አሜን።

ሕዝቡ፡አቤቱ፡ ይቅር፡በለን፡ይበሉ።

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| **ትእዛዝ።** ወእምዝ፡ይትነሥኡ፡ሕዝብ፡ወይበሉ፡ኪርያ ላይሶን፡ዓርብዓ፡ወአሐደ፡ጊዜ፤ወያንሥእ፡ ካህን፡መስቀለ፡ወይዕትብ፡ማየ፡በትእ ምርተ፡መስቀል፡ሠለስተ፡ጊዜ፡እንዘ፡ ይብል፡አሐዱ፡አብ፡ቅዱስ፡አሐዱ፡ወልድ፡ ቅዱስ፡አሐዱ፡ውእቱ፡መንፈስ፡ቅዱስ። | **ትእዛዝ።** ከዚህ፡በኋላ፡ሕዝቡ፡ይነሱ፤አርባ፡አንድ፡ ጊዜ፡ኪርያላይሶን፡ይበሉ፤ካህኑም፡መስቀል፡ ይዞ፡ውኃውን፡ሦስት፡ጊዜ፡አሐዱ፡አብ፡ ቅዱስ፡(ልዩ፡ክቡር፡ንጹሕ፡ጽኑዕ፡ነው)፤ አሐዱ፡ወልድ፡ቅዱስ፡(ልዩ፡ክቡር፡ንጹሕ፡ ጽኑዕ፡ነው)፤ አሐዱ፡ውእቱ፡መንፈስ፡ ቅዱስ፡(ልዩ፡ክቡር፡ንጹሕ፡ጽኑዕ፡ነው)፡ እያለ፡ሦስት፡ጊዜ፡ውኃውን፡ይባርክ። |

መሪ፦ ሐዋርያቲሁ፡ከበበ፡እግረ፡አርዳኢሁ፡ሐፀበ፡ኮኖሙ፡አበ፡ወእመ፡
ወመሐሮሙ፡ጥበበ፡ሃሌ፡ሉያ፡ይበል።

ወእለ፦ ይትቄበሉ፡ኵሎሙ፡በኅብረት፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ፡እግረ፡ይበሉ።

መሪ፦ ብቻውን፡ክብር፡ይእቲ፡ዛቲ፡ለኵሉ፡ጻድቃኑ፡ይበል።
በዚያው፡በመሪው፡በኵል፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ፡እግረ፡አርዳኢሁ፡ይበል።

አንሺ፦ ሁሌ፡ሉያ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃጎል።
በአንሽ፡ሰብሕዎ፡**ለእግዚአብሔር**፡በቅዱሳኑ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃጎል።
መሪ፡ሰብሕዎ፡በጽንዐ፡ኃይሉ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃጎል።
አንሽ፡ሰብሕዎ፡በክሂሎቱ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃጎል።
መሪ፡ሰብሕዎ፡በከመ፡ብዝኃ፡ዕበዩ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃጎል።
አንሽ፡ሰብሕዎ፡በቃለ፡ቀርን፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ ሃሌ፡ሉያ።

መሪ፦ ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።

አንሺ፦ እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃጎል።
መሪ፡ሰብሕዎ፡በመዝሙር፡ወበመሰንቆ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ፡እግረ፡አርዳኢሁ።

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|

አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
አንሺ፡ሰብሕዎ፡በከበሮ፡ወበትፍሥሕት፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
መሪ፡ሰብሕዎ፡በአውታር፡ወበእንዚራ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
አንሺ፡– ሰብሕዎ፡በጸናጽል፡ዘሠናይ፡ቃሉ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
መሪ፡ሰብሕዎ፡በጸናጽል፡ወበይባቤ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
አንሺ፡ኵሉ፡ነፍስ፡ይሴብሖ፡ለእግዚአብሔር፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
መሪ፡ስብሐት፡ለአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።

አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
አንሺ፡– ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም፡ሐዋርያቲሁ፡ከበበ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– ሃሌ፡ሉያ።
መሪ፡– ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ።
አንሺ፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል።
በኅብረት፡– እንዘ፡ንብል፡ኢንትኃሎል፡እምከብካበ፡ወልዳ፡ለድንግል፡ይበሉ።

| ዕጣን፡ሞገር፡በ፩፡ሃሌ፡ሉያ፡ኀፀበ፡እግረ፡አርዳኢሁ፡ ወይቤሎሙ፡ አነኒ፡ ኀፀብኩ፡ እገሪክሙ፡ አንትሙኒ፡ ከመዝ፡ ግበሩ፡ ለቢጽክሙ። | ዕጣን፡ሞገር፡በአንድ፡ሃሌታ፡የደቀ፡መዛሙርቱን፡እግር፡አጠበ፤እንዲህም፡አላቸው፤ እኔ፡ እግራችሁን፡ አጠብኩ፤ እናንተም፡ እንዲሁ፡ለወንድሞቻችሁ፡አድርጉ። |
|---|---|

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወእምዝ ፡ ይግበር ፡ ካህን ፡ ኅጽበተ ፡ እግር ፡
ዘከመ ፡ ሥርዓቱ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ይግበሩ ፡
ሥርዐተ ፡ ቍርባን ፡ እንዘ ፡ ይለብሱ ፡ ልብሰ ፡
ጸሊመ።ወኢያስምዑ፡ድምፀ፡ናብሊስ።

ምንባብ።

፩ እግዚእ፡አንበረ፡አልባሲሁ፡ወቀነተ፡ለንጻ፡
ወሶጠ፡ማየ፡ውስተ፡ምኅፃብ፡ወኀጸበ፡እግረ፡
አርዳኢሁ፡ወአዘዘ፡ለስምዖን፡ጴጥሮስ፡ከመ፡
ይኅፅብ፡እገሪሁ።
፪ ወይቤሎ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ለእግዚእ ፡
ኢየሱስ፡ኢትኅፅበኒ፡እገርየ፡ለዓለም።
፫ ወይቤሎ ፡ መድኃኒነ ፡ ለስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡
ለከ፡ እብለከ ፡ ለእመ ፡ ኢኀፀብኩከ ፡ አነ ፡
እገሪከ፡አልብከ፡ክፍል፡ምስሌየ።
፬ ወይቤሎ፡ስምዖን፡ለመድኅን፡አ፡እግዚእየ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አኮ፡እገርየ፡ባሕቲቶ፡ዘተ
ኀፅበኒ፡አላ፡እደውየኒ፡ወርእስየኒ።
፭ ወመሀሮሙ፡እንዘ፡ይብል፡አነ፡ኀፀብኩ፡
እገሪክሙ፡አንትሙኒ፡ርቱዕ፡ይደልወክሙ፡
ትግበሩ፡ከመዝ፡ለቢጽክሙ።
፮ ወይእዜኒ ፡ ሰአሉ ፡ ለነ ፡ አ ፡ ሊቃውንት ፡
አበዊነ፡ ሐዋርያት ፡ ሰብዓ ፡ ወክልኤቱ ፡
አርድእት፡ከመ፡ይስረይ፡ለነ፡ኀጣውኢነ።

ወይበል ፡ ካህን ፡ ዘንተ ፡ ጸሎተ ፡ እምድኅረ ፡
ኀፅበተ፡እግር።

፩ እግዚእ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡አኀዜ፡
ኵሉ፡ነአኵተከ፡በኵሉ፡ወላዕለ፡ኵሉ፡
እስመ፡ረሰይከነ፡ድልዋነ፡በዛቲ፡ሰዓት፡
ከመ፡ንፈጽም፡አምሳለ፡ኀፅበትከ፡ቅዱስ፡
ዘመሀሮሙ፡ለአርዳኢሁ፡ዋሕድ፡ወልድከ፡
እግዚእነ፡ወአምላክነ፡መወድኃኒነ፡ወመም
ሀርነ፡ዘሎቱ፡ስብሐት።
፪ ንስእል፡ወናስተበቍዕ፡ዘእምአድኅኖትከ፡አ፡
መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ኅድግ ፡ ለነ ፡ ብዙኀ ፡
ኃጢአተነ ፡ ወተሣሀለነ ፡ በከመ ፡ ብዝኀ ፡
ሣህልከ፡ወፈኑ፡ሰላመከ፡ለቅድስት፡ቤተ፡
ክርስቲያን።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ከዚህ፡በኋላ፡ካህኑ፡እንደ፡ሥርዓቱ፡ኀጽበተ፡
እግርን፡ያድርግ፤(ይፈጽም)፤ከዚህ፡በኋላም፡
ጥቁር፡ልብስ፡ለብሰው፡ሥርዐተ፡ቅዳሴውን፡
ይጀምሩ፤የቃጭል፡ድምፅንም፡አያሰሙ።

ምንባብ።

፩፤ ጌታ፡ልብሶቹን፡አስቀምጦ፡ሽርጥ፡ታጠቀ፤በኵ
ስኵስትም፡ውኃ፡ጨምሮ፡የደቀ፡መዛሙርቱን፡
እግር ፡ አጠበ ፤ እግሩንም ፡ ያጥበው ፡ ዘንድ ፡
ስምዖን፡ጴጥሮስን፤አዘዘው።
፪፤ ስምዖን፡ጴጥሮስም፡ጌታ፡ኢየሱስን፡አንተ፡
ፈጽሞ፡እግሬን፡አታጥበኝም፡አለው።
፫፤ መድኃኒታችንም፡ስምዖን፡ጴጥሮስን፡እኔ፡
እግርህን፡ካላጠብኩህ፡ከእኔ፡ጋር፡ዕድል፡
ፈንታ፡እንደሌለህ፡ላንተ፡እነግርሃለሁ፡አለው።
፬፤ ስምዖንም፡መድኃኒታችንን፤ጌታዬ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ሆይ፡የምታጥበኝ፡እግሬን፡ብቻ፡
አይደለም፤እጆቼንም፡ራሴንም፡እንጂ፡አለው።
፭፤ እንዲህም፡ብሎ፡አስተማራቸው፤እኔ፡እግራ
ችሁን፡አጠብኳችሁ፤እናንተም፡ለወንድሞ
ቻችሁ፡እንዲህ፡ታደርጉ፡ዘንድ፡ይገባችኋል።
፮፤ አሁንም፡ሊቃውንት፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡
ሰባ፡ሁለቱም፡አርድእት፡ሆይ፡ኃጢአታችንን፡
ያስተሰርይልን፡ዘንድ፡ለምኑልን።

ከእግር፡እጥበት፡በኋላ፡ካህኑ፡ይህን፡ጸሎት፡
ይበል።

፩፤ ሁሉን፡የያዝክ፡አምላካችን፤ጌታችን፡እግዚአ
ብሔር፡ሆይ፡በሁሉ፡ዘንድ፡ከሁሉ፡በላይ፡እናመ
ሰግንሃለን፤የክብር፡ባለቤት፡አንድ፡ልጅህ፡
ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒታችን፡መምህ
ራችን፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ያስተማራቸውን፡
የከበረ፡ኀፅበትህን፡አምሳል፡እንፈጽም፡ዘንድ፡
በዚች፡ሰዓት፡የተዘጋጀን፡አድርገኸናልና።
፪፤ ሰውን፡ወዳጅ፡ሆይ፡ከትድግናህ፡የሚገኘውን፡
ቸርነትህን፡ፈጽመን፡እንማልዳለን፤ብዙውን፡
ኃጢአታችንን፡ተውልን፤እንደ፡ይቅርታህም፡
ብዛት፡ይቅር፡በለን፤ለከበረች፡ቤተ፡ክርስቲያ
ንህም፡ፍቅር፡አንድነትን፡ስጥ።

Scanned by CamScanner

ዘሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት፡ዘሐሙስ።

በ፲፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፫፤ ዕቀበነ፡በሰላም፡ወበጽድቅ፡ወበርትዕ፡ወበፈ ሪሆትከ፡ከመ፡ንዕቀብ፡ኵሎ፡ትእዛዛቲከ፡ በዝ፡ዓለም፡ወበዘይመጽእ።

፬፤ ረስየነ፡ሰብአ፡ሠናያነ፡ለዝሉፉ፡በዋሕድ፡ ወልድከ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እግዚእነ፡ ዘሎቱ፡ስብሐት፡ወኃይል፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

ይ፡ዲ፡ጸልዩ፡፡።

፭፤ ይ፡ካ፡ነአኵተከ፡እግዚአብሔር፡ወሀቤ፡ ኵሉ፡ ኂሩት፡ ዘረሰይከነ፡ ድልዋነ፡ ለዛቲ፡ መልእክት፡ ከመ፡ ንኩን፡ ሱታፌ፡ ለፍቁራኒከ፡ ምስለ፡ ዋሕድ፡ ወልድከ፡ በመንፈስ፡ በከመ፡ ትእዛዙ፡ ቅዱስ።

፮፤ ወዕቀበነ፡በኃይለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሀበነ፡ ከመ፡ንፈጽም፡በኵሉ፡ከመ፡ናእኵትከ፡ በጸጋከ፡ወበሣህለከ፤እ፡መፍቀሬ፡ሰብእ።

፯፤ በዋሕድ፡ ወልድከ፡ እግዚእነ፡ ወመድኃኒነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ዘሎቱ፡ ስብሐት፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

ማኅተመ፡ ፍጻሜ፡ ጸሎትሰ፡ ኀትሙ፡ በጥንቃቄ፡ወበሥርዐት፡በከመ፡ኀተምክሙ፡ በዕለተ፡ሰኑይ፡ጊዜ፡ተሰዐቱ፡ሰዓት።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፫፤ ትእዛዞችህን፡እንፈጽም፡ዘንድ፡በዚህ፡ዓለም፥ በሚመጣውም፡ዓለም፡በፍቅር፡በዕውነት፡ በቅንነት፡አንተን፡በመፍራት፡ጠብቀን።

፬፤ የክብር፡የኃይል፡ባለቤት፡በሆነ፡በአንድ፡ ልጅህ፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ለዘወትር፡ቅኖች፡(መልካሞች)፡ሰዎች፡ አድርገን፤ለዘላለሙ፡አሜን።

ዲያቆን፡ጸልዩ፡ይበል፤

፭፤ ካህኑ፡ቸርነትህን፡ሁሉ፡የምትሰጥ፡እግዚአ ብሔር፡ከወዳጆችህ፡ጋር፡አንድ፡እንሆን፡ ዘንድ፡እንደ፡ቅዱስ፡ፈቃዱ፡ካንድ፡ ልጅህም፡ጋር፡በመንፈስ፡አንድ፡እንሆን፡ ዘንድ፡ለዚች፡መልእክት፡የተዘጋጀን፡ያደረ ግኸንን፡እናመሰግንሃለን፡ይበል።

፮፤ በመንፈስ፡ቅዱስም፡ኃይል፡ጠብቀን፤ሰው ወዳጅ፡ሆይ፤በለጋስነትህና፡በይቅርታህ፡እና መሰግንህ፡ዘንድ፡ማመስገኑን፡ስጠን።

፯፤ ተቀዳሚ፡ ተከታይ፡ በሌለው፡ ክብር፡ በሚገባው፡ ልጅህ፡ በጌታችን፡በመድኃኒ ታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ዘንድ፤ ለዘላለሙ፡አሜን።

ሰኞ፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡እንዳደረጋችሁ፡የመፈጸ ሚያውን፡ጸሎት፡በጥንቃቄና፡በሥርዓት፡ ጨርሱ።

## ምዕራፍ፡፵፫።

ወእምዝ፡ይትጋብኡ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስ ቲያን፡ቅድስት፡ጊዜ፡ዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ ሰዓት፡ዘኀሙስ፡ወየአኀዙ፡ሥርዐተ፡ጸሎት፡ ከመ፡ዘትማልም፡ጊዜ፡ዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ ሰዓት።

### ክፍል፡፩።

በዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ ዘኀሙስ፡ዘይትነበብ።

ዘኤርምያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ ምስሌነ፡ለዓለም፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፥፴፩፥፲፭—፳፮።

፲፭፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ቃል፡ በራማ፡ተሰምዐ፡ብካይ፡ወላህ፡ወገዐር፡ ራሄል፡እንዘ፡ትበክዮሙ፡ለደቂቃ፡ወአበየት፡ ተናዝዞ፡ወነጊፈ፡ላህ፡ላዕለ፡ደቂቃ፡እስመ፡ ኢሀለዉ።

## ምዕራፍ፡፵፫።

ከዚህ፡በኋላ፡በከበረች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ውስጥ፡ኀሙስ፡በዐሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡ ይሰብሰቡ፤የጸሎቱንም፡ሥርዓት፡ይጀምሩ፤ ትናንት፡በዐሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡እንዳደ ረጉት።

### ክፍል፡፩።

ኀሙስ፡ከቀኑ፡በዐሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡ የሚነበብ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትሁ ርና፡የነቢዩ፡ኤርምያስ፡ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፥፴፩፥፲፭—፳፮።

፲፭፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤በራማ፡ቃል፡ ተሰማ፤ሐዘንና፡ልቅሶ፡ጩኸትም፡ተሰማ፤ ራሄል፡ለልጆቿ፡ስታለቅስላቸው፡በልጆቿ፡ ላይ፡ ልቅሶ፡ መተውንና፡ መረጋጋትን፡ እምቢ፡አለች፤ልጆቿ፡የሉምና።

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፮ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ክልኢ፡ቃለኪ፡
እምብካይ ፡ ወአዕይንተኪ ፡ እምአንብዕ ።
እስመ፡ቦ፡ዕሴት፡ለምግባርኪ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡ወይሠወጡ፡እምድረ፡ፀር።

፲፯ ወቦ፡ተስፋ፡ለደኃሪትኪ፡ ይቤ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ወይትመየጡ፡ ደቂቅኪ፡ ውስተ፡
ደወሎሙ።

፲፰ ሰማዕኩ፡ ሰሚዐ፡ ኤፍሬም፡ እንዘ፡
ይገዕር ። ወይብል ፡ ገሠጽከኒ ፡ ወተገ
ሠጽኩ፡ከመ፡ላሕም፡ዘኢተምህረ። ሚጠኒ፡
ወእትመየጥ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚአ ፡
አምላኪየ።

፲፱ ወእምድኅረ፡ተመየጥኩ፡ተፈሣሕኩ፡ወእም
ድኅረ፡ አእመርኩ፡ ጠፋሕኩ፡ እደውየ፡
ወኀፈርኩ፡ ወእትኀፈር፡ እስመ፡ ነሣእኩ፡
ጽዕለተ፡ንእስየ።

፳ ወልድ፡ ዘአፈቅር፡ ኤፍሬም፡ ሊተ፡ ከመ፡
ሕፃን፡ ልህድ፡ ለለተናገርክዎ፡ ተዘክሮ፡
እዜክሮ፡ በእንተዝ፡ ተሀውካ፡ አማዑትየ፡
ወሎቱ፡ ተሣህሎ፡ እሣህሎ፡ ይቤ፡ እግዚአ
ብሔር።

፳፩ አቅሚ፡ ለኪ፡ ጸወናተኪ ። ወግበሪ፡ ለኪ፡
ትእምርታተ ። ደዪ ፡ ውስተ ፡ ልብኪ ፡
መጽያሕተ፡ፍኖት፡ከመ፡ትሠወጢ፡ውስተ፡
ሀገርኪ፡ ድንግለ፡ እስራኤል፡ ተሠወጢ፡
ውስተ፡ሀገርኪ።

፳፪ እስከ፡ ማእዜኑ፡ ትላህዊ፡ ወለት፡ ዕሉት፡
እስመ፡እግዚአብሔር፡ ገብረ፡ሐዲሰ፡ውስተ፡
ምድር፡ ወይመጽእ፡ ሰብእ፡ ውስተ፡
መድኃኒት።

፳፫ ከመ፡ ዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ጸባኦት፡
አምላከ፡ እስራኤል፡ ዓዲ፡ ይብሉ፡ ዘነገረ፡
በይሁዳ፡ ወበአህጉሪሁ፡ አመ፡ ሜጥኩ፡
ፄዋሆሙ። ይባርከ፡እግዚአብሔር፡ ማኅደረ፡
ጽድቅ፡ደብረ፡መቅደስከ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፮፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ቃልሽን፡ከልቅሶ፡
ዐይኖችሽንም፡ከእንባ፡ከልክዪ፤እግዚአብሔር፡
ለሥራሽ፡ዋጋ፡አለው፡ብኋልና፡ልጆችሽም፡
ከጠላት፡አገር፡ይመለሳሉ።

፲፯፤ እግዚአብሔርም፡ ለፍጻሜ፡ ዘመንሽ፡
አለኝታ፡ አለው፤ ልጆችሽም፡ ወደ፡
አገራቸው፡ይመለሳሉ፡አለ።

፲፰፤ ኤፍሬም፡ በመከራው፡ ተይዞ፡ ሲጮህ፡
መስማትን፡ሰማሁ፤አንተም፡በመከራው፡
ገሠጽኸኝ፤እኔም፡ቀምበር፡መሸከምን፡እንዳ
ልተማረ፡ወይፈን፡በመከራው፡ተገሠጽኩ፤
አቤቱ፡ፈጣሪዬ፡አንተ፡ነህና፡ወደ፡አገሬ፡
መልሰኝ፤እኔም፡ልመለስ፡ይላል፡አለ።

፲፱፤ ከተመለስኩ፡በኋላ፡ደስ፡አለኝ፤መመለሴንም፡
ከአወቅሁ፡ በኋላ፡ እጄን፡ አጨበጨብኩ፤
በመከራው፡አፈርኩ፤የሕፃንነቴን፡ስድብ፡ተቀ
ብያለሁና፡እንግዲህም፡በመከራው፡አፍራለሁ።

፳፤ ኤፍሬም፡ለኔ፡የምወደው፡ልጅ፡ነበር፤እያስ
ተማርኩት፡ ድልድል፡ ቅምጥል፡ ልጅ፡
ቢሆንብኝ፡ማሰብን፡አስበዋለሁ፤ስለዚህ፡
አንጀቴ፡ ታውካለች፤ እግዚአብሔርም፡
መራራትን፡እራራለታለሁ፡አለ።

፳፩፤ ለአንቺ፡አምባዎችሽን፡አጽኚ፤ምልክቶች
ሽንም፡አድርጊ፤ወደ፡አገርሽ፡ትመለሺ፡
ዘንድ፡የቀና፡ሕግን፡በልቡናሽ፡አኑሪ፤የእስ
ራኤል፡ቆንጆ፡ወደ፡አገርሽ፡ተመለሺ።

፳፪፤ እግዚአብሔር፡ በምድር፡(በባቢሎን)፡አዲስ፡
ሚጠትን፡አደርጋልና፤ሰውም፡ድኅነት፡ወደ፡
ሚያደርግበት፡አገር፡ይመጣልና፤አንቺ፡ወንጀለኛ፡
ልጅ፡እስከ፡መቼ፡ድረስ፡ታለቅሳለሽ፡አለ።

፳፫፤ የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡አለ፤ምርኳቸውን፡በመለስኩ፡ጊዜ፡
በአውራጃውና፡ በይሁዳ፡ ይህንን፡ ነገር፡
ይናገራሉ፤የቸርነት፡ባለቤት፡እግዚአብሔር፡
በምስጋናህ፡ተራራ፡ያከብርህ፡ይላሉ።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡...

፳፬፡ ወእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ ፡ ወእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ ፡
ምስለ ፡ አህጉሪሁ ፡ ኀቡረ ፡ ሐረሳውያን ፡
ያነሥኡ፡መራዕየ።

፳፭፡ እስመ፡አርወይኩ፡ኵላ፡ነፍሰ፡ጽምዕተ፡ወአጽገብኩ፡ኵላ፡ነፍሰ፡ርኅብተ።

፳፮፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነቃሕኩ ፡ ወርኢኩ ፡ ወጥዕመኒ፡ንዋምየ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡እምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፴፪፡፩-፰።

፩፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ብፁዕ ፡ ዘቦ ፡ ዘርዕ ፡ በጽዮን ፡ ወዘቦ ፡ አብያት ፡ በኢየሩሳሌም። እስመ፡ናሁ፡ንጉሥ፡ጻድቅ፡ይነግሥ፡ወመላእክትኒ፡በጽድቅ፡ይኴንኑ።

፪፡ ወየኀብእ፡ሰብእ፡ቃሎ፡ወይትኀባእ፡ከመ፡ዘይሥጠም፡ውስተ፡ቀላይ።
ወያስተርኢ ፡ በጽዮን ፡ ከመ ፡ ፈለግ ፡ ዘይውኅዝ፡ክብሩ፡በምድር፡ጽምእት።

፫፡ ወኢይትዌከሉ፡እንከ፡በዕጓለ፡እመሕያው፡ዳእሙ፡ያፀምዑ፡በዕዝኖሙ።

፬፡ ወልብ፡ድኩም፡ይሰምዕ፡አእምሮ፡ልሳንኒ፡ጸያፍ፡ፍጡነ፡ይትሜሀር፡ነገረ፡ሰላም።

፭፡ ወኢታጽምዖ ፡ እንከ ፡ ለአብድ ፡ ወሶበ ፡ ይብለከ፡እንከ፡ወዓሊከ፡አርምም።

፮፡ እስመ፡አብድሰ፡ዕበደ፡ይነብብ፡ወልቡኒ፡ከንቶ፡ይኄሊ፡ከመ፡ይግበር፡ዐመፃ፡ወከመ፡ይንብብ፡ኃጢአተ፡ቡነበ፡**እግዚአብሔር**፡ወከመ፡ይዝሩ፡ነፍሰ፡ርኅብተ፡ወከመ፡ያዕርቅ፡ነፍሰ፡ጽምእተ።

፯፡ እስመ፡ኀሊናሆሙ፡ለእኩያን፡ዐመፃ፡ትመክር፡ከመ፡ይቅትልዎ፡ለነዳይ፡በነገረ፡ዐመፃሆሙ፡ወከመ፡ይገፍትኡ፡ፍትሐ፡ምስኪናን።

፳፬፡ በይሁዳ፡አገሮች፡በአውራጃዎቿም፡ሁሉ፡አንድነት፡የሚኖሩ፡አራሾች፡መንጋዎችን፡ነድተው፡ይሄዳሉ።

፳፭፡ የተጠማችውን ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ አርክቼ ለሁና ፤ የተራበችውንም ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ፡ረድኤቴን፡አጥግቤያለሁና።

፳፮፡ ስለዚህ፡ተኛቼ፡ነቃሁ ፤ ራእይም፡አየሁ፡እን ቅልፌም፡ጣፈጠኝ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገረው፡ትንቢት፡ይህን፡ነው።

ምዕ፡፴፪፡፩-፰።

፩፡ **እግዚአብሔር** ፡እንዲህ፡አለ ፤ በጽዮን፡ዘር፡ያለው፡በኢየሩሳሌምም፡ቤት፡ያለው፡ሰው፡ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፤ እነሆ ፡ ደግ ፡ ንጉሥ፡ይነግሣል ፡ አለቆችም ፡ በዕውነት ፡ ይፈርዳሉና።

፪፡ ሸፋጭ፡ሰው፡ቃሉን፡ይሠውራል ፤ በባሕር፡እንደሚሠጥም፡ዓሣም፡ይሠወራል ፤ በተጸማች ፡ ምድር ፡ እንደሚፈስ ፡ ፈሳሽ፡ክብሩ፡በጽዮን፡ይገለጣል።

፫፡ በጆሮአቸው ፡ ያደምጣሉ ፡ እንጂ ፡ እንግዲህ፡ወዲህ ፡ በሰው ፡ (ሰው ፡ በሠራው ፡ ጣዖት)፡ አያምኑም።

፬፡ ደካማ ፡ ልቡና ፡ ዕውቀትን ፡ ያውቃል ፤ ዲዳ፡እንደበትም፡ፈጥኖ፡የሰላምን፡ነገር፡ይማራል።

፭፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰነፍ ፡ ሰውን ፡ አታድ ምጠው ፤ ሎሌህ፡ጣዖት፡እናምልክ፡ቢልህ፡ዝም፡በል።

፮፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ስንፍናን ፡ ይናገራልና፡ልቡም፡ኃጢአት፡ይሠራ፡ዘንድ ፤ በ**እግዚአብ ሔርም** ፡ ላይ ፡ በደልን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ፡የተጠማች፡የተራበች፡ሰውነትንም፡ያሳዝን፡ዘንድ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ ያስባልና ፡ ሰነፍ፡ሰውን፡አታድምጠው።

፯፡ ድኃውን፡በግፍ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡የጠማ፡አዳሪውንም፡ፍርድ፡ለውጡ፡ዘንድ፡የክፉ፡ሰዎች፡ልቡና፡ዐመፅን፡ትመክራለችና።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፳፬፤ ወእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ ፡
ወዙሉ ፡ አህጉሪሁ ፡ ኅቡረ ፡ ሐረሳውያን ፡
ያነሥኡ፡መራዕየ።
፳፭፤ እስመ፡አርወይኩ፡ኵላ፡ነፍሰ፡ጽምዕተ፡ወእ
ጽገብኩ፡ኵላ፡ነፍሰ፡ርኅብተ።

፳፮፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነቃሕኩ ፡ ወርኢኩ ፡
ወጥዕመኒ፡ንዋምየ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፴፪፡፩–፰።

፩፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብፁዕ ፡ ዘቦ ፡
ዘርዕ ፡ በጽዮን ፡ ወዘቦ ፡ አብያት ፡ በኢየሩ
ሳሌም።እስመ፡ናሁ፡ንጉሥ፡ጻድቅ፡ይነግሥ፡
ወመላእክትኒ፡በጽድቅ፡ይኴንኑ።

፪፤ ወየኀብእ፡ሰብእ፡ቃሎ፡ወይትኀባእ፡ከመ፡
ዘይሠጠም፡ውስተ፡ቀላይ።
ወያስተርኢ ፡ በጽዮን ፡ ከመ ፡ ፈለግ ፡
ዘይውኅዝ፡ክብሩ፡በምድር፡ጽምእት።
፫፤ ወኢይትዌከሉ፡እንከ፡በዕጓለ፡እመሕያው፡
ዳእሙ፡ያፀምዑ፡በዕዝኖሙ።

፬፤ ወልብ፡ድኩም፡ይሰምዕ፡አእምሮ፡ልሳንኒ፡
ጸያፍ፡ፍጡነ፡ይትሜሀር፡ነገረ፡ሰላም።
፭፤ ወኢታጽምዖ ፡ እንከ ፡ ለአብድ ፡ ወሶበ ፡
ይብለከ፡እንከ፡ወዓሊክ፡አርምም።

፮፤ እስመ፡አብድሰ፡ዕበደ፡ይነብብ፡ወልቡኒ፡
ከንቶ፡ይኄሊ፡ከመ፡ይግበር፡ዐመፃ፡ወከመ፡
ይንብብ፡ኃጢአተ፡በኀበ፡እግዚአብሔር፡
ወከመ፡ይዝሩ፡ነፍሰ፡ርኅብተ፡ወከመ፡
ያዕርቅ፡ነፍሰ፡ጽምእተ።

፯፤ እስመ፡ኄሊናሆሙ፡ለእኩያን፡ዐመፃ፡ትመክር፡
ከመ፡ይቅትልዎ፡ለነዳይ፡በነገረ፡ዐመፃሆሙ፡
ወከመ፡ይገፍትኡ፡ፍትሐ፡ምስኪናን።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፬፤ በይሁዳ፡አገሮች፡በአውራጃዎቿም፡ሁሉ፡
አንድነት፡የሚኖሩ፡አራሾች፡መንጋቸውን፡
ነድተው፡ይሄዳሉ።
፳፭፤ የተጠማችውን ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ አርክቻ
ለሁና ፤ የተራበችውንም ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ፡
ረድኤቴን፡አጥግቤያለሁና።
፳፮፤ ስለዚህ፡ተኘቼ፡ነቃሁ፤ራእይም፡አየሁ፤እን
ቅልፌም፡ጣፈጠኝ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህን፡ነው።

ምዕ፤፴፪፡፩–፰።

፩፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤በጽዮን፡ዘር፡
ያለው፡በኢየሩሳሌምም፡ቤት፡ያለው፡ሰው፡
ንዑድ፡ክቡር፡ነው፤እነሆ፡ደግ፡ንጉሥ፡
ይነግሣል ፡ አለቆችም ፡ በዕውነት ፡ ይፈር
ዳሉና።
፪፤ ሽፋጭ፡ሰው፡ቃሉን፡ይሠውራል፤በባሕር፡
እንደሚሠጥም፡ዓሣም፡ይሠወራል፤
በተጸማች ፡ ምድር ፡ እንደሚፈስ ፡ ፈሳሽ፡
ክብሩ፡በጽዮን፡ይገለጣል።
፫፤ በጆሮአቸው፡ያደምጣሉ፡እንጂ፡እንግዲህ፡
ወዲህ ፡ በሰው ፡ (ሰው ፡ በሠራው ፡ ጣዖት)፡
አያምኑም።
፬፤ ደካማ ፡ ልቡና ፡ ዕውቀትን ፡ ያውቃል፤ዲዳ፡
እንደበትም፡ፈጥኖ፡የሰላምን፡ነገር፡ይማራል፡
፭፤ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰነፍ ፡ ሰውን ፡ አታድ
ምጠው፤ሎሌህ፡ጣዖት፡እናምልክ፡ቢልህ፡
ዝም፡በል።
፮፤ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ስንፍናን ፡ ይናገራልና፤
ልቡም፡ኃጢአት፡ይሠራ፡ዘንድ፤በእግዚአብ
ሔርም ፡ ላይ ፡ በደልን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ፡
የተጠማች፡የተራበች፡ሰውነትንም፡ያሳዝን፡
ዘንድ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ ያስባልና ፡ ሰነፍ፡
ሰውን፡አታድምጠው።
፯፤ ድኃውን፡በግፍ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡የጠም፡
አዳሪውንም፡ፍርድ፡ለውጡ፡ዘንድ፡የክፉ፡
ሰዎች፡ልቡና፡ዐመፅን፡ትመክራለችና።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፰ መጸድቃንሰ ፡ ጥበበ ፡ ይመክሩ ፡ ወትነብር ፡ ይእቲ፡ምክር፡ለዓለም።

፱ አንስት ፡ ብዑላት ፡ ተንሥኣ ፡ ወስምዓኒ ፡ ቃልየ፡ ወአዋልድ ፡ ምእመናት ፡ አጽምዓኒ ፡ ነገርየ።

፲ ለለ፡መዋዕል፡ወለለ፡ዓመት፡ግበራ፡ተዝካረ፡ ዕለተ፡ሕማም፡እንዘ፡ትትሔዘባ። ኀለፈ ፡ ቀስም ፡ ወኀልቀ ፡ ማእረር ፡ ወኢይ መጽእ፡እንከ።

፲፩ ደንግፃ ፡ ወተከዛ ፡ ወእለ ፡ ተአንማ ፡ ዕርቃ ፡ ወተሰለባ፡ወእስራ፡ሐቌክን።

፲፪ ወሕፍጣ ፡ አጥባተክን ፡ ወገጸክን ፡ በእንተ ፡ ገራህት፡መፍትው፡ወበእንተ፡ዐጸደ፡ወይን፡ መፍርይ ። ወበእንተ ፡ ምድረ ፡ ሕዝብየ ፡ መፍትው።

፲፫ ወይበቊል፡ሦክ፡ወአሜከላ፡ውስተ፡ገራውሂሆሙ ። ወይሠዓር ፡ ትፍሥሕት ፡ እምኵሉ ፡ አብያቲሆሙ ። ሀገር፡ብዕልት፡ይተመዘበራ፡ አብያቲሃ።

፲፬ ወየኀድጉ፡አህጉሪሆሙ፡ብዕለ፡ወትርሢተ፡ አብያቲሆሙ ፡ ወይከውና ፡ አህጉሪሆሙ ፡ በአታተ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ በዓሎሙ ፡ ለአ እዱግ ፡ ገዳም ፡ ወለምርዓየ ፡ እንስሳ ፡ እስከ ፡ ይመጽእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መንፈስ ፡ እም ፡ አርያም።

፲፭ ወይከውን ፡ በድው ፡ ከርሜለ ፡ ወከርሜል ፡ አመ።

፲፮ ወየዓርፍ፡ፍትሑ፡ውስተ፡ገዳም፡ወጽድቁሂ፡ የኀድር፡ውስተ፡ቀርሜሎስ።

፲፯ ወካዕበ፡ይከውን፡ሰላም፡ወምግባረ፡ጽድቅ፡ ወትእኅዝ፡ጽድቅ፡መካነ፡ምዕራፍ፡ወይትዌከሉ፡ቦቱ፡እስከ፡ለዓለም።

፲፰ ወይነብሩ ፡ ሕዝብ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ሰላም ፡ ወይነብሩ፡ተአሚኖሙ፡ወየዓርፉ፡ውስተ፡ ብዕል።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፰፤ ጻድቃን፡ግን፡ጥበብን፡ይመክራሉ፤ይህቺም፡ ለዘላለሙ፡ጸንታ፡ትኖራለች።

፱፤ በብዕለ፡ጣዖት፡የከበራችሁ፡ሴቶች፡ተነሡ ታችሁ ፡ ቃሌን ፡ ስሙኝ ፤ የታመናችሁ ፡ ሴቶች፡ልጆች፡ነገሬን፡አድምጡኝ።

፲፤ መከራ፡የሚደረግበትን፡ቀን፡እያሰባችሁ፡ በየዓመቱና፡በየወራቱ፡መታሰቢያ፡አድርጉ፤ የወይኑ ፡ አዝመራ ፡ አለፈ ፤ የእህሉም ፡ አዝመራ፡አለቀ፤እንግዲህ፡አይመጣም።

፲፩፤ ለጣዖቱ ፡ መጋረጃ ፡ የምትፈትሉ ፡ ሴቶች ፡ ደንግጡ፤እዘኑ፤ልብሳችሁን፡ተገፈፉ፤ወገባ ችሁንም፡እሰሩ።

፲፪፤ ስለተወደደችው ፡ እርሻና ፡ ስለሚያፈራ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ስለተወደደ ፡ የሕዝቤ ፡ አገር ፡ ደረታችሁን ፡ ምቱ ፤ ፊታችሁንም ፡ ንጩ።

፲፫፤ በእርሻቸውም ፡ አሜከላና ፡ እሾኽ ፡ ይበቅል በታል፤ከቤታቸውም፡ሁሉ፡ተድላ፡ደስታ፡ ይጠፋል ፤ የተወደደች ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ የከበረች፡የኢየሩሳሌም፡ቤቶቿ፡ይፈርሳሉ።

፲፬፤ በአትክልት፡የከበሩ፡አገሮቻቸውና፡የቤቶቻ ቸውንም ፡ ጌጥ ፡ ይተዋሉ ፤ አገሮቻቸውም ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ዋሻ ፡ ይሆናሉ ፤ ከሰማይ፡ መንፈስ ፡ ረድኤት ፡ እስኪመጣ ላቸው፡ ድረስ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አህዮች ፡ ማረፊያ፡የከብቶችም፡መሰማሪያ፡ይሆናሉ።

፲፭፤ ምድረ፡በዳው፡ችፍርግ፡ይሆናል፤ችፍርጉም፡ ዛፍ፡ይሆናል።

፲፮፤ የእግዚአብሔር ፡ ፍርዱ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይደረጋል፤ቸርነቱም፡በጺጋው፡ጸንቶ፡ይኖራል።

፲፯፤ ዳግመኛም፡ሰላም፡የጽድቅም፡ሥራ፡ይሆናል፤ ዕውነትም ፡ የምታርፍበት ፡ ቦታ ፡ ታገኛለች ። እስከ፡ዘላለሙ፡ድረስም፡ያምኑበታል።

፲፰፤ ሕዝቡም ፡ ሰላም ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ ተዘ ልለው ፡ ይቀመጣሉ ፤ በባለጸግነትም ፡ ይኖራሉ።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፱፡ ወእመኒ፡ወረደ፡በረድ፡ኢይበጽሆሙ፡ወይት
አመኑ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡አም፡ወእለ፡
ይነብሩ፡ሐቅለ።

፳፡ ብፁዓን፡እለ፡ይዘርዑ፡ኀበ፡ቦቱ፡ማይ፡ወኀበ
ይከይድዎ፡ላሕም፡ወአድግ።

ምዕ፡፴፫፡፩-፲፩።

፩፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ያኀሥሩክሙ ።
ወለክሙሰ፡ አልቦ ፡ ዘያኀሥረክሙ ።
ወዘለክሙ፡ዐለወ፡አኮ፡ኪያክሙ፡ዘዐለወ።
ወይሠግሩ፡ዐላውያን፡ወይእኀዙሙ፡ድንጋጼ፡
ወከመ ፡ ቍንቍኔ ፡ ልብስ ፡ ከማሁ ፡
ይትበልዑ።

፪፡ እግዚኦ፡ተሣሃለነ፡እስመ፡ኪያከ፡ተወከልነ፡
ወኮነ፡ዘርዖሙ፡ለዓላውያን፡ለሐጕል። ወመ
ድኃኒትነሰ ፡ ለአመ ፡ ምንዳቤነ ፡ አንተ ፡
ውእቱ።

፫፡ ወእምግርማ ፡ ቃልከ ፡ ደንገፁ ፡ አሕዛብ ፡
ወተዘርዉ፡በፈሪሆትከ።

፬፡ ወይእዜኒ ፡ ናሁ ፡ ይትጋባእ ፡ ምህርካክሙ ፡
ንኡሱ፡ወዐቢዩ፡ከመ፡ዘይትጋባእ፡አንበጣ፡
ከማሁ፡ይትጋባእ፡ለክሙ።

፭፡ ወየኀድር ፡ ማእከሌክሙ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ዘየኀድር፡ውስተ፡ጽዮን፡ወውስተ፡
አርያም ። ወመልአት ፡ ጽዮን ፡ ጽድቀ ፡
ወርትዐ።

፮፡ ወያስተጋብእዎሙ ፡ በሕግ ፡ ውስተ ፡
መዛግብተ ፡ መድኃኒት ። መጽአት ፡ ጥበብ ፡
ወምክር፡ወጽድቅ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡
እስመ፡ተረከበት፡ጽድቅ።

፯፡ ናሁ ፡ እምግርማክሙ ፡ ፈርሁክሙ ፡ እለ ፡
ቀዲሙ ፡ ትፈርህዎሙ ፡ አንትሙ ፡ ወት
ርዕዱ ፡ እምኔሆሙ ። ወይትፌነዉ ፡ ሐዋር
ያት ፡ እንዘ ፡ መሪረ ፡ ይበክዩ ፡ ወይስእሉ ፡
ሰላመ።

፰፡ እስመ ፡ ማሰነ ፡ ፍኖቶሙ ፡ ወኀለፈ ፡
ግርማሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወተስዕረ ፡
ኪዳኖሙ ፡ ወኢትረስይዎሙ ፡ ከመ ፡
እደው።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፱፡ በረዶም ፡ ቢዘንም ፡ አይደርስባቸውም ፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚኖሩና ፡ በዱር ፡ የሚኖሩ፡
ሰዎችም፡ያምናሉ።

፳፡ ውኃ፡ባለበት፤አህያና፡ላም፡በሚረግጡት፡ቦታ፡
ዘር፡የሚዘሩ፡ሰዎች፡ንዑዳን፡ክቡራን፡ናቸው።

ምዕ፡፴፫፡፩-፲፩።

፩፡ ለሚያጕሳቍሏችሁ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው፡
እናንተን ፡ ግን ፡ የሚያጕሳቍላችሁ ፡ የለም፡
እናንተንም ፡ የወነጀለ ፡ ሰው ፡ እናንተን፡
የወነጀለ፡አይደለም፤ወንጀለኞች፡ይጠፋሉ፡
ድንጋጼ ፡ ይይዛቸዋል ፤ ብል ፡ ልብስን፡
እንዲበላ፡እንዲሁ፡ይበላሉ።

፪፡ አንተን፡ተስፋ፡አድርገናልና፡የወንጀለኞች፡
ሰዎች ፡ ልጅም ፡ ለጥፋት ፡ ሁኗልና፡ አቤቱ፡
ይቅር በለን ፤ ለእኛም ፡ በመከራችን ፡ ጊዜ፡
መድኃኒታችን፡አንተ፡ነህ።

፫፡ ከቃልህ ፡ ማስፈራት ፡ የተነሣ ፡ አሕዛብ፡
ደነገጡ፤አንተንም፡በመፍራት፡ተበተኑ።

፬፡ አሁንም ፡ እነሆ ፡ ታናሹም ፡ ታላቁም፡ምር
ኦችሁ ፡ አንበጣ ፡ በአጥር ፡ እንዲሰበሰብ፡
እንደዚሁ፡ይሰበሰብላችኋል።

፭፡ በአርያምና ፡ በጽዮን ፡ የሚኖር ፡ የተመሰገነ፡
እግዚአብሔር ፡ በመካከላችሁ ፡ በረድኤት፡
ይኖራል ፤ ጽዮንም ፡ የቀና ፡ ፍርድንና፡
ዕውነት፤ነገርን፡ተመላች።

፮፡ ድኅነት ፡ ወደ ፡ ሚደረግባት ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ በሕግ ፡ ይሰበስቧቸዋል ። ዕውነት፡
ነገር፡ ተገኝታለችና፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡
ጥበብ፡ምክር፡ዕውነት፡መጣች።

፯፡ ቀድሞ፡እናንተ፡ትፈሩአቸው፡የነበረ፡ከእነር
ሳቸውም ፡ የተነሣ ፡ ትንቀጠቀጡ ፡ የነበረ፡
አሕዛብ ፡ እነሆ ፡ ከግርማችሁ ፡ የተነሣ፡
ፈሩአችሁ፤መልእክተኞችም፡ጽኑ፡ልቅሶን፡
እያለቀሱ፡ይላካሉ፤ሰላምን፡ይለምናሉ።

፰፡ ጐዳናቸው፡ጠፍቷልና፡የአሕዛብ፡መፈራ
ቸውም ፡ ቀርቷልና ፡ መሐላቸውም፡
ፈርሷልና፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ እንጂ ፡ እንደ፡
ወንዶች፡አታድርጓቸው።

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፱ ለሐወት ፡ ምድር ፡ ወተነፍረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወለመ፡ከነ፡ሣሮን፡ወተዓውቀ፡ገሊላ፡ወቀርሜሎስ።

፲ ናሁ ፡ ይእዜ ፡ እትነሣእ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይእዜ ፡ እሴባሕ ፡ ወይእዜ ፡ እትሌዓል፡አነ።

፲፩ ወይእዜ፡ትሬእዩኒ፡ወይእዜ፡ታነክሩኒ።

ምዕ፡፶፪፡፲፫–፲፭።

፲፫ ናሁ ፡ ይሌቡ ፡ ቍልዔየ ፡ ወይትሌዓል ፡ ወይከብር፡ወይትፌሣሕ፡ፈድፋደ።

፲፬ ወያነክሩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ብዙኃን ፡ ከመ ፡ ዘነኪር፡ ራእዩ ፡ እምሰብእ ፡ ወክቡር ፡ እምዕጓለ፡እመሕያው።

፲፭ ወኪያሁ ፡ ያነክሩ ፡ አሕዛብ ፡ ብዙኃን ፡ ወኢይፈትሑ ፡ አፉሆሙ ፡ ነገሥት ፡ እስመ ፡ እለ፡ኢዜነውዎሙ፡በእንቲአሁ፡ያእምርዎ፡ ሀለዎሙ ፡ ወእለሂ ፡ ኢሰምዕዎ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይለብውዎ።

ምዕ፡፶፫፡፩–፲፪።

፩ እግዚኦ፡መኑ፡የአምነነ፡ቃለነ፡ወስምዓነ፡ ወለመኑ ፡ ተከሥተ ፡ መዝራዕቱ ፡ ለእግዚአብሔር።

፪ ወነገርነኒ ፡ ከመ ፡ ሕፃን ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወከመ፡ሥርው፡በውስተ፡ምድር፡ጽምእት፡ አልቦ ፡ ራእይ ፡ ወኢትርሲት ፡ ወርኢናሁ ፡ ወአልቦ፡ራእይ፡ወአልቦ፡ላህይ።

፫ ወራእዩኒ፡ምኑን፡ወትሑት፡እምኵሉ፡ሰብእ፡ ብእሲ፡ቅሡፍ፡ውእቱ፡ወሕሙም፡እስመ፡ ሜጠ፡ገጾ፡ወአስተሐቀርዎ፡ወኢሰብሕዎ።

፬ ውእቱ፡ነሥአ፡ደዌነ፡ወጾረ፡ሕማመነ፡ወበእንቲአነ፡ሐመ፡ወንሕነኒ፡ርኢናሁ፡ሕሙመ፡ ወቅሡፈ፡በሕማም።

፭ ወውእቱሰ ፡ ቈስለ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትነ ፡ ወሐመ ፡ በእንተ ፡ ጌጋይነ ፡ ትእምርተ ፡ ሰላምነ።

፮ ወበቍስለ ፡ ዚአሁ ፡ ሐየውነ ፡ ቊስለነ ፡ ኵልነ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ተገደፍነ ። ብእሲኒ፡ዘዘዚአሁ፡ሖረ፡በፍኖቱ ። ወስሕተ ፡ ወመጠዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትነ።

፯ ወውእቱሰ፡ኢከሠተ፡አፉሁ፡በሕማሙ፡



፱፥ ምድር ፡ አለቀሰች ፤ ሊባኖስም ፡ አፈረ ፤ (ንጉሡ)፡አክርማው፡ዛፍ፡ሆነ፤ገሊላም፡ከቀርሜሎስ፡ጋራ፡በጥፋት፡ታወቀ።

፲፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ እነሣለሁ፤አሁንም፡እመሰገናለሁ፤አሁንም፡እኔ፡ከፍ፡ከፍ፡እላለሁ፡አለ።

፲፩፥ አሁን፡ታዩኛላችሁ፤ዛሬ፡ታደንቁኛላችሁ።

ምዕ፡፶፪፡፲፫–፲፭።

፲፫፥ እነሆ፡ወዳጄ፡ልብ፡ያደርጋል፡ከፍ፡ከፍም፡ይላል፤ይከበራል፡ፈጽሞም፡ደስ፡ይለዋል።

፲፬፥ መልኩ፡ከሰው፡ልዩ፡እንደመሆኑ፡ከሰውም፡ይልቅ፡የተወደደ፡እንደመሆኑ፡ብዙ፡ሰዎች፡የሱን፡ነገር፡ያደንቃሉ።

፲፭፥ ብዙዎች ፡ አሕዛብም ፡ እሱን ፡ ያደንቃሉ ፤ ነገሥታቱ ፡ ግን ፡ አያመሰግኑትም ፤ ነቢያት ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ ያልነገርዋቸው ፡ ኋላ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አላቸውና ፤ ያልሰሙትም ፡ ሰዎች ፡ ልብ፡ያደርጉት፡ዘንድ፡አላቸውና።

ምዕ፡፶፫፡፩–፲፪።

፩፥ አቤቱ ፡ ነገራችንን ፡ ማን ፡ ያምነናል ? የእግዚአብሔርስ ፡ ክንድ ፡ ለማን ፡ ተገለጸ።

፪፥ ነገራችንም ፡ በፊታቸው ፡ እንደ ፡ ሕፃንና ፡ በተጠማች ፡ ምድር ፡ እንዳለ ፡ ሥር ፡ ነው ፤ መልክ ፡ ጌጥ ፡ የለውም ፤ እነሆ ፡ አየነው ፤ መልክ፡የለውም፤ደም፡ግባትም፡የለውም።

፫፥ መልኩም ፡ የተናቀ ፤ ከሰውም ፡ ሁሉ ፡ የተዋረደ፣ የተገረፈ ፤ የታመመ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ፊቱን፡መልሷልና፡ናቁት፡አላከበሩትም።

፬፥ እርሱ ፡ ደዌያችንን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ (ተቀበለ)፡ ሕማማችንንም ፡ ተሸከመ ፤ ስለእኛም ፡ ታመመ ፤ እኛም ፡ ታሞ ፡ በመከራም፡ተጨንቆ፡አየነው።

፭፥ እርሱ፡ግን፡ስለ፡ኃጢአታችን፡ቈሰለ፤ስለ፡በደላችንም፡ታመመ፤የፍቅር፡የአንድነታችንም፡ምልክት፡እርሱ፡ነው።

፮፥ ሁላችን፡ቃባ፡እንደ፡ያዘው፡በግ፡ወድቀን፡ሳለን፡በእርሱ፡መቊሰል፡ከቊስላችን፡ዳን፤ሰው፡ሁሉ፡እየራሱ፡በኃጢአቱ፡ጸንቶ፡ኖረ፤ስለ፡ኃጢአታችንም፡እግዚአብሔር፡ለሞት፡አሳልፎ፡ሰጠው።

፯፥ እርሱ፡ግን፡በመከራው፡ጊዜ፡ነገር፡አልተናገረም፤

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወመጽአ ፡ ይጠባሕ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ወከመ ፡
በግዕ፡ ኢይነብብ ፡ በቅድመ ፡ ዘይቀርጾ ፡
ከማሁ፡ኢከሠተ፡አፉሁ፡በሕማሙ።
፰፡ እስመ ፡ ይነሥእዋ ፡ ለነፍሱ ፡ ወኢየ
አምርዎ ፡ ለልደቱ ፡ ወይነሥእዋ ፡ ለሕ
ይወቱ ፡ በኃጢአተ ፡ ሕዝብየ ፡ በጽሐ ፡
ለሞት።
፱፡ ወእሁብ ፡ እኩያነ ፡ ህየንተ ፡ ሞቱ ፡ ወአብ
ዕለተ፡ ህየንተ፡መቅበርቱ፡እስመ፡ኢገብረ፡
ኃጢአተ ፡ ወኢተረክበ ፡ ሐሰት ፡ ውስተ ፡
አፉሁ።
፲፡ ወፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያንጽሖ ፡ እምነ ፡
መቅሠፍቱ ። ወእመኒ ፡ ወሀብክሙ ፡ በእንተ ፡
ኃጢአትክሙ ፡ ትሬኢ ፡ ነፍስክሙ ፡ ዘርዐ ፡
ዘነዋኅ፡የሐዩ።
፲፩፡ ወይፈቅድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያእትት ፡
ሕማመ ፡ እምነፍሱ ። ወያርእዮ ፡ ብር
ሃነ ፡ ወይፈልጦ ፡ በጥበቡ ፡ ወያጸድቆ ፡
ለጻድቅ፡ለዘይትቀነይ፡ለጽድቅ፡ወለሠናይ፡
ወለብዙኃን ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ውእቱ ፡
ይደመስስ።
፲፪፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ይወርሶሙ ፡ ለእስ
ራኤል ፡ ወይማኅርኮሙ ፡ ለጽኑዓን ፡ እስመ ፡
ተውህበት ፡ ለሞት ፡ ነፍሱ ፡ ወተኈለቈ ፡
ምስለ፡ኃጥአን።
ወውእቱ ፡ ፆረ ፡ (የዐርግ) ፡ ኃጢአቶሙ ፡
ለብዙኃን። ወበእንተ፡ኃጢአቶሙ፡ተውህበ፡
ውእቱ።

ምዕ፡፶፬፡፩–፰።

፩፡ ትትፌሣሕ ፡ መካን ፡ እንተ ፡ ኢትወልድ ፡
ወትኬልሀ ፡ ወተዐወዩ ፡ እንተ ፡ ኢሐመት ፡
እስመ ፡ ብዙኃን ፡ ውሉዳ ፡ ለመዓስብት ፡
እምእንተ፡ባቲ፡ምት።
፪፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
አርኅቢ፡ መታክለ ፡ ደብተራኪ ፤ ወትክሊ ፡
ዓጸደኪ ፤ ወኢትምሀኪ ፡ አንኂ ፡ አሕባለኪ ፡
ወአንሥኢ፡ሠርዌኪ።
፫፡ ወአጽንዒ ፡ መታክለኪ ፤ ወዓዲ ፡ ለየማን ፡
ወለፀጋም ፡ አንጦልዒ ፡ እስመ ፡ ዘርዕኪ ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ገረም ፤ እንደ ፡ በግ ፡ ይታረድ ፡ ዘንድ ፡ መ...
በግ፡ በሚሸልተው፡ ሰው ፡ ፊት ፡ እንዳይናገር
እንደዚያ፡በመከራው፡ጊዜ፡አልተናገረም፡
፰፡ ሰውነቱን፡ይይዟታልና፡ልደቱንም፡አያውቋ
ትምና ፡ ሕይወቱንም ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ይወስዷ
ታልና ፡ በወገኖቼ ፡ ኃጢአት ፡ ለሞት ፡
ደረሰ።
፱፡ ኃጢአት ፡ አልሠራምና ፤ በአንደበቱም ፡
ሐሰት፡ ነገር ፡ አልተገኘምና ፤ ስለሞቱ ፡
ክፉዎችን፡ለሞት፡እሰጣለሁ፤ስለመቃበሩም፡
ባለጸጎችን፡አሳልፌ፡እሰጣለሁ።
፲፡ እግዚአብሔርም፡ከግርፋቱ፡ያነጻው፡ዘንድ፡
ወደደ ፤ ስለ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ ገንዘባችሁን
ብትሠዉ ፡ ሰውነታችሁ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡
የሚኖር፡ዘርን፡ታያለች።
፲፩፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰውነቱ ፡ ሕማምን ፡ ያርቅ ፡
ዘንድ ፡ ይወዳል ፤ ብርሃንንም ፡ ያሳየዋል ፤
በባሕርዩ ፡ ጥበቡም ፡ ይለየዋል ፤ ለበጎ ፡ ነገር፡
ለጽድቅም ፡ የሚገዛውን ፡ እውነተኛውን ፡ ሰው፡
የጽድቁን፡ዋጋ፡ይሰጠዋል፤ያከብረዋል፤የብዙ፡
ሰዎችንም፡ኃጢአት፡እርሱ፡ይደመስሳል።
፲፪፡ ሰውነቱ ፡ ለሞት ፡ ተሰጥታለችና ፤ ከኃጢአተ
ኞችም ፡ ጋራ ፡ ተቈጥሮአልና ፤ ስለዚህ፡እስራ
ኤልን ፡ እርሱ ፡ ይወርሳቸዋል ፤ ጽኑዓን፡
የሚሆኑ፡አሕዛብንም፡ይማርካቸዋል።
እርሱም፡የብዙ፡ሰዎችን፡ኃጢአት፡ተሸክሞ፡
(ይዞ፡ወደ፡መስቀል፡ይወጣል)፡ስለኃጢአታ
ቸውም፡እሱ፡ለሞት፡ተሰጠ።

ምዕ፡፶፬፡፩–፰።

፩፡ ያልወለደች፡መካን፡ሴት፡ደስ፡ይላታል፤(ሊያ
ሳሌም)፡ባል፡ካላት፡ይልቅ፡ባል፡የሌላት፡ሴት
(ባቢሎን)፡ልጆቿ፡ብዙ፡ናቸውና፡አምጣ፡ያል
ወለደች፡ሴት፡ጮኺ፡ታለቅሳለች።
፪፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፤ የድንኳ
ንሽን፡መትከያ፡ቦታ፡አስፊ፤ድንኳንሽንም፡
ትከዪ ፤ አትሽልጊ ፤ አውታሮችሽንም፡
አርዝሚ፡ተራዳሽንም፡አንሺ።
፫፡ ካስማሽንም ፡ አጽኚ ፤ ዳግመኛም ፡ በቀኝና፡
በግራ፡መጋረጃሽን፡ጋርጂ፤ጠፍተው፡የነበሩ፡

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ይወርሱ ፡ አሕዛበ ፡ ወትነብሪ ፡ አህጉረ ፡
መዝበረ።
ወኢትፍርሂ ፡ እስመ ፡ ተኃፊርኪ ፡ ወኢት
፬ ኀፈሪ፡ እስመ ፡ ጸአሉኪ ። ወትረሥዒ ፡
ኀፍረተኪ ፡ ዘለዓለም ፤ ወኢትዘከሪዮ ፡ ለጽእ
ለትኪ፡ዘእመ፡ምዕስብናኪ።
፭ እስመ፡ዘገብረ፡ለኪ፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡
ስሙ፡ወውእቱ፡አምላከ፡እስራኤል፡ዘአድ
ኀነኪ፡ወዘይሰመይ፡በኵሉ፡ምድር።
፮ እኮ ፡ ከመ ፡ ብእሲት ፡ ኅድግት ፡ ወዕ
ንብዝት ፡ ዘጸውዓኪ ፡ እግዚአብሔር ።
ወእኮ ፡ ከመ ፡ ብእሲት ፡ ጽእልት ፡
እምንእሳ።
፯ ይቤ ፡ አምላክኪ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡
ኀደጉኪ ፡ ወበዐቢይ ፡ ምሕረት ፡ እሣ
ሀለኪ።
፰ በኅዳጥ፡መዐት፡ሜጥኩ፡ገጽየ፡እምኔኪ፡ወበ
ምሕረት፡ዘለዓለም፡እሣሃለኪ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡ዘአድኃነኪ፡እምነ፡ማይ፡ዘአመኖኅ።

ክፍል፡፲፪።

መጽሐፈ፡ዶርሆ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
አሐዱ፡አምላክ፡ድርሳን፡ወትምህርት፡
ዘአበዊነ፡ሐዋርያት፡ቅዱሳን፡ዘመሀሩነ፡
መንፈሳውያን።
፩ እሉ፡እሙንቱ፡እለ፡ይገብሩ፡ኀይላተ፡ወተአ
ምራተ፡ወትምህርተ፡ሕይወት።

፪ ወዝ ፡ ነገር ፡ ዘከመ ፡ ገብሩ ፡ አይሁድ ፡
ላዕለ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘጾረ ፡
ሕማማተ ፡ በዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ቅዱስ ፡
በእንቲአነ ፡ ለክርስቲያን ። ወሞተ ፡ ወተ
ነሥአ ፡ እሙታን ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡
ዘይእቲ፡ዕለተ፡ትንሣኤሁ፡ቅድስት፡ከመ፡
ያድኅነነ።
፫ ወካዕበ ፡ በእንተ ፡ ዘከሕዶ ፡ ጴጥሮስ ፡
ረድኡ።
፬ ወበእንቲአነ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡ዘሐመ፡በእ
ንቲአነ፡ይባርከ፡ላዕሌነ ። ወላዕለ ፡ ኵሎሙ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ልጆችሽ ፡ አሕዛብን ፡ ይወርሳሉና ። የፈረሱ
ትንም፡ከተሞች፡መኖሪያ፡ታደርጊያለሽና።
፬ ስላፈርሽም ፡ አትፍሪ ፤ ስለሰደቡሽም ፡
አትፈሪ፤ የዘላለም ፡ ኀፍረትሽንም ፡ ትረሺ
ያለሽ፡ጋለሞታ፡በነበርሽ፡ጊዜ፡ትሰደቢ፡የነ
በረውንም፡ስድብ፡አታስቢውም።
፭ ይኸን፡ያደረገልሽ፡ስሙ፡አሸናፊ፡የሚባል፡እግ
ዚአብሔር፡ነውና፡ያዳነሽ፡ስሙም፡በዓለም፡
ሁሉ፡የተጠራ፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡ነውና።
፮ እንደ ፡ ተተወች ፡ አእምሮዋን ፡ እንዳጣች ፡
ሴት፡ እግዚአብሔር ፡ የጠራሽ ፡ አይደለም ፤
ከሕፃንነቷ፡ጀምራ፡እንደተሰደበች፡ሴትም፡
የተጠራሽ፡አይደለም።
፯ ፈጣሪሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡
ተለየሁሽ ፤ ኋላ ፡ በብዙ ፡ ቸርነት ፡ ይቅር ፡
እልሻለሁ፡አለ።
፰ በኖኅ፡ጊዜ፡እንደተደረገ፡ካለ፡ውኃ፡ያዳነሽ፡
እግዚአብሔር ፡ በጥቂት ፡ ቍጣ ፡ ገጼ ፡
ምሕረቴን፡ካንቺ፡መለስኩ፡አለ።

ክፍል፡፲፪።

መጽሐፈ፡ዶርሆ።

አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ያስተማሩን፡የከበሩ፡
መንፈሳውያን፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡የደረ
ሱትና፡ያስተማሩት፡ይህ፡ነው።
፩ እነርሱም ፡ ኃይልን ፡ ተአምራትን ፡ የሚያ
ደርጉ፡ሕይወት፡የሚገኝበትንም፡ትምህርት፡
የሚያስተምሩ፡ናቸው።
፪ ይህ ፡ ነገር ፡ ስለእኛ ፡ ስለ ፡ ክርስቲያኖች ፡
በከበረ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ መከራ ፡
በተቀበለ፡ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ላይ ፡
አይሁድ ፡ እንዳደረጉ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡
እንደሞተ ፡ በእሑድ ፡ ቀንም ፡ እንደተነሣ ፡
እርሷም ፡ ልዩ ፡ የሆነች ፡ የትንሣኤው ፡ ቀን ፡
ናት።
፫ ዳግመኛም፡ደቀ፡መዝሙሩ፡ጴጥሮስ፡ክዶት፡
እንደነበረ፡የሚገልጽ፡ነው።
፬ ስለእኛ ፡ ፍቅር ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ አምላ
ካችን፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርከን ፤ ያክብረን ፤

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ይትጋብኡ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
እስከ፡ነፍስ፡ቅድስት፡ጉቡአን፡ይዕቀቦሙ፡እስከ፡ነፍስ፡
ደኃሪት፤
፭ ወይዕቀበነ ፡ ለኵልነ ፡ ውሉደ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
፮ ወእምድኅረ፡ሠላሳ፡ወሠለስቱ፡ዓመቱ፡ለእግ
ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ሕያው ፡ መጽአ ፡ ኀቤነ ፡ ኀበ ፡
አርድእቱ፡ዐሥርቱ፡ወክልኤቱ፡ወይቤለነ፡
አ፡አኀውየ፡ወፍቁራንየ፡ቀርበ፡ዝ፡መዋዕል፡
ቀሊል፡ዘጽሑፍ፡በእንቲአየ፡ውስተ፡ዝንቱ፡
ዓለም።
፯ ወአነ ፡ አቅደምኩ ፡ ነጊሮተክሙ ። ወእም
ድኅረ፡ ውኁድ ፡ መዋዕል ፡ ኢይትናገር ፡
ምስሌክሙ፡ወምስለ፡ኵሉ፡ዓለም።
፰ ወይትነሥኡ ፡ ላዕሌየ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡
ዐበይት፡ወጸሐፍተ፡አይሁድ፡እለ፡እምኢየሩ
ሳሌም፡ይቅትሉኒ።
፱ ወእምድኅረ ፡ ሠሉስ ፡ ዕለት ፡ እትነሣእ ፡
እሙታን ። ተንሥኡ ፡ ንሑር ፡ እምዝየ ።
ወቀርበ ፡ ዝ ፡ መዋዕል ፡ ዘእሜጡ ፡ ነፍስየ ፡
በእንተ፡መድኃኒተ፡ኵሉ፡ዓለም።
፲ ወእምድኅረዝ ፡ ተንሥአ ፡ እግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡
ዘይት ፤ ወነበረ ፡ መልዕልተ ፡ እብን ። ወገጹ ፡
ሕዙን።
፲፩ ወይቤሎሙ ፡ ለአርድእት ፡ ነፍስየ ፡ ተሐዝን ፡
በእንቲአክሙ ፡ ወአሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡
ይሜጥወኒ ፡ ለሞት ፡ ወይትከዐው ፡ ደምየ ፡
ንጹሕ ፡ በእንቲአሁ ። እምኄሶ ፡ ሶበ ፡
ኢተወልደ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ውስተ ፡
ዓለም።
፲፪ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ዐሠ
ርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ከደኑ ፡
ገጾሙ ፡ ወበከዩ፡ ኵሎሙ ፡ ብካየ ፡ መሪረ ፡
እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ንስእል ፡ እምኀቤከ ፡ አ ፡
ሊቅነ ። ከመ ፡ መኑ ፡ እምኔነ ፡ ዘያገብአከ ፡
መሐረነ፡አ፡እግዚእነ፡መኑሁ፡እምኔነ፡ንሕነ፡
ዘተሎናከ፡ዐሠርቱ፡ወክልኤቱ፡ሐዋርያት፡
ዝ፡ ነገር ፡ ዘትትናገረነ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡
ወመድምም፡ሰሚዖቱ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

በከበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰብስበው ፡
ያሉትንም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ መጨረሻይቱ ፡
ሕቅታ፡ድረስ፡ይጠብቃቸው።
፭ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ልጆች ፡ ሁላችንንም ፡
ለዘላለሙ፡ይጠብቀን፤አሜን።
፮ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሆነው ፡
በኋላ ፡ ወደእኛ ፡ ወደዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ደቀ ፡
መዛሙርቱ ፡ መጥቶ ፡ የተወዳዳችሁ ፡
ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡
የተጻፈው ፡ ይህ ፡ አጭር ፡ ወራት ፡ ቀረበ ፡
አለን።
፯ እኔም ፡ አስቀድሜ ፡ ነግሬአችሁ ፡ ነበር ፡
ከጥቂት ቀንም ፡ በኋላ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡
ከሰውም፡ሁሉ፡ጋር፡አልናገርም።
፰ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ታላላቆቹ ፡
የካህናት፡ አለቆችና ፡ የአይሁድ ፡ ጸሐፎች ፡
ይገድሉኝ፡ዘንድ፡በእኔ፡ላይ፡ይነሣሉ።
፱ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ተለይቼ ፡
እነሣለሁ ፤ ተነሡ ፡ ከዚህ ፡ እንሂድ ፤ ለዓለም ፡
ሁሉ ፡ ድኅነት ፡ ነፍሴን ፡ ለሞት ፡ የምሰጥበት ፡
ቀን፡ቀርቧል።
፲ ከዚህም፡በኋላ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ተነሥቶ፡ወደ፡ደብረ፡ዘይት፡ሄደ፡በደንጊያ፡
ላይም፡ተቀመጠ፤በፊቱም፡የሐዘን፡መልክ፡
ይታይ፡ነበር።
፲፩ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ ልቡናዬ ፡ ስለ ፡
ናንተ ፡ ታዝናለች ፤ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ለሞት ፡
አሳልፎ፡ ይሰጠኛል ፤ በእርሱም ፡ ምክንያት ፡
ንጹሕ ፡ ደሜ ፡ ይፈሳል ፡ አላቸው ፤ ያ ፡ ሰው ፡
በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ባለተወለደ ፡ በተሻለው ፡
ነበር፡አለ።
፲፪ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያትም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡
በሰሙ፡ጊዜ፡ፊታቸውን፡ሸፍነው፡ሁላቸውም፡
መራራ፡ልቅሶ፡አለቀሱ፤እንዲህ፡ኢየሱስ፡መም
ራችን፡ሆይ፡ካንተ፡ዘንድ፡እንለምናለን፡ከእኛ፡
መካከል፡አሳልፎ፡ለአይሁድ፡የሚሰጥህ፡ማን፡
እንደሆነ፡ግለጥልን፤ጌታ፡ሆይ፡ከእኛ፡ከተከታ
ልንህ፡ከዐሥራ፡ሁለቱ፡ሐዋርያት፡ማንነው፤ለእኛ፡
የምትናገረው፡ነገር፡ታላቅ፡ነው፤መስማቱም፡
ድንቅ፡ነው።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፫ መኑ፡ዘይከሕድ፡እምኔነ፡ንግረነ፡ገሀደ፡በእንቲአሁ፡ገ፡ሐዘንነ፡ያረምመነ።

፲፬ ወይቤሎሙ፡መድኃኒነ፡አነ፡አቅዲሙ፡ነገርኩክሙ፡ወአነ፡ለእመ፡አርመምኩ፡ይትናገር፡ገ፡እብን፤ወይቤልዎ፡ሠናየ፡ትቤ።

፲፭ ወእምድኅረዝ፡ይቤሎሙ፡ትሬእዩ፡ዘይከውን፡አነ፡ለልየ፡በአፉየ፡ተናገርኩክሙ፡መኑ፡እምኔክሙ፡ዘያገብአኒ፡ከመ፡ኢይበል፡አሐዱ፡አሐዱ፡አነኑ፡እንጋ፡በልቡ፡ወአነ፡አአምር፡ዘትብሉ።

፲፮ አንጽሑ፡ልበክሙ፡ወኢትብክዩ፡ቀሊል፡ውእቱ፡እስከ፡ተአምሩ፡ዘይከውን።

፲፯ ዝ፡ዕምደ፡እብን፡ዘሀለወ፡ቅውመ፡ላዕለ፡ደብረ፡ዘይት፡ይትናገር፡ኀበ፡ሀለዉ፡ንቡራን፡(ኑቡአን)።

፲፰ ወይቤሎ፡እግዚእነ፡ለዐምድ፡አንተ፡ዐምደ፡እብን፡ቀዊመከ፡ዘሀሎከ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ደብር፡አንተ፡ዘአልብከ፡ነፍስ፡አዘዝኩከ፡ተነቀል፡እመካንከ፡ወተናገር፡እሙነ፡ምስለ፡አርድእት፡መኑ፡እምኔሆሙ፡ዘይሜጥወኒ፡ለሞት፤ወሶበ፡ፈርሀ፡ዐምድ፡ወተነቅለ፡እምታሕቱ።

፲፱ ወያዶሙ፡ለአርድእት፡ወቆመ፡ከመ፡አክሊል፡ላዕለ፡ርእሰ፡እግዚእነ።

፳ ወካዕበ፡ዖደ፡ላዕለ፡ርእሰ፡ይሁዳ፡አስቆሮታዊ፤ወሶበ፡ነጸረ፡ይሁዳ፡ቀዊሞ፡ዓምድ፡መልዕልተ፡ርእሱ፡ሐዘነ፡ፈድፋደ።

፳፩ ወተናገረ፡ይሁዳ፡ወይቤሎ፡ለእግዚእነ፡አዝዝ፡ዳግመ፡ይዑድ፡ላዕሌነ፡ከመ፡ናእምር፡ዘያገብአከ፡እምኔነ፡ለእመ፡ኮንኩ፡አነ።

፳፪ ወይቤሎ፡እግዚእነ፡ለዐምድ፡ዳግመ፡ዑድ፡ላዕሌሆሙ፡ወተናገር፡እሙነ፡መኑ፡እምኔሆሙ፡ዘይፈቅድ፡ያግብአኒ፡ለሞት።

፳፫ ወበጊዜሃ፡ፈርሀ፡ወቆመ፡ዐምድ፡ወዖደ፡ላዕለ፡ርእሰ፡ይሁዳ፤ወወፅአ፡ቃል፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፫፤ ከእኛ፡ውስጥ፡የሚክድ፡ማነው? ስለእርሱ፡ገልጠህ፡ንገረን፤ይህ፡ከሐዘናችን፡ዝም፡ያሰኘናል፡አሉት።

፲፬፤ መድኃኒታችንም፡እኔ፡አስቀድሜ፡ነግሬአችኋለሁ፤አሁንም፡እኔ፡ዝም፡ብል፡ይኸ፡ደንጊያ፡ይናገራል፡አላቸው፤እነርሱም፡መልካም፡አልክ፡አሉት።

፲፭፤ ከዚህም፡በኋላ፡የሚሆነውን፡ታያላችሁ፤እኔ፡ራሴ፡በአፌ፡ተናገርኋችሁ፤ከእናንተ፡ማን፡አሳልፎ፡እንደሚሰጠኝ፤አንዱም፡አንዱ፡እኔ፡እሆን? እንጃ፡እንዳይል፤እኔም፡የምታስቡትን፡አውቃለሁና፡አላቸው።

፲፮፤ ከመጠራጠር፡ልባችሁን፡አንጹ፤የሚሆነውን፡እስከምታውቁ፡ድረስ፡ይህ፡ቀላል፡ነውና፡አታልቅሱ።

፲፯፤ ይህ፡በደብረ፡ዘይት፡ተራራ፡ላይ፡ቁሞ፡ያለው፡ትክል፡ደንጊያ፡ከዚህ፡ተቀምጠው፡(ተሰብስበው)፡በአሉት፡ዘንድ፡ይናገራል፡አለ።

፲፰፤ ጌታችንም፡በዚህ፡ተራራ፡ላይ፡ቁመህ፡ያለህ፡የደንጊያ፡ዐምድ፡አንተ፡ነፍስ፡የሌለህ፡ስትሆን፡ከቦታህ፡ተነቅለህ፡ከሐዋርያት፡ዘንድ፡ለሞት፡አሳልፎ፡የሚሰጠኝ፡ማን፡እንደሆነ፡ዕውነቱን፡ተናገር፡ብዬ፡አዘዝኩህ፡አለው፤ወዲያው፡ያ፡የደንጊያ፡ምሰሶ፡ፈርቶ፡ከሥሩ፡ተነቀለ።

፲፱፤ ሐዋርያትንም፡ዞሮ፡በጌታችን፡ራስ፡ላይ፡እንደ፡አክሊል፡ሁኖ፡ረበበ።

፳፤ ዳግመኛም፡በአስቆሮቱ፡ይሁዳ፡ራስ፡ላይ፡ዞረ፤ይሁዳም፡ደንጊያው፡በራሱ፡ላይ፡ቁሞ፡በተመለከተ፡ጊዜ፡እጅግ፡አዘነ።

፳፩፤ ይሁዳም፡ተናገረ፤ከእኛ፡ውስጥ፡አሳልፎ፡የሚሰጥህን፡ምናልባት፡እኔ፡ብሆን፡እናውቅ፡ዘንድ፡በእኛ፡ላይ፡እንዲዞር፡ጌታችንን፡ዳግመኛ፡እዘዝ፡አለው።

፳፪፤ ጌታችንም፡ደንጊያውን፡ዳግመኛ፡በላያቸው፡ዞር፤ከእነርሱም፡ለሞት፡አሳልፎ፡ይሰጠኝ፡ዘንድ፡የሚፈልግ፡ማን፡እንደሆነ፡እውነቱን፡ተናገር፡አለው።

፳፫፤ በዚያን፡ጊዜም፡ያ፡የደንጊያ፡ዐምድ፡ፈርቶ፡በዚያን፡ራስም፡ላይ፡ዞረ፤የአስቆሮቱ፡ተነሣ፤በይሁዳ፡ራስም፡ላይ፡ዞረ፤የአስቆሮቱ፡

Scanned by CamScanner

### በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

መደንግፅ፡ዘይብል፡ወይ፡ለከ፡ይሁዳ፡ወልደ፡ስምዖን፡አስቆሮታዊ፡ወዝ፡ነገር፡ማሕዘኒ፡ዘሀሎ፡ውስተ፡ልብከ፡በዝ፡መዋዕል።

፳፬፤ ወብዙኅ፡ጊዜ፡ትፈቅድ፡ትመጥዎ፡ለሞት፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአብሔር።

፳፭፤ ወይ፡ለከ፡ይሁዳ፡ዘአበይካ፡ለበረከት፡ወትርሕቅ፡እምኔከ፡ወለበስካ፡ለመርገም፡ከመ፡ልብስ፡ወቦአ፡ከመ፡ማይ፡ውስተ፡አማዑቲከ፡ወከመ፡ቅብዕ፡ውስተ፡አዕፅምቲከ፡ወከመ፡ቅናት፡ውስተ፡ሐቌከ።

፳፮፤ ወዝ፡ደም፡ንጹሕ፡ዘሀሎ፡ነቢሮ፡ዝየ፡ይትከዐው፡በእንቲአከ።

፳፯፤ ወዘይቤ፡ወንጌል፡በጽሐ፡እምኀየሰከ፡ይእስሩ፡በከሣድከ፡ማሕረጸ፡አድግ፡ወያስጥሙከ፡ውስተ፡ቀላየ፡ባሕር። ወበእንቲአከ፡እምይትከዐው፡ደም፡ንጹሕ፡እምኀየሰከ፡ከርሠ፡እምከ፡ይኩንከ፡መቃብረ፡እምትትወለድ፡ተባዕተ፡በዕለተ፡ዐመፃ።

፳፰፤ እምኀየሰከ፡የኀጥከ፡ዐዘቅት፡ዕሙቅ፡እምትመጡ፡ደመ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ንጹሐ፡በዐመፃ፡ለሞት።

፳፱፤ ወሰበ፡ሰምዐ፡ይሁዳ፡ቃለ፡ዘይዘልፎ፡ላዕሌሁ፡እምዐምድ፡በአ፡ቅንዓት፡ላዕሌሁ፡እምቅንዓተ፡ሰይጣን፡አቡሁ፤ወይቤሎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡የአክለከ፡ወልደ፡ፀራቢ፡(ሎቱ፡ስብሐት)፡ሥራይ፡ዘትገብር፡እብነ፡አስተናገርከ።

፴፤ ወምድር፡ትጸውር፡ዐመፃከ፡ወዝ፡ግብር፡ዘትገብር፡በዝ፡መዋዕል፡እንዘ፡ትብል፡አማንየ፡እግዚአብሔር፡አኃዜ፡ኵሉ፤አንሰ፡አሐውር፡በጽባሕ፡ኢየሩሳሌም፡ኀበ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወዐበይተ፡አይሁድ፡ወእነግሮሙ፡ዘትገብር፡ሥራያተ።

፴፩፤ ወእምዝ፡በጽባሕ፡እምቅድመ፡ሥርቀተ፡ፀሐይ፡ተንሥአ፡ይሁዳ፡ወኀደጎሙ፡ለአር

### ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ስምዖን፡ልጅ፡ይሁዳ፡ሆይ፡ወዮልህ! በዚህ፡ወራት፡ይህ፡አሳዛኝ፡ነገር፡በልብህ፡አለ፡የሚል፡አስደንጋጭ፡ቃል፡ወጣ።

፳፬፤ የእግዚአብሔርን፡ልጅ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ለሞት፡አሳልፈህ፡ትሰጠው፡ዘንድ፡ብዙ፡ጊዜ፡ትፈልጋለህ።

፳፭፤ በረከትን፡አልቀበልም፡ብለህ፡ካንተ፡ያራቅሃት፡ይሁዳ፡ሆይ፡ወዮልህ! ርግመንም፡እንደልብስ፡ለበስካት፤እንደ፡ውኃ፡በአንጀትህ፡እንደ፡ቅባትም፡በአጥንቶችህ፡ገባች፤እንደዝናርም፡በወገብህ፡ታጠቅሃት።

፳፮፤ ይህም፡ከዚህ፡ተቀምጦ፡ያለ፡ንጹሕ፡ደም፡በአንተ፡ምክንያት፡ይፈስሳል።

፳፯፤ ወንጌልም፡አህያ፡የሚያዞረውን፡ወፍጮ፡በአንገትህ፡አሥረው፡በባሕር፡ጥልቅ፡አዙሪት፡ውስጥ፡ቢያሰጥሙህ፡በተሻለህ፡ነበር፡ያለው፡ደረሰ፤በአንተ፡ምክንያትም፡ንጹሕ፡ደም፡ከሚፈስስ፡ዐመፅም፡በተፈጸመባት፡ቀን፡ተፀንሰህ፡ወንድ፡ልጅ፡ሁነህ፡ከምትወለድ፡ይልቅ፡የእናትህ፡ማሕፀን፡መቃብርህ፡ቢሆን፡በተሻለህ፡ነበር።

፳፰፤ የእግዚአብሔርን፡ልጅ፡ንጹሕ፡ደም፡በግፍ፡ለሞት፡አሳልፈህ፡ከምትሰጥ፡ይልቅ፡ጥልቅ፡ዐዘቅት፡ቢውጥህ፡በተሻለህ፡ነበር።

፳፱፤ ይሁዳም፡በላዩ፡ሁኖ፡የሚዘልፈውን፡ቃል፡ከደንጊያው፡በሰማ፡ጊዜ፡ከግብር፡አባቱ፡ከሰይጣን፡የሆነ፡ቅናት፡አደረበት፤ጌታችን፡ኢየሱስን፡(ሎቱ፡ስብሐት)፡አንተ፡የጠራቢ፡ልጅ፡ደንጊያውን፡በእኔ፡ላይ፡አናገርከ፡እንግዲህ፡የምታደርገው፡ሥራይ፡በቃህ፡አለው።

፴፤ ምድርም፡በእውነት፡ሁሉን፡የያዝ፡እግዚአብሔር፡እኔ፡ነኝ፡እያልክ፡በዚህ፡ወራት፡የምትሠራውንና፡የአንተን፡ዓመፅ፡ተሸክማለች፡እኔ፡በጥዋት፡ወደኢየሩሳሌም፡ሂጄ፡ለካህናት፡አለቆችና፡ለአይሁድ፡ታላላቆች፡የምትሠራውን፡ሥራይ፡እነግራቸዋለሁ፡አለው።

፴፩፤ ከዚህ፡በኋላ፡በጥዋት፡ገና፡ፀሐይ፡ሳይወጣ፡ይሁዳ፡ተነሣ፤ጌታችንን፡ደቀ፡መዛሙርቱን

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፭፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ዕለት፡መለእግዚእነ፡ውስተ፡ደብረ፡ዘይት፤
ወስሙ፡ ለውእቱ ፡ መካን ፡ ከራድዮስ ፡
ወተንሢኦ፡እምእግዚእነ፡ሖረ፡ኢየሩሳሌም፤
ወቦአ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወይቤሎሙ፡ለሊቃነ፡
ካህናት ፡ ወመምህራነ ፡ ኦሪት ፤ ምንተ ፡
ትሁቡኒ፡ለእመ፡መጠውኩክሙ፡ኢየሱስሃ፡
ዘይብልዎ፡መሲሕ፤ንግሩኒ፡ዘትሁቡኒ፡ወእ
ሜጥወክሙ፡ዘከመ፡ፈቀድክሙ፡ትግበሩ፤
ወአነ፡ቀዳሚ፡አእመርኩ፡ትእሕዝዎ፡(ከመ፡
ተአኅዝዎ) ፡ ወይትኀባእ ፡ እምኔክሙ ፡
በእንተ፡ምግባሩ፡እኩይ፡(ሎቱ፡ስብሐት)።

፴፯ ወይቤልዎ፡ሊቃነ፡ካህናት፡እለ፡ስሞሙ፡
ሐና፡ሐሙሁ፡ለቀያፋ፡ወሲናን፡ጸሐፌ፡
ወዮድና፡ወሚልክያስ፡ወአርማንያስ፡ወእለ
እስክንድሮስ ፡ እለ ፡ ጉቡአን ፡ ለዕከይ ፡
ነቢሮሙ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡አሐተኔ፤
ሠናየ ፡ ገበርከ ፡ አ ፡ እኁነ ፡ ወፍቁርነ ፡
ብሥራተ፡ ሠናየ ፡ አብሠርከነ ፡ በአማን ፡
ተፈሣሕነ፡ ኵልነ ፡ በዝ ፡ ነገር ፡ ዘትብለነ ፤
ለእመ ፡ ትሜጥወነ ፡ ኪያሁ ፡ በውስተ ፡
ጽላሎተ ፡ ቤት ፡ ወመስኮት ፡ ወኵሎ ፡
ዘትፈቅድ፡ንሁበከ፡ዘሀሎ፡ብኑረ።

፴፰ ወይቤሎ፡ሲናን፡ጸሐፌ፡ኦሪት፡ለይሁዳ፡
ንሕነ፡ንሬእየከ፡ከመ፡አንተ፡ረድኡ፡
እንዳኢ፡ገቢአከ፡ኢትክሐደነ።

፴፱ ወይቤሎሙ፡ይሁዳ፡ሕያው፡እግዚአብሔር፡
ወቡሩክ፡አምላክ፡አኃዜ፡ኵሉ፡ከመ፡አነ፡
በአማን፡እሙነ፡እትናገር፡ወእሜጥወክሙ፡
ወለእመ፡ኢአመንክሙ፡ይምጻእ፡አሐዱ፡
እምኔክሙ፡ምስሌየ፡ወአነ፡አርእዮ፡ኀበ፡
ሀሎ፡ምስለ፡አርዳኢሁ።

፵ ወእምድኅረ፡ዝ፡አነ፡እመጽእ፡ወእነሥ
እክሙ፡ወእሜጥወክሙ፡ኪያሁ።
ወሊቀ፡ካህናት፡ለአከ፡ገብሮ፡ወተለዎ፡
ድኅሬሁ፡ለይሁዳ፡ወበጽሐ፡ኀበ፡ሀሎ፡
እግዚእነ፡ምስለ፡አርዳኢሁ።

፭፻፸፫

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፭፡ሰዓት።

በደብረ ፡ ዘይት፡ ተዋቸው ፤ የዚያም ፡ ቦታ ፡
ስሙ፡ከራድዮስ፡ይባላል፤ከጌታችን፡ዘንድ፡
ተነሥቶ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ሔደ፤ወደ፡ቤተ፡
መቅደስም ፡ ገብቶ ፡ የካህናት ፡ አለቆችንና ፡
የኦሪቱን ፡ መምህራን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤
መሲሕ ፡ የሚሉት ፡ ኢየሱስን ፡ አሳልፌ ፡
ብሰጣችሁ ፡ ምን፡ ትሰጡኛላችሁ ? እንደፈለ
ጋችሁ፡ታደርጉት፡ዘንድ፡እኔ፡አሳልፌ፡እሰ
ጣችኋለሁ ፤ የምትሰጡኝን ፡ ንገሩኝ ፤
ቀድሞም፡ትይዙት፡ዘንድ፡እንደምትፈልጉ፡
እኔ ፡ አውቃለሁ ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡
ሥራው ፡ (ሎቱ ፡ ስብሐት) ፡ ከእናንተ ፡
ይሠወር፡ነበር፡አላቸው።

፴፯፤ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለክፉ ፡ ሥራ ፡
አንድነት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ስማቸው ፡ የቀያፋ ፡
አማት ፡ ሐና ፡ ጸሐፊው ፡ ሲናኝ ፡ ዮድና ፡
ሚልክያስ ፡ አርማንያስ ፡ እለእስክንድሮስ ፡
የተባሉት ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ የምንወድህ ፡
ወንድማችን ፡ ይሁዳ ፡ ሆይ ፡ መልካም ፡
አደረግህ ፤ መልካም ፡ የምሥራችም ፡ አበሠ
ርከን ፤ በዚህ ፡ በምትነግረን ፡ ነገርም ፡
ሁላችንም ፡ ደስ ፡ ብሎናል ፤ በቤት ፡ ጥላ ፡
ውስጥም ፡ በመስኮትም ፡ ቢሠወር ፡ እርሱን ፡
ብታስይዘን፡የምትሻውን፡ሁሉ፡ካለው፡ብር፡
እንሰጥሃለን፡አሉት።

፴፰፤ የሕግ ፡ ጸሐፊ ፡ ሲናንም ፡ ይሁዳን ፡ አንተ ፡
የእርሱ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ እንደሆንክ ፡ እኛ ፡
እናይሃለን ፤ ተመልሰህ ፡ እንዳትከዳን ፡ እንጃ ፡
አለው።

፴፱፤ ይሁዳም ፡ ሁሉን ፡ የያዘ ፡ ፈጣሪ ፡ የተመሰገነ ፡
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እኔ ፡ በእውነት ፡
እርግጡን ፡ ተናገርኩ ፤ አሳልፌም ፡ እሰጣች
ኋለሁ ፤ ካላመናችሁም ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡
ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይምጣ ፤ ከደቀመዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡
ያለበትንም፡አሳየዋለሁ፡አላቸው።

፵፤ ከዚያ፡በኋላም፡እኔ፡መጥቼ፡እወስዳችኋለሁ፤
እርሱንም፡አሳልፌ፡እሰጣችኋለሁ፡አለ።
ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ሎሌውን ፡ ላከ ፤ ይሁዳንም ፡
ተከተለው ፤ ጌታችንም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
ጋራ፡ወዳለበት፡ደረሱ።

Scanned by CamScanner

| በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፴፮፤ ወእምዝ፡ቦአ፡ይሁዳ፡ወይቤሎ፡እግዚእነ፡አ፡ ገባሬ፡እኪት፡ፈጸምከ፡ኵሎ፡ግብረከ፡ ወመጻእከ፡ኀቤነ፡ወይቤ፡ይሁዳ፡አነኑ፡ ገባሬ፡እኪት፡ወእምዝ፡ካዕበ፡አሐውር፡ወአ ስተዋድየከ፡ኀበ፡ካልአን። | ፴፮፤ ከዚያም፡ይሁዳ፡ወደጌታችን ጌታችንም፡አንተ፡ክፉ፡ሠሪ፡ሥራህን፡ሁሉ፡ ፈጽመህ፡ወደ፡እኛ፡መጣህ፡አለው፤ ይሁዳም፡ክፉ፡ሠሪ፡እኔ፡ነኝን፧አሁንም፡ ሁለተኛ፡ወደሌሎቹ፡ሂጄ፡ነገር፡እሠራብ ሃለሁ፡አለው። |
| ፴፯፤ ወይቤሎ፡እግዚእነ፡አነ፡አአምር፡ዘትገብር፤ ወእምዝ፡ሖርከ፡ኢየሩሳሌም፡እምኀቤነ፡ ወበጸሕከ፡ኀበ፡አይሁድ፡ወሊቃነ፡ካህናት፤ ወትቤሎሙ፡ሀቡኒ፡ሠላሳ፡ብሩረ፤ወአነ፡ እሜጥወክሙ፡ኢየሱስሃ፡ወመጽአ፡አሐዱ፡ እምኔሆሙ፡ምስሌከ፡ይስማዕ፡ዘንትናገር፤ ወተመይጠ፡ይንግሮሙ፡ኀበ፡ሀሎነ፡ንሕነ፡ ወውእቱኒ፡ወልደ፡ዐመፃ፡መክፈልቱ፡ ምስሌከ። | ፴፯፤ ጌታችንም፡የምትሠራውን፡እኔ፡አውቃለሁ፤ ከዚህ፡ከእኛ፡ዘንድ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ ሒደህ፡ወደ፡አይሁድና፡ወደ፡ካህናት፡ አለቆች፡ደረስክ፤እኔ፡ኢየሱስን፡አሳልፌ፡ እሰጣችኋለሁና፡ሠላሳ፡ብር፡ስጡኝ፡ አልካቸው፤ከእነርሱም፡አንዱ፡የምንና ረውን፡ይሰማ፡ዘንድ፡ከአንተ፡ጋራ፡መጣ፤ እኛ፡ያለንበትንም፡ቦታ፡ይነግራቸው፡ ዘንድ፤የዐመፅ፡ልጅ፡እሱም፡ዕድል፡ ፈንታው፡ካንተ፡ጋራ፡ነው፡አለው። |
| ፴፰፤ ወሶበ፡ሰምዐ፡ዘይትናገሩ፡ገብር፡እኩይ፡ ወዘይቤሎ፡እግዚእነ፡ለይሁዳ፡አፍጠነ፡ ሐዊረ፤ወበጽሐ፡ኀበ፡አይሁድ፡ወዜነዎሙ፡ ዘሰምዐ፡በኀበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ። | ፴፰፤ ያ፡ክፉ፡ባርያ፡ጌታ፡ለይሁዳ፡የተናገረ ውንና፡ያለውንም፡በሰማ፡ጊዜ፡ፈጥኖ፡ሔደ፤ ወደ፡አይሁድም፡ደርሶ፡ከጌታ፡ኢየሱስ፡ ዘንድ፡የሰማውን፡አወራላቸው። |
| ፴፱፤ ወሶቤሃ፡ነደ፡ልቦሙ፡ከመ፡እሳት፡ወፈቀዱ፡ የአኀዝዎ፤ወሶበ፡አእመረ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ግብሮሙ፡ለአይሁድ፡ይቤሎሙ፡ለአር ድእት፡ተንሥኡ፡ንሑር፡እምዝየ፡ቀርበ፡ መዋዕለ፡ፋሲካ፡ወእፈቅድ፡እብላዕ፡ፍሥሓ፡ ምስሌክሙ፡እምቅድመ፡ይኩን። | ፴፱፤ ያንጊዜም፡ልባቸው፡እንደ፡እሳት፡ነደደ፤ ሊይዙትም፡ቸኰሉ፤ጌታ፡ኢየሱስም፡ አይሁድ፡የሚሠሩትን፡ስለሚያውቅ፡ደቀ፡ መዛሙርቱን፡ተነሡ፤ከዚህ፡እንሂድ፤ የፋሲካው፡ቀን፡ደረሰ፤የፋሲካውን፡በግ፡ ከእናንተ፡ጋራ፡እበላ፡ዘንድ፡እወዳለሁ፡ አላቸው። |
| ፵፤ ወተንሥአ፤ወተለውዎ፡ፍኖተ፡ዘይወስድ፡ ለቢታንያ፡ኀበ፡አንሥኦ፡ለአልዓዛር። | ፵፤ ከዚያ፡ተነሣ፤ከሙታን፡ለይቶ፡ያስነሣው፡ አልዓዛር፡ወዳለበት፡ወደቢታንያ፡በሚወ ስደው፡መንገድም፡ተከተሉት። |
| ፵፩፤ ወይቤሎሙ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ለጴጥሮስ፡ወለዮሐንስ፡ሑሩ፡ወባኡ፡ሀገረ፡ እንተ፡ቅድሜክሙ፤ወትረክቡ፡ብእሴ፡ ዘይጸውር፡ጸሕበ፡ማይ፡ዘስሙ፡ስምዖን፡ ወበልዎ፡ይቤለከ፡ሊቅ፡መዋዕልየ፡ቀርበ፡ ወበጽሐ፡አስተዳሉ፡ለነ፡ንባእ፡ቤተከ፡ ወእብላዕ፡ፍሥሓ፡ምስለ፡አርዳእየ፡ ወእምዝ፡ዳግመ፡ኢይበልዕ፡ምስሌክሙ። | ፵፩፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ዮሐንስና፡ ጴጥሮስን፡በፊታችሁ፡ወዳለች፡መንደር፡ ሒዱ፤ስትገቡም፡የውኃ፡ማድጋ፡የተሸከመ፡ ስሙ፡ስምዖን፡የሚባል፡ሰው፡ታገኛላችሁ፤ ጊዜየ፡ቀርቧልና፡መምህር፡ከደቀ፡ መዛሙርቴ፡ጋር፡የፋሲካውን፡በግ፡እበላ፡ ዘንድ፡ቤትህን፡አዘጋጅልን፡ብሎሃል፡ በሉት፤እንግዲህ፡ዳግመኛም፡ከእናንተ፡ጋር፡ አልበላምና፡አላቸው። |

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፵፪ ወሶቤሃ፡ተንሥኡ፡ወሖሩ፡ወቦኡ፡አበዊነ፡
ቀዱሳን፡አርድእት፡ሀገረ፡ቢታንያ፡ወረከቡ፡
ብእሴ፡ጸሒበ፡ማይ፡ጸዊሮ።
፵፫ ወይቤልዎ፡ ይቤለከአ ፡ ሊቅ ፡ እግዚእ ፡
ኢየሱስ ፡ አስተዳሉአ ፡ ቤተከአ ፡ በህየአ ፡
እገብር ፡ ፋሲካ ፡ ምስለ ፡ አርዳእየ ፡ ከመ ፡
እፈጽም፡ኵሎ፡እስመ፡መዋዕል፡ቀርበ።
፵፬ ወተፈሥሐ፡ውእቱ፡ብእሲ፡ሶቤሃ፤ወይቤ፡
ይደልወኒኑ፡ይባእ፡ቤትየ፡እግዚአ፡ሰማያት፡
ወምድር፡ ወይኩን ፡ በረከቱ ፡ ወምሕረቱ ፡
ውስተ፡ቤትየ።
፵፭ ወእምድኅረዝ፡ነሥአሙ፡ውእቱ፡ብእሲ፡
ለአርድእት፡ውስተ፡ቤቱ፤ወተናገረ፡ምስለ፡
አክሮስና፡ብእሲቱ፡እንዘ፡ይብል፡ንዒ፡
ስምዒ፡እኅትየ፡ዘንተ፡ነገረ፡ኢየሱስ፡
ዘይብልዎ፡መሲሕ፡ዘቦአ፡ውስተ፡ዝንቱ፡
ሀገር፡ዘአንሥአ፡ለአልዓዛር፡እሙታን፡
ሊተኒ፡ዘአንጽሐ፡ሥጋየ፡እምርኵሰ፡
ኃጢአት፡ወውእቱ፡ዘለአከ፡ክልኤተ፡
አርድእተ፡ይቤአ፡አስተዳሉ፡ሊተ፡ቤተከ፡
በዛቲ፡ዕለት፡ከመ፡እብላዕ፡ፍሥሓ፡ምስለ፡
አርዳእየ።
፵፮ ወትቤ፡እወ፡ንትፈሣሕ፡ወንትሐሠይ፡በዝ፡
ነገር፡አነ፡ወአንተ፡ኅቡረ፡ዐቢየ፡ፍሥሐ።
፵፯ ወእምዝ፡ አኀዝዎሙ፡ ለአርድእት፡ በእደ
ዊሆሙ፡ወአብእዎሙ፡መልዕልተ፡ተሥላስ፡
ቤት፡ወአርአይዎሙ፡ቤተ፡ርሡየ፡ወሥርግወ፡
ወአስተዳለዉ፡ሎሙ፡በህየ፡ምሳሐ።
፵፰ ወትቤሎ፡ አክሮስና፡ ለምታ፡ ሀሎ፡ ኀበ፡
ገራህትነ፡ዶርሆ፡ሑር፡አፍጥን፡እኊዞቶ፡
ወአምጽእ፡ዝየ፡ወሕርዶ፡ከመ፡ይኩን፡
ምሳሐ፡ለእግዚእነ፤ወንሕነ፡ወአርድእቱ፡
ንመስሕ፡ኅቡረ፤ወእምዝ፡አምጽኡ፡ዶርሆ፡
ወሐረድዎ።
፵፱ ወበተሰዐቱ፡ ሰዓት፡ ተንሥአ፡ እግዚእነ፡
ምስለ፡ አርዳኢሁ፡ ቦአ፡ ሀገረ፤ ወረከቦ፡
ለስምዖን፡እንዘ፡ይመጽእ፡ኀቤሁ፡ወይቤሎ፡
ሰላም፡ለከ፡እግዚእ፡ወመድኅን፡ወመምህር፡
ወእምዝ፡ ሰገደ፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ ለእግዚእ፡
ኢየሱስ፡ በአሚን፡ ምስለ፡ ኵሉ፡ ሰብአ፡
ቤቱ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፵፪ ያን፡ጊዜም፡የከበሩ፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡
ተነሥተው፡ሒደው፡ወደቢታንያ፡ገቡ፤ሰው
የውንም፡የውኃ፡ማድጋ፡ተሸክሞ፡አገኙት።
፵፫ መምህር፡ ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ቤትህን፡ አዘጋ
ጅልን፤ጊዜው፡ስለደረሰ፡ሁሉን፡እፈጽም፡
ዘንድ፡ ከደቀ፡ መዛሙርቴ፡ ጋር፡፡ በዚያ፡
ፋሲካ፡አደርጋለሁ፡አለህ፡አሉት።
፵፬ በዚያን፡ ጊዜ፡ ሰውዬው፡ ደስ፡ አለው፤
የሰማይና፡የምድር፡ጌታ፡ ከቤቴ፡ ውስጥ፡
ይገባ፡ ዘንድ፡ ይገባኛልን? በረከቱና፡
ቸርነቱም፡በቤቴ፡ውስጥ፡ይሁን፡አለ።
፵፭ ከዚህም፡በኋላ፡ያ፡ሰው፡ሐዋርያትን፡ወደ፡
ቤቱ፡ወሰዳቸው፤ከሚስቱ፡ከአክሮስና፡ጋራ፡
እንዲህ፡ብሎ፡ተነጋገረ፤እኅቴ፡ነዪ፡ይህን፡
መሲሕ፡የሚሉትን፡የኢየሱስን፡ነገር፡ስሚ፤
ወደዚህ፡አገር፡ገብቶ፡አልዓዛርን፡ከሞት፡
ያስነሣው፤እኔንም፡በኃጢአት፡ምክንያት፡
ከሚመጣው፡ ከለምጽ፡ ሥጋዬን፡ ያነጻ፤
እርሱ፡ ሁለቱን፡ ደቀ፡ መዛሙርቱን፡ ልኮ፡
ከደቀ፡መዛሙርቴ፡ጋራ፡በዛሬዋ፡ቀን፡የፋሲ
ካውን፡ በግ፡ እበላ፡ ዘንድ፡ ቤትህን፡ አዘጋ
ጅልኝ፡ብሎአል፡አላት።
፵፮ እርሷም፡አዎን፡እኔና፡አንተ፡በዚህ፡ነገር፡
በታላቅ፡ ደስታ፡ አንድነት፡ ፈጽሞ፡ ደስ፡
ይበለን፡አለች።
፵፯ ከዚህ፡ በኋላ፡ ሐዋርያትን፡ እጆቻቸውን፡
ይዘው፡ ወደ፡ ሦስተኛው፡ ደርብ፡ አስገቡ
አቸው፤የተነጠፈ፡ያጌጠ፡ቤትንም፡አሳዩ
አቸው፤በዚያም፡ምሳ፡አዘጋጁላቸው።
፵፰ አክሮስናም፡ባልዋን፡በጓሮአችን፡ዶሮ፡አለ፤
ፈጥነህ፡ ይዘህ፡ ወደዚህ፡ አምጣው፤
ለጌታችን፡ምሳ፡ሊሆን፡እረደው፤ደቀ፡መዛ
ሙርቱም፡እኛም፡በአንድነት፡ምሳ፡እንበ
ላለን፡አለችው፤ከዚህም፡በኋላ፡ዶሮውን፡
አምጥተው፡አረዱት።
፵፱ በዘጠኝ፡ሰዓትም፡ጌታችን፡ተነሥቶ፡ከደቀ፡
መዛሙርቱ፡ ጋር፡ ወደ፡ መንደሩ፡ ገባ፤
ስምዖንም፡ሊቀበለው፡ወደእርሱ፡ሲመጣ፡
አገኘው፤ጌታ፡መድኅን፡መምህር፡ሆይ፡
ፍቅር፡አንድነት፡ይገባሃል፡ብሎ፡ከመላ፡
ቤተ፡ሰቡ፡ጋር፡በግንባሩ፡ወድቆ፡ከጌታ፡
ኢየሱስ፡ፊት፡በእምነት፡ሰገደ።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፶፤ ወይሁዳ ፡ ይትናገር ፡ ምስለ ፡ ካልአን ፡ እንዘ ፡ ይትኀፀብ፡ኀበ፡ዐይነ፡ማይ።

፶፩፤ ወእምዝ፡ተናገረ፡ስምዖን፡ምስለ፡አክሮስና፡ ብእሲቱ ፡ ታምጽእ ፡ ሎቱ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ሠናያተ፡ወትንጽፍ፡ታሕተ፡እግረ፡እግዚእ፡ እግዚእን፡ወእ ኢየሱስ፡ወይኪድ፡ላዕሌሆን እግዚእን፡ወእ ርዳኢሁ ፡ ወይዕርግ ፡ መልዕልተ ፡ ተሥላስ ፡ ዘላዕላይ፡ቤት፡ዘአስተዳለውነ፡ሎቱ።

፶፪፤ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወቦአ ፡ ኀበ፡ሠርዑ፡አርዳኢሁ።

፶፫፤ ወአክሮስና፡ብእሲተ፡ፈሪሳዊ፡ስምዖን፡ኢያ እመረቶ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፶፬፤ ወቦአት፡እንዘ፡ትትፌሣሕ፡ወርእየቶሙ፡ለአ ርድእት ፡ እንዘ ፡ ይቀውሙ ፡ ወይጼልዩ ፡ ወትቤሎሙ ፡ መኑ ፡ እምኔክሙ ፡ መምህር ፡ እስግድ፡ሎቱ፡ወአርመመ፡ኵሎሙ።

፶፭፤ ወርእየት፡ኀበ፡ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ዘራእዩ፡ ሠናይ፡ወትቤ፡ዝኑ፡እግዚእ፡ከመ፡እስግድ፡ ሎቱ።

፶፮፤ ወይቤላ ፡ ጴጥሮስ ፡ ረድእ ፡ ዐቢይ ፡ ሀሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ውስተ ፡ ውሳጣይ ፡ ቤት ፡ ቀዊሞ ፡ ይጼሊ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእ ፤ ወበዊኣ ፡ ሰገደት ፡ ሎቱ ፤ ወይቤላ ፡ ተኀድገ ፡ ለኪ ፡ ኃጢአትኪ ፡ ወአርድእት ፡ ቅውማን ፡ ሀለዉ ፡ ኀበ፡ጸሎት።

፶፯፤ ወመጽአ ፡ ይሁዳ ፡ ወልደ ፡ ስምዖን ፡ አስቆ ሮታዊ፡ኀበ፡አንቀጽ፡ዘአፍአ፡ጸዊሮ፡ሣፁነ።

፶፰፤ ወይቤሎ ፡ ለዓቃቤ ፡ አንቀጽ ፡ አርኅ ፡ ሊተ ፡ እባእ፡ኀበ፡እኀውየ፡አርድእት፡ወአነሂ፡እም አርዳኢሁ፡ለእግዚእ።

፶፱፤ ወይቤሎ፡እለእስክንድሮስ፡ዐቃቤ፡አንቀጽ፡ ተገሐሥ፡ንስቲተ፡እስከ፡አዐጽፍ፡አልባሰ፡ ዘንጹፋት፡ታሕተ፡እግረ፡እግዚእ።

፷፤ ወይቤሎ ፡ እለእስክንድሮስ ፡ ዳግመ ፡ አንሰ ፡ ርኢኩ ፡ እንዘ ፡ ይበውኡ፡ እግዚእ ፡ምስለ ፡ አር ዳኢሁ ፡ ወበእደዊሆሙ ፡ ማዕጠንታት ፡ ወመኃ ትው፡ብሩሀት፡እንዘ፡የሐውሩ፡ቅድሜሁ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፶፤ ይሁዳ፡ግን፡ከውኃ፡ምንጭ፡በታ፡እየታጠበ፡ ከሌሎች፡ሰዎች፡ጋር፡ይነጋገር፡ነበር።

፶፩፤ ስምዖንም ፡ ከሚስቱ ፡ ከአክሮስና ፡ ጋር፡ መልካሞች፡የሆኑ፡ልብሶቻቸውን፡አምጥታ፡ ከጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ እግር ፡ በታች ፡ ታነጥፍ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ አዘጋጀንለት፡ ወደ፡ ሦስተኛው፡ ደርብ ፡ በልብሶቹ ፡ ላይ ፡ ረግጦ ፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ አንጥፊ፡ ብሎ፡ተናገራት።

፶፪፤ ከዚህ፡በኋላ፡ ጌታ፡ኢየሱስ፡ከዐሥራ፡ሁለቱ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ መጥቶ ፤ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ወደ፡አዘጋጁለት፡ቤት፡ገባ።

፶፫፤ የፈሪሳዊው ፡ ስምዖን ፡ ሚስት ፡ አክሮስና፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አታው ቀውም፡ነበር።

፶፬፤ ደስ ፡ እያላት ፡ ገብታ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን፡ ቁመው ፡ ሲጸልዩ ፡ አየቻቸው ፤ እሰግድለት፡ ዘንድ፡ከእናንተ፡ውስጥ፡መምህር፡ማን፡ነው፡ አለቻቸው፤እነርሱም፡ዝም፡አሉ።

፶፭፤ መልከ ፡ መልካም ፡ ወደሆነው ፡ ወደ፡ወን ጌላዊው ፡ ዮሐንስ ፡ ተመልክታ ፡ እሰግድለት፡ ዘንድ፡ ጌታ፡ይህ፡ይሆን፡አለች።

፶፮፤ ታላቁ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ጴጥሮስም፡ ጌታ፡ ኢየሱስ ፡ ከውስጠኛው ፡ ክፍል ፡ ቆሞ፡ ይጸልያል ፤ ጌታ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ አላት፤ እርስዋም፡ ገብታ ፡ ሰገደችለት ፤ ጌታም፡ ኃጢአትሽ፡ተሰረየልሽ፡አላት፤ደቀ፡መዛሙ ርቱም፡ቁመው፡ይጸልዩ፡ነበር።

፶፯፤ የአስቆሮቱ ፡ የስምዖን ፡ ልጅ ፡ ይሁዳም፡ ከውጭው፡በር፡ሳጥን፡ተሸክሞ፡መጣ።

፶፰፤ በር ፡ ጠባቂውንም ፡ እኔ ፡ ከጌታ ፡ ደቀ፡ መዛሙርት፡ውስጥ፡ነኝና፤ወደ፡ወንድሞቼ፡ እገባ፡ዘንድ፡ክፈትልኝ፡አለው።

፶፱፤ በር ፡ ጠባቂው ፡ እለእስክንድሮስም፡ ከጌ[illegible] እግር ፡ በታች ፡ ተነጥፈው ፡ የነበሩትን፡ ልብሶች ፡ እስካጥፍ ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ በል፡ አለው።

፷፤ ዳግመኛም ፡ እለእስክንድሮስ ፡ እንዲህ፡ አለው፤ ጌታ ፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋር፡ሲገባ፡ [illegible] በእጆቻቸው ፡ ማዕጠንትና ፡ የበራ[illegible] መብራቶች፡ይዘው፡በፊቱ፡ሲሔዱ፡አየሁ[illegible]

Scanned by CamScanner

## ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወእከለ፡ አሬእየከ ፡ ጽዋዐ ፡ ደም ፡ ምሉእ ፡
ውስተ፡ እዴከ ፡ ወላዕሌሁ ፡ ጽዋዐ ፡ ማይ ፡
ጸዐዱ፡ ከመ ፡ ማየ ፡ ገነት ፡ ወይጸዐዱ ፡
እምሐሊብ።

ወእነ፡ አሬእየከ፡ ከይሲ ፡ ዐቢይ ፡ ወጸሊም ፡
ውስተ፡ ክሣድከ ፡ ወለውለወ ፡ ልሳኖ ፡ ከመ ፡
ይሰወም፡ አፉከ፡ ወየሀብከ፡ ጽንዓተ፡ ልብ።

ወይቤሎ፡ ቁም ፡ ወጽናሕ ፡ እስከ ፡ አዐጽፍ ፡
አልባሳተ ፡ ንጹፋተ ፡ እለ ፡ ኬዶን ፡ እግዚእ ፡
ወኢትባእ ፡ ምስለ ፡ ዝ ፡ ጽዋዐ ፡ ደም ፡ ዐቢይ ፡
ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ከመ ፡ ኢይትከዐው ፡
ላዕለ፡አልባስ፡ወኢይሕዝን፡እግዚእየ፡ላዕሌየ።
ወሰበ፡ሰምዐ፡ዘንተ፡ነገረ፡ይሁዳ፡እምኀበ፡
አለእስክንድሮስ፡ተሐዘበ፡ወአንከረ፡ወቆመ፡
እስከ፡ የዐጽፍ ፡ አልባሰ ፤ ወእምዝ ፡ ኀደጎ ፡
ወቦአ ፡ ወዐርገ ፡ ይሁዳ ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡
አርድእት፡ወቆመ፡ማዕከሎሙ።

ወእምድኅረ ፡ ጸሎት ፡ ነበሩ ፡ ዐሠርቱ ፡
ወክልኤቱ፡ ሐዋርያት ፡ ወአምጽኡ ፡ ማዕደ ፡
ከመ፡ይብልዑ።

ወሰምዐት ፡ ብእሲት ፡ ኀጥእት ፡ እምሰብአ ፡
ይእቲ፡ሀገር፡ ከመ፡ ሀሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ዘለምጽ ፤ ወተንሥአት ፡
ወበጽሐት፡ኀበ፡ሠያጤ፡ዕፍረት።

ወትቤሎ፡እፈቅድ፡ተሀበኒ፡ዕፍረተ፡ሠናየ፡
ዘብዙኅ፡ሤጡ፡ወሠናይ፡መዐዛሁ፡እሢየጥ፡
እምኔከ፡ ከመ ፡ እሰድ ፡ ወእቅብዖ ፡ ለርእሰ ፡
እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ይምሐረኒ ፡
ወይሥረይ፡ኃጢአትየ።
ወወሀባ፡ዕፍረተ፡ሠናየ፡ዘብዙኅ፡ሤጡ፤ወተ
ሣየጠት፡እምኔሁ፡በሠለስቱ፡ምዕት፡ዲናር፡
ወሖረት፡ኀበ፡ቤተ፡ስምዖን፡እንዘ፡ታፈጥን፡
ወትትፌሣሕ።
ወረከበቶ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እንዘ፡ ሀሎ፡
ነቢር፡ወሶጠት፡ዕፍረተ፡ዲበ፡ርእሱ፡ወአር
ሐሰት፡ እገሪሁ ፡ በአንብዓ ፡ ወመዝመዘቶ ፡
በሥዕርተ፡ርእሳ፡ወመልአ፡ጼና፡መዐዛሁ፡
ኵሎ፡ቤተ።



## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፩፤ አንተን ፡ ግን ፡ አይሃለሁ ፤ ደምን ፡ የተመላ ፡
ጽዋ፡ በእጅህ ፡ አለ ፤ በላዩም ፡ ከወተት ፡
የሚነጻ፡ከአትክልት፡ቦታ፡የሚገኝ፡ንጹሕ፡
ውኃ፡አለ።
፳፪፤ እኔም፡ ሳይህ፡ ታላቅ፡ የሆነ፡ ጥቁር፡ ከይሲ፡
በአንገትህ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ይስምህ ፡ ዘንድ ፡
የልብ፡ ድንዳኔንም፡ ይሰጥህ፡ ዘንድ፡ ምላሱን፡
ያውለበልባልና።
፳፫፤ ጌታዬም ፡ እንዳያዝንብኝ ፡ ደሙም ፡
በልብሶቹ፡ ላይ ፡ እንዳይፈስስ ፡ ጌታ ፡
በላያቸው፡ የሔደባቸውን ፡ የነጹ ፡ ልብሶች ፡
እስካጥፍ፡ድረስ፡ቁመህ፡ቆይ፤ከዚህ፡ከደም፡
ጽዋ፡ጋር፡አትግባ፡አለው።
፳፬፤ ይሁዳም፡ ይህንን፡ ነገር፡ ከእለእስክንድሮስ፡
በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ተጠራጠረው ፤ አደነቀም ፤
ልብሶቹን ፡ እስኪያጥፍም ፡ ድረስ ፡ ቆመ ፤
ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ተወው ፤ ገብቶም ፡ ወደ ፡
ደርቡ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወዳሉበት ፡ ወጣ ፤
በመካከላቸውም፡ቆመ።
፳፭፤ ከጸሎት፡በኋላም፡ዐሥራ፡ሁለቱ፡ሐዋርያት፡
ይመገቡ ፡ ዘንድ ፡ ማእድ ፡ አቅርበው ፡
ተቀመጡ።
፳፮፤ ከዚያች፡ አገር፡ ሰዎች፡ የምትሆን፡ አንዲት፡
ኃጢአተኛ ፡ ሴት ፡ ለምጻም ፡ በነበረው ፡
ስምዖን፡ቤት፡ጌታ፡ኢየሱስ፡እንዳለ፡ሰማች፤
ተነሥታም፡የሽቱ፡ነጋዴ፡ወደሆነው፡ሰው፡
ቤት፡ደረሰች።
፳፯፤ መዐዛው፡መልካም፡ሁኖ፡ዋጋው፡ብዙ፡የሆነ፡
ሽቱ ፡ ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ እንድገዛ ፡
እሻለሁ፤ወስጄም፡የጌታችንን፡የክርስቶስን፡
ራሱን ፡ ዕቀባው ፡ ዘንድ ፤ ይቅር ፡ ብሎ ፡
ኃጢአቴን፡ያስተሰርይልኝ፡ዘንድ፡አለችው።
፳፰፤ ዋጋው፡ብዙ፡የሆነውን፡መልካሙን፡ሽቱ፡
ሰጣት ፤ እርስዋም፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡
ወርቅ፡ከሱ፡ገዝታ፡ወደ፡ስምዖን፡ቤት፡ደስ፡
እያላት፡ፈጥና፡ሔደች።
፳፱፤ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘችው ፤
ሽቱውንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰችው ፤
እግሩንም ፡ በዕንባዋ ፡ አራሰችው ፤ በራስ ፡
ጠጕርዋም ፡ አሸችው ፤ የመዓዛውም ፡ ሽታ ፡
ቤቱን፡ሁሉ፡መላው።

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፴፤ ወሐዘነ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ ወይቤ ፡ ለምንት፡ አህጕለት ፡ ዘመጠንዝ ፡ ዕፍረተ ፡ እምኢተሠይጠ፡በሠለስቱ፡ምዕት፡ዲናር፡ ወየሀብዎ፡ምጽዋተ፡ለነዳያን።

፴፩፤ አኮ፡ዘይቤ፡ዘንተ፡በእንተ፡ፍቅረ፡ነዳያን፡ አላ ፡ እስመ ፡ ሠራቂ ፡ ውእቱ ፤ ወሙዳየ ፡ ምጽዋት፡በኀቤሁ፡ሀሎ፡ዘእግዚእ፡አመገበ፡ ወአእመረ፡ከመ፡ይረክብ፡ምክንያተ።

፴፪፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ለምንት ፡ ታሰርሕዋ፡ለይእቲ፡ብእሲት፡ሠናየ፡ግብረ፡ ገብረት፡ላዕሌየ፡ወለነዳያንሰ፡ዘልፈ፡ትረክ ብዎሙ ፡ ወሀለዉ ፡ ምስሌክሙ ፤ ወአኮ ፡ ዘእሄሉ፡አነ፡ምስሌክሙ፡ወትረ፤ወዘንተ፡ ዕፍረተ፡ዘሶጠት፡ላዕሌየ፡ለቀበርየ፡ገብረት።

፴፫፤ አማን፡እብለክሙ፡ኀበ፡ሰበክዎ፡ለወንጌል፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ይዝክርዋ ፡ ለዛቲ፡ብእሲት፡ዘገብረት።

፴፬፤ ወእምዝ፡ሚጠ፡ገጾ፡ኀቤሃ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወይቤላ፡ተኀድገ፡ለኪ፡ኃጢአትኪ፡ብዙኅ፡ እስመ ፡ ብዙኅ ፡ አፍቀርክኒ ፤ ሑሪ ፡ ዕትዊ ፡ ቤተኪ ፡ በሰላም ፤ ወእምዝ ፡ ዳግመ ፡ ኢተአብሲ፡ወሖረት፡ይእቲ፡ብእሲት።

፴፭፤ ወስምዐ ፡ ኮነ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል፡ከመዝ፤ወእምቅድመ፡በዐለ፡ፋሲካ፡ ሶበ ፡ አእመረ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ መጠዎ፡አብ፡ኵሎ፡ውስተ፡እዴሁ፡ወከመ፡ መጽአ፡እምኀበ፡አብ፡ወየሐውር፡ኀበ፡አብ።

፴፮፤ ወተንሥአ ፡ እምኀበ ፡ ይዴረሩ ፡ ወአንበረ ፡ አልባሲሁ፡ ወቀነተ፡ለንጸ፡ውስተ፡ሐቌሁ፡ ወሶጠ፡ማየ፡ውስተ፡ጻሕል፡ወኀፀበ፡እግረ፡ አርዳኢሁ፡ወመዝመዘ፡በለንጽ።

፴፯፤ ወይቤሎ ፡ ለስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ነዓ ፡ ከመ ፡ እኅፅብ፡እገሪከ፡እስመ፡አንተ፡ቀዳማዊ፡እም አርድእት፡ወይቤሎ፡ጴጥሮስ፡ኢተኀፅበኒ፡ እገርየ፡ለዓለም።

፴፰፤ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አማን፡እብለከ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፴፤ የአስቆሮቱ ፡ ሰው ፡ ይሁዳም ፡ አዘነ፤ይ... ያህል፡ሽቱ፡ለምን፡አባከነች፤በሦስት፡መ... ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ተሸጦ ፡ ለድሆች፡ምጽዋ... አይሰጥም፡ነበርን?አለ።

፴፩፤ ይህን ፡ ያለ ፡ ድሆችን ፡ በመውደድ... አይደለም፤ ሌባ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ፤... እርሱን ፡ ሹሞ ፡ ያስጠበቀው ፡ ሙዳ... ምጽዋት ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ነበረና፤ም... ያትም፡እንደሚያገኝ፡ያውቅ፡ነበር።

፴፪፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ይህቺን፡ሴት፡ለምን፡ታ... ሚታላችሁ?እርስዋ፡ለእኔ፡መልካም፡ሥራ... ሠርታለች፤ድሆችንስ፡ዘወትር፡ታገኙዋ... ላችሁ፤ከእናንተ፡ጋርም፡ይኖራሉ፤እኔ፡ግ... ከእናንተ፡ጋር፡ዘወትር፡የምኖር፡አይደለሁ... ይህም ፡ በላዬ ፡ ያፈሰሰችው ፡ ሽቱ፡ለመ... ሪያዬ፡አደረገችው።

፴፫፤ ይህንንም፡የከበረ፡ወንጌል፡በሚሰብኩበ... በዓለሙ፡ሁሉ፡ይችን፡ሴት፡ስለአደረገችው... ያስቡአት፡ብዬ፡እውነት፡እነግራችኋለሁ።

፴፬፤ ከዚህ፡በኋላ፡ፊቱን፡ወደእርሷ፡መልሶ፡ጌ... ኢየሱስ ፡ ብዙ ፡ ወደሽኛልና ፡ ብዙው፡ኃ... አትሽ፡ተሰርዮልሻል፤ሒጂ፤ወደ፡ቤትሽ... በሰላም፡ግቢ፤እንግዲህ፡ዳግመኛ፡አትበደ... አላት፤ያችም፡ሴት፡ወደ፡ቤቷ፡ሔደች።

፴፭፤ ወንጌላዊው ፡ ዮሐንስም ፡ እንዲህ ፡ ሲ... መሰከረ፤ከፋሲካ፡በዓል፡አስቀድሞ፡... ኢየሱስ፡አብ፡ሁሉን፡በእጁ፡እንደሰጠው... ከአብ፡እንደወጣ፡ወደ፡አብም፡እንደሚሄድ... ባወቀ፡ጊዜ።

፴፮፤ ራት ፡ ከሚበሉበት ፡ ተነሥቶ ፡ ልብሱን... አኖረና፡ሽርጥ፡ወስዶ፡በወገቡ፡ታጠቀ፡ው... ስኰስትም ፡ ውኃ ፡ ጨምሮ ፡ የደቀ፡መዛ... ርቱን፡እግር፡አጠበ፤በሽርጡም፡ወለወለ... 

፴፯፤ ስምዖን፡ጴጥሮስን፡ከደቀ፡መዛሙርት፡... ትቀድም፡አንተ፡ነህና፤እግሮችህን፡አጥብ... ዘንድ፡ና፡አለው፤ጴጥሮስም፡አንተ፡ለዘ... እግሮቼን፡አታጥበኝም፡አለው፤

፴፰፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እኔ ፡ እግሮችህን ፡ ካ...

Scanned by CamScanner

### በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እሙ፡ኢኀፀብኩከ፡ አነ ፡ እገሪከ ፡ አልብከ ፡
መክፈልት፡ወርስት፡ምስሌየ።

፳፱ ወሰብ፡ሰምዐ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘንተ ፡ ደንገፀ ፤
ወአድነነ ፡ ክሣዶ ፡ ወርዕደ ፡ ወሰገደ ፡
ለእግዚእ፡ መድኅን ፡ ወይቤሎ ፡ ለመድኅን ፡
አኮ፡እገርየ፡ባሕቲቶ፡ዓዲ፡እደውየኒ፡ወርእ
ስየኒ።

፴ ወይቤሎ፡እግዚእነ፡ዘሰ፡ይፈቅድ፡ተኀፅቦ፡
ኢይትኀፀብ፡ዘእንበለ፡እገሪሁ፡ባሕቲቱ፡
ዳእሙ ፡ እስመ ፡ ንጹሕ ፡ ኵለንታሁ ፡
አንትሙሰ፡ንጹሓን፡አንትሙ፡ወባሕቱ፡
አኮ፡ኵልክሙ።

፴፩ ወእምድኅረ ፡ ይቤሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ኀፀበ ፡
እገሪሁ፡ለጴጥሮስ፡ወመዝመዘ፡በለንጽ፡
ወኀፀበ፡እገሪሁ፡ለያዕቆብ፤ወኀፀበ፡እግረ፡
ዮሐንስ፤ወኀፀበ፡እግረ፡ፊልጶስ፤ወኀፀበ፡
እግረ፡በርተሎሜዎስ ፤ ወኀፀበ ፡ እግረ ፡
ቶማስ፤ወኀፀበ፡እግረ፡ማቴዎስ፤ወኀፀበ፡
እግረ፡ታዴዎስ፤ወኀፀበ፡እግረ፡ናትናኤል፤
ወኀፀበ፡እግረ፡ያዕቆብ፡ወልደ፡እልፍዮስ፤
ወኀፀበ፡እግረ፡እንድርያስ፤ወኀፀበ፡እግረ፡
ይሁዳ፡አስቆሮታዊ፡ዘያገብእ።

፴፪ ወእምድኅረ ፡ ፈጸመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ኀጺበ፡እግረ፡አርዳኢሁ፡ገሰሶሙ፡በለንጽ፡
ዘሀሎ፡ውስተ፡ሐቌሁ፡ወኀፀበ፡እገሪሁ፡
በማይ፡ዘኀፀበ፡እግረ፡አርዳኢሁ።

፴፫ ተንሥአ፡ወቆመ፡ይጸሊ፡ወይቤ፡ዝ፡ግብር፡
ዘገበርኩ፡አነ፡ለክሙ፡ወአንትሙ፡ከመ፡ዝ፡
ግበሩ፡ለቢጽክሙ።

፴፬ ወእምድኅረ ፡ ይቤሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ነሥአ ፡
አልባሲሁ፡ወለብሰ፡ወነበረ፡ከመ፡ይብላዕ፡
ማእደ።

፴፭ ወይሁዳ ፡ ሀሎ ፡ ይመክር ፡ በዘያገብኦ ፡
ወአእመረ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡
ለአርዳኢሁ ፡ አማንየ ፡ እብለክሙ ፡ በዛቲ ፡
ሌሊት፡ትክሕዱኒ፡ወተኀድጉኒ፡ባሕቲትየ፡
ኵልክሙ ፡ ወሀሎ ፡ ዘያገብአኒ ፡ ዝየ ፡ ወዘያ
ቀድም፡አዴሁ፡ጸቢኀ፡ምስሌየ።

### ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ብኩህ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ርስትና ፡ ዕድል ፡ እንደ ፡
ሌለህ፡በእውነት፡እነግርሃለሁ፡አለው።

፳፱፤ ጴጥሮስም፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡ደነገጠ፤አንገ
ቱንም፡ዝቅ፡አድርጎ፡ለመድኅን፡ጌታ፡ሰገደ፤
መድኃኒታችንንም፡እንዲህ፡አለው፤የምታ
ጥበኝ፡እግሮቼን፡ብቻ፡አይደለም፤ደግሞ፡
እጆቼንም፡ራሴንም፡ነው፡እንጂ።

፴፤ ጌታችንም፡ መታጠብ ፡ የሚሻ ፡ ከእግሮቹ ፡
ብቻ ፡ በቀር ፡ አይታጠብም ፤ ሁለመናው ፡
ንጹሕ፡ነውና፤እናንተም፡ንጹሐን፡ናችሁ፤
ነገር፡ግን፡ሁላችሁ፡አይደላችሁም፡አለው።

፴፩፤ እንደዚህም ፡ ካላቸው ፡ በኋላ ፡ የጴጥሮስን ፡
እግር ፡ አጥቦ ፡ በሽርጡ ፡ ወለወለ ፤ የያዕቆ
ብንም፡እግር፡አጠበ፤የዮሐንስንም፡እግር፡
አጠበ፤የፊልጶስንም፡እግር፡አጠበ፤የበርተ
ሎሜዎስን ፡ እግር ፡ አጠበ ፤ የቶማስንም ፡
እግር፡አጠበ፤የማቴዎስንም፡እግር፡አጠበ፤
የታዴዎስንም፡እግር፡አጠበ፤የናትናኤልን፡
እግር ፡ አጠበ ፤ የእልፍዮስን ፡ ልጅ ፡ የያዕ
ቆብን፡ እግር ፡ አጠበ ፤ የእንድርያስንም ፡
እግር፡አጠበ፤የሚያስይዘውን፡የአስቆሮቱ፡
የይሁዳንም፡እግር፡አጠበ።

፴፪፤ የደቀ፡መዛሙርቱን፡እግር፡አጥቦ፡ከፈጸመ፡
በኋላ፡በወገቡ፡ታጥቆት፡በነበረው፡ሽርጥ፡
አሻቸው፤የደቀ፡መዛሙርቱን፡እግር፡በአጠ
በበት፡ውኃ፡እግሩን፡ታጠበ።

፴፫፤ ይጸልይ፡ዘንድ፡ተነሥቶ፡ቆመ፤እንዲህም፡
አለ ፤ ይህ ፡ ለእናንተ ፡ እኔ ፡ ያደረግሁትን ፡
ሥራ፡እናንተም፡ለወንድሞቻችሁ፡እንዲሁ፡
አድርጉ፡አለ።

፴፬፤ እንዲህም ፡ ካላቸው ፡ በኋላ ፡ ይመገብ ፡
ዘንድ ፡ ልብሱን ፡ ወስዶ ፡ ለብሶ ፡ በማእድ ፡
ተቀመጠ።

፴፭፤ ይሁዳም፡ጌታን፡እንዴት፡አሳልፎ፡እንደሚሰ
ጠው፡ይመክር፡ነበር፤ጌታ፡ኢየሱስም፡አውቆ፡
ደቀ፡መዛሙርቱን፡በዚች፡ሌሊት፡ሁላችሁም፡
ትክዱኛላችሁ ፤ ብቻዬንም ፡ ትተዉኛላችሁ ፡
ብዬ፡በእውነት፡እነግራችኋለሁ፤አሳልፎ፡የሚ
ሰጠኝም፡ ከዚህ፡ አለ፤ እርሱም፡ ከእኔ፡ ጋራ፡አስ
ቀድሞ፡ወደ፡ወጭቱ፡እጁን፡የሚያገባው፡ነው።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፹፯፤ ወይቤሎ፡ ስምዖን፡ ጴጥሮስ፡ እ፡ እግዚእየ፡ ለእመ፡ ኵሎሙ፡ ክሕዱከ፡ አንሰ፡ ኢይክ ሕደከ፡ ለዓለም፡ አላ፡ እሜጡ፡ ነፍስየ፡ በእን ቲአከ።

፹፰፤ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ አማን፡ እብለከ፡ እ፡ ጴጥሮስ፡ አንተሰ፡ ቅድመ፡ ይንቁ፡ ዶርሆ፡ ሥልሰ፡ትክሕደኒ።

፹፱፤ ወሶቤሃ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ቀደመ፡አእምሮ፡ ከመ፡የሐዝኑ፡በልቦሙ፡አርድእት፡በእንተ፡ ዘሰምዑ፡ ቃለ፡ በደብረ፡ ዘይት፡ በእንተ፡ ይሁዳ፡ወጸንዐ፡ልቦሙ፡ለአርድእት።

፺፤ ወጴጥሮስ፡ ሐተቶ፡ ለዮሐንስ፡ ወይቤሎ፡ ሑር፡ተሰአል፡በኀበ፡እግዚእነ፡ወዮሐንስሰ፡ ዘረፈቀ፡ ዲበ፡ እንግድዓሁ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡በእንተ፡ንጽሑ፡ይቤሎ፡እግዚእ፡ መኑ፡ዘያገብአከ፡እምኔነ።

፺፩፤ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እ፡ ዮሐንስ፡ ወልድየ፡ ወፍቁርየ፡ ዘእነ፡ እጸብኅ፡ ሎቱ፡ ኅብስተ፡ወእሜጥዎ፡ውእቱ፡ያገብአኒ።

፺፪፤ ወእምድኅረ፡ ይቤሎሙ፡ ዘንተ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡አንቃዕደወ፡ሰማየ፡ነሥአ፡ኅብስተ፡ ባረከ፡ ወቀደሰ፡ ወነሥአ፡ እምኔሁ፡ ወወሀቦሙ፡ ለአርዳኢሁ፤ ወይቤሎሙ፡ ንሥኡ፡ብልዑ፡ዝ፡ውእቱ፡ሥጋየ፡ዘበእንቲ አክሙ፡ይትፌተት፡ወበእንተ፡መድኃኒተ፡ ኵሉ፡ዓለም፡በዘይትኀደግ፡ኃጢአት።

፺፫፤ ወእምድኅረዝ፡ነሥአ፡ወይነ፡ወማየ፡ቶስሐ፡ አእኰተ፡ባረከ፡ወቀደሰ፡ወሰትየ፡እምኔሁ፡ ወወሀቦሙ፡እንዘ፡ ይብል፡ ንሥኡ፡ ስትዩ፡ እምኔሁ፡ኵልክሙ።

፺፬፤ ዝ፡ውእቱ፡ደምየ፡ዘሐዲስ፡ሥርዓት፡ዘይት ከዐው፡ በእንቲአክሙ፡ ወለብዙኃን፡ ለኅድገተ፡ኃጢአት።

፺፭፤ ወአንትሙኒ፡ ግበሩ፡ ተዝካርየ፡ እስከ፡ እመጽእ፡በደኀሪት፡ዕለት፤ ዜንዉ፡ሞትየ፤ ወእመኑ፡ትንሣኤየ፤ ወእስምዑ፡ከመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡እኅዜ፡ኵሎ።

፺፮፤ ወአንሰ፡ኢይሰትዮ፡ለዝንቱ፡ጽዋዕ፡ዳግመ፡ እስከ፡እሰትዮ፡ሐዲሰ፡በመንግሥተ፡አቡየ፡ ዘበሰማያት።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፹፯፤ ስምዖን፡ ጴጥሮስም፡ ጌታዬ፡ ሆይ፡ ሁሉም፡ ቢክዱህ፡እኔ፡ለዘላለሙ፡አልክድህም፡ስለ፡ አንተ፡ነፍሴን፡አሳልፌ፡እሰጣለሁ፡እንጂ፡ አለው።

፹፰፤ ጌታም፡ ጴጥሮስ፡ ሆይ፡ አንተስ፡ ዶሮ፡ ሳይጮህ፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ትክደኛለህ፡ ብዬ፡ በእውነት፡እነግርሃለሁ፡አለው።

፹፱፤ ያን፡ ጊዜ፡ ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ሐዋርያት፡ ስለ፡ ይሁዳ፡ በደብረ፡ ዘይት፡ ስለሰሙት፡ ቃል፡ በልባቸው፡እንደሚያዝኑ፡አስቀድሞ፡ያውቅ፡ ነበር፤የሐዋርያትም፡ልባቸው፡ጸና፤(ረጋ)።

፺፤ ጴጥሮስም፡ ዮሐንስን፡ ጠየቀው፤ ከጌታ፡ ዘንድም፡ሒደህ፡ጠይቅ፡አለው፤ዮሐንስም፡ ስለ፡ ንጽሕናው፡ በጌታ፡ ኢየሱስ፡ አጠገብ፡ የሚቀመጥ፡ ነበርና፤እርሱም፡ አቤቱ፡ ከእኛ፡ መካከል፡የሚያስይዝህ፡ማነው?አለው።

፺፩፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ልጄ፡ወዳጄ፡ዮሐንስ፡ሆይ፡ እኔ፡ ከወጡ፡ እንጀራ፡ ጠልቄ፡ የምሰጠው፡ እርሱ፡ያስይዘኛል፡አለው።

፺፪፤ ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ይህን፡ ካላቸው፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ቀና፡ብሎ፡ኅብስቱን፡አንሥቶ፡ባረከ፡ አከበረ፤ ለወጠ፤ ከሱም፡ አንሥቶ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሰጣቸው፤ኃጢአት፡በሚሰረይ፡ ገንዘብ፡ ስለ፡ እናንተና፡ ስለ፡ ዓለሙ፡ ሁሉ፡ ድኅነት፡ የሚፈተተው፡ ሥጋዬ፡ ይህ፡ ነውና፡ እንኩ፡ንሡ፡ብሉ፡አላቸው።

፺፫፤ ከዚህም፡ በኋላ፡ ወይኑን፡ አንሥቶ፡ ከውኃ፡ ጋራ፡ አዋሕዶ፡ አመሰገነ፤ ባርኮ፡ አከብሮ፡ ከእርሱ፡ ጠጣ፤ ሁላችሁም፡ ከእርሱ፡ ጠጡ፡ ብሎ፡ሰጣቸው።

፺፬፤ ኃጢአትን፡ ለማስተስረይ፡ ስለ፡ ብዙዎች፡ የሚፈሰው፡ የሐዲስ፡ ሥርዓት፡ ደሜ፡ ይህ፡ ነው።

፺፭፤ እናንተም፡ እስከምመጣበት፡ እስከ፡ ኋለኛይቱ፡ ቀን፡ ድረስ፡ መታሰቢያዬን፡ አድርጉ፤ሞቴን፡ንገሩ፤ መነሣቴንም፡እመኑ፡ ዓለሙን፡ሁሉ፡የያዝኩ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ እንደሆንኩ፡አስሙ።

፺፮፤ በሰማያት፡በአለ፡በአባቴ፡ሥልጣን፡በሐዲስ፡ ሥጋ፡ ተነሥቼ፡ ዳግመኛ፡ እስከምጠጣው፡ ድረስ፡እኔ፡ይሕን፡ጽዋ፡አልቀምሰውም፡አለ

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወእምዝ ፡ ነሥኡ ፡ አርድእት ፡ ወበ
ሉ፡ወሰትዩ፡እምዘባረከ፡እግዚእ፡ኢየ
ሱስ፡ወውእቱ ፡ ይሁዳ ፡ በሥጋ ፡ ዘእም
እዝማዲሁ፡ወርሑቅ፡እምበረከት፡ነሥአ፡
ምስሌሆሙ።
ፃማሕኬ፡ነበ፡ጥንተ፡ነገር፡ወእምዝ፡
አክሮስና፡ብእሲተ፡ስምዖን፡ፈሪሳዊ፡
እምጽአት፡ዶርሆ፡ዘጥቡስ፡በመቅፀት፡
ወወደየት፡ውስተ፡ጻሕል፡ሠናይ፡ወአብአት፡
ውስተ፡ማእድ፡ወአንበረት፡ቅድሜሁ፡ለመ
ድኃኒነ።
ወሰበ፡ርእየ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ማእደ፡
ሥሩዐ፡ይቤ፡በጽሐ፡ኵሉ፡ዘጽሑፍ፡በእን
ቲአየ።ወእምዝ፡ጸብኀ፡ኅብስተ፡ወወሀቦ፡
ለይሁዳ፡ወልደ፡ስምዖን፡አስቆሮታዊ፡
ዘውእቱ፡ይፈቅድ፡ያግብኦ።
ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ቦአ ፡ ሰይጣን ፡ ላዕ
ሌሁ፡ወአንደደ፡ልቦ፡ከመ፡እሳት፡ወአ
ዝዘ፡አጽባዕቶ፡ዲበ፡አፉሁ፡ወርእየ፡
ለመድኃኒነ።
ወይቤሎሙ፡እግዚእነ፡ለአርዳኢሁ፡አነኒ፡
ፈጸምኩ፡ኵሎ፡ተንሥኡ፡ንሑር፡እምገዝየ፡
ኀበ፡ደብረ፡ዘይት፡ወንቢት፡ህየ፡በዛቲ፡
ሌሊት።
ወሰበ፡ሰምዐ፡ይሁዳ፡ዘንተ፡ነገረ፡ተፈሥሐ፡
ወአእመረ፡ከመ፡አልቦ፡ሐሰት፡ዘወፅአ፡እም
ቅድስት፡አፉሁ፡ለእግዚእነ፡ወአልቦ፡
ምግባእ፡ድኅረ፡እምቃሉ። ወተንሥአ፡
በቅንዓተ፡ሰይጣን፡ዘቦአ፡ላዕሌሁ፡ምስለ፡
ኅብስት።
ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ዘትፈቅድ፡
ግበር፡አ፡ፍቁርየ፡ወሶበሃ፡ወፅአ፡ወኢነሥአ፡
በረከተ፡እምእግዚአብሔር፡ወሖረ፡ኢየሩ
ሳሌም፡ኀበ፡አይሁድ።
ወእምዝ፡ለከፎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በአጽ
ባዕቱ፡ለውእቱ፡ዶርሆ፡ዘሕሩድ፡ዘሀሎ፡
ቅድሜሁ፡በጻሕል፡ንቡር።
ወሶቤሃ፡ተንሥአ፡ሕያው፡ዶርሆ፡ከመ፡
ትካት፡ወቆመ፡በአንጻሪሁ፡ከመ፡ዘኢለከፎ፡
መጥባሕት፡ርእሶ፡ወኢነትጉ፡አሐዱ፡
እምሥጋሁ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፺፮፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ የባረከውን ፡ ሐዋርያት ፡ በሉ ፤ ጠጡ ፤ በሥጋ ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ከበረከትም ፡ የራቀ ፡ ያ ፡ ይሁዳ፡ ከእርሳቸው፡ ጋር፡ ቅዱስ፡ ቍርባንን፡ ተቀብሎ፡ነበር።
፺፯፤ ወደ፡ቀደመው፡ነገር፡እንመለስና፤አሁን፡የፈሪሳዊው ፡ ስምዖን ፡ ሚስት ፡ አክሮስና ፡ በምንቸት ፡ የተጠበሰ ፡ ዶሮ ፡ አምጥታ ፡ በመልካም ፡ ወጭት ፡ አቀረበችው ፤ ወደ ፡ ማዕዱም፡አስገብታ፡በመድኃኒታችን፡ፊት፡አኖረችው።
፺፰፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ የተሠራውን ፡ ማእድ ፡ አይቶ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ፤ ብሎ፡ ኅብስቱን ፡ ከወጡ ፡ ጠልቆ ፡ ሊያስይዘው፡ ለሚሻው ፡ ለአስቆሮቱ ፡ ስምዖን ፡ ልጅ፡ለይሁዳ፡ሰጠው።
፺፱፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰይጣን ፡ አደረበት ፤ ልቡንም፡በቅንዓት፡እንደ፡እሳት፡አነደደው፤ ጣቱንም ፡ በአፉ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ መድኃኒታችንን፡አየው።
፻፤ ጌታችንም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እኔ ፡ ሁሉን፡ፈጸምኩ፤ተነሡ፤ወደ፡ደብረ፡ዘይት፡ እንሒድ ፤ በዚች ፡ ሌሊት ፡ በዚያ ፡ እንደር ፡ አላቸው።
፻፩፤ ይሁዳም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ከጌታችንም ፡ ከቅድስት ፡ አንደበቱ ፡ የሚወጣ፡ሐሰት፡እንደሌለው፡ከቃሉ፡የሚወጣውም ፡ ወደኋላ ፡ እንደማይመለስ ፡ አወቀ ፤ ከኅብስቱ፡ጋር፡ባደረበት፡የሰይጣን፡ቅንዓት፡ ተነሣሣ።
፻፪፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ልትሠራው ፡ የምትሻውን፡ሥራ፡አለው፤ወዲያውኑ፡ወጣ፤ ከእግዚአብሔርም፡በረከትን፡አልተቀበለም፤ ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ወደ፡አይሁድ፡ሔደ።
፻፫፤ ከዚህም፡በኋላ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ያንን፡ታርዶ፡ ተጠብሶ፡በፊቱ፡በወጭት፡የተቀመጠውን፡ ዶሮ፡በጣቱ፡ነካው።
፻፬፤ ወዲያውም፡ዶሮው፡እንደቀድሞው፡ደኅና፡ ሁኖ፡ቢላዋም፡ራሱን፡እንዳልነካው፡ሆኖ፡ ከሥጋውም፡አንድም፡ሳይጎድል፡በአንጻሩ፡ ቆመ።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፻፭፧ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ አነ፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ትትሉ፡
እኤዝዘከ፡ አንተ፡ ዶርሆ፡ ከመ፡ ትትሉ፡
ድኅሬሁ፡ለይሁዳ፡በኅቡእ።
ወባእ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወአእምር፡ ዘይገብር፡
ይሁዳ፡ በቤቱ፡ ወበኅበ፡ አይሁድ፡ ወበኅበ፡
ቤተ፡ መቅደስ፡ ወብጻሕ፡ ህየ፡ ሰሪረከ፡
ዘእንበለ፡ፍርሀት።
ወይትወሀበከ፡ ልሳን፡ ከመ፡ ዕጓለ፡
እመሕያው፡ ወበቃል፡ ተናገሮሙ፡ ለሐዋ
ርያት፡ኵሎ፡ዘኮነ።

፻፮፧ ወሶቤሃ፡ ሰረረ፡ ዶርሆ፡ ወተለዎ፡ ለይሁዳ፡
ወበጽሐ፡ይሁዳ፡ኢየሩሳሌም።
ወውእቱ፡ ባሕቲቱ፡ ዘይገብር፡ ኃጢአተ፡
እምነ፡ኵሎሙ፡አርዳኢሁ።
ወእምድኅረ፡ ተለውዎ፡ ለእግዚእነ፡ አልቦ፡
ዘገብአ፡ ኀበ፡ ኀጢአት፡ ዘእንበለ፡ ይሁዳ፡
ባሕቲቱ።

፻፯፧ ወሖረ፡ ይሁዳ፡ ወቦአ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡
ወዶርሆ፡ይተሉ፡ድኅሬሁ፤ወውእቱ፡ርጉም፡
ኢያእመረ።
ወአስተጋብአሙ፡ ለአይሁድ፡ ወለሊቃነ፡
ካህናት።

፻፰፧ ወይቤሎሙ፡ ንግሩኒ፡ ዘትፈቅዱ፡ ወዘት
ሁቡኒ፡ዐስብየ፡ወአነ፡እሜጥወክሙ፡ኪያሁ፡
በዛቲ፡ሌሊት።

፻፱፧ ወወሀብዎ፡ ሠላሳ፡ ብሩረ፡ ወይ
ቤሎሙ፡ ተደለዉ፡ ወንዑ፡ ምስሌየ፡ አነ፡
እሜጥወክሙ።
ወይቤልዎ፡ ለእመሰ፡ መጠውከነ፡ ወአግ
ባእኮ፡ኀቤነ፡ንሰቅሎ፡ዲበ፡ዕፅ፡ወንወግኦ፡
በኲናት።

፻፲፧ ወሊቃነ፡ካህናት፡ወጸሐፍት፡ወፈሪሳውያን፡
ተበሀሉ፡በበይናቲሆሙ፡በጽልመተ፡ሌሊት፡
ምንተ፡ ንሬኢ፡ ወምንተ፡ ንገብር።
ወይቤሎሙ፡ወልደ፡ስምዖን፡አስቆሮታዊ፡
በእንተ፡ምንትኑ፡ተሐዝኑ፡ወአነ፡አአምር፡
ኀበ፡ሀሎ፡መካን።

፻፲፩፧ ወይቤልዎ፡ አይሁድ፡ በአይቴ፡ ነአምሮ፡
ወይቤሎሙ፡ ይሁዳ፡ ዘብዙኅ፡ አበሳሁ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፻፭፧ ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስም፡ አንተ፡ ዶሮ፡
ይሁዳን፡ በኋላ፡ በኋላው፡ በሥውር፡
ትከተለው፡ዘንድ፡እኔ፡አዝዝሃለሁ፡
ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ገብተህ፡ ይሁዳ፡ በቤቱ፡
የሚያደርገውን፤በአይሁድም፡ዘንድ፤በቤተ፡
መቅደስም፡ የሚሠራውን፡ አይተህ፡ ያለ፡
ፍርሃትም፡በርረህ፡ወደዚያ፡ድረስ፤
እንደ፡ ሰውም፡ አንደበት፡ ይሰጥህ፤ለሐዋር
ያትም፡የሆነውን፡ሁሉ፡በቃል፡ንገራቸው፡
አለው።

፻፮፧ ያን፡ጊዜ፡ዶሮው፡በርሮ፡ይሁዳን፡ተከተለው፤
ይሁዳም፡ኢየሩሳሌም፡ደረሰ፤
ከደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ሁሉ፡ ኃጢአትን፡
የሚሠራ፡እርሱ፡ብቻ፡ነበር፤
ጌታችንንም፡ ከተከተሉት፡ በኋላ፡ ከብቻው
ከይሁዳ፡ በቀር፡ ወደ፡ ኃጢአት፡ ሥራ፡
የተመለሰ፡የለም።

፻፯፧ ይሁዳም፡ ሒዶ፡ ወደ፡ ምኵራብ፡ ገባ፤
ዶሮውም፡ ይከተለው፡ ነበር፤ የተረገመ፡
ይሁዳ፡ግን፡አላወቀም፤
አይሁድንና፡ የካህናት፡ አለቆችን፡ ሰበሰ
ባቸው።

፻፰፧ የምትሹትን፡ ለእኔም፡ የምትሰጡኝን፡
ዋጋዬን፡ ንገሩኝ፤ እኔም፡ በዚች፡ ሌሊት፡
እርሱን፡አሳልፌ፡እሰጣችኋለሁ፡አላቸው።

፻፱፧ ሠላሳ፡ ብርም፡ ሰጡት፤ እርሱም፡ ተቀብሎ፡
ተዘጋጅታችሁ፡ከእኔ፡ጋራ፡ኑ፤እኔም፡አሰጣ
ችኋለሁ፡አላቸው።
እነርሱም፡ አሳልፈህ፡ ወደእኛ፡ ካስገባኸው፡
በዕንጨት፡ ላይ፡ ሰቅለን፡ በጦር፡ እንወጋ
ዋለን፡አሉት።

፻፲፧ የካህናት፡ አለቆችና፡ ጻፎች፡ ፈሪሳውያንም፡
እርስ፡በርሳቸው፡በሌሊት፡ጨለማ፡ምን፡እናደ
ርጋለን፤ምንስ፡እንሠራለን?ተባባሉ።
የአስቆሮቱ፡ስምዖን፡ልጅ፡ይሁዳም፡ስለምን፡
ታዝናላችሁ? ያለበትን፡ ቦታ፡ እኔ፡
አውቃለሁ፡አላቸው።

፻፲፩፧ አይሁድም፡ በየት፡ እናውቀዋለን፡ አሉት፤
በደሉ፡የበዛ፡ይሁዳም፡ምን፡ያሳዝናችኋል፤

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ምት፡ያሐዝነክሙ፡ወአነ፡እሜጥወክሙ፡
ውስተ፡እደዊክሙ፡ወእሁበክሙ፡
ትእምርተ፡ወእስዕሞ።
ወዘሀሎ፡ፈቃር፡ውስተ፡ክሣዱ፡ውእቱ፡
ሀገሁ።
ወባሕቱ፡እምድኅረ፡መጠውኩክሙ፡
ውስተ፡እደዊክሙ፡አልብየ፡ዕዳ።
ወእውሥአ፡አሐዱ፡እምውስተ፡አይሁድ፡
ዘስሙ፡ሳውል፡እምሰብአ፡ጠርሴስ፡
ወቂልቅያ፡ወልደ፡ዮስአል፡ወልደ፡ማሶን፡
ወልደ፡ከዳፊና፡እምዘመደ፡ጸሐፍተ፡ኦሪት፡
ዘእምአዝማደ፡ሙሴ፡ወውእቱ፡ብእሲ፡
ዘተሐፅነ፡እምሀገረ፡ቂልቅያ፡ዘቤተ፡
ገማልያል፡ፈሪሳዊ፡መምህረ፡ኦሪት፡ዘተና
ገሮሙ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ወይቤሎ፡አንተሰ፡
መጥወኒ፡ውስተ፡እዴየ፡ዘእንበለ፡ዕዳ፤
ወሶበ፡ሰምዐ፡ዶርሆ፡ዘይብሉ፡ከመዝ፡እንዘ፡
ይወፅኡ፡እምቤተ፡መቅደስ፡ተውህበ፡ሎቱ፡
ኃይል፡ወሰረረ፡በክንፍ። ወበጽሐ፡ቢታንያ፡
ወበጽሐ፡መልዕልተ፡ቤት፡ኀበ፡ገብረ፡ፋሲካ፡
መድኃኒነ፡ምስለ፡አርዳኢሁ።
ወሰገደ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ውእቱ፡ዶርሆ፡ወቆመ፡እንዘ፡ይበኪ፡ብካየ፡
መሪረ። ወተውህቦ፡ቃለ፡ዕጓለ፡እመሕያው።
ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ንግር፡ዘዘ
ርእሆ፡ዘርኢከ፡ወዘሰማዕከ፤ ወሶቤሃ፡
ፈትሐ፡አፉሁ፡ዶርሆ፡ወተናገረ፡
በቃለ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ኵሎ፡ዘከመ፡
ገብረ፡ይሁዳ፡በኀበ፡ቤቱ፡ወዘከመ፡
ነሥአ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ወዘከመ፡ተጋብኡ፡
አይሁድ፡ወተማከሩ፡ወዘከመ፡ይቤሎሙ፡
ይሁዳ፡ትልዊኒ፡ወአነ፡እሜጥወክሙ፡
ኢየሱስሃ፡ወዘከመ፡ይቤሉ፡መጥወነ፡
ውስተ፡እዴነ፡ከመ፡ንስቅሎ፡ዲበ፡ዕፅ፡
ወንውግዞ፡በኵናት።
ወአንበ፡ኅደግዎሙ፡እንዘ፡ይትጋብኡ፡
ወይመጽኡ፡የአኀዙከ፡ወበእንተዝ፡ይበክዩ፡
ኵሉ፡ፍጥረት።
ወሶበ፡ሰምዐ፡አርድእት፡ዘንተ፡ቃለ፡እንዘ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

እኔ፡አሳልፌ፡በእጃቻችሁ፡እሰጣ
ችኋለሁ፤ ምልክትም፡እሰጣችኋለሁ፤ እስ
መዋለሁም።
በአንገቱም፡ኮሌታ፡ያለው፡ቀሚስ፡የለበሰ፡
ምልክቱ፡እርሱ፡ነው።

፻፲፪፤ በእጃችሁ፡ከሰጠኋችሁ፡በኋላ፡ግን፡ዕዳ፡
የለብኝም፡አላቸው።

፻፲፫፤ ከጠርሴስና፡ከቂልቅያ፡ሰዎች፡ወገን፡
የሚሆን፡ስሙ፡ሳውል፡የሚባል፡የዮስአል፡
ልጅ፤ የማሶን፡ልጅ፤ የከዳፊና፡ልጅ፡ከሕግ፡
ጸሐፎች፡ወገን፡የሙሴ፡ዘመዶች፡ወገን፡የሆነ፤
ይህም፡ከቂልቅያ፡ሀገር፡ከሚሆን፡ከፈሪ
ሳዊው፡ከምሑረ፡ኦሪቱ፡ከገማልያል፡ቤት፡
እየተማረ፡ያደገ፡ሊቃነ፡ካህናቱን፡የተናገራ
ቸውን፡አንተስ፡ያለ፡ዕዳ፡በእጄ፡ስጠኝ፡
ብሎ፡መለሰለት።

፻፲፬፤ ዶሮውም፡እንዲህ፡የሚናገሩትን፡በሰማ፡
ጊዜ፤ ከምኵራቡ፡ሲወጡ፡ኃይል፡
ተሰጥቶት፡በክንፍ፡በረረ፤ ወደ፡ቢታንያም፡
ደርሶ፡መድኃኒታችን፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡
ጋር፡ፋሲካ፡ወደ፡አደረገበት፡ቤት፡ወጣ።

፻፲፭፤ ያ፡ዶሮ፡ለጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሰግዶ፡መሪር፡ልቅሶን፡እያለቀሰ፡በፊቱ፡
ቆመ፤ የሰው፡ቃልም፡ተሰጠው።

፻፲፮፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ያየኸውንና፡የሰማኸውን፡
ሁሉ፡በየተራው፡ተናገር፡አለው፤ ያን፡
ጊዜም፡ዶሮው፡አፉ፡ተፈትቶ፡ይሁዳ፡
በቤቱ፡ያደረገውን፡ከአይሁድም፡ሠላሳ፡
ብር፡እንደ፡ተቀበለ፡አይሁድም፡ተሰብ
ስበው፡እንደተማከሩ፡ይሁዳም፡ተከተሉኝ፡
እኔም፡ኢየሱስን፡አሳልፌ፡እሰጣችኋለሁ፡
እንዳላቸው፡እነርሱም፡በእጃችን፡ስጠን፡
እንዳላቸው፡እንሰቅለው፡ዘንድ፡
በዕንጨት፡ላይ፡እንሰቅለው፡ዘንድ፡
በጦርም፡እንወጋው፡ዘንድ፡እንዳሉ፡በሰው፡
አንደበት፡ተናገረ።

፻፲፯፤ እኔም፡ሲሰበሰቡ፡ትቻቸው፡መጣሁ፡
ይይዙህም፡ዘንድ፡ይመጣሉ፤ ስለዚህም፡
ፍጥረት፡ሁሉ፡ያለቅሳሉ፡አለ።

፻፲፰፤ ሐዋርያትም፡ይህን፡ቃል፡ዶሮው፡ሲናገር፡

| በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ይትናገር ፡ ዮርሆ ፡ ወውእቱ ፡ ይበኪ ፡ ውእቶሙ፡በከዩ፡ወመጽአ፡ዐቢይ፡ፍርሀት፡ ላዕሌሆሙ። | በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር፡ እነርሱም ፡ አለቀሱ ፤ ታላቅ ፡ ፍርሀትም፡ በላያቸው፡አደረ። |
| ፻፲፱፡ ወውእተ፡ጊዜ፡አውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወይቤሎ፡ለዮርሆ፡አንተሰ፡ፈጸምከ፡መልእ ክተከ፡ወይእዜኒ፡ንሣእ፡ኃይለ፡ወሥርር፡ በክንፍ፡ወዕርግ፡ሰማያተ፡እምዮም፡እስከ፡ እልፍ፡ዓመት። | ፻፲፱፤ በዚያን፡ጊዜም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ዮርወን፡ አንተስ፡መልእክትህን፡ፈጽመሃል፤አሁንም፡ ኃይል ፡ ተቀበል ፤ በክንፍም ፡ በርረህ፡ወደ፡ ሰማያት ፡ ውጣ ፤ ከዛሬም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ አሥር፡ሺ፡ዓመት፡ኑር፡ብሎ፡መለሰለት፡ |
| ፻፳፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ዐቢይ፡ እምአርድእት ፡ ግበር ፡ ጸሎተ ፡ ወበረከተ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ ቅድመ፡ ንዓእ፡እምዝየ። | ፻፳፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ከሐዋርያት ፡ ታላቅ፡ የሆነውን ፡ ጴጥሮስን ፡ ከዚህ ፡ ከመውጣ ታችን፡በፊት፡በዚህ፡ቤት፡ውስጥ፡ጸሎትና፡ ቡራኬ፡አድርግ፡አለው። |
| ፻፳፩፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወሰገደ ፡ ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡እንዘ፡ይብል፡ሥረይ፡ ሊተ፡እግዚእየ፡ኃጢአትየ።እስመ፡አንተ፡ ውእቱ፡መድኃኔ፡ነፍሳቲነ፡ወለከ፡ይደሉ፡ ክብር ፡ ወቡራኬ ፡ ወስብሐት ። ወለነሰ ፡ አልብነ፡ሥልጣን፡ንግበር፡ዘንተ፡እንዘ፡ ሀሎከ፡አንተ። | ፻፳፩፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሥቶ ፡ ለጌታ ኢየሱስ ፡ ሰገደ ፤ እንዲህ ፡ እያለ ፤ አቤቱ ጌታዬ! ኃጢአቴን፡ይቅር፡በለኝ፤አንተ፡የነ ፍሳችን ፡ መድኃኒት ፡ ነህና ፤ ለአንተም፡ ክብር፡ ምስጋና ፡ ጌትነት ፡ ቡራኬም፡ ይገባል። ለእኛስ ፡ አንተ ፡ እያለህ ፡ ይህን፡ እናደርግ፡ዘንድ፡ሥልጣን፡የለንም፡አለው፡ |
| ፻፳፪፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ተንሥአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወቆመ ፡ ማዕከለ ፡ አርዳኢሁ ። ወጸለየ ፡ እንዘ፡ ይብል ፡ እባርከከ ፡ አቡየ ፡ እግዚአ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ወአንቃዕዱ ፡ ኀቤከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡየ ፡ ወአነ ፡ ወረድኩ ፡ እምሰማይ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ እምኔከ ። አንተ ፡ ውእቱ ፡ አቡየ ፡ ወአነ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ ዘወጻእኩ ፡ እምኔከ ፡ ወተ ሰመይኩ ፡ ወልደከ ፡ ዋሕደከ ፡ ወእ ንተ፡ምስሌየ፡ወአነ፡ምስሌከ፡ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡አሐዱ፡ንሕነ። | ፻፳፪፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ተነሥቶ፡ በደቀ፡መዛሙርቱ፡መካከል፡ቆሞ፡እንዲህ፡ እያለ፡ጸለየ፤የሰማይና፡የምድር፡ጌታ፡አባቴ፡ ሆይ፡አመሰግንሃለሁ፤አባቴ፡እግዚአብሔር፡ ሆይ ፡ አይኖቼን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ አነሣለሁ፡ እኔም፡ከአንተ፡ሕልውና፡ሳልለይ፡ከሰማይ፡ ወረድኩ ፤ አንተም ፡ አባቴ፡ ነህ ፤ እኔም፡ ከዓለም፡አስቀድሞ፡ከአንተ፡ጋራ፡የነበርኩ፡ ከአንተ፡የተገኘሁ፡ቀዳማዊ፡ቃልህ፡ስሆን፡ አንድ፡ልጅህ፡እባላለሁ፤አንተ፡ከእኔ፡ጋር፡ ነህ፤እኔና፡መንፈስ፡ቅዱስም፡ከአንተ፡ጋር፡ አንድ፡ነን። |
| ፻፳፫፡ ወወረድኩ ፡ እምሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወተሰ ባእኩ፡እማርያም፡ድንግል ። ወወለደትኒ ፡ እንዘ ፡ ድንግልናሃ ፡ ኅቱም ፡ ወሐፀነተኒ ፡ በሐሊበ፡አጥባቲሃ፡እንዘ፡ድንግል፡ይእቲ፡ ወእንዘ፡አነ፡ውእቱ፡ዘእሁብ፡ሲሳየ፡ለኵሉ፡ ዘሥጋ። | ፻፳፫፤ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወርጄ ፡ ከድንግል፡ ማርያም ፡ ከሥጋዋ ፡ ሥጋን ፡ ከነፍስዋ፡ ነፍስን ፡ ነሥቼ ፡ ሰው ፡ ሆንኩ ፤ ድንግል ናዋም፡ ሳይለወጥ፡ወለደችኝ፤እኔ፡ሥጋዊ፡ ደማዊ፡ፍጥረትን፡የምመግብ፡ስሆን፡በድን ግልና፡ሳለች፡በጡቶቿ፡ወተት፡አሳደገችኝ፡ |
| ፻፳፬፡ እስእል ፡ ኀቤከ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ወበእንተ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ ብየ ፡ በፍሥሐ ፡ ወእለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስምየ ፡ ወሕ ማምየ ፡ ዘይዜከሩ ፡ እወ ፡ ባርኮሙ ፡ | ፻፳፬፤ ስለ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ደስ፡ ብሏቸው ፡ በእኔ ፡ ስለሚያምኑና ፡ ስሜን፡ ስለሚወዱ ፡ መከራዬንም ፡ ስለሚያስቡ፡ አወን ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ በሰማይና ፡ በምድር፡ |

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወሕማምየ ፡ ዘይዜከሩ ፡ እወ ፡ ባርኮሙ ፡
በበረከተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፤ ወኵሎ ፡
ንዋዮሙ።
፻፳፭፡ ወባርክ ፡ ዘንተ ፡ ማእደ ፡ ወኵሎ ፡
ዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ በከመ ፡ ባረከ ፡ ቤተ ፡
አብርሃም ፡ አበ ፡ አበው ፡ ወኢዮብ ፡
ጻድቅ።
፻፳፮፡ ወሀበሙ ፡ ሀየንተ ፡ ዘዝየ ፡ ዘበ
ሰማያት ፡ ወሀየንተ ፡ ዘየኀልቅ ፡ ዘኢየ
ኀልቅ ፡ ወሀየንተ፡ ዘይበሊ ፡ ዘኢይበሊ ፡
በዝ ፡ ዓለም ፡ ዕስዮሙ ፡ ወበዘኢይማስን ፡
ዓለም።
፻፳፯፡ ወኢትሕሰብ፡ኵሎ፡እከዮሙ፡ዘላዕሌሆሙ፡
ወላዕለ፡ሕዝቦሙ።
ወኢይርኀቡ ፡ በመዋዕለ ፡ ረኀብ ፡ ወኢይት
ኀፈሩ ፡ በመዋዕለ ፡ እኩያት ፡ ከመ ፡ ተሀ
በሙ ፡ ሰላመ ፡ ወዳኅና ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡
ብየ ፡ እስእለከ ። አንተ ፡ ውእቱ ፡ አም
ላከ ፡ ሰላም ፡ ወሕይወት ፡ አንተ ፡ ወአነ ፡
አሐዱ፡ንሕነ።
፻፳፰፡ ወባርክ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ቤት፡ወርድአሙ፡
በምግባረ፡ሠናይ፡አሜን።
አውሥኡ ፡ ሐዋርያት ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡
አሜን፡ለይኩን፡ለይኩን።

## ጸሎተ፡ስምዖን፡ዐምዳዊ።

፩፡ እ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ዘወሀብከ ፡ ሥጋከ ፡ ቅዱሰ ፡ ለአር
ዳኢከ ፡ ንጹሓን ፡ ሀበኒ ፡ ለገብርከ ፡
ኅብስተ ፡ ሕይወት ። አንተ ፡ ውእቱ ፡
ኅብስተ ፡ ሕይወት ፡ አሕይወኒ ፡ እስመ፡
አንተ ፡ መጻእከ ፡ ከመ ፡ ታሕዩ ፡
ዓለመ።
፪፡ ኅብስተ ፡ ሕይወት ፡ አብሕአኒ ፡ በም
ሕረትከ ፡ ከመ ፡ እትዋሐድ ፡ ምስለ ፡
ኃይልከ ፡ ትኅድር ፡ በውሳጤ ፡ ነፍስየ ፤
አሜን።

## አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዐቱ።

እመጽሐፈ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘአበዊነ ፡
ሐዋርያት ። በረከቶሙ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
፫፡ ወእንዘ፡ንበልዕ፡ምስሌሁ፡ፈቀደ፡እግዚእነ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

አወን ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡
በረከት ፡ እንድትባርካቸው ፡ ወዳንተ ፡ እለም
ናለሁ፤ገንዘባቸውንም፡ባርክ።
፻፳፭፡ የአባቶች ፡ አባት ፡ የሆነ ፡ የአብርሃምን ፡
ቤትና ፡ የጻድቁ ፡ የኢዮብን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡
ባረከህ ፡ ይህን ፡ ማእድና ፡ በዚህም ፡ ቤት ፡
ያለውን፡ሁሉ፡ባርክ።
፻፳፮፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ባደረጉት ፡ ፈንታ ፡ በሰማይ ፡
ስጣቸው ፤ በሚያልቀው ፡ ፈንታ ፡ የማያል
ቀውን ፡ በሚጠፋው ፡ ፈንታ ፡ የማይጠ
ፋውን፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ በማይጠፋውም ፡
ዓለም፡ስጣቸው።
፻፳፯፡ በላያቸውና ፡ በወገኖቻቸው ፡ ያለውን ፡
ክፋት፡ሁሉ፡አትቍጠርባቸው፤
በረኀብ ፡ ዘመን ፡ እንዳይራቡ ፡ ክፉዎች ፡
በሆኑ፡ወራቶችም፡በመከራው፡እንዳያፍሩ፡
በእኔ ፡ የሚያምኑብኝን ፡ ሰላምን ፡ ድኅነትን ፡
ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፤ አንተ ፡
የሰላምና ፡ የሕይወት ፡ አምላክ ፡ ነህና ፤
አንተና፡እኔ፡አንድ፡ነን።
፻፳፰፡ በዚህም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በረከት ፡ አሳድር ፤
በበጎ፡ሥራ፡ሁሉ፡እርዳቸው፤አሜን።
ሐዋርያትም ፡ አሜን ፡ በውነት ፡ ይሁን ፡
ይደረግ፡እያለ፡መለሱ።

## የዐምዳዊ፡ስምዖን፡ጸሎት።

፩፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ቅዱስ ፡
ሥጋህን ፡ ለንጹሐን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትህ ፡
የሰጠህ ፡ ለኔ ፡ ለባርያህ ፡ የሕይወት ፡
እንጀራ ፡ እንጀራን፡ ስጠኝ ፤ የሕይወት ፡ እንጀራ ፡
አንተ፡ ነህና ፤ ሕያው ፡ አድርገኝ ፤ አንተ ፡
ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ሕያው ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡
መጥተሃልና።
፪፡ በውስጣዊ ፡ ሰውነቴ ፡ ታድር ፡ ዘንድ ፡ በጸጋ ፡
ከመለኮትህ ፡ ኃይል ፡ ጋራ ፡ እንድዋሐድ ፡
የሕይወት ፡ እንጀራ ፡ አንተ ፡ በቸርነትህ ፡
እርሾ፡አድርገኝ፡አሜን።

## ሃያ፡ዘጠነኛው፡አንቀጽ።

በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፤
አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ከተናገሩት፡
ከሥርዐት፡መጽሐፍ፡የተገኘ፡ይህ፡ነው።
፫፡ ከእርሱ ፡ ጋርም ፡ ስንበላ ፡ ጌታችን ፡ ይሁዳን ፡

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ይገሥጽ ፡ ለይሁዳ ፡ ወናሁ ፡ አለበወነ ፡ ከመ ፡
ውእቱ፡ያገብአ።
፳፪ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ አማን ፡ አማን ፡
እብለክሙ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡
ያገብአኒ።
ወተባሀልነ ፡ በበይናቲነ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡
እንዘ፡ንብል፡አነኑ፡እግዚኦ፡እንጋ።
፳፫ ወተንሥእኩ ፡ አነ ፡ ዮሐንስ ፡ አሐዱ ፡ እምዐ
ሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኪያየ ፡
ያፈቅረኒ ፡ እምኵሎሙ ፡ አርድእት ፡ ወተሰአ
ልክዎ፡ወእቤሎ፡እግዚኦ፡መኑ፡ውእቱ፡ዘያገ
ብአከ፡ወእግዚእነሰ፡ኢነገረኒ፡ስሞ።
፳፬ ወባሕቱ ፡ አመረኒ ፡ በክልኤ ፡ ትእምርት ፡
ቀዳሚሁሰ ፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ ዘይጸብኅ ፡
እዴሁ፡ ምስሌየ ፡ ውስተ ፡ መጽብኅ ፡ ውእቱ ፡
ያገብአኒ ። ወዳግመ ፡ ይቤ ፡ ዘእሜጥዎ ፡ አነ ፡
ኅብስተ ፡ ውእቱ ፡ ያገብአኒ ። እስመ ፡ ይቤሎ ፡
አነኑ ፡ ውእቱ ፡ እግዚኦ ፡ ወእግዚእነሰ ፡
ኢይቤሎ ፡ እወ ፡ አንተ ፡ አላ ፡ ይቤሎ ፡ አንተ ፡
ትቤ።
፳፭ ወውእቱሰ፡ኢፈቀደ፡ያግህድ፡ቦቱ፡ዳእሙ፡
ይቤ ፡ እምኅየሰ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ሶበ ፡
ኢተወልደ ፡ ዘበእዴሁ ፡ ይትሜጠውዎ ፡
ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው።
፳፮ ወሰሚዖ ፡ ዘንተ ፡ ይሁዳ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡
ካህናት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ምንተ ፡ ትሁቡኒ ፡
ወአነ፡አገብአ፡ለክሙ።
፳፯ ወተማከሩ ፡ የሀብዎ ፡ ሠላሳ ፡ ብሩረ ፡
ውእተ ፡ አሚረ ፡ ኀሙስ ፡ ዕለት ፡ አመ ፡
በልዐ ፡ ፍሥሓ ፡ ምስሌነ ፡ እግዚእነ ፡
ወይሁዳሰ ፡ ነሥአ ፡ ኅብስተ ፡ ወጸብኀ ፡
እዴሁ ፡ ውስተ ፡ መጽብሕ ፡ ወወጽአ ፡
ሌሊተ።
፳፰ ወይቤለነ ፡ እግዚእነ ፡ በጽሐት ፡ ሰዓት ፡
ናሁ ፡ ትዘረዉ ፡ ኵልክሙ ፡ ወተኀድጉኒ ፡
ባሕቲትየ።
፳፱ ወንቤ፡አሐዱ፡አሐዱ፡እምኔነ፡ኢነኀድገከ፡
ወእቤሎ ፡ አነ ፡ ጴጥሮስ ፡ እመኒ ፡ ኵሎሙ ፡
ኀደጉከ ፡ አንሰ ፡ ኢየኀድገከ ፡ ወእመውት ፡
ምስሌከ።
ወይቤለኒ ፡ አማን ፡ እብለከ ፡ ዘእንበለ ፡ ይንቁ

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ይገሥጸው፡ዘንድ፡ወደደ፤እርሱ፡እንደሚያሲ
ይዘውም፡አሁን፡አስገነዘበን።
፳፪ ስለዚህም፡ከእናንተ፡አንዱ፡እንዲያሲይዘኝ
እውነት፡እላችኋለሁ፡አለ፤

አንዱም ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ እሆን ? እኔ ፡ እሆን
እንጃ፡እያልን፡እርስ፡በርሳችን፡ተነጋገር፡
፳፫ ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ ዮሐንስ
ተነሥቼ ፡ ከሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ እኔን
ይወደኝ ፡ ነበርና ፤ አቤቱ ፡ የሚያሲዝህ ፡ ማን
ነው ? ብዬ ፡ ጠየቅሁት ፤ ጌታችንም ፡ ስሙን
አልነገረኝም።
፳፬ ነገር ፡ ግን ፡ በሁለት ፡ ምልክት ፡ አመለከተኝ
መጀመሪያውም ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ እጁን ፡ ወደ
ወጭቱ ፡ የሚሰደው ፡ እርሱ ፡ ያስይዘኛል
ስለአለው ፡ ነው ፤ ሁለተኛውም ፡ ከኅብስቱ
ቁርሼ ፡ የምሰጠው ፡ እርሱ ፡ ያሲዘኛል
ስለአለው ፡ ነው ፤ አቤቱ ፡ እኔ ፡ እሆን ፡ ብሎት
ነበርና ፡ ጌታችን ፡ ግን ፡ አወን ፡ አንተ ፡ ነህ
አላለውም፤አንተ፡አልክ፡አለው፡እንጂ፡
፳፭ እርሱም ፡ ሊገልጽበት ፡ አልወደደም ፤ ነገር
ግን ፡ የሰው ፡ ልጅን ፡ በእርሱ ፡ እጅ ፡ ለሚያ
በሉት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ባይወለድ ፡ በተሻለው
ነበር፡አለ፡እንጂ።
፳፮ ይሁዳም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ካህናት
አለቆች፡ሄዶ፡እኔ፡በእጃችሁ፡አሲዛችኋለሁ
ምን፡ትሰጡኛላችሁ፡አላቸው።
፳፯ ሠላሳ፡ብር፡ይሰጡት፡ዘንድ፡ተማከሩ፤ያ
ጊዜም፡ቀኑ፡ኀሙስ፡ነው፤ጌታችን፡ከእኛ
ጋር ፡ የፋሲካውን ፡ በግ ፡ በበላ ፡ ጊዜ ፡ ነው
ይሁዳ ፡ ግን ፡ እንጀራ ፡ አንሥቶ ፡ እጁን
ከወጭቱ፡አስገብቶ፡ከወጡ፡አጥቅሶ፡ጉርሶ
በሌሊት፡ወጥቶ፡ሔደ።
፳፰ ጌታችንም ፡ እነሆ ፡ ሰዓቲቱ ፡ ደረሰች
ሁላችሁም ፡ ብቻዬን ፡ ትታችሁኝ ፡ ትበተ
ናላችሁ፡አለን።
፳፱ ከእኛ፡አንዱም፡አንዱ፡አንተውህም፡አለን
እኔ ፡ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ ቢተዉህ
ብቻህን፡ አልተውህም ፤ አብሬህ ፡ ከአንተ
ጋራ፡እሞታለሁ፡አልሁት፤
ጌታም፡እንደማታውቀኝ፡ዶሮ፡ሳይጮኽ፡ሦስት

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ጸሐፍ፡ ሥልሰ ፡ ትክሕደኒ ፡ ከመ ፡ ዘኢ.ትአ ምረኒ።

ናሁ፡ አለበወነ ፡ ዘንተ ፡ ምሥጢረ ፡ ቅዱሰ ፡ ዘውእቱ፡ ሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ ወደሙ ፡ ክቡር ፡ እንዘ፡ሀሎ፡ይሁዳ፡ምስሌነ።

ምንተኑ፡በል።

ተአምረሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላ ዲት ፡ አምላክ ፡ ጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ቀሲስ ፡ በሀገረ ፡ ቂሳርያ ፡ ዘስሙ፡እንድርያስ፤ወሀለወት፡አሐቲ፡ቤተ፡ ክርስቲያን፡ዘተሐንጸት፡በስመ፡እግዝእትነ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ፡አምላክ፡ወብዙኃን፡ካህናት፡ወዲያ ቆናት፡ይነብሩ፡ውስቴታ።

ወውእቱሰ ፡ ቀሲስ ፡ እንድርያስ ፡ ሠናየ ፡ ሐረት፡ወጥቀ፡የዋሀ።

ወያፈቅራ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድን ግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በኵሉ ፡ ልቡ ፡ ወበኵሉ ፡ ከሂሎቱ።

ወይቄድስ ፡ ቀሲስ ፡ እንድርያስ ፡ ዘልፈ ፡ ቅዳሴሃ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድ ስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወኢየአምር ፡ ካልአ ፡ ቅዳሴ፡ዘእንበሌሃ።

ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ጸውዖ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለውእቱ፡ ቀሲስ ፡ እንድርያስ ፡ ወገሠጾ ፡ ወይቤሎ፡ለምንት፡ኢትቄድስ፡ካልአ፡ቅዳሴ፡ ዘእንበለ ፡ አሐዱ ፡ ቅዳሴ ፡ ለለኵሉ ፡ ዕለት ፡ ወበኑ፡ኢተአምር፡ባዕደ።

አውሥአ ፡ ውእቱ ፡ ቀሲስ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢየአምር፡ካልአ፡ቅዳሴ፡ዘእንበለ፡ቅዳሴሃ፡ ለእግዝእትነ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ።

ወተምዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ፡ ኢይትለአክ ፡ ለእመ ፡ ኢያቀ ፡ ካልአ ፡ ቅዳሴ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ጊዜ ፡ እንደምትክደኝ ፡ በእውነት ፡ እነግር ሃለሁ፡አለኝ።

፲፡ እነሆ ፡ ይሁዳ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ልዩ ፡ የሆነ፡ ምሥጢር ፡ እንድናስተውል ፡ አደረገን፤ ይኸውም፡ክቡር፡ሥጋው፡ክቡር፡ደሙ፡ነው።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ በውነት ፡ ይኑርና ፤ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ያደረ ገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፡ ቂሳርያ፡በሚባል፡አገር፡እንድርያስ፡የሚባል፡ አንድ ፡ ቀሲስ ፡ ነበረ ፤ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ፡ነፍስ፡በጸናች፡አምላክን፡በወለደች፡ በክብርት እመቤታችን ፡ ስም ፡ የተሠራችም ፡ አንዲት ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ነበረች ፤ በውስ ጥዋም፡ብዙዎች፡ካህናት፡ዲያቆናት፡ነበሩ።

፪፡ ይህም፡ቀሲስ፡እንድርያስ፡በበጎ፡ሥራ፡የጸና፡ ፍጹም፡የዋህ፡ቅን፡ነበር።
በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያምን ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ በፍጹም ፡ ችሎታው፡ይወዳት፡ነበር።

፫፡ ቀሲስ ፡ እንድርያስም ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡የአምላክ፡እናት፡ የክብርት፡እመቤታችን፡የማርያምን፡ቅዳሴ፡ ዘወትር፡ይቀድሳል፤ከእርሷም፡በቀር፡ሌላ፡ ቅዳሴ፡አያውቅም፡ነበር።

፬፡ አንድ፡ቀንም፡ቀሲስ፡እንድርያስን፡ኤጲስ ቆጶሱ፡ጠርቶ፡ሁልጊዜ፡ካንድ፡ቅዳሴ፡በቀር፡ ሌላ፡ቅዳሴ፡የማትቀድስ፡ለምንድን፡ነው? ከአንድ፡ቅዳሴ፡በቀር፡በውኑ፡ሌላ፡ቅዳሴ፡ አታውቅምን፡ብሎ፡ገሠጸው።

፭፡ ያም ፡ ቄስ ፡ አምላክን ፡ ከወለደች ፡ ከእመቤ ታችን፡ማርያም፡ቅዳሴ፡በቀር፡ሌላ፡ቅዳሴ፡ አላውቅም፡ብሎ፡መለሰለት።

፮፡ ኤጲስቆጶሱም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ተቆጣ ፡ ሌላውን፡ ቅዳሴ ፡ ካላወቀ ፡ እንዳይቀድስ ፡ ከለከለው።

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፯ ወወፅአ ፡ ውእቱ ፡ ቀሲስ ፡ እምኀበ ፡ ኤጲስ
ቆጶስ፡እንዘ፡ይቴክዝ፡ወይበኪ።

፰ ወበይእቲ ፡ ሌሊት ፡ አስተርአየቶ ፡ እግዝእትነ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወትቤሎ ፡ ለውእቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለምንት ፡ አው ገዝኮ ፡ ለላእክየ ፡ ወከላእኮ ፡ እምተቀንዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በበይነ ፡ ዘቀደሰ ፡ ቅዳሴ ፡ ዚአየ ፡ ወትረ ፡ አማን ፡ እብለከ ፡ እመ ፡ ኢያግባእኮ ፡ ኀበ ፡ ቀዳሚ ፡ መልእክቱ ፡ እምዮም ፡ እስከ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕል፡ እኩየ ፡ ሞተ፡ትመውት።

፱ ወሰበ ፡ ሰምዐ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘንተ ፡ ወድቀ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለቀሲስ ፡ ወይ ቤሎ ፡ በትሕትና ፡ እስእለከ ፡ ከመ ፡ ትስ ረይ ፡ ሊተ ፡ በእንተ ፡ ዘአውገዝኩከ ፡ ወኩን ፡ ፍቱሐ ፡ ወተመየጥ ፡ ኀበ ፡ ቅዳ ሴከ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ እስመ ፡ ነገረተኒ ፡ በእንቲአከ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ። እምይእዜ ፡ ኢትቀድስ ፡ ካልአ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘእንበለ፡ቅዳሴሃ።

፲ ወሰረየ ፡ ሎቱ ፡ ቀሲስ ። ወአንበሮ ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ኀቤሁ ፡ ወኮነ ፡ ያረፍቆ ፡ ምስሌሁ ፡ ወይሴስዮ ፡ ወያለብሶ ፡ ወያከብሮ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይ ወቱ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

፲፩ ወፈጺሞ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ኀዊበ ፡ አእጋረ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አር ዳኢሁ ፡ ወነበሩ ፡ አርዳኢሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ዲበ፡ማእድ።

፲፪ ወሶበ ፡ ነበሩ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ ትቴክዝ ፡ ነፍስየ ፡ ጥቀ ፡

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፯ ቄሱም ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ዘንድ ፡ እያዘነና ፡ እያለቀሰ፡ወጥቶ፡ሔደ።

፰ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ አምላክን ፡ የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ ተገልጣ፡ያንን፡ኤጲስቆጶስ፡የእኔን፡ቅዳሴ፡ ስለቀደሰ፡አገልጋዬን፡ያወገዝከው፡እግዚአ ብሔርንስ ፡ ከማገልገል ፡ የከለከልከው ፡ ለምንድን፡ነው?ከዛሬ፡ጀምሮ፡እስከ፡ሦስት፡ ቀኖች፡ድረስ፡ወደ፡ቀድሞ፡አገልግሎቱ፡ ካልመለስከው ፡ በክፉ ፡ አሟሟት ፡ እንድ ትሞት፡በውነት፡እነግርሃለሁ፡አለችው።

፱ ኤጲስቆጶሱም፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡ከቄሱ፡ እግር ፡ በታች ፡ ወድቆ ፤ ስለ ፡ አወገዝኩህ፡ ይቅር፡ትለኝ፡ዘንድ፡እለምንሃለሁ፤ከውግዘ ትህም ፡ የተፈታህ ፡ ሁን ፤ ወደ ፡ ቀድሞው፡ ቅዳሴህም ፡ ተመለስ ፤ በድንጋሌ ፡ ሥጋ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ስለ፡ አንተ፡ነግራኛለችና፤ከዛሬ፡ጀምሮ፡ከእመቤ ታችን፡ቅዳሴ፡በቀር፡ሌላ፡ቅዳሴ፡አትቀድስ፡ አለው።

፲ ቄሱም ፡ ይቅርታ ፡ አደረገለት ፤ ኤጲስቆ ጶሱም፡ከእርሱ፡ዘንድ፡አኖረው፤ምግቡንም፡ አብሮት፡እንዲመገብ፡አደረገ፤ልብሱንም፡ ያለብሰው፡ነበር፤በዘመኑ፡ሁሉ፡ያከብረውና፡ ይረዳው፡ነበር።
ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል፥

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይደርብንና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡ ተአምር፡ይህ፡ነው፡አሜን።

፲፩ ጌታችን፡ኢየሱስ፡የዐሥራ፡ሁለቱ፡ደቀ፡መዛ ሙርቱን፡እግር፡አጥቦ፡በፈጸመ፡ጊዜ፡ደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በማእድ ፡ አብረው፡ተቀመጡ።

፲፪ በተቀመጡ፡ጊዜ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ በዚች ፡ ምሽት ፡ ነፍሴ ፡ እጅግ ፡ ትታዘ

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

በዘቲ፡ምሴት፡እስመ፡እዴሁ፡ለዘያገብአኒ፡ምስሌየ፡ውስተ፡ማእድ።

ወሶበ፡ይቤ፡ዘንተ፡እኅዙ፡አርዳኢሁ፡ይትናጸሩ፡በበይናቲሆሙ።

ወይቤሎሙ፡ይሁዳ፡አስቆሮታዊ፡ይደልወነ፡ከመ፡ንትዐዐው፡ለንርአይ፡መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘያገብአ፡እምኔነ፡ወተዐዐዉ፡ሠለስተ፡ጊዜ፡ወወረደ፡ዕፃ፡ላዕለ፡ይሁዳ።

ወሶበ፡ወድቀ፡ዕፃ፡ላዕሌሁ፡ይቤሎ፡ለእግዚእነ፡እግዚኦ፡ትብልኑ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡ዘአገብአከ። ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አንተ፡ትቤ፡ወእምዝ፡ይቤ፡እግዚእነ፡እስመ፡ዘእሁቦ፡ኅብስተ፡ጠሚዕየ፡በማይ፡ውእቱ፡ዘያገብአኒ። ወጠምዐ፡ኅብስተ፡ወመጠዎ፡ለይሁዳ።

ወበይእቲ፡ሰዓት፡ቦአ፡ሰይጣን፡ውስተ፡ልቡ፡ለይሁዳ፡ወወፅአ፡እምህየ፡ወሖረ፡ኀበ፡አይሁድ፡ወይቤሎሙ፡ሀቡኒ፡ብሩረ፡ዘተሰነዓውነ፡ቦቱ፡ወአነ፡አገብኦ፡ለክሙ፡ለኢየሱስ።

ወመሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ከመ፡ይትፈጸም፡ቃለ፡ነቢይ፡ዘይቤ፡ይሠየጥ፡ክቡር፡ለሠላሳ፡ብሩር።

ወይእተ፡ዕለተ፡እንዘ፡ሀለዉ፡ኵሎሙ፡አርዳኢሁ፡ምስሌሁ፡ዲበ፡ማእደ፡ፋሲካ፡ነሥአ፡ኅብስተ፡እምነ፡ማእድ፡ወባረከ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወፈተተ፡ወይቤ፡ዝንቱ፡ሥጋየ፡ዘይትፌተት፡በእንቲአከሙ፤ ንሥኡ፡ብልዑ፡እምኔሁ፡ኵልክሙ። እስመ፡ኵሉ፡ዘይበልዕ፡እምኔሁ፡በሃይማኖት፡ይሠረይ፡ኃጢአቱ፡ወጌጋዩ።

ወእምዝ፡ነሥአ፡ጽዋዐ፡ዘምሉእ፡ወይነ፡ወይቤ፡ንሥኡ፡ስትዩ፡እምዝንቱ፡ጽዋዕ፡ኵልክሙ፡እስመ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ደምየ፡ዘይትከዐው፡በእንቲአክሙ። ወቦቱ፡ይከውን፡ሥርየተ፡ኃጢአት፡ለኵሉ፡ዘይሰቲ፡እምኔሁ፡እስመ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ኪዳንየ፡ሐዲስ።

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ዛሬ፡ እኮን፡ አሳልፎ፡ የሚሰጠኝ፡ እጁ፡በማእድ፡ከእኔ፡ጋራ፡ነውና፡አለ።

፲፰፤ ይህን፡ባለ፡ጊዜ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡እርስ፡በርሳቸው፡ይተያዩ፡ጀመር።

፲፱፤ የአስቆሮቱ፡ይሁዳም፡ከእኛ፡ውስጥ፡አሳልፎ፡የሚያሲዘው፡ማን፡እንደሆነ፡እናይ፡ዘንድ፡ዕጣ፡መጣጣል፡ይገባናል፡አላቸውና፤ ዕጣ፡ቢጣጣሉ፡በይሁዳ፡ላይ፡ሦስት፡ጊዜ፡ወጣ።

፳፤ ዕጣውም፡በወጣበት፡ጊዜ፡ጌታችንን፡አቤቱ፡የማስይዝህ፡እኔ፡እንደሆንኩ፡ትናገራለህን? አለው፤ ጌታችን፤ ኢየሱስም፡አንተ፡አልክ፡አለው፤ ከዚህም፡በኋላ፡ጌታችን፡ኅብስቱን፡በመጻጻው፡ውኃ፡ጠልቄ፡የምሰጠው፡የሚያስይዘኝ፡እርሱ፡ነውና፡ብሎ፡ኅብስቱን፡በመጻጻው፡አጥቅሶ፡ሰጠው።

፳፩፤ በዚያችም፡ሰዓት፡ሰይጣን፡በይሁዳ፡ልብ፡አደረ፤ ከዚያም፡ወጥቶ፡ወደ፡አይሁድ፡ሔዶ፡የተስማማንበትን፡ብር፡ስጡኝ፤ እኔም፡ኢየሱስን፡አሳልፌ፡እሰጣችኋለሁ፡አላቸው።

፳፪፤ ለሠላሳ፡ብር፡ክቡር፡(አምላክ)፡ይሸጣል፡ብሎ፡ነቢይ፡ኤርምያስ፡የተናገረው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ሠላሳ፡ብር፡ሰጡት።

፳፫፤ በዚያች፡ቀን፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ከእርሱ፡ጋር፡በፋሲካው፡ማእድ፡ተቀምጠው፡ሳሉ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከማእዱ፡ኅብስቱን፡አንሥቶ፡ያዘ፤ባረከ፤አከበረ፤ቆረሰ፤ ስለእናንተ፡የሚፈተት፡ሥጋዬ፡ይህ፡ነውና፤ ሁላችሁም፡ከእርሱ፡እንክኡ፡ብሉ፡አለ፤ በሃይማኖት፡ጸንቶ፡ከዚህ፡ኅብስት፡የሚበላ፡ሁሉ፡ኃጢአቱና፡በደሉ፡ይሠረይለታልና።

፳፬፤ ከዚህም፡በኋላ፡ወይን፡የተመላን፡ጽዋ፡አንሥቶ፡እንዲህ፡አለ፤ ሁላችሁም፡ከዚህ፡ጽዋ፡እንክኡ፡ጠጡ፤ ስለእናንተ፡የሚፈሰው፡ደሜ፡ይህ፡ነውና፡የሚጠጣውም፡ሁሉ፡በእርሱ፡የኃጢአት፡ሥርየት፡ይሆናል፤የምስጣችሁ፡አዲሱ፡ቃል፡ኪዳኔ፡እርሱ፡ነውና።

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፲፤ ወካዕበ፡ይቤ፡ተከዘት፡ነፍስየ፡እስከ፡ለሞት፡
አባ፡አድኅና፡እምዛቲ፡ሰዓት።
ወይቤሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ትግሁ ፡ እስመ ፡
በጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ዘያገብአኒ ፡ ወኵልክሙ ፡
ተኀደጉኒ፡በዛቲ፡ሌሊት፡ወትጐይዩ።

፲፩፤ ወይቤሎ፡ስምዖን፡ጴጥሮስ፡ለእመ፡ኀደጉከ፡
ኵሎሙ፡አንሰ፡ኢየኀድገከ፡ወኢይትሌለይ፡
እምኔከ።

፲፪፤ ወነጸረ፡ኀቤሁ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ወይቤሎ፡አማን፡እብለከ፡ኦ፡ስምዖን፡ወልደ፡
ዮና፡ከመ፡ትክሕደኒ፡በዛቲ፡ሌሊት፡ሥልሰ፡
ጊዜ፡እምቅድመ፡ይንቁ፡ዶርሆ።
ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

### ክፍል፡፫።

ዲ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፵፱፡፲፯።

ወአንተሰ ፡ ጸላዕከ ፡ ተግሣጽየ ። ወአግባእከ ፡
ድኅሬከ ፡ ቃልየ ። እመኒ ፡ ርኢከ ፡ ሰራቄ ፡
ትረውጽ፡ምስሌሁ።

### ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፲፫፡፳፩–፳፭።

፳፩፤ ወዘንተ፡ብሂሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ተሀውከ፡
በመንፈሱ ፡ ወስምዐ ፡ ኮነ ፡ ወይቤ ፡ አማን ፡
አማን፡እብለክሙ፡ከመ፡አሐዱ፡እምኔክሙ፡
ያገብአኒ።

፳፪፤ ወተናጸሩ ፡ አርዳኢሁ ፡ በበይናቲሆሙ ፡
እስመ፡ኢያእመሩ፡ወኃጥኡ፡ከመ፡እንበይነ፡
መኑ፡ይብል፡ዘንተ።

፳፫፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ እምአርዳኢሁ ፡ ዘይረፍቅ ፡
ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ወያፈቅሮ፡እግዚእ፡ኢየሱስ።

፳፬፤ ወቀጸቦ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ሎቱ ፡ ወይቤሎ ፡
ተሰአል ፡ ወንግረነ ፡ እንበይነ ፡ መኑ ፡ ይብል ፡
ዘንተ።

፳፭፤ ወረፈቀ ፡ ውእቱ ፡ ረድእ ፡ ዲበ ፡ እንግድዓሁ ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡እግዚእ፡መኑ፡
ውእቱ፡ዘያገብአከ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፤ ዳግመኛ፡ሰውነቴ፡እስከ፡ሞት፡ደርሳ፡ተከዘች፡
አባት፡ሆይ፡ከዚች፡ሰዓት፡አድናት፡አለ።
ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ ትጉ ፡ አሳልፎ ፡
የሚሰጠኝ፡ጊዜው፡ደርሶአልና፤በዚች፡ሌሊት፡
ሁላችሁም፡ትታችሁኝ፡ትሸሻላችሁ፡አላቸው።

፲፩፤ ስምዖን፡ጴጥሮስም፡ሁሉም፡ቢተዉህ፡እኔ፡
ብቻህን ፡ አልተውህም ፤ ከአንተም ፡
አልለይም፡አለው።

፲፪፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ እርሱ
ተመልክቶ፡የዮና፡ልጅ፡ስምዖን፡ሆይ፡ዶሮ፡
ከመጮኹ ፡ በፊት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እንደምት
ክደኝ፡በዕውነት፡እነግርሃለሁ፡አለው።
ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

### ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፤፵፱፡፲፯።

አንተ ፡ ግን ፡ ምክሬን ፡ ጠላሀ ። ሕጌን ፡ ወደ፡
ኋላህ፡ጣልህ። ሌባ፡ሊሰርቅ፡ሲሔድ፡ብታይ፡
አብረኸው፡ትሮጣለህ።

### የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፲፫፡፳፩–፳፭።

፳፩፤ ይህንንም ፡ ተናግሮ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በልቡ፡
አዘነ ፤ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ እንዲአሰይዘኝ፡
እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ብሎም፡
መሰከረ።

፳፪፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡
ተያዩ ፤ ስለማን ፡ ይህን ፡ እንደሚናገር ፡ አላወ
ቁምና።

፳፫፤ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ አጠገብ ፡ የሚቀመጥ ፡ ጌታ፡
ኢየሱስም ፡ የሚወደው ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ፡
አንዱ፡ነበር።

፳፬፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ እርሱን ፡ ጠቅሶ ፡
ይህን ፡ ስለማን ፡ ይናገራል ፤ ጠይቀህ ፡ ንገረን፡
አለው።

፳፭፤ ያም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከጌታ ፡ ኢየሱስ ፡
አጠገብ፡ቀረብ፡ብሎ፤አቤቱ፡የሚያሰይዘህ፡
ማን፡ነው?አለው።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፳፮ ወአውሥአ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ወይቤሎ፡ዝ፡
ውእቱ፡ዘአነ፡እጸብሕ፡ሎቱ፡ኅብስተ፡
ወእሜጥዎ፡ውእቱ፡ዘያገብእኒ፡ወጸብሐ፡
ኅብስተ፡ወመጠዎ፡ለይሁዳ፡ስምዖን፡አስቆ
ሮታዊ።
፳፯ ወእምድኅረ፡ውእቱ፡ኅብስት፡ሶቤሃ፡ቦአ፡
ሰይጣን፡ውስተ፡ልቡ፡ለይሁዳ፡ወይቤሎ፡
**እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ዘትገብር፡እንከ፡ፍጡነ፡
ግበር።
፳፰ ወኢያእመሩ፡እለ፡ይረፍቁ፡ምስሌሁ፡
በእንተ፡ምንት፡ይቤሎ፡ዘንተ።
፳፱ ወቦ፡እለ፡መሰሎሙ፡ከመ፡በእንተ፡
አስከሬን፡ቀምጠራ፡ዘሙዳየ፡ምጽዋት፡
ዘሀሎ፡በኀበ፡ይሁዳ፡ዘይቤሎ፡**እግዚእ፡
ኢየሱስ**፡ተሣየጥ፡ዘንፈቅድ፡ለበዓል፡አው፡
ዘንሁብ፡ለነዳያን፡እስመ፡ውእቱ፡የዐቅብ፡
አስከሬን፡ቀምጠራ፡ዘሙዳየ፡ምጽዋት።
፴ ወተመጢዎ፡ይሁዳ፡ውእተ፡ኅብስተ፡ወፅአ፡
ሶቤሃ፡በሌሊት።
ዘየአምን፡**በወልድ**፡በል።

## ክፍል፡፬።

በጊዜ፡ቍርባን፡ዘይትነበብ፡መልእክተ፡
ጳውሎስ፡ቀዳማዊ፡ኀበ፡ሰብአ፡ቆሮ
ንቶስ።

ምዕ፡፲፩፡፳፫–፴፬።

፳፫ እስመ፡ዘከመ፡ተመሀርኩ፡በኀበ፡**እግዚአ
ብሔር**፡መሀርኩክሙ፡እስመ፡ለሊሁ፡
**እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡አመ፡ርእሶ፡
ይእኅዝዎ፡በይእቲ፡ሌሊት፡ነሥአ፡ኅብስተ።
፳፬ አእኰተ፡ባረከ፡ወፈተተ፡ወይቤሎሙ፡
ንሥኡ፡ብልዑ፡ዝ፡ውእቱ፡ሥጋየ፡ዘይት
ወሀብ፡በእንቲአክሙ፡ወከመ፡ዝ፡ግበሩ፡
ተዝካርየ።
፳፭ ወከማሁ፡ጽዋዐኒ፡እምድኅረ፡ተደሩ፡
ይቤሎሙ፡**ዝ፡ውእቱ፡ጽዋዕ፡ዘሐዲስ፡
ሥርዐት፡ውእቱ፡ደምየ**፡ከመዝ፡ግበሩ፡
ወሶበ፡ትሰትይዎ፡ተዘከሩኒ።
፳፮ አምጣነ፡ትበልዕዎ፡ለዝንቱ፡ኅብስት፡ወትሰ

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፮፤ **ጌታ፡ኢየሱስም**፡መልሶ፡የሚያስይዘኝ፡ይህ፡
እኔ፡ከእንጀራው፡ቆርሼ፡ከወጡ፡አጥቅሼ፡
የምሰጠው፡ነው፡አለውና፡እንጀራውን፡
አጥቅሶ፡ስምዖን፡ለሚባለው፡ለአስቆሮቱ፡
ሰው፡ለይሁዳ፡ሰጠው።
፳፯፤ እንጀራውንም፡ከተቀበለ፡በኋላ፡ወዲያውኑ፡
ከእንጀራው፡ጋር፡በይሁዳ፡በልቡ፡ሰይጣን፡
አደረበት፤**ጌታ፡ኢየሱስም**፡እንግዲህ፡የምታ
ደርገውን፡ፈጥነህ፡አድርግ፡አለው።
፳፰፤ አብረውት፡የሚመገቡት፡ግን፡ስለምን፡
ይህን፡እንዳለው፡አላወቁም።
፳፱፤ ምጽዋት፡የሚሰበስቡበትም፡በይሁዳ፡
ዘንድ፡ስላለው፡የገንዘብ፡ሣጥን፡**ጌታ፡
ኢየሱስ**፡ለበዓል፡የምንሻውን፡ወይም፡
ለነዳያን፡የምንሰጠውን፡ግዛ፡ያለው፡የመሰ
ላቸው፡ነበሩ፤እሱ፡ምጽዋት፡የሚሰበሰብ
በትን፡ሣጥን፡ይጠብቅ፡ነበርና።
፴፤ ይሁዳም፡ያን፡እንጀራ፡ተቀብሎ፡ያን፡ጊዜ፡
በሌሊት፡ወጣ።
**በወልድ**፡የአመነ፡በል።

## ክፍል፡፬።

በቍርባን፡ጊዜ፡የሚነበብ፡ወደ፡ቆሮንቶስ፡
ሰዎች፡መጀመሪያ፡የተጻፈ፡የጳውሎስ፡
መልእክት።

ምዕ፡፲፩፡፳፫–፴፬።

፳፫፤ **ከእግዚአብሔር**፡እንደ፡ተማርኩ፡አስተምሬ
አችኋለሁና፡እርሱ፡ራሱ፡**ጌታችን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ**፡በያዙት፡ጊዜ፡በዚያች፡ሌሊት፡
ኅብስቱን፡አንሣ።
፳፬፤ አመሰገነ፡አከበረ፡ቈረሰ፡እንኩ፡ብሉ፡
ስለ፡እናንተ፡የሚሰጠው፡ሥጋዬ፡ይህ፡
ነው፤መታሰቢያዬንም፡እንዲህ፡አድርጉ፡
አላቸው።
፳፭፤ እንዲሁም፡ሥጋውን፡ከተቀበሉ፡በኋላ፡
**ደሙን፡ሰጣቸው፡አዲስ፡ሥርዐት፡የሚሆን፡
ደም፡ይህ፡ጽዋ፡ደሜ፡ነው**፡እንዲህ፡አድርጉ፤በም
ትጠጡበትም፡ጊዜ፡አስቡኝ፡አላቸው።
፳፮፤ ይህን፡ኅብስት፡በምትበሉበት፡ይህንንም፡

Scanned by CamScanner

ትይዎ፡ ለዝንቱ፡ ጽዋዕ፡ ሞቶ፡ ለእግዚእነ፡ ትዜንዉ፡እስከ፡አመ፡ይመጽእ።

፳፯ ወይእዜኒ ፡ ዘበልዖ ፡ ለዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ ወዘሰትዮ፡ለዝንቱ፡ጽዋዕ፡እንዘ፡ኢይደልዎ፡ ዕዳ፡ይትኃሠሥዎ፡በእንተ፡ሥጋሁ፡ወደሙ፡ ለእግዚእነ።

፳፰ ወይእዜኒ ፡ አመኪሮ ፡ ሰብእ ፡ ርእሶ ፡ ወእንጺሖ፡ ይብላዕ፡ እምውእቱ፡ ኅብስት፡ ወይስተይ፡እምውእቱ፡ጽዋዕ።

፳፱ እስመ፡ዘበልዖ፡ወዘሰትዮ፡እንዘ፡ኢይደልዎ፡ ደይኖ ፡ ወመቅሠፍቶ ፡ በልዐ ፡ ወሰትየ ፡ ለርእሱ፡ለእመ፡ኢያእመረ፡ሥጋ፡እግዚእነ፡ ወኢኮነ፡ንጹሐ፡ነፍሱ።

፴ ወበእንተዝ ፡ ብዙኃን ፡ ድውያን ፡ ወሕሙማን፡እምውስቴትክሙ፡ወብዙኃን፡ ይሰክቡ፡ግብተ።

፴፩ ወሶበ፡ኰንነ፡ለሊነ፡ርእሰነ፡እምኢተኰነነ።

፴፪ ወእመሰ፡ እግዚአብሔር፡ የሐትተነ፡ ወይጌሥጸነ፡ከመ፡ኢንዕረ፡ተኰንኖ፡ምስለ፡ዓለም።

፴፫ ወይእዜኒ፡አኀዊነ፡ሶበ፡ተሐውሩ፡ትምስሑ፡ ተጸንሑ፡ቢጸክሙ።

፴፬ ወዘኒ ፡ ርኅበ ፡ በቤቱ ፡ ለይብላዕ ፡ ከመ ፡ ኢትርኩቱ ፡ ለኵነኔ ፡ ወኢትትሐየሱ ፡ ወባዕደሰ፡መጺእየ፡እሠርዐክሙ።

## መልእክተ፡ጴጥሮስ፡ቀዳሚት።

ምዕ፥፪፥፲፩–፳፭።

፲፩ አ ፡ አኀውየ ፡ ፍቁራንየ ፡ እስእለክሙ ፡ ብቍዐኒ፡ ከመ ፡ ፈላሲ ፡ ወከመ ፡ ነግድ ፡ ወከመ፡ ድኩም ፡ ታርኅቅዋ ፡ ለፍትወተ ፡ ሥጋክሙ፡እንተ፡ትፀብእ፡ለነፍስክሙ።

፲፪ ወግዕዝክሙኒ፡ በማእከለ፡ አሕዛብ፡ ሠናየ፡ ለይኩን፤ከመ፡ኢይርከቡ፡በዘይሔምዩክሙ፡ ከመ፡ገባሬ፡እኪት፡ወሠናየ፡ምግባሪክሙ፡ ይርአዩ፡ወይሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ከመ፡ ይትመየጡ።

፲፫ አትሕቱ፡ርእሰክሙ፡ለኵሉ፡ፍጥረተ፡ዕጓለ፡ እመሕያው፡ በእንተ፡ እግዚአብሔር፡ ወለንጉሥኒ፡እስመ፡ኵሉ፡ሎቱ።



ጽዋ፡ በምትጠጡበት፡ ጊዜ፡ ሁሉ፡ እስከምመጣበት፡ ድረስ፡ የጌታችን፡ ሞቱን፡ ትናገራላችሁ።

፳፯ አሁንም፡ ሳይገባው፡ ይህን፡ ኅብስት፡ የበላ፡ ይህን፡ጽዋ፡የጠጣ፡ስለ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሥጋና፡ ደም፡ በፍዳ፡ ይመረመራል።

፳፰ አሁንም፡ ሰው፡ ራሱን፡ መርምሮ፡ አንጽቶ፡ ከዚህ ፡ ኅብስት ፡ ይብላ ፤ ከዚህም ፡ ጽዋ ፡ ይጠጣ።

፳፱ ሳይገባው ፡ የበላው ፡ የጠጣው ፡ የጌታችን ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካላወቀ ፡ ሰውነቱም ፡ ንጹሕ፡ ካልሆነ ፡ ለራሱ ፡ ደይኑን ፡ መቅሠፍቱን፡ይበላልና፡ይጠጣልምና።

፴ ስለዚህ ፡ ከመካከላችሁ ፡ ብዙዎች ፡ በሽተኞች፡ ናቸው ፤ ብዙዎችም ፡ በድንገት ፡ ይሞታሉ።

፴፩ እኛ ፡ በራሳችን ፡ ብንፈርድ ፡ ባልተፈረደብንም፡ነበር።

፴፪ እግዚአብሔር፡ቢመረምረንና፡ቢገሥጸን፡ግን፡ ከዓለም፡ጋር፡በፍርድ፡እንዳንተካከል፡ነው።

፴፫ አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ለምሳ ፡ በምትሔዱበት፡ጊዜ፡ወንድሞቻችሁን፡ተጠባበቁ።

፴፬ የተራበ፡ቢኖር፡በቤቱ፡ይብላ፤ለፍርድ፡እንዳትሰበሰቡ ፡ እንዳትነቃቀፉ ፡ ሌላውን ፡ ግን ፡ መጥቼ፡እሠራላችኋለሁ።

## የጴጥሮስ፡መልእክት፡አንደኛ።

ምዕ፥፪፥፲፩–፳፭።

፲፩ የተወደዳችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ እንደ ፡ መጻተኛ ፡ እንደ፡እንግዳና፡እንደ፡ደካማ፡መስላችሁ፡ነፍሳችሁን፡የምትወጋትን፡የሥጋችሁን፡ፈቃድ፡ ታርቋት፡ዘንድ፡እለምናችኋለሁ፤በጅ፡በሉኝ።

፲፪ አካሔዳችሁም፡ በአሕዛብ፡ መካከል፡ ያማረ፡ ይሁን፤እንደ፡ክፉ፡አድራጊ፡አድርገው፡የሚነቅፉአችሁ ፡ ምክንያት ፡ እንዳያገኙ ፡ መልካሙን፡ሥራችሁን፡አይተው፡እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑት፡ ዘንድ፡ ወደ፡ እርሱም፡ ይመለሳቸው፡ዘንድ።

፲፫ ስለ፡ እግዚአብሔር፡ ብላችሁ፡ ለሰው፡ ሁሉ፡ ራሳችሁን፡ዝቅ፡አድርጉ፤ለንጉሥም፡ተገዙ፡ ለእርሱ፡ሁሉ፡ተሰጥቶታልና።

Scanned by CamScanner

| በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ። | ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፲፬፤ ወለመኳንንትኒ፡እስመ፡ውእቱ፡ይፌንዎሙ፡ ከመ ፡ ይኰንንዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብርዋ ፡ ለእኪት፡ወያእኵትዎሙ፡ለእለ፡ይገብርዋ፡ ለሠናይት። | ፲፬፤ ለመኳንንትም፡ታዘዙ፡ክፉ፡አድራጊዎችን፡ ሊቀጡ፡በጎ፡አድራጊዎችንም፡ሊያከብሩ፡ እሱ፡ይሾማቸዋልና። |
| ፲፭፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ፈቃዱ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ከመ ፡ በሠናይ ፡ ምግባሪክሙ ፡ ትእስሩ፡አፉሆሙ፡ለአብዳን፡ሰብእ፡እለ፡ኢየ አምርዎ፡ለእግዚአብሔር። | ፲፭፤ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፤ በበጎ ፡ ሥራችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያው ቁትን፡የሰነፎችን፡ሰዎች፡አፍ፡ትዘጉ፡ዘንድ፡ ነው። |
| ፲፮፤ ወኩኑ፡ከመ፡አግዓዝያን፡ወአኮ፡ከመ፡እለ፡ በሙ፡ጌጋይ፡ዘእኩይ። | ፲፮፤ ከክፋት፡ነፃ፡እንደሆናችሁ፡ኑሩ፤ክፉ፡ኀጢና፡ የሚያመጣ፡በደል፡እንዳለባቸው፡ሰዎች፡ አትኑሩ። |
| ፲፯፤ ወአንትሙሰ ፡ ከመ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ኵሎ ፡ አክብሩ ፡ ወቢጸክሙኒ ፡ አፍቅሩ፤ ወለእግዚአብሔርኒ፡ፍርህዎ፡ወለን ጉሥኒ፡አክብርዎ። | ፲፯፤ እናንተስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ እንደ፡መሆናችሁ፡መጠን፡ሁሉን፡አክብሩ፤ ባልንጀራችሁን፡ውደዱ፤ እግዚአብሔርን፡ ፍሩት፤ንጉሥንም፡አክብሩት። |
| ፲፰፤ ወአንትሙኒ ፡ ነባሬ ፡ ተኰነኑ ፡ ለአጋዕዝ ቲክሙ፡እንዘ፡ትፈርሁ፡ወአኮ፡ዳእሙ፡ ለኄራን፡ወለመሐርያን፡አላ፡ለእኩያንሂ። | ፲፰፤ እናንተም ፡ ቤተሰቦች ፡ እየፈራችሁ ፡ ለጌቶ ቻችሁ ፡ ተገዙ ፤ መገዛታችሁም ፡ ለክፉ ዎችም፡እንጂ፡ለደጎችና ለሚራሩት፡ብቻ፡ አይደለም። |
| ፲፱፤ እስመ፡ጸጋ፡እግዚአብሔር፡ትትወሀብ፡ለዘበ እንተ፡ሠናይ፡ምግባሩ፡ይትዔገሣ፡ለሐዘን፡ እንዘ፡የሐምም፡በግፍዕ። | ፲፱፤ ስለ ፡ በጎ ፡ ሥራው ፡ በግፍ ፡ እየተበደለ ፡ መከራን፡ ለሚታገሣት ፡ ሰው ፡ የእግዚአ ብሔር፡ጸጋ፡ትሰጣለችና። |
| ፳፤ ወምንትኑመ፡ይእቲ፡አኰቴትክሙ፡እመ፡ እንዘ ፡ ትኤብሱ ፡ ትትዔገሡ ፡ መቅሠፍ ተክሙ፡አላ፡እንዘ፡ሠናየ፡ትገብሩ፡እመ፡ ተፀገሥክሙ፡ግፍዐክሙ፡ዛቲ፡ይእቲ፡አኰ ቴትክሙ፡በኀበ፡እግዚአብሔር። | ፳፤ እየበደላችሁማ ፡ የመጣባችሁን ፡ መከራ ፡ ብትታገሡ፡መመስገናችሁ፡ምንድን፡ናት፤ መልካም፡እየሠራችሁ፡የደረሰባችሁን፡ግፍ፡ ብትታገሱ፡ግን፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የም ታስመሰግናችሁ፡ይህች፡ናት። |
| ፳፩፤ እስመ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ተጸዋዕክሙ፡እስመ፡ ክርስቶስኒ፡በእንቲአክሙ፡ሐመ፡ይኅድግ፡ ለክሙ፡ማዕተበ፡ከመ፡ትትልዉ፡አሠረ፡ ዚአሁ። | ፳፩፤ ስለዚህ ፡ ተጠርታችኋልና ፡ ክርስቶስም ፡ ፍለጋውን፡ትከተሉ፡ዘንድ፡ምልክቱን፡ሊተ ውላችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ መከራን ፡ ተቀብ ሏልና። |
| ፳፪፤ በከመ፡ውእቱ፡ኢገብረ፡ኃጢአተ፡ወኢተ ረክበ፡ሐሰት፡ውስተ፡አፉሁ። | ፳፪፤ እሱ፡ኃጢአትን፡እንዳልሠራ፡በአንደበቱም፡ ሐሰት፡እንዳልተገኘበት። |
| ፳፫፤ እንዘ ፡ ይጼእልዎ ፡ ኢጸአለ ፡ ወእንዘ ፡ ያሐምምዎ፡ኢተቀየመ፡አላ፡አግብአ፡ለዘይ ኴንን፡ጽድቀ። | ፳፫፤ እውነትን ፡ ለሚፈርድ ፡ ሰጠ ፡ እንጂ ፡ ሲሰድቡት፡አልተሳደበም፤መከራ፡ሲያጸኑ በትም፡አልተቀየመም። |
| ፳፬፤ ወበእንተ፡ኃጢአቲነ፡ውእቱ፡ተሰቅለ፡ዲበ፡ ዕፅ ፡ በሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ያውዕአነ ፡ እምኃጣ ውኢነ ፡ ወበጽድቁ ፡ ያሕይወነ ፤ እስመ ፡ በቍስለ፡ዚአሁ፡ሐየውክሙ፡ቍስለክሙ፡ እንዘ፡ከመ፡አባግዕ፡ትሳኰዩ። | ፳፬፤ ከኃጢአታችን፡ያወጣን፡ዘንድ፡በጽድቁም፡ ያድነን፡ዘንድ፡እሱ፡ስለ፡ኃጢአታችን፡ በእንጨት፡ላይ፡በሥጋው፡ተሰቀለ፤እንደ፡ በጎች፡ስትቅበዘበዙ፡በእርሱ፡ቍስል፡ቍስላ ችሁን፡ድናችኋልና። |

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፳፩፤ ወይእዜኒ ፡ ግብኡ ፡ ኀበ ፡ ኖላዊክሙ ፡ ወዓቃቢሃ፡ለነፍስክሙ።

### ግብረ፡ሐዋርያት።

ምዕ፡፲፡፴፬–፵፫።

፴፬፤ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤ ፡ አማን ፡ ርኢኩ ፡ ከመ ፡ ኢያደሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለገጽ።

፴፭፤ አላ፡በኵሉ፡አሕዛብ፡ዘይፈርሆ፡ወይገብር፡ጽድቀ፡ኅሩይ፡ውእቱ፡በኀቤሁ።

፴፮፤ ወፈነወ ፡ ቃሎ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወዜነዎሙ ፡ ሰላመ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘውእቱ፡እግዚእ፡ለኵሉ።

፴፯፤ ተአምሩ ፡ ለሊክሙ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘኮነ ፡ በይሁዳ ፡ እኂዞ ፡ እምገሊላ ፤ እምድኅረ ፡ ጥምቀት፡ዘሰበከ፡ዮሐንስ፡በእንተ፡ኢየሱስ፡ዘእምናዝሬት።

፴፰፤ ዘቀብዖ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወኃይለ ፡ ወውእቱ ፡ መጽአ ፡ ወረድአሙ ፡ ለእለ፡ይትዔገሉሙ፡ሰይጣን፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ምስሌሁ።

፴፱፤ ወንሕነ፡ኵልነ፡ሰማዕቱ፡በዘገብረ፡በይሁዳ፡ወበኢየሩሳሌም ፡ ወቀተልዎ ፡ ሰቂሎሙ ፡ ዲበ፡ዕፅ።

፵፤ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦ ፡ እሙታን ፡ በሣልስት፡ዕለት፡ወወሀቦ፡ከመ፡ያስተርኢ፡ገሀደ።

፵፩፤ ወአኮሰ፡ለኵሉ፡ሕዝብ፡አላ፡ዳእሙ፡ለእለ፡ይከውኑ፡ስምዐ፡እለ፡ኅረዮሙ፡እምትካት፡ወንሕነ፡እሙንቱ፡እለ፡በላዕነ፡ወሰተይነ፡ምስሌሁ፡እምድኅረ፡ተንሥአ፡እሙታን፡አርብዓ፡ዕለተ።

፵፪፤ ወአዘዘነ፡ከመ፡ንስብክ፡ወንንግር፡ለሕዝብ፡ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሠይመ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር፡መኰንነ፡ሕያዋን፡ወሙታን።

፵፫፤ ወኵሎሙ፡ነቢያት፡ሰማእቱ፡ከመ፡በስመ፡ዚአሁ ፡ ይትኀደግ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለኵሎሙ፡እለ፡የአምኑ፡ቦቱ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፭፤ አሁንም ፡ ወደ ፡ እረኛችሁ ፡ ወደ ፡ ነፍሳችሁ ፡ ጠባቂ፡ተመለሱ።

### የሐዋርያት፡ሥራ።

ምዕ፡፲፡፴፬–፵፫።

፴፬፤ ጴጥሮስም፡ነገር፡ጀመረ፤እንዲህም፡አለ፤እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንደማያደላ ፡ በእውነት፡አየሁ።

፴፭፤ ግን፡በሰው፡ሁሉ፡ዘንድ፡እሱን፡የሚፈራና፡እውነትን ፡ የሚያደርግ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተመረጠ፡ነው፡እንጂ።

፴፮፤ ቃሉን፡ለእስራኤል፡ልጆች፡ልኮ፡በኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ሰላምን፡ሰበከላቸው፤እርሱም፡የሁሉ፡ገዥ፡ነው።

፴፯፤ ዮሐንስ፡ስለ፡ናዝሬቱ፡ሰው፡ስለ፡ኢየሱስ፡ከሰበከው፡ጥምቀት፡በኋላ፤ከገሊላ፡ጀምሮ፡በይሁዳ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ራሳችሁ፡ታውቃላችሁ።

፴፰፤ እግዚአብሔር፡ኃይሉ፡ሕይወቱ፡በሚሆን፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡የመረጠው፡(የሾመው)፡(ያዋሐደው)፡እርሱ፡መጥቶ፡ሰይጣን፡ይታገላቸው፡የነበሩትን፡ረዳቸው፤እግዚአብሔር፡በሀልውናው፡ነውና።

፴፱፤ በይሁዳና፡በኢየሩሳሌም፡ባደረገው፡ሁሉ፡እኛ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ፤ በዕንጨት ፡ ላይም ፡ ሰቅለው፡ገደሉት።

፵፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሙታን፡ለይቶ፡አስነሣው፤በግልጥ፡እንዲታይም፡አደረገው።

፵፩፤ ግን ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አይደለም ፤ አስቀድሞ ፡ ለመረጣቸውና፡ምስክርም፡ለሚሆኑት፡ብቻ፡ነው፡እንጂ፤የመረጣቸው፡የተባልንም፡ከሙታን፡ተለይቶ፡ከተነሣ፡በኋላ፡አርባ፡ቀን፡ከእርሱ፡ጋር፡አብረን፡የበላን፡የጠጣን፡እኛ፡ነን።

፵፪፤ በሙታንና፡በሕያዋን፡ላይ፡ሊፈርድ፡በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ፈራጅ ፡ ሆኖ ፡ የተሾመ ፡ እንደ፡ሆነ፡ለሕዝቡ፡እንነግር፡እናስተምር፡ዘንድ፡አዘዘን።

፵፫፤ ለሚያምኑበት፡ሁሉ፡ኃጢአታቸው፡በስሙ፡እንደሚሰረይላቸው ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ምስክሮቹ፡ናቸው።

Scanned by CamScanner

## ዲ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፳፱፡፬—፭።፵፡፱።

መሠራዕከ፡ማእደ፡በቅድሜየ፡በአንጻሪሆሙ፡ለእለ፡ይሣቅዩኒ፡ወአጽሐድከ፡በቅብዕ፡ርእስየ። ፅዲ፡ዘይሴሰይ፡እክልየ፡አንሥአ፡ሰኰናሁ፡ላዕሌየ፤ አንተ፡እግዚኦ፡ተሣሃለኒ፡ወአንሥአኒ፡እፍድዮሙ፡በእንተዝ፡አእመርኩ፡ከመ፡ሰመርከኒ።

## ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፮፡፳—፳፱።

፳ ወምሴተ፡ከዊኖ፡ረፈቀ፡ምስለ፡ዐሠርቱ፡ወክልኤቱ፡አርዳኢሁ።
፳፩ ወእንዘ፡ይበልዑ፡ይቤሎሙ፡አማን፡እብለ ክሙ፡ከመ፡አሐዱ፡እምኔክሙ፡ያገብአኒ።
፳፪ ወተከዘ፡ጥቀ፡ወአኀዙ፡ይበሉ፡በበአሐዱ፡ አነኑ፡እንጋ፡እግዚኦ።
፳፫ ወአውሥአ፡ወይቤሎሙ፡ዘያወርድ፡እዴሁ፡ምስሌየ፡ውስተ፡መጽብሕየ፡ውእቱ፡ያገብአኒ።
፳፬ ወወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ሰ፡የሐውር፡በከመ፡ተጽሕፈ፡በእንቲአሁ፡ወባሕቱ፡አሌ፡ሎቱ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ዘያገብኦ፡ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡እምነየሰ፡ሶበ፡ኢተወልደ፡ለውእቱ፡ብእሲ።





## ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፡፳፱፡፬—፭።፵፡፱።

በፊቴ፡ማእድን፡ሠራህ፤በሚያስጨንቁኝም፡ፊት፡ራሴንም፡በዘይት፡አለዘብህ፤(ቀባህ)። ዳግመኛ፤እንጀራዬን፡የሚመገብ፡(ግብረ፡በላዬ)፡ተረከዙን፡በላዬ፡አነሣብኝ፤አቤቱ፡አንተ፡ይቅር፡በለኝ፤ፍዳቸውን፡እከፍላቸው፡ዘንድ፡አንሣኝ፤በዚህ፡እንደ፡ወደድከኝ፡አወቅሁ።

## የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፮፡፳—፳፱።

፳ በመሽም፡ጊዜ፡ከዐሥራ፡ሁለቱ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡ለራት፡ተቀመጠ።
፳፩ ሲበሉም፡ከእናንተ፡አንዱ፡አሳልፎ፡እንደሚሰጠኝ፡እውነት፡እላችኋለሁ፡አላቸው።
፳፪ እጅግ፡አዘኑና፡እያንዳንዱ፡አቤቱ፡ምናልባት፡እኔ፡እሆን?እኔ፡እሆን?ይሉ፡ጀመር።
፳፫ እሱም፡መልሶ፡ከእኔ፡ጋራ፡እጁን፡ወደ፡ወጭቱ፡የሚሰደው፡እሱ፡አሳልፎ፡ይሰጠኛል፡አላቸው።
፳፬ የሰው፡ልጅስ፡ስለ፡እርሱ፡እንደ፡ተጻፈ፡ይሞታል፤ነገር፡ግን፡የሰው፡ልጅን፡ለሚያስ ይዘው፡ለዚያ፡ሰው፡ወዮለት፤ያ፡ሰው፡ባልተወለደ፡በተሻለው፡ነበር።

ከመ ወሀበ እግዚእነ ለአርዳኢሁ ሥጋሁ ቅዱስ ወደሞ ክቡረ።



ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እንደሰጠ።

ዘከመ፡ወሀበ፡እግዚእነ፡ለአርዳኢሁ፡ሥጋሁ፡ቅዱሰ፡ወደሞ፡ክቡረ።

፳፭ ወአውሥአ፡ይሁዳ፡ዘያገብኦ፡ወይቤ፡አነሁ፡እንጋ፡ረቢ፡ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አንተ፡ትቤ።
፳፮ ወእንዘ፡ይበልዑ፡ነሥአ፡ኅብስተ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ባረከ፡ወፈተተ፡ወወሀቦሙ፡ለአርዳኢሁ፡ወይቤሎሙ፡እንክሙ፡ብልዑ፡ዝ፡ውእቱ፡ሥጋየ።
፳፯ ወነሥአ፡ጽዋዐኒ፡ወአእኰተ፡ወወሀቦሙ፡እንዘ፡ይብል፡ሰትዩ፡እምኔሁ፡ኵልክሙ።

ጌታችን፡ቅዱስ፡ሥጋውንና፡ክቡር፡ደሙን፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡እንደሠጠ።

፳፭ የሚያስይዘው፡ይሁዳም፡መልሶ፡መምህር፡ሆይ፡እኔ፡እሆን? አለው፡ጌታ፡ኢየሱስም፡አንተ፡አልክ፡አለው።
፳፮ ሲበሉም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ኅብስቱን፡አንሥቶ፡ባርኮ፡ቈርሶ፡ይህ፡ሥጋዬ፡ነው፤እንኩ፡ብሉ፡ብሎ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ሰጣቸው።
፳፯ ጽዋውንም፡አንሥቶ፡አክብሮ፡ሁላችሁም፡ከዚህ፡ጠጡ፡ብሎ፡ሰጣቸው።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

፳፰፤ ዝ፡ውእቱ፡ደምየ፡ዘሐዲስ፡ሥርዓት፡ዘይት
ከዐው ፡ በእንተ ፡ ብዙኃን ፡ ለኅድገተ ፡
ኃጢአት።
፳፱፤ ወናሁ ፡ እብለክሙ ፡ ኢይሰቲ ፡ እንከ ፡
እምዝንቱ ፡ አፂረ ፡ ፍሬ ፡ ወይን ፡ እስከ ፡
እንታክቲ ፡ ዕለት ፡ አመ ፡ እሰትዮ ፡ ሐዲሰ ፡
ምስሌክሙ፡በመንግሥተ፡አቡየ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት፡
እምዕለተ፡ኀሙስ።

፩፤ ለፀሐየ፡ጽድቅ፡አስተርአየ፡ጸዳሉ፡ወበጽሐ፡
ብርሃኑ፡እስከ፡አጽናፈ፡ምድር፤ዝ፡ውእቱ፡
ኢየሱስ፡ብርሃን፡ዘበአማን፡ዘአብርሀ፡ላዕለ፡
ኵሉ፡ሰብእ።
፪፤ መጽአ ፡ ኀበ ፡ ዓለም ፡ ኅብስት ፡ ሰማያዊ ፡
ወይቤ፡ ሕይወት ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረት ፡
ወዘይሴሲ፡ዘገብረ፡በቀዳሚ፡መዋዕል፡ወአስ
ተዳለወ ፡ ማእደ ፡ በገዳም ፡ ወሴሰዮሙ ፡
ለሕዝብ ፡ መና ፡ አርብዓ ፡ ዓመተ ፡ ወበልዑ ፡
ወሞቱ፡በከመ፡ቃሉ፡ለእግዚአብሔር።
፫፤ ማእደ፡ሐዲሰ፡አስተዳለወ፡ወልድ፡በጽርሐ፡
ጽዮን፡ሠርከ፡ዘበልዐ፡ፋሲካ፡እምፍሥሕ፡
ረፈቀ ፡ ኢየሱስ ፡ መድኃኒነ ፡ በመካን ፡
መልዕልተ፡ደብረ፡ዘይት።
፬፤ ወረፈቁ ፡ ምስሌሁ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወበልዑ ፡
ፍሥሓ ፡ ሐዲሰ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋሁ ፡
ዘበፈቃዱ ፡ መጠዎሙ ፡ በምግባር ፡
ምሥጢራዊ ፡ ወደሙ ፡ ክቡር ፡ ዘበአማን ፡
ፈድፋደ፡እምደማተ፡እንስሳ።

፭፤ ወነሥአ ፡ መድኅን ፡ ኅብስተ ፡ ወባረከ ፡
ላዕሌሁ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ፈቲቶ ፡ ወሀቦሙ ፡ ለኅሩ
ያኒሁ ፡ ሐዋርያት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እንክሙ ፡
ብልዑ ፡ እምኔሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋየ ፡
ዝንቱ ፡ ዘይትፌተት ፡ በእንቲአክሙ ፡
ወበእንተ፡ብዙኃን፡ለሥርየተ፡ኃጢአት።
፮፤ ወእምድኅሬሁኒ ፡ አኀዘ ፡ ጽዋዐ ፡ ወይን ፡
ቶሲሖ፡ ማየ ፡ ወወሀቦሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
እንክሙ ፡ ስትዩ ፡ እምዝንቱ ፡ ጽዋዕ ፡
ኵልክሙ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ደምየ ፡ ዘሐዲስ ፡
ሥርዓት፡ዝንቱ፡ዘይትከዐው፡በእንቲአክሙ፡
ወለብዙኃን፡ለሥርየተ፡ኃጢአት።
፯፤ ወኵሎ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ ትበልዑ ፡ እምዝንቱ ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፰፤ ኃጢአትን ፡ ለማስተስረይ ፡ ስለ ፡ ብዙዎች፡
የሚፈሰው ፡ የሐዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ደሚ ፡ ይህ፡
ነው።
፳፱፤ እነሆ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በአባቴ፡
መንግሥት ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ አድርጌ፡
እስከምጠጣባት ፡ እስከዚያች ፡ ቀን ፡ ድረስ፡
ከዚህ ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ ጭማቂ ፡ አልጠጣም፡
እላችኋለሁ፡አላቸው።

ኀሙስ ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከወንጌል፡
በኋላ፡የሚነበብ።

፩፤ የዕውነተኛው ፡ ፀሐይ ፡ ጨረር ፡ ጸዳል ፡ ታየ፡
ብርሃኑም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ደረሰ፡
ይኸውም ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚያበራ፡
ዕውነተኛ፡ብርሃን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ነው፤
፪፤ በመጀመሪያ ፡ ዘመን ፡ የፈጠረውን ፡ የሚመ
ግብና፡ለፍጥረት፡ሁሉ፡ሕይወትን፡የሚሰጥ፡
ሰማያዊ ፡ ኅብስት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጣ፤
በበረኻም ፡ ማእድን ፡ አዘጋጅቶ ፡ አርባ ፡
ዓመት፡ ሕዝቡን ፡ መገባቸው ፤ እነርሱም፡
እንደ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡በልተው፡ሞቱ።
፫፤ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡በሰርክ፡የፋሲካውን፡
ቂጣ ፡ በበላበት ፡ አዳራሽ ፡ አዲስ ፡ ማእድን፡
አዘጋጀ ፤ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በደብረ፡
ዘይት፡ላይ፡ባለው፡ቦታ፡ተቀመጠ።
፬፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡
ተቀመጡ፤ አዲሱንም ፡ የፋሲካ ፡ በግ ፡ በሉ፤
ይኸውም ፡ ምሥጢራዊ ፡ በሆነ ፡ በግብረ፡
አምላክ ፡ የተለወጠ ፡ በፈቃዱ ፡ የሰጣቸው፡
ሥጋውና ፡ ከእንስሳትም ፡ ደም ፡ ልዩ ፡ የሆነ፡
እውነተኛ፡ክቡር፡ደሙ፡ነው።
፭፤ መድኃኒታችንም ፡ ኅብስቱን ፡ አንሥቶ ፡
ባርኮና ፡ ቈርሶ ፡ ለመረጣቸው ፡ ሐዋርያት፡
ኃጢአትን ፡ ለማስተስረይ ፡ ስለ ፡ እናንተና፡
ስለ፡ ብዙዎች ፡ የሚፈተት ፡ ሥጋዬ ፡ ይህ፡
ነውና፤እንኩ፡ብሉ፡ብሎ፡ሰጣቸው።

፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የወይኑን ፡ ጽዋ ፡ አንሥቶ፡
ይዞ፡ውኃ፡ጨምሮ፡ይህ፡ኃጢአትን፡ለማስተ
ሥረይ ፡ ስለ ፡ እናንተና ፡ ስለ ፡ ብዙዎች፡
የሚፈስስ፡ የአዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ደሜ ፡ ነውና፤
ከዚህ፡ጽዋ፡ሁላችሁም፡እንኩ፡ጠጡ፡ብሎ፡
ሰጣቸው።
፯፤ ሁልጊዜ፡ከዚህ፡ኅብስት፡ስትበሉ፡ከዚህም፡

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ጎለስት ፡ ወትሰትዩ ፡ እምዝንቱ ፡ ጽዋዕ ፡
ዘንጪ፡ ምትየ ፡ ወትንሣኤየ ፡ ወግበሩ ፡
ተዝካርየ፡እስከ፡እመጽእ።
ዝንቱ፡ውእቱ፡ፍሥሐ፡ለመድኃኒትነ፡በግዕ፡
ዘበአማን፡ኢየሱስ፡መድኃኒነ።
፳ ይቤ ፡ ኢይሰቲ ፡ እምዛቲ ፡ ወይን ፡ እስከ ፡
እሰትያ ፡ ምስሌክሙ ፡ በመንግሥተ ፡
ሰማያት።
፳፩ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡
ያገብአኒ፡ውስተ፡እደ፡ዐላውያን፡ወአኀዙ፡
የኀልዩ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እንጻረ ፡ ካልኡ ፡
ወይቤሉ፡መኑ፡ይገብር፡ዘንተ፡ወይደፍር።

፳፪ ወይሁዳ ፡ አሐዱ ፡ እምእለ ፡ ይረፍቁ ፡ ይቤ ፡
አነኑ፡እንጋ፤ይቤሎ፡እግዚእ፡አንተ፡ትቤ፤
ወአመረ ፡ እግዚእ ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
እስመ ፡ ዘይወዲ ፡ እዴሁ ፡ ምስሌየ ፡ ውስተ ፡
መጽብኅ።
፳፫ ተሐዘብከ ፡ ኃጢአተ ፡ ዐላውያን ፡ እስመ ፡
ኢፈጠርከ ፡ በእንተ ፡ ገቢረ ፡ እከይ ፤ እስመ ፡
ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው ፡ መጽአ ፡ ከመ ፡ ያድኅኖ ፡
ለቀዳማዊ፡ብእሲ፡እምሀጕል።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።

## ትእዛዝ።

ወኢይትአምኑ ፡ በበይናቲሆሙ ፡
ወኢየአምኑ ፡ ወንጌለ ፡ ወመስቀለ ፡
በእንተ ፡ ዘአምኆ ፡ ይሁዳ ፡ ወኢይ
ዝክሩ ፡ ስሞሙ ፡ ለእለ ፡ ኖሙ ፡ ቅዱ
ሳን፡አበው።
ወኢይበሉ፡ኀዳፌ፡ነፍስ።
ወሰበ፡ያቄርቡ፡ይበሉ፡መዝሙረ፡ዘምዕት፡
ወኀምሳ።
ወኢይበሉ ፡ ክብር ፡ ይእቲ ፡ አላ ፡ ያንብቡ ፡
ካህናት፡ዘንተ።

## ክፍል፡፫።
## ሃይማኖተ፡አበው።
## ዘይትነበብ፡በጊዜ፡ቅዳሴ።

ምዕ፤፸፩፡፴–፴፪።

፩ ይቤ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእለእስ

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ጽዋ፡ስትጠጡ፡ሞቴንና፡መነሣቴን፡ተናገሩ፤
አስተምሩ፤እስከምመጣም፡ድረስ፡መታሰቢ
ያዬን፡አድርጉ።
ለድኅነታችን፡የሚሆን፡የፋሲካው፡ዕውነተኛ፡
በግ፤መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ይህ፡ነው።
፳፤ ከእናንተ፡ጋራ፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡እስከ
ምጠጣት፡ድረስ፡ከዚች፡ወይን፡አልጠጣም፡
አለ።
፳፩፤ ጌታ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ በወንጀለኞች ፡ እጅ ፡
አሳልፎ ፡ እንደሚሰጠኝ ፡ እላችኋለሁ ፡ አለ ፤
አንዱም ፡ አንዱ ፡ በጓደኛው ፡ አንጻር ፡ ይህን ፡
ለመሥራት ፡ ማን ፡ ይደፍራል? እያሉ ፡ ያስቡ ፡
ጀመር።
፳፪፤ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ ይሁዳ ፡ እኔ ፡ እሆን?
እንጃ ፡ አለ ፤ ጌታም ፡ አንተ ፡ አልክ ፡ አለው ፤
ጌታም ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ወጭቱ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡
የሚሰድ ፡ እሱ ፡ ነውና ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡
አመለከተ።
፳፫፤ የወንጀለኞችን ፡ ኃጢአት ፡ ተመራመርከን ፤
ለክፉ፡ሥራ፡አልፈጠርከም፡ነበርና፤የእግዚ
አብሔር፡ልጅ፤የሰው፡ልጅ፡ነውና፤የቀደመ፡
ሰው ፡ አዳምን ፡ ከጥፋት ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡
መጣ።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሁኖ፡መከራ፡
ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።

## ትእዛዝ።

እርስ፡በእርሳቸው፡እጅ፡አይነሣሡ፤ወንጌልና፡
መስቀልን ፡ አይሳለሙ ፤ ይሁዳ ፡ ትእምርተ ፡
ፀብዑን ፡ ትእምርተ ፡ ሰላም ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡
ሳመው ፤ የሞቱ ፡ የቅዱሳን ፡ አባቶችን ፡
ስማቸውን፡አይጥሩ።
ኀዳፌ፡ነፍስንም፡አይበሉ።
በሚያቈርቡበት ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፡ ሃምሳኛውን ፡
መዝሙር፡ይበሉ።
ክብር ፡ ይእቲ ፡ አይበሉ ፤ ካህናቱ ፡ ይህን ፡
ያንብቡ፡እንጂ።

## ክፍል፡፫።
## የአባቶች፡ሃይማኖት።
## በቅዳሴ፡ጊዜ፡የሚነበብ።

ምዕ፤፸፩፡፴–፴፪።

፩፤ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ክንድርያ፡ወቦ፡እለ፡ይብሉ፡ዘይትሜጦ፡እም ሥጢራተ፡ቅድሳት፡ቅድመ፡ኅሩይ፡ውእቱ፡ ፈድፋደ ፡ እምዘይትሜጦ ፡ድኅረ ፤ ወእለ ፡ ይብሉ፡ዘንተ፡ይከፍልዎ፡ለ፩፡ሥጋ፡ክቡር፡ ዘእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀበ ፡ ክልኤቱ፡ክፍል።

ይነብቡ ፡ ወኢየአምሩ ፡ ወይብሉ ፡ ከመ ፡ ቦቱ ፡ ክፍል ፡ ኅሩይ ፡ ውእቱ ፡ ዘቅድም ፡ ወደኃራዊስ ፡ ሕፁፅ ፡ ውእቱ ፡ በጸጋ ፡ ወዝንቱ፡ነገር፡ኃጢአት፡ወጌጋይ፡ውእቱ፡ ጥቀ።

፴፩፤ ንሕነሰ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማይ ፡ ወደኃራይ ፡ ወለእመኒ ፡ ጐንደየ ፡ እምኔሁ፡ኢየሐፅፅ፡በምንትኒ፡እምጸጋ፡አላ፡ ጽሑፍ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘትማልም ፡ ወዮም፡ወከመ፡ውእቱ፡እስከ፡ለዓለም።

፴፪፤ ወዳእሙ ፡ ኢኑኅኢ ፡ በአልባቢነ ፡ ከመ ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ ያዐርጉ ፡ ምሥጢራተ ፡ እሙንቱ፡ ያስተዳልውዎ ፡ ለነ ፡ አው ፡ ይመጥውዎ፡ለነ፡ኪያሁ፡አላ፡እሙንቱሰ፡ ይገብሩ ፡ ግብረ ፡ መልእክት ፡ ዘከመ ፡ ክሂሎቶሙ፡ወእግዚእነ፡ክርስቶስ፡ውእቱ፡ ዘይፌጽም፡ኵሎ፡ወውእቱ፡ዘይሜጥዎሙ፡ ለእለ፡ይከውኑ፡ድልዋነ፡ሎቱ።

ምዕ፤፻፷፡፩፤፳፩–፳፪።

፩፤ ዓዲ ፡ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአቡነ ፡ ክቡር፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአን ጾኪያ፡ኀበ፡አባ፡ፍሎንጎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእ ለእስክንድርያ።

አአምን ፡ ወእትአመን ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥላሴ ፤ በተዋሕዶ ፡ ቅዱሳን ፡ ዕሩያን ፡ በመለኮት ፤ ወዕሩያን ፡ በስባሔ፡ወበገቢረ፡ኵሉ፡ግብር።

፳፩፤ ወንትአመን፡ዓዲ፡ከመ፡ውእቱ፡አምላክ፡ ወሰብእ፡ኅቡረ፡ወይትዔረዮ፡ለአብ፡በህላዌ፡ መለኮቱ ፡ ወይትዔረየነ ፡ ለነ ፡ በህላዌ ፡ ትስብእቱ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ቄርሎስ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በኋላ፡ ከሚቀበል፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ በፊት ፡ የሚቀበል፡ ክብር ፡ በማግኘት ፡ ይበልጣል ፡ የሚሉ ፡ አሉ፤ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ የከበረውን ፡ አንዱን፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሥጋ፡ ከሁለት፡ይከፍሉታል።

ምሥጢሩን ፡ ሳያውቁት ፡ ይናገራሉ፤ ልዩነት፡ እንዳለው፡ አድርገው፡ በፊት፡ የተቀበለ፤ በጸጋ፡ በክብር፡ የተመረጠ፡ ጸጋ፡ ክብር፡ (በመስጠት፡ ይበልጣል) ፡ በኋላ ፡ የተቀበለ ፡ ግን ፡ በክብር፡ የሚያንስ፡ ነው፡ (ያንሳል)፡ ይላሉ፤ ይህ፡ ነገር፡ ፈጽሞ፡ኃጢአትና፡ክሕደት፡ነው።

፴፩፤ እኛ ፡ ግን ፡ በፊት ፡ የተቀበሉት ፡ በኋላም ፡ የሚ ቀበሉ፡ ሥጋው፡ ደሙ፡ አንድ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እናም ናለን፤ በኋላ፡ የተቀበለ፡ በፊት፡ ከተቀበለ፡ ከጸጋ፡ ክብር፡ በመስጠት፡ በምንም፡ አያንስም፤ ክርስቶስ ዓለም፡ ሳይፈጠር፡ የነበረ፤ ዛሬም፡ ያለ፤ መኼም፡ መኾ፡ ለዘላለም፡ የሚኖር፡ እንደ፡ ሆነ፡ ተጽፎአልና፡

፴፪፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ የሚያቀርቡ፡ ካህናት ፡ እነርሱ ፡ አክብረው ፡ ለውጠው፡ እርሱን ፡ እንደሚሰጡን ፡ በልቡናችን፡ እናስብ፤ እነርሱ ፡ እንደተቻላቸው ፡ የአገል ግሎት ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ፡ እንጂ ፡ ሁሉን፡ የሚፈጽም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ነው ፤ ለበቂትም፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ የሚሰ ጣቸው፡እርሱ፡ነው።

ምዕ፤፻፷፡፩፤፳፩–፳፪።

፩፤ የአንጾኪያ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ የከበረ፡ አባታችን፡ አትናቴዎስ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ወደ ፡ ፍሎንጎስ ፡ ጽፎ ፡ ከላከው፡ ሲኖዶሳዊ፡መልእክት።

በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ አምናለሁ፤ እታመናለሁ፤ ሥላሴ፡ በአንድነት፡ የጸኑ ፡ ናቸው ፤ በመለኮትም ፡ አንድ ፡ ናቸው፡ በክብርና ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመፍጠር፡ አንድ፡ናቸው፤ (ቊጥሩ፡አያለፈ፡ነው።)

፳፩፤ አሁንም ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ እናምናለን፤ በባሕርዩ ፡ መለኮቱ ፡ አብን ፡ ይመ ስለዋል፤ በባሕርዩ ፡ ትስብእቱም ፡ እኛን ፡ ይመ ስለናል።

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

ወሶቤ፡አካል፡ለዐላዊ፡**እምላካዊ**፡ከመ፡
ይደሉ፡**ለመለኮቱ**፡እስመ፡ለሊሁ፡**እምላክ**፡
ወግብረ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡በኃይለ፡
መለኮቱ፡እንዘ፡ኢይትፌለጥ፡እምትስብእቱ፡
ወግብረቶሂ፡ትሑታት፡ረሰየ፡ሎቱ፡
ዘሙእቶሙ፡ረኀብ፡ወጽምእ፡ወድካም፡ወዘ
ይመስሎሙ፡ለእሉ፡ወሐመ፡በሕማመ፡
ሥጋ፡ማሕየዊት፡በፈቃዱ፡ወሞተ፡በዲበ፡
ዕፀ፡መስቀል፡በእንቲአነ።

፳፯ ወነአምን፡ዓዲ፡በትንሣኤሁ፡እምድኅረ፡
ሠለስ፡መዋዕል፡ዘይደሉ፡**ለመለኮቱ**፡
ቀተሎ፡ለሞት፡በሞቱ፡ወሠዐረ፡ሕማመ፡
እምኔነ፡ወአንሥአነ፡ምስሌሁ፤ወረሰየነ፡
ከመ፡ንኩን፡ኢሐማምያነ፡ወኢንስሰል፡ወኢ
ንርሐቅ፡እምነ፡ጽድቅ፡ወኢንትወለጥ፡ወአ
ሰፈወነ፡ሕይወተ፡ብዕዕተ፡እንተ፡
ኢትኀልፍ፡ወኢተሐልቅ።

፳፰ ወእለሰ፡ይብሉ፡ከመ፡**ሥጋሁ፡ቅዱስ፡ለእግ
ዚእነ**፡ዘአልቦቱ፡ደነስ፡እምሰማይ፤አው፡
እምካልዕ፡ፍና፤አው፡አልቦቱ፡ነፍስ፡
ወልቡና፤አው፡ኢየሐምም፡ወኢይመውት፡
እለሰ፡ይብሉ፡ዘንተ፡ይከውኑ፡በኀቤነ፡ከመ፡
አብዳን፡እለ፡አልቦሙ፡ልብ፡ወአእምሮ።

ወንሕነሰ፡ናርኁቅ፡ኪያሆሙ፡ወናወግዞሙ፡
በኵሉ፡ጊዜ፡ወለኵሎሙ፡ዓላውያን፡አዕራረ፡
ጽድቅ፡ወተላውያነ፡ሐሰት፡በከንቱ።

ምዕ፡፻፲፯፡፲፪-፲፫።

ወካዕበ፡እምቃለ፡ግዘት፡ዘቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡
ዘግሬ፡መንክራት።

፲፪ እመቦ፡ዘይብል፡በእንተ፡**ክርስቶስ**፡ኢኮነ፡
ሰብአ፡ፍጹመ፡ከማነ፡ወኢይትአመን፡ቦቱ፡
ከመ፡ውእቱ፡ተመሰለነ፡በኵሉ፡ግብር፡
ዘእንበለ፡ኃጢአት፡ባሕቲታ፡በከመ፡ጽሑፍ፡
ውግዘ፡ለይኩን።

፲፫ ወካሬ፡ወእሮኑ፡ይብልዎ፡ለ፩ዱ፡**ክርስቶስ**፡
ኢኮነ፡ሰብአ፡ፍጹመ፡አላ፡ነሥአ፡ክፍለ፡

ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፯፤ **ለመለኮቱ**፡እንደሚገባ፡የባሕርይ፡**አምላ
ክነቱ**፡ገንዘቡ፡የሚሆን፡አካል፡አለው፤
እርሱ፡**አምላክ**፡ነውና፤ከሥጋ፡ባሕርይ፡
ሳይለይ፡በሥልጣነ፡**መለኮቱ**፡ድንቅ፡ድንቅ፡
ተአምራትን፡አደረገ፤የድካም፡ሥራዎ
ችንም፡ለእርሱ፡ገንዘብ፡አደረገ፤እነዚህም፡
ረኀብ፡ጽምእ፡ድካምና፡እነዚህንም፡
የመሰሉ፡ሁሉ፡ናቸው፤በፈቃዱም፡
የምታድን፡የሥጋ፡ሕማምን፡ታመመ፤ስለ፡
እኛም፡በመስቀል፡ላይ፡ሞተ።

፳፰፤ ዳግመኛም፡**ለመለኮቱ**፡የሚቻል፡እንደ፡
መሆኑ፡ከሦስት፡ቀን፡በኋላ፡መነሣቱን፡እና
ምናለን፤ሞትን፡በሞቱ፡አጠፋው፤ከእኛም፡
ሕማምን፡ሽሮ፡ከእርሱ፡ጋር፡አስነሣን፤የማን
ታመም፡እንድንሆን፡ከጽድቅ፡ፈጽመን፡እን
ዳንርቅ፡እንዳንለወጥም፡አደረገን፤
የማታልፍ፡የማትፈጸም፡የተመሰገነች፡ሕይ
ወትንም፡እንዲሰጠን፡ነገረን።

፳፱፤ ኃጢአት፡የሌለበት፡**የጌታችን፡ንጹሕ፡
ሥጋው**፡ከሰማይ፡እንደ፡ተገኘ፡ወይም፡ከሌላ፡
ባሕርይ፡እንደ፡ተገኘ፡ወይም፡ነፍስ፡ዕውቀት፡
እንደሌለው፡ወይም፡የማይታመም፡
የማይሞት፡እንደ፡ሆነ፡የሚናገሩ፡ግን፡ይህን፡
የሚናገሩ፡በእኛ፡ዘንድ፡ልብና፡አእምሮ፡እንደ፡
ሌላቸው፡ሰነፎች፡ይሆናሉ።
እኛም፡እነርሱን፡እናርቃለን፤በጊዜውም፡
ሁሉ፡የጽድቅ፡ጠላቶች፡የሆኑ፡ሐሰት፡
ነገርን፡በከንቱ፡የሚከተሉ፡መናፍቃንን፡
ሁሉ፡እናወግዛቸዋልን።

ምዕ፡፻፲፯፡፲፪-፲፫።

ዳግመኛም፡ተአምራትን፡ከሚያደርግ፡
ከቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡የውግዘት፡ቃል።

፲፪፤ **ክርስቶስ**፡እንደ፡እኛ፡ፍጹም፡ሰው፡
አልሆነም፡የሚል፡እንደ፡ተጻፈም፡
ከኃጢአት፡ብቻ፡በቀር፡በሥራ፡ሁሉ፡እሱ፡
እንደ፡መሰለን፡የማያምን፡ቢኖር፡ውጉዝ፡
ይሁን።

፲፫፤ ትርጓሜ፡እሱ፡ነፍሴን፡ስለ፡በጎቼ፡ቤዛ፡
አድርጌ፡እሰጣለሁ፤ሥጋዬም፡ዕውነተኛ፡

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሐሙስ።

እምሰብእ፡ወለሊሁ፡ይብል፡አንሰ፡እሜጡ፡ ነፍስየ፡ህየንተ፡አባግዕየ፡ቤዛ፡ወሥጋየኒ፡ መብልዐ፡ ጽድቅ፡ ዘበአማን፡ ወዘበልዐ፡ ሥጋየ፡ ወሰትየ፡ ደምየ፡ ቦ፡ ሕይወት፡ ዘለዓለም።

### ክብር፡ይእቲ፡ህየንተ፡ቅኔ።

መዝ፡፹፱፡፲፯።

ወአንተሰ፡ጻላእከ፡ተግሣጽየ።
ወአግባዕከ፡ድኅሬከ፡ቃልየ።
እመኒ፡ርኢከ፡ሠራቄ፡ትረውጽ፡ምስሌሁ።

ወረሰይከ፡መክፈልተከ፡ምስለ፡ዘማውያን።

### ዝማሬ።

አመ፡ይእኀዝዎ፡በይእቲ፡ሌሊት፡ነሥአ፡ ኅብስተ፡በእደዊሁ፡ቅዱሳት፡አእኰተ፡ባረከ፡ ወፈተተ፡ ወወሀቦሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ እንዘ፡ ይብል፤ንሥኡ፡ብልዑ፡ዝ፡ኅብስት፡ሥጋየ፡ ውእቱ፡ ለዘበእንቲአከሙ፡ ይትፌተት፡ ወይ ትወሀብ፡ለቤዛ፡ብዙኃን፡ወከማሁ፡ጽዋዐኒ፡ እምድኅረ፡ተደረ፡መጠዎሙ፡እንዘ፡ይብል፡ ንሥኡ፡ስትዩ፡ዝ፡ጽዋዕ፡ደምየ፡ውእቱ፡ለዘ በእንቲአከሙ፡ ይትከዐው፡ ወይትወሀብ፡ ለቤዛ፡ብዙኃን፡ካዕበ፡ይቤሎሙ፡ንሥኡ፡ መንፈስ፡ቅዱሰ፡ለእለ፡ኅደግሙ፡ኃጢአት፡ ይትኃደግ፡ሎሙ።

### ዕጣነ፡ሞገር፡(ምዕራገ፡ቍርባን)።

(በ፩)፡ ሃሌ፡ ሉያ፡ ረፈቀ፡ ምስሌሆሙ፡ በድራር፡ዘዲበ፡ኪሩቤል፡ይነብር፡ወሎሙ፡ አርአየ፡ ሥርዓተ፡ ምሥጢር፡ ዘቍርባን፡ ንጉሠ፡ነገሥት፡ወእግዚአ፡ኵሉ፡ፍጥረት።

ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ኅትም፡በከመ፡ኅተምከ፡ በዕለተ፡ሰኑይ፡ጊዜ፡ዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት።

## ምዕራፍ፡፵፯።

ትዕዛዝ።

ወእምዝ፡ይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡ዐርብ፡በጊዜ፡ አሐዱ፡ ሰዓተ፡ ሌሊት፤ ወይጸልዩ፡ ጸሎተ፡ በከመ፡ጸለዩ፡በዕለተ፡ኀሙስ።

## ሐሙስ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ምግብ፡ነው፤ሥጋዬን፡የበላ፡ደሜን፡የጠጣ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ አለው፡ ሲል፡ አንዷን፡ ክርስቶስን፡ ከሰውነት፡ ከፍሎ፡ ተዋሐደ፡ እንጂ፡ ፍጹም፡ ሰው፡ አልሆነም፡ እንደምን፡ ይሉታል።

### ክብር፡ይእቲ፡በቅኔ፡ፈንታ።

መዝ፡፵፱፡፲፯።

አንተ፡ግን፡ምክሬን፡ትምህርቴን፡ጠላሀ።
ሕጌንም፡ ወደ፡ ኋላህ፡ ጣልኸው፡ ሌባ፡ ሊሰርቅ፡ ሲሔድ፡ያየህ፡እንደ፡ሆነ፡አብረህ፡ ትሮጣለህ።
ዕድል፡ ፈንታህንም፡ ከአመንዝሮች፡ ጋር፡ አደረግህ።

### ዝማሬ።

በዚያች፡ሌሊት፡ጌታን፡በሚይዙበት፡ጊዜ፡ በከበሩ፡ እጆቹ፡ ኅብስቱን፡ አንሥቶ፡ ባርኮ፡ ቈርሶ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ሰጣቸው፤ስለ፡እናንተና፡ስለ፡ብዙዎች፡የሚፈ ተትና፡የሚሰጥ፡ሥጋዬ፡ይህ፡ነው፤እንኩ፡ ብሉ፡ ብሎ፤ እንዲሁም፡ ከራት፡ በኋላ፡ (ሥጋውን፡ ከተቀበሉ፡ በኋላ)፡ ጽዋውን፡ አንሥቶ፡እንዲህ፡ብሎ፡ሰጣቸው፤ይህ፡ጽዋ፡ ስለ፡ እናንተና፡ ስለ፡ ብዙዎች፡ ቤዛ፡ የሚፈ ሰውና፡ የሚሰጥ፡ ደሜ፡ ነው፤ ንሡ፡ ጠጡ፡ አላቸው፤ ዳግመኛም፡ እንዲህ፡ አላቸው፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተቀበሉ፤ ይቅር፡ ላላቸ ኋቸው፡ኃጢአታቸው፡ይቀርላቸዋል፡አለ።

### መሥዋዕት፡ማሳረጊያ።

አስቀድሞ፡ የነበረ፡ ዛሬም፡ ያለ፡ ዓለም፡ አሳልፎ፡ የሚኖር፡ በኪሩቤል፡ ላይ፡ የሚኖር፡ በራት፡ጊዜ፡ከእነርሱ፡ጋር፡ተቀመጠ፤እሱም፡ የነገሥታት፡ንጉሥ፤የፍጥረት፡ሁሉ፡ጌታ፡የቍ ርባኑን፡ምሥጢር፡ሥርዓቱን፡አሳያቸው።
የጸሎት፡ መፈጸሚያውን፡ ሰኞ፡ በዐሥራ፡ አንድ፡ሰዓት፡እንደፈጸምክ፡አድርገህ፡ፈጽም።

## ምዕራፍ፡፵፯።

ትእዛዝ።

ከዚህ፡በኋላም፡በከበረች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ውስጥ፡ዐርብ፡ከሌሊቱ፡በአንድ፡ሰዓት፡ተሰ ብስበው፡ ኀሙስ፡ በአንድ፡ ሰዓት፡ እንደ፡ ጸለዩ፡ይጸልዩ።